ማውጫ ገጽ


| | |
|---|---|
| አሪት ዘፍጥረት | 9 |
| አሪት ዘጸአት | 79 |
| አሪት ዘሌዋውያን | 133 |
| አሪት ዘኍልቁ | 160 |
| አሪት ዘዳግም | 174 |

# ፔንታቱክ

አምስቱ

የሙሴ

መጻሕፍት።

ዝግጅቱ - በጥያቄና መልስ መልክ

አዘጋጅ - መምህር ጉስታቭ ካይዘር

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 127

አዲስ አበባ።

ማውጫ | ገጽ


አሪት ዘፍጥረት .......................... 9

አሪት ዘጸአት .......................... 79

አሪት ዘሌዋውያን .......................... 133

አሪት ዘኍልቍ .......................... 160

አሪት ዘዳግም .......................... 174

# ፔንታቱክ

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ወይም ሕገ ኦሪት።)

የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ፥ ወደፊት አንድ አስተማሪ በሚያስተምርበት ጊዜ ጥሩ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ ይረዳል ተብሎ የታሰበ ነው።

የሙሴን መጻሕፍት ስታጠኑ በትምህርቱ ውስጥ «እግዚአብሔር» የሚለው ቃልና «ክርስቶስ» የሚለው እንደተጠቀሰ ታስተውላላችሁ። ይህ ሲደረግ በብሉይ ኪዳን ለሰዎች ይገለጥ የነበረው እግዚአብሔር አብ ሳይሆን እግዚአብሔር ወልድ መሆኑ በተማሪዎች አእምሮ እንዲቀረፅ ለማድረግ ነው። እርሱም መንፈስ ነበር፥ እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነበር፥ እርሱም አምላክ ነበር። በእርሱም (በክርስቶስ) እግዚአብሔር አብ የፍጥረትን ሥራ ሁሉና ለሰው የመገለጥን ሥራ ይሠራ ነበር።

የእርሱም ሙሉ ስምና መጠሪያው «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ» ነው። «ጌታ» የተባለበት ምክንያት ሰውንና ለሰው የሆነውን ሁሉ ስለሚገዛ ነው። «ኢየሱስ» የተባለው ሰው ስለሆነ ነው። «ክርስቶስ» የተባለው አምላክ ስለሆነ ነው።

1. እርሱ ቀድሞም ነበር።
2. ፈጣሪ ነበር።
3. እግዚአብሔር ለዓለም የተናገረበት የእግዚአብሔር ቃል ነበር።
4. በሰው ታይቶ ነበር።
5. እንደ አዳኝ፥ መሢሕ፥ ለደኅንነት የሚታመንበት መሆኑ ታውቆ ነበር።

1. ክርስቶስ ቀድሞም ነበር። ሚክያስ 5፡2፤ ዮሐ. 8፡58፤ 17፡5፥ 24፤ ቆላ. 1፡17፤ ራእይ 22፡13 ተመልከት።

2. ክርስቶስ ፈጣሪ ነበር። ኤፌ. 3፡9 «እግዚአብሔር ሁሉን በክርስቶስ ፈጠረ» (ዮሐ. 1፡10፥ 13፥ 14)። ሁሉ በእርሱ ሆነ (ሁሉ በእርሱ ተፈጥሮ ነበር) (ቆላ. 1፡6)። ሁሉ ለእርሱና በእርሱ ተፈጠረ። (1ኛ ቆሮ. 8፥6)። ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። (ዕብ. 1፥2) ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ።

3. ክርስቶስ «ቃል» ነበር። ዮሐ. 1፡1-5 እና ቁጥር 10፡14።

የአንድ ሰው አሳብ የሚታወቀው ሲናገረው ወይም ሲጽፈው ነው። ስለሆነም ሰው ሊሰማው ወይም ሊያነበው ይችላል። የእግዚአብሔር ፍላጎት በብሉይ ኪዳን በልጁ በክርስቶስ በኩል ተገልጦአል። በቃሉ ተናገረ፥ ደግሞ እንዲጻፍ አደረገ፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብን ስለገለጠ ነው። እርሱም «ቃል» ተባለ።

ክርስቶስ (ቃሉ) ባይገልጠው ኖሮ ማንም ስለ እግዚአብሔር አብ አንዳች እንኳ ሊያውቅ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር በእርሱ ተናገረ። ከአዳም ጋር የተነጋገረው ፈጣሪው የሆነ «ቃል» ነበር። ከኖኅ፥ ከአብርሃም፥ ከይስሐቅ፥ ከያዕቆብ፥ ከሙሴና ከነቢያት ጋር ይነጋገር የነበረው «ቃል» ነበር። አብም በእርሱ ሆኖ ተናገረ። ዮሐ. 1:18ን ተመልከት። «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።»

4. <u>በብሉይ ኪዳን ለሰዎች ታይቶ ነበር</u>።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ሰው እግዚአብሔርን አይቶ አይኖርም ይላል። በዮሐ. 1:18 «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም ይላል።» ማንም ያላየው አብን ነው። ይህም በሚከተለው ዓረፍተ ነገር በዚያው ጥቅስ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ይታያል። «በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።» በብሉይ ኪዳን ሰዎች እግዚአብሔርን አይተዋል። እርሱም ልጁ የሆነውን ክርስቶስን ነው።

ዮሐ. 6:46 «አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ አብን አይቶአል» ብሎ ክርስቶስ ተናገረ።

1ኛ ጢሞ. 6:16 «... አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም።»

ለ. እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ጊዜ ታይቶም ተሰምቶም ነበር (ዘጸአት 24:10)። ከእስራኤልም ሰባ ሽማግሌዎች ወጡ የእስራኤልንም አምላክ አዩ። ዘጸአት 24:11 «እጁንም በእስራኤል አዛውንቶች ላይ አልዘረጋም፤ እነርሱም እግዚአብሔርን አዩ በሉ ጠጡም።» ትርጓሜውም እግዚአብሔርን አዩ፤ ነገር ግን በዚያ ምክንያት አልሞቱም ማለት ነው።

ማንን ነው ያዩት? ኢየሱስ «አብን ያየ ማንም የለም» ዮሐ.6:46) አለ። ያዩት ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ልጅ ነበር። «... ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ» (ኢሳ. 6:5)። «አላችሁም:- እነሆ፥ አምላካችን እግዚአብሔር ክብሩንና ታላቅነቱን አሳይቶናል፥ ከእሳቱም ውስጥ ድምፁን ሰምተናል፤ እግዚአብሔርም ከሰው ጋር ሲነጋገር ሰውዬውም በሕይወት ሲኖር ዛሬ አይተናል» (ዘጸ. 5:24)። «እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር» (ዘጸ. 33:11)። ሰዎች ያዩት አብን ሳይሆን ክርስቶስን፥ ልጁን፥ ቃሉን ነበር።

ሰው ክርስቶስን ከነሙሉ ክብሩ አይቶ ደግሞ አይድንም (ዘጸ. 33:20)። ክርስቶስ ለሙሴ «ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም» አለው። በዚያን ጊዜ ጀርባውን እንዲያይ ፈቀደለት። ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር እንዲያይ ጠይቆ ነበር (ዘጸ. 33:18)። ማንም የክርስቶስን ሙሉ ክብር አይቶ አይኖርም። ክርስቶስ እራሱን በደመናና በእሳት የገለጸው ለዚህ ነበር። አንድ ሰው ፀሐይን በሚያይበት ጊዜ ዓይኑን ይጎዳል፥ ነገር ግን ትንሽ ደመና

ፀሐይን በጋረዳት ጊዜ ሰውዬው ፀሐይን ቢያይ ዓይኑ አይጎዳም። ምክንያቱም ኃይሏ በደመና ስለተሸፈነ ነው። ደግሞም በጥቁር መስተዋት አንድ ሰው ፀሐይን በሙሉ ሊያይ ይችላል፥ ዓይኑ ግን አይጎዳም። ሰዎች ክርስቶስን አዩ፥ ነገር ግን ክብሩ ተሸፍኖ ስለ ነበር አይተው አልሞቱም።

ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ክርስቶስን በክብር ከተራራው ላይ ባዩ ጊዜ (ማቴ. 17:1-7) ደመና ሸፈናቸው፤ ይህ ባይሆን ክብሩን አይተው ባልዳኑም ነበር። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑንና በብሉይ ኪዳን ከሰዎች ጋር ግንኙነት ያደርግ የነበረው እርሱ መሆኑን ይገልጣሉ። እንደገና ዮሐ. 5:37፤ 1ኛ ጢሞ. 6:16፤ ዘጸ. 6:3 ና ዘዳ. 5:24 እግዚአብሔር ታይቶአል፥ ተሰምቶም ነበር። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር መፍጠርንና ከሰዎች ግንኙነት ማድረግንም ጭምር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል አደረገ።

## 5. በብሉይ ኪዳን ክርስቶስን እንደ አዳኝ አምነውበት ነበር።

አብርሃም በክርስቶስ አምኖ ዳነ። ክርስቶስ «አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው» አላቸው (ዮሐ.8:56)። አብርሃም በእምነት ክርስቶስንና ሞቱን አይቶ ደስ አለው። ደኅንነቱም በክርስቶስ እንደሆነ ተመለከተ።

ስምዖን (ሉቃ. 2:26-30)፤ ሐና (ሉቃ. 2:36-38)፤ የአይሁድ ሰዎች (ሉቃ. 3:15)፤ መጥምቁ ዮሐንስ (1:31)፤ የሰማሪያዪቱ ሴት (ዮሐ. 4:25)፤ 12ቱ የእስራኤል ነገዶች (የሐዋ. ሥራ 26:7)፤ እነኝህ ሁሉ የክርስቶስን በሥጋ መምጣት ይጠብቁ ነበር። ከእግዚአብሔር ቃል ደኅንነት የክርስቶስን ሞት በማመን መሆኑን የሚገልጽ በቂ ማስረጃ ነበራቸው።

የሚያስፈልጋቸው በነቢያት ውስጥ ታሪኩ በሙሉ የሚገኝበትን ኢሳ. 53ን ማንበብ ብቻ ነበር። ጳውሎስ ለአይሁዶች ምክንያት ሲሰጥ ከብሉይ ኪዳን ይህ ኢየሱስ እነርሱ የሚያውቁት ክርስቶስ እንደነበር ይገልጽላቸዋል (የሐዋ. ሥራ 17:2፥3፤ 18፥ 28)። ከዚያ በኋላ በክርስቶስ ማመን አስፈለጋቸው።

ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ክርስቶስ ከድንግል እንደሚወለድ ለዓለም ኃጢአት እንደሚሞትና በሞቱ በእምነት መዳን እንዳለባቸው ገልጦ ነበር። እርሱም «የሴቲቱ ዘር» ነበር (ዘፍ.3:15)። ነገር ግን የወንድ ዘር አልነበረም። «እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳ.7:14) ትርጉሙም እግዚአብሔር ከሰው ጋር በመሬት ላይ በሰው አምሳል ማለት ነው። ማቴ. 1:23ን ተመልከት።

«እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤» (ገላ.3:24)። ሕጉ እስራኤላውያንን ስለ ደኅንነት

መንገድ አስተምሮአቸዋል፤ ይህም እኛ የምናውቀው መንገድ ነው፥ ሌላ መንገድ ፈጽሞ አልነበረም።

በ1ኛ ቆሮ. 10፡4 እስራኤላውያን የክርስቶስን መንፈሳዊ መጠጥ እንደጠጡ ይነግረናል። እርሱን ተቀብለው ያላወቁት ቢሆኑ መንፈሳዊ መጠጥ ከእርሱ ሊጠጡ አይችሉም ነበር።

በብሉይ ኪዳን የዳኑት ሰዎች ለደኅንነታቸው ልክ እንደ እኛ በክርስቶስ ሞት አምነው ነበር። እነርሱ ወደፊት በእምነት የእርሱን መምጣትና መሞት ተስፋ አደረጉ። እኛ ወደኋላ መስቀሉን በእምነት እናያለን። የደም መሥዋዕት እስራኤላውያንን አላዳናቸውም። «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነው፥» (ዕብ. 10፡4፤ 9፡12)። እነዚህ መሥዋዕቶች ክርስቶስ የኃጢአታቸውን ፍርድ እንደተሸከመላቸው የሚያሳዩአቸው ነበሩ።

ከክርስቶስ ደም በስተቀር በሌላ መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚደርስ አንድ እንኳን አይገኝም፤ በራእይ 5፡9 በመንግሥተ ሰማያት ከአዳም ጀምሮ የዳኑት እንዴት እዚያ እንደደረሱ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ እናያለን። «ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው።»

<u>ዋና ዋናዎቹ ፍሬ ነገሮች</u>። ክርስቶስ የእስራኤል ንጉሥ ነበር (ዘጸ. 19፡5-6፤ ዘኁ. 23፡16-21፤ 1ኛ ሳሙ. 8፡7፤ 12፡12፤ ኢሳ. 6፡5)። ሰው ያየውና ከሰው የተነጋገረው እርሱ ነበር። በብሉይ ኪዳን ሰዎች እርሱ ሰው እንደሚሆንና ለዓለም ኃጢአት እንደሚሞት ያውቁ ነበር። ሰው በክርስቶስ በማመን ድኖአል። ክርስቶስ ቃል በመሆኑ እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ይናገር ነበር። አብ ሳይሆን ወልድ እራሱ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት ነበረው። በዚህ ምክንያት ጳውሎስ በመንፈስ ተሞልቶ በ1ኛ ቆሮ. 10፡4 እስራኤላውያን መንፈሳዊውን መጠጥ ከመንፈሳዊው ዓለት እርሱም ክርስቶስ ከሆነው ጠጡ፤ መንፈሳዊውንም ትምህርት ከእርሱ ተማሩ፥ በዚህም ምክንያት ጳውሎስ በገላትያ 3፡24 በእምነት ይድኑ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚት ወይም አስተማሪ ሆነላቸው ብሎ ይነግረናል።

በጣም የሚገርመው ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ብዙ ያላመኑ እንደመብዛታቸው መጠን በዚያም ጊዜ ብዙ እስራኤላውያን የደኅንነትን መንገድ አላወቁም። ምክንያቱም ኃጢአታቸውን ለመተው ስላልፈቀዱ ነው። ደኅንነትን የፈለጉት በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ለመዳን ቻሉ። ነገር ግን ሌሎቹ መንፈሳዊው ዓይናቸው ታውሮ ነበር።

ይህን ሁሉ በመገመት እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለሰዎች ይገለጽ እንደ ነበረ የተገለጸውም አምላክ ክርስቶስ እንደሆነና እግዚአብሔር የሚለው ቃልና ክርስቶስ የሚለው ቃል ሁለቱም በዚህ ትምህርት ውስጥ እንዳሉ ለተማሪዎች መግለጽ አስፈላጊ መስሎ ታይቶናል።

## 6. ክርስቶስ የሚለው ቃል ትርጓሜ።

ክርስቶስ የሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ነው፥ ትርጓሜውም «የተቀባ» ማለት ነው። ይህም በአዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ ተጽፎ ይታያል፤ ምክንያቱም አዲስ ኪዳን በመሠረቱ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር ልጁን የዓለም አዳኝ እንዲሆን ቀባው (ራእይ 13፡8)። ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በዕብራውያን ቋንቋ ነው። በዚህ ቋንቋ ክርስቶስ «መሲሕ» ተብሎ ይጠራል። ትርጉሙ ግን አንድ ነው፤ እርሱም «የተቀባ» ማለት ነው።

## 7. ክርስቶስ የሚለውን ስም ከብሉይ ኪዳን ለማስተማር ልንጠቀምበት እንችላለን።

ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ከብሉይ ኪዳን ለማስተማር መልእክቶቹን በጻፈ ጊዜ «ክርስቶስ» የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ ጠርቶታል (ገላ.3፡24)። ስለዚህ እኛም ሆንን የብሉይ ኪዳን ሰዎች በእምነት እንድን ዘንድ ሕጉ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል (ገላ.3፡24)። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 10፡4 እስራኤላውያን በብሉይ ኪዳን «ይከተላቸው ከነበረውና መንፈሳዊ ዓለት ከሆነው ከክርስቶስ መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ ብሎ ጽፎአል። (ከእስራኤላውያን አንዳንዶቹ) «ጌታን እንደ ተፈታተኑት በእባቦቹም እንደ ጠፉ ጌታን አንፈታተን» (1ኛ.10፡9)። «ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፥ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር፤ ሲተረጉምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሳ ይገባው ዘንድ እያስረዳ፡- ይህ እኔ የምሰብከላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር» (የሐዋ.17፡2-3)። የሐዋ. ሥራ 18፡28፤ ሉቃ. 24፡25-27ን ተመልከት።

### ክርስቶስ፥ ያልታየው የእስራኤል ንጉሥ።

የሙሴን መጻሕፍት በምናጠናበት ጊዜ ልጅ የሆነው ክርስቶስ እርሱም አምላክ በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ንጉሥ ተብሎ እንደሚጠራ እናገኛለን።

በጥቂቶች ብቻ ስለታየ «ያልታየው የእስራኤል ንጉሥ» ተብሎ ይጠራል። የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ የሚያስረዱ ጥቂት ጥቅሶች፡-

«አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ . . . እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ» (ዘጸ.19፡5-6)። በዘኍ. 23፡16-21 ደግሞ እግዚአብሔር በበለዓም አፍ የተናገረው ቃል ይህ ነበር፥ «. . . የንጉሥም እልልታ በመካከላቸው አለ . . .»። በ1ኛ ሳሙ. 8፡7 እንደዚህ የሚል ቃል እናነባለን፤ «እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፡- በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ።» 1ኛ ሳሙ. 12፡12 «የአሞንም ልጆች ንጉሥ ናዖስ እንደ መጣባችሁ ባያችሁ ጊዜ አምላካችሁ እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ሳለ፡- እንዲህ አይሁን፥ ነገር ግን ንጉሥ ይንገሥልን አላችሁኝ።» «እኔም፡- ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል

በመቀመጡ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ! አልሁ» (ኢሳ. 6፡5)። «የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም» (ኢሳ.44፡6)። ከመጀመሪያ ጀምሮ ክርስቶስ የእስራኤል ንጉሥ ነበር። እግዚአብሔር አብ የፍጥረት ሁሉ ንጉሥና ጌታ ነው። በ1ኛ ቆሮ. 15፡27-28 እንደተገለጸው አብ ሁሉን ነገር ይገዛ ዘንድ በልጁ ሥር አድርጎታል። አዲስ ሰማይና ምድር ከተፈጠረና ሞት ድል ከተነሳ በኋላ ክርስቶስ ደግሞ ለአብ ይገዛል። ክርስቶስ አንድ ሺህ ዓመት ከነገሠ በኋላ (ራእይ 20፡9፤ ኢሳ. 65፡20)። ክርስቶስ አብ ከሁሉ በላይ እንደሆነና የፍጥረት ሁሉ ንጉሥና ጌታ መሆኑን ይገልጻል (1ኛ ጢሞ. 6፡15-16)።

## በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበረው ወንጌል።

በአማርኛ «ወንጌል» የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን ነው። «ወንጌል» የሚለው ቃል ከግሪክ የተወረሰ ነው፥ ትርጓሜውም «መልካም ዜና» ማለት ነው። የግሪክ ቃል በመሆኑ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው። ሆኖም መልካሙ የደኅንነት ዜና በብሉይ ኪዳን ሁሉ ደግሞ ይገኛል። እንዲያውም ለአዳምና ለሔዋን ተሰጥቶ ነበር። በኋላ ግን የክርስቶስን ሕይወትና ትምህርት በያዙት በአራቱ መጽሐፎች ማለትም በማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስና ዮሐንስ ተሰጠ። በነቢያት የተነገረው ወንጌል በማርቆስ 1፡1-2 በግልጥ ይታያል። «በነቢያት እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ ...» ማርቆስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የነቢያት መልእክት ስለ ክርስቶስ ወንጌል ብሎ ጠርቶታል። እኛም ከብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አማኞች በምናስተምርበት ጊዜ ቃሉ ምን እንደሚል ግልጽ ካደረግንላቸው ልንጠቀምበት እንችላለን።

8. <u>ሥላሴ</u>። እግዚአብሔር አንድ አምላክ ሆኖ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በሦስት ይጠራል። ነገሩ እንዲገባን ለማድረግ በጣም ከባድ ቢሆንም በምሳሌ ብንረዳ ለማወቅ ቀላል ይሆንልናል።

<u>ምሳሌ</u>፡- ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጠረ (ዘፍ. 1፡26)።

<u>በእግዚአብሔር መልክ</u>፡- እግዚአብሔር መንፈስ ቢሆንም በብሉይ ኪዳን በሰው አምሳልና ቅርጽ ታይቶአል።

<u>የእግዚአብሔር ምሳሌ</u>፡- እግዚአብሔር ሥላሴ ነው። እርሱም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሆነ አንድ አምላክ ነው። ሰውም በሥላሴ አምሳል የሚጠራበት ሁኔታ አለው። እርሱም ሥጋ፥ ነፍስና መንፈስ የሆነ አንድ ሰው ነው። ሰው ሲለያይ፥ ደግሞም አንድ ሰው ሊሆን ይችላል። ሲሞት ነፍሱና መንፈሱ ከሥጋው ይለያያል። ሥጋው አለ፥ ነፍሱና መንፈሱም ደግሞ አሉ። ያ መለያየት ሞት ይባላል። ሥጋው ወደ መቃብር ይሄዳል፤ ነፍሱና መንፈሱ ደግሞ ወደ ሲኦል ወይም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይሄዳሉ፤ አሁንም ቢሆን አንድ ሰው

ነው። በትንሣኤ ቀን ነፍሱና መንፈሱ አዲስ ሥጋ ይለብሳሉ። አሁንም ይህ ሰው ሦስት ሆኖ ነገር ግን አንድ ሰው ነው።

እግዚአብሔርም በተለያየ ሁኔታ ይጠራል። ነገር ግን እርሱ አንድ አምላክ ነው። ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ሰማያት ወርዶ ሰው ሆነ። ሞቶም ተነሣ። እንደገና ከአብ ጋር ነው። ነገር ግን አንድ አምላክ ነው። በዚህ ዓይነት የሰው ሦስትነት የሥላሴን ምስጢር ሳይበዛ በጥቂት ያስረዳል።

ሦስት የተለያዩ ፍጥረታት አሉ።

1. አትክልቶችና ዛፎች። አካል ብቻ አላቸው፥ ይኖራሉ፥ ፍሬ ይሰጣሉ፥ ይባዛሉ፥ ይሞታሉ።

2. እንስሳት። አካልና ነፍስ አላቸው፥ የነፍሳቸው ቋንቋ ስሜት ነው። ይኸውም፥ ፍቅር፥ ጥላቻ፥ ፍላጎት፥ የጋለ ስሜት፥ እንስሳት ይህ አላቸው።

3. ሰው። ሰው ሥጋ ነፍስ መንፈስ ነው። የመንፈሱ ቋንቋ ጸሎትና አምልኮ ነው። ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ ተፈጥሮአል። እንስሳ ግን ምንም ብልህ እንኳን ቢሆን መንፈስ ስለሌለው ይህን አያደርግም። የሰው መንፈስ በሥጋውና በነፍሱ ላይ ይገዛል። ኃጢአት ለማድረግ የሚፈቅደው ወይም የሚከለክለው በሰው ውስጥ ያለው መንፈስ ነው። እንስሳት ለማድረግ የፈለጉትን ነገር ያደርጋሉ። ነገር ግን ላደረጉት ነገር ኃላፊነት አይሰማቸውም። ሰው መንፈስ ስላለው ራሱን መቆጣጠር ይማራል። ደግሞም በኋላ ከክርስቶስ ጋር ይነግሣል።

እዚህ ላይ በሥላሴ አሠራርና በሰው የሦስቱ ክፍሎች አሠራር መካከል ያለውን መመሳሰል ተመልከት። እግዚአብሔር አብ ይወስናል፤ ዕቅድ ያወጣል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለተወሰነው ነገር ሕይወት ይሰጠዋል። እግዚአብሔር ወልድ ይሠራዋል።

የሰው መንፈስ ያቅዳል፥ ይወስናል፥ በአእምሮም አሳብ ይሠራል። ነፍሱ ለተወሰነው ነገር ሕይወትን ይሰጠዋል፥ በጣም ጠንካራ አሳብና ሥራውን ለማከናወን ፍላጎት ያሳድርበታል። ሰውነቱ (ሥጋው) ባደሩበት ስሜት መሠረት ሥራውን ይሠራል።

1. መንፈስ ባያቅድ ኖሮ ነፍስ ለመሥራት ፍላጎትን አይሰጥም፥ ያለዚህ ፍላጎትም አካል ሊሠራው አይችልም። ያለ ዓላማና ያለ ፍላጎት ለመሥራት መነሳት እንዴት ይቻላል?

2. መንፈስና ነፍስ የተጋጨ ወይም የማይስማማ አሳብ ቢኖራቸው አካል ሊሠራው አይችልም።

3. ነፍስና መንፈስ ቢስማሙና ነገር ግን አካል ቢታመም ሥራው ሊሠራ አይችልም። ሦስቱም አካል ነፍስና መንፈስ ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት አስፈላጊዎች ናቸው። ደግሞ በእግዚአብሔር በኩል ሥላሴ (ሦስቱም) ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት አስፈላጊዎች ናቸው። ሰው አንድ ሰው ለመሆን

አካል ነፍስ መንፈስ መሆን እንዳለበት ሁሉ ደግሞም እግዚአብሔር አምላክ ለመሆን ሦስት በአንድ መሆን አለበት።

## ፔንታቱክ (ሕገ ኦሪት)

መግቢያ፡-

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ዘፍጥረት፥ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኍልቁ፥ እና ዘዳግም ሕገ ኦሪት ይባላሉ። ይህ ቃል ከግሪክ የተወረሰ ነው። ይህ ስም ለእነዚህ መጻሕፍት የተሰጣቸው ከተጻፉ ከብዙ ዓመታት በኋላ ቆይቶ ነው። ይህን መጽሐፍ አይሁዳውያን ከእግዚአብሔር የተመረጡት ሰዎች የሕግ መጽሐፍ ወይም የሙሴ ሕግ ብለው ይጠሩታል (ዕዝራ 6፡18፤ ነህምያ 13፡1፤ 8፡1፤ 2ኛ ዜና 25፡4፤ 34፡14፤ 35፡12)።

በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበሩ። ነገር ግን በኋላ በአምስት ተከፈሉ። ከሕገ ኦሪት አብዛኛው ክፍል ሙሴ እግዚአብሔርን በሲና ተራራ ከተገናኘው በኋላ የጻፈው ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ሥጋ ለብሶ ወደ መሬት ከመምጣቱ በፊት እራሱን እንደ እግዚአብሔር ለሙሴ የገለጠው ልጁ (ወልድ) ክርስቶስ ነበር። ሙሴም ሕግጋትን፥ በእርግጥም የፍጥረትን ታሪክ የሰውን መውደቅ ስለጥፋት ውኃና የጻፈውን ሁሉ ከክርስቶስ ተቀበለ። ሙሴም ይህንን የተቀበለው በ1491-1451 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እንደተስማሙበት አዳም የተፈጠረው ክርስቶስ ከመወለዱ አስቀድሞ ከ4004 ዓመት በፊት ነው ይላሉ። ነገር ግን በእርግጥ ለማወቅ አዳጋች ነው።

ማንም መሬት የተፈጠረችበትን ጊዜ ሊያውቅ አይችልም። ምናልባትም አዳም ከተፈጠረ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ሊሆን ይችላል።

# ኦሪት ዘፍጥረት

1. ዘፍጥረት የመጀመሪያው መጽሐፍ ሲሆን፥ በግሪክ ቋንቋ የተሰጠው የስም ትርጓሜ መጀመሪያ የሚል ነው።

በዚሁ መጽሐፍ እግዚአብሔር የገለጸልንን የመጀመሪያ ነገሮች ልትዘረዝር ትችላለህን?

መልስ።

1. የሁሉ ነገር መፈጠር (ዘፍ. 1፡1)።

2. የኃጢአትና የሞት መጀመር።

3. ስለ ደኅንነት መጀመርና አዲስ መንፈሳዊ ኑሮ።

4. ክርስቶስ ሊመጣበት ያለው የእስራኤል ወገን መጀመር።

2. ሀ. የዘፍ. 1፡1-2፡3 ትምህርት ምንድር ነው?

ለ. እግዚአብሔር ጨለማ የነበረውን ዓለም እንደገና በስንት ቀን ውስጥ ነው «አዲስ» አድርጎ የሠራው?

መልስ።

ሀ. ይህ የመጽሐፍ ክፍል የእግዚአብሔርን የመፍጠር ሥራ ይናገራል።

ለ. እግዚአብሔር ዓለምን እንደ «አዲስ» አድርጎ የፈጠረው በስድስት ቀን ውስጥ ነው። መልካምና ለሰው የሚስማማ አድርጎ ፈጠረው። ሰውን ከመፍጠሩ በፊት የሚበቃውን ሁሉ አዘጋጀለት፤ ዝቅ ብለን እንደ «አዲስ» የሚለው ቃል በመልሱ ውስጥ ለምን እንደገባ እናያለን።

3. «መፍጠር» የሚለውን ቃል ከ(ዕብ. 11፡3፤ ሮሜ 4፡17፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡28) ስናወዳድረው ምን ማለት ነው?

መልስ።

በዕብ. 11፡3 ስንመለከት እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ ከማይታይ ነገር አበጀው ይላል። መፍጠር ማለት የሌለውን ነገር ወደመኖር ማምጣት፥ ደግሞም የሚታየውን ነገር ከማይታይ ነገር ማበጀት ማለት ነው። (እግዚአብሔር ይህንን በቃሉ አደረገ)።

4. በመጀመሪያ ከሥላሴ ማንኛው ክፍል ነው እንዲፈጥር የተወሰነው? ቆላ. 1፡15፥ 16፤ ዕብ. 1፡12፤ ዮሐ. 1፡3፤ ኤፌ. 3፡9።

መልስ።

ሥላሴ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ተባብሮአል (ኤፌ. 3፡9)። ነገር ግን የመፍጠርን ሥራ ያከናወነው ወልድ ነው (ቆላ. 1፡15-16)። እርሱም የሥላሴ ሠራተኛው ክፍል ነው (ምሳሌ 8፡30)። ስለ ልጁ የተነገረውን ለማረጋገጥ ቁጥር 22-36 አንብብ። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ 8፡30 ላይ ክርስቶስን ሠራተኛ ይለዋል። ደግሞም ቃል ተብሎ ይጠራል። ዓለም የተፈጠረው በእግዚአብሔር ቃል ነው (ዕብ. 11፡3)። እርሱም ፈጣሪና የፍጥረቱ ሁሉ አዳኝ ነው። 84 ሐ ጥያቄ ተመልከት።

5. መሬት የተፈጠረችው ለምን ዓላማ ነበር? ምሳሌ 8፡22-36፤ ቆላ. 1፡16፤ ኢሳ. 45፡18።

መልስ።

በምሳሌ 8 እንደምናይ «ጥበብ» የሚለው ክርስቶስን ነው። የልጁን ከአብ ጋር መሥራት ያሳያል። ሰው ከመፈጠሩ በፊት፥ ክርስቶስ ወደፊት መሬት በሰው የምትሞላበትን ጊዜ በደስታ ይጠብቅ ነበር (ቁጥር 30 ና 31፤ ኢሳ. 45፡18፤ ቆላ. 1፡16)። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር መሬትን በክርስቶስና ለክርስቶስ ፈጥሮ ለሰው ጥቅም እንዳሰባት ያስተምረናል። ዓላማው ሰውን ለራሱ በመፍጠር ለዘለዓለም ከእርሱ ጋር እንዲሆንና ደግሞም በፍጥረታት ላይ አብሮ እንዲነግሥ ነበር።

6. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰማይና ስለ ሰማያት ይናገራል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልክተህ «ሰማይ» የሚለው ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ የምታስበውን ግለጽ። ዘፍ. 1፡1፤ ዘፍ. 1፡8-14፤ 17፡20፤ 7፡11፤ 8፡2፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡5፥ 7፡14፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡2፤ አሞጽ 9፡6፤ ኤፌ. 4፡10፤ መዝ. 148፡4፤ ዕብ. 9፡24፤ ራእይ 21፡1፤ 1ኛ ነገ. 8፡27፤ ዘዳ. 30፡19፤ ዘዳ. 4፡26፤ ዳን. 4፡13-35።

መልስ።

በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት ሦስት ሰማያት አሉ (2ኛ ቆሮ. 12፡2)። የመጀመሪያው ሰማይ በዘፍጥረት 1፡6-8፡20፤ 8፡2 የሚገኘው ነው። እርሱም በመሬት አካባቢ ያለው አየር ነው። ሁለተኛው ሰማይ ከዋክብት የሚገኙበት ነው። ብዙዎች ጥቅሶች ወደዚህኛው ሰማይ ያመለክታሉ (ዘፍ. 1፡14)። ሦስተኛው ሰማይ የእግዚአብሔር፥ የመላእክትና ከዚህ ዓለም የሄዱት ቅዱሳት መኖሪያ ነው። ጳውሎስ ያየው ሰማይም ያንን ነው (2ኛ ቆሮ. 12፡2፤ ኤፌ. 4፡10፤ ዕብ. 9፡24)። በዘፍ. 1፡1 እንደምናይ እግዚአብሔር የፈጠረው ሰማይ ከመሬት በላይ ያለው ፍጥረት ሁሉ ነው። ይህም መላእክትን፥ ከዋክብትንና በሰማይ የሚኖሩትን ሁሉ ያጠቃልላል።

7. ቁጥር 2 ፍጥረታት ከተፈጠሩ በኋላ መሬት በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረች ይናገራልን? ምክንያት ስጥ። ኢሳ. 45፡18፤ ኤር. 4፡19-31፤ ሕዝ. 28፡1-15፤ ኢሳ. 14፡9-17።

መልስ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት መሬት ከተፈጠረች በኋላ ጥፋት ደርሶባታል ብለው ያምናሉ። ይህም የተፈጸመው ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1እና2 መካከል ነበር። ከኢሳይያስ፥ ከኤርምያስና ከሕዝቅኤል መጽሐፍ እንደምንረዳው ይህ የሆነው በሰይጣን መውደቅና መፈረድ ጊዜ ነው። (ኢሳ. 14፡12 አጥቢያ ኮከብ) የሚከተለው የዚህ ትምህርት ምክንያት ነው። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ፍጹም የሆነ መሬት እፅዋትና እንስሳን በመልካም እንደችሎታው ፈጥሮ ነበር። ይህም በዘፍ. 1፡1 ከሚሊዮን ዓመታት በፊት ሆነ። «ባዶ» የሚለው ቃል በዘፍ. 1፡2 በመሠረቱ «ከንቱ» ከሚለው በኢሳ. 45፡18 ከሚገኘው ጋር አንድ ነው። በኢሳ. 45፡18 እንደምናነብ እግዚአብሔር መሬትን በከንቱ ወይም ባዶ አድርጎ አልፈጠረም። እንደሌላው ትርጉም ሁሉ አሮጌው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢሳ. 45፡18 እግዚአብሔር ምድርን በከንቱ አልፈጠረም ይላል። እግዚአብሔር በዘፍ. 1፡1 ምድርን ባዶ አድርጎ ካልሠራት 1፡1 እና 2 መካከል አንድ ዓይነት ነገር የተፈጸመ መሆን አለበት። ሁሉን እንድናውቅ እግዚአብሔር አልፈቀደልንም፤ ነገር ግን መሬት የመላእክት አለቃ ሰይጣን በወደቀና በተፈረደ ጊዜ ጠፍታ እንደ ነበር ገልጾልናል።

ኤር. 4፡19-31 በዚህ ቁጥር እንደምናይ ኤርምያስ ስለ ይሁዳ መቀጣት ትንቢት ተናገረ። ከዚያም እንደ ማስጠንቀቂያ አድርጎ የእግዚአብሔርን ፍርድ መክበድ ይገልጻል። በቁጥር 23-26 በዘፍ. 1፡2 የተገለጸውን የመሬትን ሁኔታ ያብራራል። መሬት እንደተፈረደች ወይም በፍርድ ጠፍታ እንደነበር ይሁዳም ለጊዜው ይፈረድበታል የሚል አሳብን ይዞአል፤ (ኢሳ. 24፡1 አንብብ)።

እግዚአብሔር በሕዝ. 28 መሬት ለምን ጨለማና ባዶ እንደነበረች፥ ለምን እንደ ጠፋችና በዘፍ. 1፡2 እንደተገለጠው ለምን ከንቱ እንደነበረች ይገልጽልናል።

በሕዝ. 28 እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ስለጢሮስ ጥፋት ትንቢት እንዲናገር ገልጦለት ነበር። የጢሮስ ንጉሥ ከወደቀው ከመላእክት አለቃ ከሰይጣን ጋር አወዳደረው። ይህ የመላእክት አለቃ ሀብት ነበረው፥ ጥበብ ነበረው፥ ቁንጅናም ነበረው። የጢሮስም ንጉሥ እንደዚሁ ነው። ሰይጣን በትምክህቱና በኩራቱ እንደተፈረደበት ንጉሡም ይፈረድበታል ብሎ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ነገረው (ሕዝ. 28፡12-15)።

እግዚአብሔር ሰይጣንን ምሳሌ አድርጎ የጢሮስን ንጉሥ አስጠነቀቀው። በቁጥር 13 የመላእክት አለቃ በኤደን በእግዚአብሔር አትክልት ቦታ ነበር። የጢሮስ ንጉሥ ግን አልነበረም። የጢሮስ ንጉሥ አልተፈጠረም፥ ነገር ግን

ተወልዶ አድጎ እንደ ሰው ሆነ። የመላእክት አለቃ ከብዙ ሀብት ክብርና ኃይል ጋር ተፈጠረ። በቁጥር 14 እንደምናይ ኪሩብ የሆነው መልአክ ነበር። በቁጥር 15 ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ በደል እስኪገኝበት ድረስ በመንገዱ ፍጹም ነበር። የጢሮስ ንጉሥ በኃጢአት ተወልዶ ነበር። ቁጥር 16 «ከእግዚአብሔር ተራራ ተጣለ» ይህም የወደቀውን መልአክ ያመለክታል። ይህ ንጉሡን ለማስጠንቀቅ በእግዚአብሔር የተሰጠው ምሳሌ ስለወደቀው የመላእክት አለቃ እርሱም ሰይጣን ስለሆነው ይነግረናል።

በኢሳ. 14፡9-14 እግዚአብሔር ለምን ይህ አጥቢያ ኮከብ የተባለው የመላእክት አለቃ እንደወደቀና ምን በደል እንደተገኘበት ይነግረናል። በዚህ ላይ እግዚአብሔር ያንን ምሳሌ ስለ ባቢሎን ንጉሥ ለመተንበይ ተጠቀመበት። ቁጥር 12 «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ!» በቁጥር 13፡16 እንደምናይ የመውደቁ ምክንያት የሆነው ትዕቢት (ኩራት) ነበር። ስለዚህ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ አዘቅት ወደሆነው ሲዖል ወደቀ። በቁጥር 16 ና 17 ኃጢአቱ ከሰይጣን ጋር አንድ ለሆነው የባቢሎን ንጉሥ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

ይህ የመላክእት አለቃ ከሰማይ ስለተጣለ መንግሥቱ በመሬት ነበረች። ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባለው ጥላቻ የተነሳ መሬትን ያጥፋት ወይም እግዚአብሔር የሰይጣን መንግሥት በመሆንዋ መሬትን በፍርድ ያጥፋት ልናውቅ አንችልም። ቀደም ብሎ በተገለጸው ጥቅስ መሠረት ከሆነ እግዚአብሔር ነው በመሬት ላይ የፈረደው። ይህም የተፈጸመው ከዘፍጥረት 1፡1 በኋላ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፤ ምክንያቱም ያ የመላእክት አለቃ በዚያን ጊዜ ተፈጥሮ ስለነበር ነው (ሕዝ. 28፡1፥ 15)። ምናልባትም በዘፍ. 1፡1 ሳይፈጠር አልቀረም። ይህ ፍርድ ከዘፍ. 1፡2 በፊት መፈጸሙ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም በዘፍጥረት 1፡2 መሬት እንደተፈረደባት እናያለን። እግዚአብሔር መሬትን አድሶ አዳምና ሔዋንን በዚያ ባስቀመጣቸው ጊዜ ሰይጣን ለመፈተን በዚያ ነበር። የወደቀው ከዚያ በፊት ነበር። ስለዚህ ሰይጣን ከዘፍጥረት 1 ቁጥር 1 ና 2 መካከል ብቻ ነው ወደቀ ልንል የምንችለው።

እግዚአብሔር መሬትን ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ፈጥሮአት ይሆናል፥ ነገር ግን እግዚአብሔር መሬትን እንደ አዲስ አድርጎ ሲፈጥራት (በዘፍ. 1፡3) በጣም ብዙ ዓመት አላለፈም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑ አስተማሪዎች እንደሚያምኑትና እንደተቀበሉት አዳም የተፈጠረው በግምት ከ6000 ዓመት በፊት ነው።

8. ሀ. በዘፍ. 1፡2 የሚታየው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድር ነው?

ለ. ይህ ስለ እግዚአብሔር ጠባይ ምን ያሳያል?

መልስ።

«የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።» ወደ ሕያውነት ሊመልሳት ሙት በሆነችው ምድር ላይ ይንቀሳቀስ ነበር። በ2ኛ ቆሮ. 3፡6

እንደምናነብ «መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል» ይላል። ያ ስለ ኃጢአተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያመለክት ነው። ነገር ግን አንድ ሕያው ነገር በተፈጠረ ጊዜ የሚከናወነው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ክርስቶስ በዚህ ዓለም ለመኖር ቅዱስና ኃጢአት ያላየው ሥጋ ባስፈለገው ጊዜ የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነበር። ይህም በሉቃስ 1፡35 እንደምናገኘው የሴቲቱ ዘር ሕይወት በኢየሱስ እናት በማርያም ውስጥ ነው። እግዚአብሔር በመንፈስ ሙታን ለሆነችው መሬት ሕይወት ሰጠ። እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ነገር ፈጠረ። መንፈስ ሕይወት የሚሰጥና የሚያነቃቃ ሲሆን ክርስቶስ ደግሞ የሚፈጥር ነው። እግዚአብሔር (ሥላሴ) አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን የሚሠራና የሚፈጥር ነው። ሥላሴ በሥራው ተካፋይ ነው። አንድ ሰው ልዩነቱን ለማወቅ ብሎ የመፍጠርን ሥራ የሚሠራው ማን ነው ቢል መልሱ «ልጁ» ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት። ኤፌ. 3፡9፤ ቆላ. 1፡15ና 16፤ ዕብ. 1፡1 ና 2፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡6፤ ዮሐ. 1፡3።

ለ. እግዚአብሔር ስለ ፍጥረቱ ያስባል። ከጠፉኙ በኋላ አደሳት። ይህ ሰውም በወደቀ ጊዜ ታይቷል። ይድኑ ዘንድ ወዲያውኑ ለአዳምና ለሔዋን የመሢሕ ተስፋ «በሴቲቱ ዘር» ሰጣቸው። እግዚአብሔር አሁንም ለሚጠፉት አስቦ ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ብሎ አዘዘ። ወደ ንስሐና ወደ እምነት ሊያመጣቸው መንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ ውስጥ ይሠራል።

9. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት የማያጠራጥሩት የእግዚአብሔር ፍጥረታት ምንድር ናቸው?

መልስ።

1. ቁጥር 1 እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።

2. ቁጥር 21 እግዚአብሔርም ታላላቆች ዓሣዎችን፥ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾችን፥ የሚተነፍሱም ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፥ እንደወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ።

3. ቁጥር 27 እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ።

በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ዛፍን፥ አትክልትንና ሣርን እንደፈጠረ አናነብም። ነገር ግን መሬት አትክልትን እንድታወጣ ትእዛዝ ሰጣት። ሰይጣን በተፈረደበትና በወደቀ ጊዜ ሕያው ነፍስ ያላቸው ሁሉ ስለሞቱ እንደገና መፈጠር ነበረባቸው። ነገር ግን የአትክልት ሥር በመሬት ውስጥ የቀረ ይመስላል። ሥራቸው እንደተፈጠረ ነበር። ምድሩ በታየ ጊዜ ማደግ ጀመሩ፥ እንደገና ሊፈጠሩ አያስፈልጋቸውም ነበር (ዘፍ. 1፡12)።

ሳይንስ ከ100,000 ዓመታት በፊት ሰው የሚመስል ፍጥረት በመሬት ላይ ነበር ብሎ ይነግረናል። ምክንያቱም ይህን ያህል ዕድሜ አለው ብለው የሚገምቱት የሰው አጥንት የሚመስል አጥንት ስላገኙ ነው። ሳይንስ አጥንቱ ያንን ያህል ዕድሜ እንዳለው ሊያረጋግጥ አይችልም። ደግሞም ሰው የሚመስሉ

እንስሳት ሰይጣን ከመውደቁ በፊት ኖረው ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዚያ አይናገርም። ኖረው እንኳን ቢሆን ሰይጣን በወደቀ ጊዜ የነበረውን ፍርድ አላለፋትም። አዳም አዲስ ፍጥረት ነበር። ዛሬ በመሬት ላይ ያሉ ሰዎች የአዳም ዘሮች ናቸው እንጂ ከ100000 ዓመታት በፊት የነበሩ የእንስሳት ዘር አይደሉም። ያ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ግልጽ ነው።

ደግሞም እግዚአብሔር ከዋክብትን በዚያን ጊዜ አልፈጠረም። በዘፍ. 1፡1 ተፈጥረው ነበር። እግዚአብሔር ከዋክብትን፥ ፀሐይንና ጨረቃን በየወገናቸው አደረገ። ደግሞም የመሬትን መሽከርከር መሬት ለሰው መኖሪያ የምትስማማ እንድትሆን ወራትንና ጊዜን በመከፋፈል ሙቀትንና ብርሃንን እንድትሰጥ አስተካከላት። በቁጥር 16 እግዚአብሔር ፀሐይንና ጨረቃን በቦታቸው በማድረግ ሰውን እንዲያገለግሉ አደረገ። መሬት ሰይጣን በወደቀ ጊዜ ወደ ጨለማ ውስጥ የተጣለችና እግዚአብሔርም ሰውን እንድታገለግል በዚህም ፍላጎቱን እንድታሟላ ወደ አስፈላጊነትና ወደጥቅም የመለሳት ይመስላል።

10. እግዚአብሔር ሲፈጥር በሰው ላይ የጫነው ኃይል፥ ሥራና የማያቋርጥ ኃላፊነት ምን ነበር? ዘፍ. 1፡28።

መልስ።

እግዚአብሔር አዳምን ንጉሥ እንዲሆንና በመሬት ላይ እንዲገዛ ፈጠረው። ስለዚህ አዳም በመሬት ላይ ላሉት ሁሉ በእግዚአብሔር የተሾመ ኃላፊ ነበር።

11. ምዕራፍ 1 ና 2 ፍጥረት ሁሉ በፍጹም የማይለወጡ ሆነው መኖር የጀመሩ መሆናቸውን ያሳያልን? ምዕራፍ 1፡11፥ 12፡21፥ 24፥ 25፤ 2፡5፥ 19፡20።

11. በሰውና በእንስሳት መካከል ግንኙነት ወይም አንድነት አለን?

መልስ።

ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር «እንደ ወገኑ» እንዲበዛ መፍጠሩን ያሳያል። ማንኛውም እንስሳ ወይም አትክልት ወፍ ወይም ዓሣ ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዲለወጥ አልተፈቀደለትም። በተፈጠሩ ጊዜ እንደ ነበሩ በየወገናቸው ዛሬም እንደዚያው ናቸው (ዘፍ. 2፡19)። እንስሳት ወፎችና ዓሦች ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚፈልጋቸው ሆነው ከምድር አፈር ተፈጠሩ። አዳም ደግሞ ከምድር አፈር ነበር የተሠራው፥ ከመጀመሪያ ሰው ነበር፥ አሁንም ሰው ነው። ለወደፊትም እስከ ዘለዓለም ሰው ይሆናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጹልን ዘመናት ሁሉ ከአንዱ ወገን ወደሌላው ለመለወጥ (ኢቮሉሽን) ከእግዚአብሔር ፈቃድ አልተሰጠም። ከሰይጣን መውደቅ በፊት ከአንዱ ወገን ወደሌላው የመለወጥ ደረጃ እንደነበር እንኳን ማወቅ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አይናገርም። ቢኖርም እንኳን ሰይጣን ሲወድቅ ጠፍቶአል። መሬት ከታደሰች በኋላ ከዘፍ. 1፡3 ጀምሮ ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው መለወጥ አልነበረም። ከሰይጣን መውደቅ በኋላ በበቀለው በአትክልት ላይ እንኳን ሲፈጸም አናይም።

ይህ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። ዘፍጥረት 2፥4-3፥24 አንብብ።

12. ሀ. እግዚአብሔር የሰውን አካል ከምን ሠራው?

ለ. ፍጹም የሆነ መፍጠር ነበርን?

መልስ።

ሀ. እግዚአብሔር የሰውን አካል ከምድር አፈር አበጀው።

ለ. የመፍጠር ሥራ አልነበረም። እግዚአብሔር የአዳምን አካል በፊት ተፈጥሮ ከነበረ ነገር አበጀው። አበጀው እንጂ አልፈጠረውም።

ሐ. በዘፍ. 1፥26 ና 27 እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ። መንፈሱንና ነፍሱን ፈጥሮ ሕይወት ሰጠው። መንፈሱና ነፍሱ ከዚያ በፊት አልነበሩም። ተፈጠሩ። የመንፈሱና የነፍሱ መኖሪያ የሆነው አካሉ ግን ተበጀ። በዘፍ. 2፥7 እግዚአብሔር በሰው አፍንጫ ውስጥ የሕይወት እስትንፋስ እፍ ባለበት ጊዜ የመፍጠር ሥራ ነበር። ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። ሰው በእግዚአብሔር እስትንፋስ ዘለዓለማዊ ነፍስ ሆነ። ይህም ሰውን ከእንስሳ የተለየ አደረገው። እንስሳት ነፍስ አላቸው፥ ነገር ግን መንፈስ የላቸውም። ሰው መንፈስ ስላለው ነፍሱ ዘላለማዊ ነው። ሦስት የተለያዩ ፍጥረታት አሉ።

1. አትክልቶች አካል ብቻ እንጂ ነፍስና መንፈስ የላቸውም። ይኖራሉ፥ ያድጋሉ፥ ይባዛሉ፥ ይሞታሉ።

2. እንስሳት አካልና ነፍስ አላቸው። የነፍሳቸው ቋንቋ ፍቅር፥ ጥላቻ፥ ስሜት፥ የጋለ ስሜት፥ ፍላጎት ነው። እንስሳት ያ ሁሉ አላቸው። ነገር ግን ዘላለማዊ ነፍስ የላቸውም። ነፍሳቸው በሥጋቸው የተያዘ ስለሆነ ሥጋቸው ሲሞት ነፍሳቸው አብሮ ይሞታል። ኢዮብ 12፥10 ተመልከት።

3. ሰው አካል፥ ነፍስና መንፈስ አለው። መንፈስ ሁሉ ለዘላለም ይኖራል። የሰው ነፍስ ከሰው መንፈስ ጋር በመዋሃዱ «ሕያው ነፍስ» ያለው ሆነ (ዘፍ. 2፥7)። ደግሞም ለዘለዓለም የሚኖር ነፍስ ሆነ። የመንፈስ ቋንቋ ጸሎት፥ አምልኮ፥ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ሰዎች ሁሉ ቢያምኑም ባያምኑም እግዚአብሔርን ያውቃሉ። ደግሞም አሕዛቦች ሁሉ ያውቃሉ፥ ነገር ግን ምንም ብልጥ ቢሆን እንኳ ከእንስሳት ውስጥ አንድም እግዚአብሔርን የሚያውቅ የሚያመልክና የሚጸልይ የለም። ምክንያቱም መንፈስ ስለሌለው ነው። ይህም ሰው እንስሳ እንዳልሆነ ሌላው ማረጋገጫ ነው። የተለየ ፍጥረት ነው።

13. እግዚአብሔር የሔዋንን አካል ከምንድር ነው የሠራው? ዘፍ. 2፥21-25

መልስ።

እግዚአብሔር የሔዋንን አካል ከአዳም የጎድን አጥንት ሠራው። ስለዚህ ሴት ከወንድ ጋር አንድ አካልና አንድ አጥንት ናት (ዘፍ. 2፥23)። ባልና ሚስት

የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት (ዮሐ. 3፡28፥ 29፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡2፤ ኤፌ. 5፡25-32፤ ራእይ 19፡7-9)። አዳምና ሔዋን ያለ ኃጢአት በነበሩ ጊዜ እግዚአብሔር እንደፈለገው በሁሉ ነገር ፍጹም አንድነት ነበራቸው።

14. ለመጀመሪያው ሰው ስለተሠራለት ቤት አብራራ። ከዚያ የላቀ ቤት ሊሠራለት ይቻል ኖሮአልን?

መልስ።

እግዚአብሔርም በኤደን ገነት አትክልትን ተከለ (ዘፍ.2፡8)። እግዚአብሔር የተከለው አትክልት ማንም ሰው ሊተክለው ከማይችለው በላይ የሆነ የተሻለ አትክልት ነው (ዘፍ. 1፡29)። እግዚአብሔርም የተለያዩትን ዓይነት ምግቦች ማለት እንደ ፍራፍሬ እህልና አትክልት ያሉትን ለአዳም መብል አድርጎ ሰጠው። የሚጠቅሙትን ነገሮች ሁሉ አብዝቶ ተቀበለ። እያንዳንዱም ዛፍ ለዓይን ያማረና ለመብልም መልካም ነበር (ዘፍ. 2፡9)። የሕይወት ዛፍና ክፉውንና ደጉን የሚያስለየውም ዛፍ በዚያው ነበር። ከኤደን ገነት ውስጥም የሚፈስ አንድ ወንዝ ነበር። ይህም ወንዝ ከአትክልቱ ውጭ እንደወጣ ለአራት ተከፍሎ አራት ወንዝ በመሆን ይፈሳል (ዘፍ. 2፡10)። የእግዚአብሔር ሥራ ሁልጊዜ ፍጹም ነው። ስለዚህ ሊስተካከልና ሊታረም የሚገባው ምንም ነገር የለም።

15. እግዚአብሔር ለሰውዬው ምን ትእዛዝ ሰጠው? ደግሞስ ትእዛዙን ባይጠብቅ ምን ቅጣት ተወስነበት?

መልስ።

ዘፍ. 2፡17 ትእዛዝ «ክፉውንና ደጉን ከምታስታውቀው ዛፍ አትብላ» የሚል ሲሆን፥ ትእዛዙን ባይጠብቅ ደግሞ የሚደርስበት ቅጣት «ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» የሚል ነበር። እነርሱም ከዚያች ዛፍ በበሉ ዕለት መንፈሳዊ ሞት ሞተው ከዚያም በኋላ ቆይተው ሥጋዊ ሞት ሞቱ። መንፈሳዊ ሞት በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው (ሮሜ 8፡6)። ሞት ማለት ለብዙዎቻችን እንደሚገባን በሕይወት መኖርን ማብቃት ማለት ሳይሆን መለየት ማለት ነው። መንፈሳዊ ሞት ማለት ኃጢአት በመኃል ስለገባ የነፍስና የመንፈስ ከእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ያልዳኑ ሰዎች ሁሉ መንፈሳዊውን ሞት የሞቱ ናቸው።

ሥጋዊ ሞት የነፍስና የሥጋ መለየት ነው። አንድ ሰው ነፍስም መንፈስም ሥጋም ስላለው እነዚህ ሦስቱ ሲለያዩ ሞተ ይባላል። «ሁለተኛው ሞት» ግን የመጨረሻውና ያልዳኑት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር የሚለዩበት ነው። እነርሱም ለዘለዓለም በሕይወት ይኖራሉ። ነገር ግን ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር እንደተለዩ ይቀራሉ (ራእይ 20፡14፤ 21፡8)። ከዚህም በቀር ሮሜ 6፡23 እና ሕዝ. 18፡4፡20 ተመልከት።

16. እግዚአብሔር ለፈጠራቸው እንስሳት ሁሉ ስም ያወጣላቸው ማን ነው?

መልስ።

በዘፍ. 2፡19 ላይ እግዚአብሔር ሕያው ነፍስ ያላቸውን ፍጥረቶች ሁሉ ወደ አዳም እንዳመጣቸውና አዳምም ስም እንዳወጣላቸው እናነባለን። ይህም ደግሞ አዳም እንደ እንስሳቶቹ ጠባይና መልክ ስም በማውጣቱ አዳም በዚያን ጊዜ የነበረውን ከፍተኛ የማስተዋል ችሎታ ያመለክታል። አዳም በመማር እውቀቱን አላዳበረም። እርሱም እግዚአብሔር በፈጠረው ቀን ፍጹምና አዋቂ ሆኖ ተፈጠረ። «ኢቮሉሽን» የተባለው ትምህርት እንደሚያስተምረው የመጀመሪያው ሰው ከዝንጀሮነት እየተሻሻለ በመምጣት ሰው አልሆነም። እርሱም ቀጥታ በእግዚአብሔር እጅ እንደ ተሠራ ፍጹምና አዋቂ ሆኖ ተፈጠረ።

17. ዘፍ. 2፡8-11፤ 26፡3፥ 4፤ ዘጸአት 23፡31፤ ዘኁልቁ 34፡3፤ ዘዳ. 1፡24፤ ሕዝቅ. 47፡18 በምድር ላይ የኤደን ገነት በየትኛው ስፍራ ነበር የሚገኘው? በተጨማሪ ደግሞ ሕዝ. 15፡17፤ ዘዳግም 32፡8፥ 9፤ መዝ. 86(87)፡1፥ 2፤ ዘኁልቁ 35፡34 ተመልከት። የዔደን ገነት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እርስት አድርጎ በሰጣቸው ምድር እንደሆነ አመልከት።

መልስ።

እንደነዚህ ጥቅሶች ከሆነ የዔደን ገነት የምትገኘው በአረባውያን መሬት ማለት በሰሜኑ በኩል አድርጎ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ከዚያም እስከ ታላቁ ባሕር ይደርሳል። ይህ ነው ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ እስራኤል የምትወርሰው ድንበርዋ። እግዚአብሔርም አትክልትን በዔደን ገነት በስተምሥራቅ በኩል ተከሎ ነበር (ዘፍ. 2፡8)። ይህም ማለት የኤፍራጥስ ወንዝ የሚዞርበትን ባቢሎንን ይዞ ወንዙ እስከገባበት እስያ ሸልቆ ድረስ ነው።

18. የአዳምንና የሔዋንን ፈተናና ውድቀት አብራራ፤ በተጨማሪ ደግሞ የያዕቆብን መልእክት ምዕራፍ 1፡12-15 ያለውን አንብብ።

መልስ።

ሰይጣን በዓለም ውስጥ እንደመኖሩ ሁሉ አዳምና ሔዋንን ምንም ስለ ኃጢአት ሳያውቁ ኃጢአት አሠርቶ እንዲጠፉ ባደረጋቸውም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ክፉንና ደጉን የምታስታውቀውን የዛፍ ፍሬ በዔደን ገነት ተከለ። ከእርሷም እንዳይበሉ ክለከላቸው፤ እነርሱም ክፉ ምን እንደሆነና ደግ ምን እንደሆነ ያውቁ ነበር። እግዚአብሔርን መታዘዝ መልካምና ሕይወት ነው። ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ክፉ የሆነና ሞት ነው። እግዚአብሔር ካስጠነቀቃቸው በኋላ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በመረጡ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን በክፉ ባይፈትንም ሰዎች ክፉውን ነገር ለማድረግ መረጡ (ያዕቆብ 1፡13)። እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ከነበረች ከክፉዋ ዛፍ ሰውን አስጠንቅቆት ነበር። ሰው ግን አልታዘዘም። አዳምና ሔዋን ኃጢአት

ማድረጋቸውን ሳያውቁ በየዋህነት ሰይጣንን እንዳይከተሉትና ሳይሞቱ በሕይወት እንዲኖሩ እግዚአብሔር ያችን ዛፍ በዔድን ገነት ውስጥ ተከለ።

ያዕቆብ 1፡14 «እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።» ሔዋን «ዛፉ ለመብል መልካም እንደሆነ አየች፤» ይህም የሥጋ ምኞትና ፈተና ነው። ያም ደግሞ «ለዓይን ያማረ ነው።» ለእርሱዋም መልካም እንደሆነ ታያት። ይህም ደግሞ የዓይን አምሮት ፈተና ነው። «ይህም ዛፍ የሚመኙትን ዓይነት ጥበብ ይሰጣል ስለተባለ ነው። ይህም ደግሞ በሕይወት የመታበይ ፈተና ነው።» (ዘፍጥ. 3፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡16)። ሔዋን በራስዋ ምኞት ተፈትና ወደቀች። «እርሷም ከዛፍ ፍሬ ወስዳ በላች ለባልዋም ሰጠችው፤ እርሱም በላ።» ያዕቆብ 1፡15 «ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤» ሰው ኃጢአትን ሲሠራ ሞትን ይወልዳል ማለት ነው። አዳምና ሔዋን አስቀድመው መንፈሳዊ ሞት ከሞቱ በኋላ የሥጋ ሞትና የዘለዓለም ሞት መርገም ወደቀባቸው።

ኢየሱስ በማቴ.4፡1-4 እንደተጠቀሰው በእነዚህ በሦስቱም ፈተናዎች ተፈትኖአል። በማቴ. 4፡1-4 በሥጋ ምኞት ፈተና ተፈትኖአል። ከቁጥር 5-7 ባለው ክፍል ደግሞ በኩራት ፈተና ተፈትኖአል። ከቁጥር 8-11 ባለው ክፍል ደግሞ በዓይን አምሮት ፈተና ተፈትኖአል። የሥጋ ምኞት የሥጋ ፈተና ነው። የዓይን አምሮት ደግሞ የነፍስ ፈተና ሲሆን፥ የኩራት ወይም የመመካት ፈተና ደግሞ የሰው መንፈስ ፈተና ነው።

19. እውነተኛው ፈታኝ ማን ነው? ራእይ 12፡9፤ ዮሐ. 8፡44

መልስ።

ዘፍ. 3፡1 እባቡ ሔዋንን በማናገር ፈተናት። በእባብ አምሳያ መጥቶ ሔዋንን የፈተናት ሰይጣን ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን እባብ ተባለ (ራእይ 12፡9)። አሁን እባብ ቢናገረን እኛም ብንሆን እንፈራለን። ሆኖም በዔድን ገነት ከነበሩት እባብ በጣም የሚያምር ፍጥረት ነበረ። ለዚህ ነው እንግዲህ ሰይጣን እባብን የመረጠው፥ የእባቡም መናገር ሔዋንን አላስጨነቃትም ነበር። ምክንያቱም አስቀድማ ስለ አንድ ክፉ ስለሆነ ነገር ስለማታውቅ ነው። ሔዋን በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ፍጡሮች አዲስ የተለያየ ነገር ትመለከት ስለነበር የእባቡ መናገር አላስደነቃትም ነበር። ለእርስዋ ይህ ነገር ሌላ አዲስ የተለየ ነገር ነበር።

20. ሀ. ሰይጣን ምን ዓይነት አስቸጋሪ ውሸት ነው ለሔዋን ያቀረበላት?

መልስ።

ዘፍጥ. 3፡1 «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።» ሰይጣንም የጥያቄውን አሳብ በአዕምሮዋ ውስጥ አኖረ። ይህም ጥያቄ በሔዋን አእምሮ እየተመላለሰ በእውነት እግዚአብሔር ፍቅር ከሆነ ከዚህ ከዛፍ ፍሬ እንዳንበላ አይከለክለንም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር አትብሉ ማለቱ ላይሆን ይችላል ብላ አሰበች። ስለዚህ ሔዋን በአሳብዋ ወላወለች፥ በዚህም ምክንያት የሚሆነው ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው ለሰይጣን አለመመለስዋ

ነው። ቃሉን ለወጠችው። እግዚአብሔር አዳምን «ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» አለው እንጂ ሔዋን እንዳለችው «እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም» አላለም። ቁጥር 3 እራሳችንን ደስ ለማሰኘት የእግዚአብሔርን ቃል ስንለውጥ ኃጢአት መጥፎ ነገር አይመስልም። ነገር ግን በኃጢአት እንወድቃለን።

20. ለ. ሰይጣን በድፍረት ያቀረበው ውሸት ምን ነበር?

መልስ።

ሰይጣን ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል እንደለወጠች ባየ ጊዜና የተለወጠውም ቃል በኃጢአት ላይ የሚመጣውን ጠንካራ ፍርድ እንደሚያሳይ በተመለከተ ጊዜ ሔዋንን በድፍረት «ሞትን አትሞቱም» አላት። ቁጥር 4 በሌላ አነጋገር ነገሩ በጣም የቀለለና ኃጢአት እንኳ ሊባል እንደማይቻል አድርጎ ተናገረ። ሰይጣንም እርሷ ትመኘው የነበረውን እንደ እግዚአብሔር አዋቂ የምትሆንበትን መንገድ አሳያት። እርሷም ከእግዚአብሔር እኩል የሚያደርጋትን ጥበብ ስትመኝ እግዚአብሔርን ባሪያዎቹ ሊያደርጋቸው ስለሚፈልግ እንደ እርሱ ጥበበኛ እንዲሆኑ እንዳልፈቀደላቸው አስመስሎ ተናገረ።

ከዚያም ሔዋን እግዚአብሔር ቸር አልሆነልንም ብላ ስለአመነች ታላቅ ለመሆን የተከለከለውን ፍሬ ወስዳ በላች። ቁጥር 5 ይህ ሁሉ ምክንያት መፍጠር በዚህ ጥቅስ ውስጥ ይታያል። ለአዳም ደግሞ ሰጠችው፤ እርሱም በላ። ሔዋን ተታለለች፥ አዳምም የኃጢአቱን ታላቅነት ያውቅ ነበር። እርሱም እውነቱን እያወቀ ሳለ በድፍረት በላ። እርሱም አልተታለለም። ስለዚህ የአዳም ኃጢአት ከሔዋን ኃጢአት እጅግ ይበልጣል (1ኛጢሞ. 2፡14)።

21. የአዳምና የሔዋን የመውደቃቸው ውጤት ምንድር ነው?

ሀ. ራሳቸው ከሆነው ከክርስቶስ ጋር ካላቸው አንድነት።

መልስ።

ሰዎችም ከእግዚአብሔር ጋር (ከክርስቶስ ጋር) በዔድን ገነት ከነበራቸው አንድነት ተነጠሉ፤ አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር ተሸሸጉ። እነርሱም ኃጢአት ከእግዚአብሔር ስለለያቸው ፈሩ፤ ሰውነታቸውንም ሸፍነው ከእግዚአብሔር ለመሸሸግ ሞከሩ (ዘፍ. 3፡7-8፡10)። ይህ ከእግዚአብሔር አንድነት መለየትና ኅብረትን ማቋረጥ መንፈሳዊ ሞት ይባላል (1ኛ ጢሞ. 5፡6፤ ኤፌ. 2፡1፤ ራእይ 3፡1)። እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት በነበራቸው ጊዜ ያላቸውን ክብርና ኃጢአት የሌለበት ሕይወት አጡ። ለዚህ ነው እንግዲህ ወዲያውኑ መራቆታቸው የተሰማቸው።

21. ለ. የሰው የመንፈሳዊ ሕይወቱ ውጤት ምንድር ነው?

መልስ።

ሰውም በመንፈሱ የሞተ ፍጡር ሆነ፤ ይኸውም ከእግዚአብሔር አንድነትና ኅብረት መለየት ነው። የሰውም ሕይወት ቅዱስ በመሆን ፋንታ ኃጢአትን የተሞላ ሆነ።

21. ሐ. የሰው የሰብዓዊ ሕይወቱ ውጤት ምንድር ነው?

መልስ.

ሰው ሥጋዊን ሞት እንዲሞት ተፈርዶበታል (ዘፍ. 3፡19)። ከዚህም በቀር ለዕለት ኑሮ መተዳደሪያ በርትቶ እንዲሠራ ተደርጓል (ዘፍ. 3፡17፥ 18)። ምድርም በሰው ምክንያት የተረገመች ሆነች። ሔዋንም ልጆችን በጭንቀት እንድትወልድ ተደረገች (ዘፍ. 3፡16)። አዳምና ሔዋንም በገነት ካለችው የሕይወት ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ ከገነት ተባረሩ (ዘፍ. 3፡22-24)። ያንን የሕይወት ዛፍ ቢበሉ ኖሮ የማይሞተውን ኃጢአተኛ አካል ለብሰው ለዘለዓለም በኖሩ ነበር። ብዙዎች ሰዎች በእጃቸው ሥራ እንዲሁም በኀዘንና በፍርሃት ተናዘው ከሞት በኋላ የሚገኘውን ሕይወት ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተበትን ሌላ የሕይወት ዛፍ ተከለ። ስለዚህ ማንም ከኃጢአቱ ተመልሶ በእምነት ከዚህ የዛፍ ፍሬ የሚበላ ሁሉ ለዘለዓለም ይኖራል። ይህንንም የዘለዓለም ሕይወት ኑሮ የሚኖረው ኃጢአተኛውን አካል ለብሶ አይደለም። ነገር ግን በትንሣኤ ቀን የሚቀበለውን አዲሱን አካል ለብሶ ይኖራል። አዲሱ አካል ኃጢአት፥ ፈተና፥ ሕመምና ኃዘን ወይም ሞት አይኖርበትም። እግዚአብሔር በገነት የነበረችውን የሕይወት ዛፍ እንዳይበሉ በመከልከል ሌላ የተሻለ መንገድ ለሰው አዘጋጀ። ስለዚህ ሰው አሁን በእምነት ከክርስቶስ ሥጋ በመብላትና ከደሙ በመጠጣት አዲስ መንፈሳዊ አካል ለብሶ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ይኖራል (ዮሐ. 6፡48-59)።

21. መ. ሰው ከኃጢአት ጋር ተባብሮ የማድረጉ ውጤት ምንድር ነው?

መልስ።

ሰውም የኃጢአት ባሪያ ስለሆነ ከዚህ ባርነት ራሱን ነፃ ማውጣት አይችልም። ሰውም በበደሉና በኃጢአቱ ሞቶአል (ኤፌ. 2፡1-33)።

21. ሠ. ሰው ከሰይጣን ጋር ከሚኖረው ግንኙነት የተነሳ ውጤቱ ምን ይሆናል?

መልስ.

ሰው አሁን እንኳ እየታዘዘው ካለው ከሰይጣን ኃይል በታች ሆኖአል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የሰይጣንን ፈቃድ ስለሚያደርጉ የሰይጣን ልጆች ይላቸዋል። እነርሱም ከሰይጣን ቤተሰብ ካላቸው አንድነት ካልሞቱ በስተቀር ከእርሱ ጋር በእሳት ባሕር ውስጥ ለዘለዓለም ይሰቃያሉ (ዮሐ. 8፡44፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡10)። ስለዚህ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ዳግመኛ ልደትን መቀበል አለባቸው። በዚህ ፋንታ ግን እነርሱ ሰይጣንን በመግዛት ፋንታ ሰይጣን

እነርሱን ገዝቶአቸው እናያለን (ዘፍ. 4፡7)። ከዚህም በቀር ማቴ. 13፡38 እና የሐዋ. ሥራ 13፡10 ተመልከት።

21. ረ. ሰው በፍጥረታት ላይ ሁሉ እንደመሾሙ በሥልጣኑ ላይ ምን ደረሰበት?

መልስ።

ሰው ምድርን በሰላም የመግዛቱን ኃይል አጣ። ፍጥረታትም በሙሉ ከሰው ጋር ከእርግማን በታች ሆኑ። ይህም በሮሜ 8፡18-23 ባለው ክፍል ውስጥ በሚገባ ተብራርቶአል። ንጉሥ ኃጢአትን በሚያደርግበት ጊዜ በኃጢአቱ ውጤት በግዛቱ ያሉት ሕዝቦች በሙላ ይሰቃያሉ። አዳም በኃጢአት በወደቀ ጊዜ በእርሱ ግዛት ያሉት ማለት የምድር ፍጥረታት በሙላ መሰቃየት ነበረባቸው።

21. ሰ. የሰው ልጅ የኃጢአቱ ውጤት በዘሩ ላይ ማለት (በልጆቹ) ላይ ምን አመጣ?

መልስ።

የሰውም ልጆች ሁሉ ከአዳም የወረሱትን ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ተቀበሉ። ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ምን እንደሆነ ከማወቃቸው በፊት ኃጢአተኞች ሆኑ። ሁሉም የጠፉ ሆኑ፤ ምክንያቱም ሁሉም በተፈጥሮ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ነው። ስለዚህ አዲስ በመወለድ በእግዚአብሔር ተአምራታዊ ሥራ አዲስ ፍጥረት ካልሆነ ማንም የመዳን ተስፋ አይኖረውም። ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት ሁሉ ስለሞተ እስከ አሁን ኃጢአት ምን እንደሆነ የማያውቁ ሕፃናት ብቻ ይድናሉ (1ኛ ዮሐ. 2፡2)። ነገር ግን እነዚህ አድገው ምርጫ የማድረግ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ለመዳን ምርጫ ማድረግ አለባቸው።

22. እያንዳንዳቸው ምን ዓይነት ፍርድ ተቀበሉ?

ሀ. ሰውዬው ለ. ሴቲቱ ሐ. እባቡ?

መልስ።

ሰውዬው፡- ሰውዬው በትጋት ካልሠራ በቀር ምድር ፍሬዋን እንዳትሰጠው ምድር በሰውዬው ምክንያት ተረገመች (ዘፍ.3፡17)። ምድርም እሾክና አሜከላ በማውጣት ሰውዬው በፊቱ ወዝ ጥሮና ግሮ የዕለት ምግቡን እንዲያገኝ ተደረገ (ዘፍ. 3፡18)። እርሱም መሞትና አካሉም ወደ ትብያ አፈር መመለስ አለበት (ዘፍ. 3፡19)። የከባድ ሥራ መርገም በአዳም ላይ የመጣው ለአዳም ጥቅም ነው። ዛሬም ቢሆን ብዙ ሥራ መፍታት ባለበት ቦታ ሁሉ ኃጢአት ይበዛል። አዳምም ቤተሰቡን እንዲጠብቅና እንዲረዳ ከሔዋን ይልቅ በሥጋው ጠንካራ ሆኖ ተፈጥሮአል። በዚህ ዓለም ሰይጣን የሚጠቀመው ደካማ በሆነው በኩል ነው። ስለዚህ ሴቲቱ በኃይለኛው ተገደደች። በዚህ ምክንያት ወንድ ከባዱንና አስቸጋሪውን ኃላፊነት ተሸክሞ አብዛኛውን ሥራ መሥራት ተገባው።

ለ. ሴቲቱ:- ጭንቀትዋ የበዛ ይሆናል፥ እርሷም ልጆችን በጭንቀትና በመከራ ትወልዳለች፥ ባልዋም ይገዛታል (ዘፍ.3:16)። እርሷም ደግሞ በሕይወትዋ መጨረሻ ወደ አፈር ትመለሳለች። ልጆችን በጭንቅ መውለድዋና በባልዋ መገዛትዋ ለእርሷ ጥቅም ነው። ማለት ሔዋን ትምክህቷ በአዳም ከለላ ሥር በማድረግ የምትተማመን ስለሆነች ይህንን እንደ ቅጣት ከቆጠረችው በእውነት መታለል ነው (1ኛ ጢሞ. 2:14)። እርሷም ረዳት ለመሆን ስለተፈጠረች በመግዛት ፋንታ ለመገዛትና ለመመራት ለወንድ ተሰጥታለች። እርሷም በሰይጣን ከመመራት በአዳም በተመራች ነበር። እርሷም በተፈጥሮዋ በጣም ወላዋይና በስሜትዋ የምትገፋ ስለሆነች ለሥራው የበለጠ ተገቢ እንደሆነች ይመስላት ነበር። እግዚአብሔር የመረጠላት ለባልዋ ረዳት አጋዥና ደጋፊ እንዲሁም ልጆችዋን በሚገባ አሳዳጊ እንድትሆን ነው። ቢሆንም ያነሰና ዝቅተኛ ችሎታ አልነበራትም፤ ነገር ግን በቀላሉ ትሳብና ትታለል ነበር። ስለዚህ ሔዋን እንደዚህ ያለውን ከፍተኛ እርምጃ ከመውሰድዋ በፊት ባለቤትዋን መጠየቅ ነበረባት። ነገር ግን በሌላው ማለት በክፉው አነሳሽነት ተደልላ ተሳሳተች። ሴት እግዚአብሔር ላዘጋጀው ለአንድ ለተለየ ጠቃሚ ነገር የተፈጠረች ስትሆን እግዚአብሔር ለወንድ በሰጠው ሥራ ውስጥ ዘሎ መግባት አልተፈቀደላትም ነበር። ይኸውም ሕዝብንና ቤትን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ነው።

ይህም ሆኖ በእግዚአብሔር አነሳሽነት ሴቶችንም የሕዝብ፥ የቤተ ክርስቲያን፥ እንዲሁም የቤተ ሰብ ገዢ ያደረገበት ጊዜ እንደነበረ የሚያስረዱ ብዙ ታሪካዊ ምሳሌዎች አሉ። በዚህ ደረጃዋ ሴት ልትናቅና በዝቅተኛነት ልትገመት አይገባም። በዚህ ፋንታ ግን እግዚአብሔር በወጠነላት ዓላማ ላይ ስትገኝ ከፍ ከፍ ልትደረግና ልትከበር ይገባታል። እግዚአብሔር የሰጣትን መልእክት ፈጽማ ከተገኘች ዋጋዋ ታላቅ ይሆናል። (1ኛ ቆሮ. 11:3፤ 14:34፤ ኤፌ. 5:22፥ 23፤ 1ኛ ጢሞ. 2:11-15፤ 1ኛ ጴጥ. 3:1-6፤ የሐዋ. ሥራ 2:17)። ይህ ቀርቶ ሴቶች ትንቢት እንኳ እንደ ተነበዩ ማየት እንችላለን። ለሴቶች ያልተፈቀደላቸው አንድ ነገር ወንድን እንዳይገዙና በወንድ ላይ እንዳይሰለጥኑ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህንን ሥራ ስላልሰጣቸው ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳ የመናገር ዕድል ቢገጥማት ሥልጣኑ ስብሰባውን ከሚመራው ሰው በታች ነው።

ሐ. እባብ:- ሰይጣን እባብን ስለተጠቀመበት እባብ የሰይጣንና የኃጢአት ምሳሌ ሆኖ ከመርገም በታች ሆነ (ዘፍ.3:14)። እባብም ከእንስሳቶችና ከምድር አራዊት ሁሉ ተለይቶ የተረገመ ሆነ (ራእይ 20:2)። እባብም ከመጀመሪያ የሚያምርና እግርም የነበረው ይመስላል። ከዚያ በኋላ ግን ተረገመና በሆዱ እየተንፏቀቀ አፈርን እንዲበላ ተረገመ። እባብም ከፍጥረት ሁሉ በሰው ዘንድ የተጠላ ነው። ሙሴ በእንጨት ላይ የሰቀለው የናስ እባብ ስለ እኛ መርገምና ኃጥዕ የሆነው የክርስቶስ ምሳሌ ነው (ዘኁልቁ 21:5-9፤ ዮሐ. 14:15፤ 2ኛ ቆሮ. 5:21)።

23. ሀ. አዳም ምን ዓይነት ምክንያት ለእግዚአብሔር ሰጠ?

መልስ።

እግዚአብሔር አዳምን ስለ ኃጢአቱ በጠየቀው ጊዜ አዳም እንዲህ አለ። «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ።» (ዘፍ.3፡12)። እርሱም ጥፋቱን በሴቲቱ ላይ አደረገ። እንደ እርሱ አባባል ከሆነ ሴቲቱን የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ ጥፋቱ የእግዚአብሔር መሆኑ ነው። በሌላ አነጋገር «አዳም ይህችን ወደ ኃጢአት የመራችኝን ሴት ለምን ሰጠኸኝ ማለቱ ነው።» ኃጢአትን በምናደርግበት ጊዜ እራሳችንን ታላቅ ኃጢአት እንዳላደረግን አድርገን እንገምታለን። ሁልጊዜ እራሳችንን ነፃ ለማድረግ ሌላውን በደለኛ ለማድረግ እንሞክራለን። ያም ሆኖ ይህ ፍርዱ ሞት ነው። ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ጥፋት ነው። ኃጢአታችንን ተገንዝበን በኃጢአታችን ብንናዘዝ ይቅርታንና ፈውስን እናገኛለን።

23. ለ. ሔዋን ምን ዓይነት ምክንያት ሰጠች?

መልስ።

ሔዋንም፡- «እባብ አሳተኝና በላሁ» አለች (ዘፍ.3፡13)። በእርሷም በኩል ራሷን ነፃ ለማድረግ በሌላው አመካኘች። እንደገናም፥ ኃጢአተኛ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ተናዞ ንስሐ ቢገባ ይቅርታ ይደረግለታል። በሉቃስ 18፡9-14 የተጠቀሱት ፈሪሳዊና ቀራጭ ምሳሌ ናቸው።

መልስ።

የኃጢአት ዋጋ ሞት ስለሆነ የሰው ልጆችን ከሞት ለማዳን አዳኝ አስፈለገ። እግዚአብሔር በዘፍ. 3፡15 ላይ የክርስቶስን የመምጣቱን ተስፋ በመጀመሪያ ጊዜ ለአዳምና ለሔዋን ነገራቸው። የሴቲቱም ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል፥ ማለት የሰይጣንን ራስ። ይህም ከሴት ይወለዳል የተባለው አንድ ብቻ ነው። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከእርሱ በቀር ሌላው ሰው ሁሉ ከሴትና ከወንድ ዘር የተወለደ ነው። ክርስቶስ ብቻ ምድራዊ አባት አላስፈለገውም ነበር። እርሱም ከዘለዓለም ጀምሮ እግዚአብሔር ነው። እርሱን ያስፈለገው የሰው አምሳል የሚሰጠው ሥጋዊ አካል ብቻ ነበር። አካሉም የተዘጋጀለት በመንፈስ ቅዱስ ተአምራታዊ ሥራ ነበር። በሉቃስ 1፡35 ላይ መንፈስ ቅዱስ በማርያም ሆድ ውስጥ ለነበረው የሴት ዘር ሕይወትን እንደሰጠው እናነባለን። ይህም ደግሞ በምድራዊ አባት የተደረገ አይደለም። ክርስቶስ ምድራዊ አባት ስለሌለው ከሴት ዘር ብቻ የተወለደ ነው። የወንድ ዘር ቢኖርበት ኖሮ የአዳምን ኃጢአት ይወርስ ነበር። እንደዚህ ቢሆን ኖሮ እንደማንኛውም ሰው ኃጢአት ስለሚኖረው የዓለም አዳኝ ባልሆነም ነበር። መንፈሱ አምላክ ስለሆነ በዚህ ምክንያት ኃጢአት የሌለበት ሆነ። የአካሉም ሕይወት የተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ አካሉ የአዳምንም ሆነ የሌላን ሰዎች ኃጢአት አልወረሰም። የሔዋን ኃጢአት በሕፃን አይወረስም። እርሷ ማለት እናት መስጠት የምትችለው አካል የሚሆነውን ክፍል ብቻ ነው። የአዳም ኃጢአት የሚወረሰው አባት ለልጁ ሕይወት ስለሚሰጥ ነው። የኃጢአት ውርስ የሚተላለፈው በሕይወት እንጂ ሕይወት በሌለው አካል

አይደለም። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ደጋግሞ ብዙ ጊዜ ኃጢአት በአዳም በኩል ወደ ዓለም እንደመጣ ይናገራል (ሮሜ 5፡12፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡21፥ 22)። ምንም እንኳ በመጀመሪያ ጊዜ ኃጢአት የሠራችው ሔዋን ብትሆንም እንኳ ኃጢአት በሔዋን በኩል ወደ ዓለም መጣ የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳ አልተጠቀሰም። ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ኃጢአት የሌለበት ሰው ሆኖ ተወለደ። ምክንያቱም የሴት ዘር ስለሆነ ነው። «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።» (የሐዋ.4፡12)። ለአዳምና ለሔዋን በዘፍ. 3፡15 ላይ እንደተነገራቸው ኢየሱስ ብቻ ከሴት ዘር የተወለደ አካል ሆነ።

24. ለ. ይህ ስጦታ የታቀደው በኃጢአት ከመውደቃቸው በፊት ኖሮአልን?

መልስ።

እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት የሰው ልጅ በኃጢአት እንደሚወድቅ ስለአወቀ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን እንዲቤዥ አቀደ። ለዚህ ነው እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ «ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የታረደው በግ» የተባለው (ራእይ 13፡8)። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር ደኅንነት የሚቀበሉትንና የማይቀበሉትን አስቀድሞ ያውቃል (ራእይ 17፡8፤ ኤፌ. 1፡4)። ከዚህም በቀር ቲቶ 1፡2፤ ዕብ. 4፡3፤ ምሳሌ 8፡23-35፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9።

25. «እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» (ዘፍ. 3፡15) ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ።

በክርስቶስና በሰይጣን መካከል የተደረገው ታላቁ ጦርነት የተፈጸመው በመስቀሉ አጠገብ ነበር። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ በሰይጣን ቆሰለ። ሆኖም የሰው ልጆችን ከሰይጣን እጅ ወይም ኃይል ያወጣው በዚያ ነው። ኢየሱስ የእኛን ኃጢአት ተሸክሞ በገዛ ፈቃዱ በመሞት የኃጢአታችንን ፍርድ ተቀበለ። እርሱም በሞቱ ከሰይጣን ኃይል አዳነን። ደግሞም እኛን ከሞት ኃይል ለማዳን ሞትን ድል ነሥቶ ተነስቶአል። በአዳም መውደቅ ከእግዚአብሔር ጋ መውደቃችን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ስለተመለሰልን እምነት ካለን መቀበል እንችላለን። በሰይጣንም ላይ ባደረገው ድል የተቋቋመው በዚያው ነው። በመጨረሻም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ቀጥቅጦ በፈራጅነቱ ፍርድ ሰይጣንን ወደ እሳት ባሕር ይጥለዋል (ራእይ 20፡10)።

26. እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከኃጢአት ሊያድናቸው ምን አሳያቸው?

መልስ።

አዳምና ሔዋን ኃጢአትን በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔርን ፈርተው ተሸሸጉት። እነርሱም እግዚአብሔርን ስለፈሩ ለራሳቸው ከቅጠል የተሠራ ልብስ ሠሩ (ዘፍ. 3፡7)። ከዚያም እግዚአብሔር እነርሱ የሚሠሩት ማንኛውም ሥራ

በእግዚአብሔር ፊት ብቁ ሊያደርጋቸው እንደማይችል ግልጽ አደረገላቸው። እነርሱ ከበደላቸው ሊሸፈኑ የሚችሉት በደም ብቻ ነው። ምክንያቱም «የኃጢአት ዋጋ ሞት ስለሆነ» ነው። ሌላ ዓይነት መሸፈኛ ከበደል ሊከልለን አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊሸፍናቸው ከቆዳ የተሠራ ልብስ ሠራላቸው። ይህም ቆዳ የተገኘው ደም በማፍሰስ ነው (ዘፍ. 3፡21)። በእጃቸው የተሠራው ቅጠል የእነርሱን ሙያ በሚያሳይ በሃይማኖታዊ ምግባራቸው ይመሰላል፥ ሃይማኖታዊ ሥራ ኃጢአትን ሊሸፍን አይችልም። ደኅንነት በክርስቶስ ደም ብቻ ነው (ዕብ. 9፡22፤ ማቴ. 26፡28፤ የሐዋ. ሥራ 20፡28፤ ሮሜ 5፡9፤ ዕብ. 9፡14፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፥ 19፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡7፤ ራእይ 1፡5፤ 7፡14)። እግዚአብሔርም እንስሳው ታርዶ በቆዳው የእነርሱን ራቁትነት መሸፈን እንደተገባው ሁሉ ክርስቶስ ደግሞ የእነርሱን ፍርድ ተቀብሎ ከዘለዓለም ፍርድ ሊያድናቸው እንደሚገባ ለአዳምና ለሔዋን አሳያቸው። ይህንንም ተስፋ እግዚአብሔር በዘፍ. 3፡15 ላይ ሰጥቶአቸዋል። የጠፉትን ለማዳን የሴትዋ ዘር መቀጥቀጥ ተገባው።

ከቆዳ የተሠራው ልብስ «የኃጢአት መሸፈኛ ምሳሌ ነው።» በብሉይ ኪዳን ዘመን ኃጢአት ከእምነት የተነሳ ተሸፈነ። በኋላም የዚህን ኃጢአት ፍርድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተቀበለ።

27. አዳምና ሔዋን ይህን የተቀበሉት ከጌታ ጋር የነበራቸውን አንድነት ለማደስ ነበርን?

መልስ።

አዳም ለኃጢአታቸው ሊሞት ያለውን የአዳኙን ተስፋ ባገኘ ጊዜ እግዚአብሔር የታረደውን እንስሳ ባሳየው ጊዜ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በራሱ ሥራ መመካቱን ተወ። ለራሱ የሠራት ቅጠል ደርቃና ጠውልጋ ስለጠፋች እግዚአብሔር የሰጠውን መሸፈኛ ተቀበለ። ይህንን በማድረግ ሊመጣ ያለውን የእግዚአሔር ደኅንነት በእምነት ተቀበለ። እኛ ተቀብለን እንደዳነው አዳምም የክርስቶስን ሞት በእምነት ተቀብሎ ድኖ ነበር። ሔዋንም የቆዳ ልብስ ተቀብላ ነበር። የእርስዋም ኃጢአት በተስፋ በተሰጠው በክርስቶስ ሞት ተሸፍኖ ነበር።

28. አዳም ስለሚመጣው ክርስቶስ ያለውን እምነት እንዴት ገለጠ?

መልስ።

ከሴትዋ የሚወለደው የዓለም አዳኝ የመሆኑን ተስፋ በተቀበለ ጊዜ ለሴቲቱ ሔዋን የተባለውን ስም አወጣላት። ምክንያቱም እርስዋ የሕያው ሰው ሁሉ እናት ስለምትሆን ነው (ዘፍ. 3፡20)። እርሱም ይህን ስም ያወጣላት ምክንያት ሰው የዘለዓለም ሕይወት የሚያገኝበትን አዳኝ ወልዳ የክርስቶስ ኢየሱስ እናት መሆን የምትችለው ሴት መሆንዋን ስለአወቀ ነው። እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል የዓለም አዳኝ የሆነው ክርስቶስ ከሴት እንደሚወለድና እርሱም የሴት ዘር እንጂ የወንድ ዘር እንደማይሆን ያምን ነበር። እርሱም እራሱን የሕያዋን ሁሉ አባት

ብሎ አልጠራም። እርሱም ይህን ሲናገር ሊመጣ ስላለው አዳኝ በማሰብ ነው እንጂ ስለ ሌላ የሚወለድ ልጅ አልነበረም። ከዚህም በቀር በሴትዋ ዘር ስለሚድኑትም ያስብ ነበር። እርሷም ደግሞ ብዙዎቹ የዘለዓለም ሕይወት የሚያገኙበት የአዳኙ እናት ናት። እርሱም ሴቲቱን ሔዋን በማለቱ ሊመጣ ባለው አዳኝ እንዳመነ ያመለክታል። ይህንን በብሉይ ኪዳን ስንመለከት በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች ሊመጣ ባለው በክርስቶስ እምነት እንደዳኑ እንረዳለን። ገላ. 3፡24፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡1-4፤ ዮሐ. 8፡56 እና ዕብ. 11 አንብብ።

## ዘፍጥረት ምዕራፍ 4 አንብብ።

29. ሔዋን በክርስቶስ ስለነበራት እምነት በምን ዓይነት ሁኔታ ምስክርነት ሰጠች?

መልስ።

እግዚአብሔር ለሔዋን የሴትዋን ዘር ተስፋ ሰጥቶአታል። ይህም ለሔዋን የመጀመሪያውን ልጅዋን ስትወልድ ስሙን ቃየን ብላ ጠራችው። ይህንንም ስትል «ወንድ ልጅን ከእግዚአብሔር ዘንድ አገኘሁ ማለትዋ ነው» (ዘፍ. 4፡1)። እርሷም ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣው በተስፋ የሚጠበቀው መሲሕ ለመሆኑ ጥርጥር አልነበራትም። ምንም እንኳ ጌታ ሲገለጥ ለሚፈረዱት ምክንያት ብትሆን አለመጠራጠርዋ እግዚአብሔር ለሰጠው ተስፋ የነበራትን እምነት የሚገልጽ ምስክርነት ነው። አዳምና ሔዋንም ከአመኑ በኋላ ነፍሳትን ለክርስቶስ ያጠምዱ ነበር። ለሚቀጥለው ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ተመልከት።

30. ቃየንና አቤል የደም መሥዋዕትን ምልክት በማቅረብ ተመሳሳይ ባሕላዊ ሥርዓት ፈጽመው ነበርን? መልስህን አብራራ።

መልስ።

እግዚአብሔር እራሱ ስለ ኃጢአታቸው እንስሳ ታርዶ ደም መፍሰስ እንደነበረበት ለአዳምና ለሔዋን እንደአሳያቸውና በቆዳውም እንደሸፈናቸው ሁሉ እነርሱ ደግሞ ለልጆቻቸው የደምን መሥዋዕትነት አስተማሩዋቸው። አቤል የደምን መሥዋዕት ትርጉም ያውቅ ነበር። ዕብ. 11፡4 ተመልከት። በቤተሰቡ ያልተማረ ማንም ሰብአዊ ፍጡር በምድር ላይ አይገኝም። ስለዚህ አቤል የደምን መሥዋዕት ካወቀ ቃየንም ያውቃል ማለት ነው። ቃየን ግን እንደአብዛኛዎቹ የዘመኑ ሰዎች በሃይማኖታዊ መልካም ሥራ ለመዳን ፈለገ። ቤተሰቦቻቸው በእነርሱ መልካም ማለት በሃይማኖታዊ ሥራቸው የእግዚአብሔርን ደኅንነት ማግኘት እንደማይችሉ እንዳስተማሩአቸው አያጠራጥርም። ሃይማኖታዊ ሥራዎች መልካም ናቸው፥ ነገር ግን አያድኑም። ምክንያቱም የኃጢአት ዋጋ መልካም ሥራ ሳይሆን ሞት ስለሆነ ነው።

31. የቃየን መሥዋዕት ለምን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አጣ?

መልስ።

ቃየን የእጆቹን ሥራዎች የሚገልጹትን የእርሻውን ፍሬዎች ይዞ እግዚአብሔርን ሊያመልክ መጣ። እግዚአብሔር ግን መሥዋዕቱን አልተቀበለውም (ዘፍ. 4፡3-4)። አዳምና ሔዋን በእጃቸው በተሠራው ቅጠል ራሳቸውን ለመሸፈን እንደሞከሩ ሁሉ ቃየንም በበኩሉ በእጆቹ ሥራ ማለት በሃይማኖታዊ ምግባሩ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ፈለገ። ስለዚህ እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን በንስሐ በክርስቶስ ደም አምኖ ወደ እርሱ የማይመጣውን ማንኛውንም ሰው አይቀበልም። ሰው በክርስቶስ ደም ብቻ ሊድን ይችላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ይሰዋ የነበረ የኮርማዎችና የአውራ ፍየሎች ደም አንድ ነፍስ እንኳን ማዳን አልቻለም (ዕብ. 10፡4)። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ግን ሊያድነን ችሎአል። ቃየን ባቀረበው መሥዋዕት ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ በእምነት ደኅንነት መቀበል አለመፍቀዱን ገለጠ። እርሱም መልካም ምግባሩ በቂ እንደሆነ መስሎት ነበር። አቤል ግን ሊመጣ ያለው ክርስቶስ ለኃጢአቱ እንደሚሞት ስለአመነ የደም መሥዋዕት በማቅረብ እምነቱን በእግዚአብሔር ፊት አሳየ (ዘፍ. 4፡4፤ ዕብ. 11፡4)። የመሥዋዕቱ ልዩነት ከሥራ ልዩነት ምክንያት አልነበረም። አቤል የበግ እረኛ ነበር። ይህንንም ደግሞ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር አድርጎ እንዳየነው ከማመን ወይም ካለማመን ሊሆን ይችላል። በዘፍ. 4፡6-7 ባለው ክፍል ላይ እግዚአብሔር እስከ አሁን ቃየን በንስሐ የደም መሥዋዕት እንዲያቀርብ ይፈልግበታል። ስለዚህ ቃየን መናዘዝ ስላልፈለገ የደም መሥዋዕት በእምነት ማቅረብ አልቻለም። ለኃጢአተኞች ንስሐ መግባት አይቻላቸውም። ስለዚህ በምትኩ እግዚአብሔር የማይቀበለውን ሃይማኖታዊ ሥራ ሠራ (1ኛ ሳሙ. 15፡22፤ መዝ. 50(51)፡16፥ 17፤ ኢሳ. 1፡11፤ ዕብራውያን 9፡9)።

አንዳንድ ሰዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ደም አምኖ መዳን እንደነበረ በሚሰጠው ትምህርት ቅር ይላቸዋል። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት ሰዎች ሊመጣ ስላለው መሢሕና የማዳኑ ሥራው ብዙ የማያውቁ አላዋቂዎች ናቸው ብለው ስለሚገምቱ ነው። እነርሱም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት ሰዎች የዳኑት በክርስቶስ ኢየሱስ ደም በኩል ማለት በሞቱ የሚገኘውን ደኅንነት አውቀው ሳይሆን እግዚአብሔር የሚያዘንን ብንፈጽም የምንድንበትን መንገድ ሳያዘጋጅልን አይቀርም በማለት ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ሲታዘዙት የነበረው የደም መሥዋዕት ውሎ አድሮ በክርስቶስ ደም ፍጻሜ ደርሶአል።

እርግጠኛው ነገር በፊትም ሆነ አሁን ወደፊትም የሚኖሩት ሰዎች በክርስቶስ ሞት የተሰጠው የደም መሥዋዕት ባይኖር ኖሮ በሌላ በኩል አንድም ሰው ባልዳነ ነበር። እግዚአብሔርም በዚህ ጉዳይ ላይ አላዋቂ እንዲሆኑ አላደረጋቸውም። ነገር ግን እራሱ አስተማራቸው። እግዚአብሔርም ስለ ሴቲቱዋ ዘር ለአዳም፥ ለሄኖክ፥ ለኖኅ፥ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብ፥ ለኢዮብ፥ ለሙሴ፥ ለኤልያስና ለሌሎችም ተናግሮአል። እነርሱም በተራቸው ሕዝቦቹን አስተማሩ። ሙሴም

ሕጉንና የሕጉን ትርጉም ለመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር በተራራ ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየ። «እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር» (ዘጸአት 33፡11፤ ዘዳ. 5፡4፤ 34፡10)።

ማንም ሰው የሕግን ሥራ በመሥራት አይጸድቅም። ሮሜ 3፡20 «የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው።» ሮሜ 8፡3 እና ዕብ. 7፡19 ተመልከት። ሕግ የተሰጠው ሰው በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን ደኅንነት እንዲያውቅ የተሰጠው የደኅንነት መንገድ ነው (ገላ. 3፡24)። «እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል» (ገላ.3፡24)። እስራኤላውያንም ስለ ክርስቶስ ስለሚያውቁ እንደኛው ስለተቀበሉት በእምነት ድነዋል።

አብርሃም፥ ኢየሱስ ክርስቶስንና ቀኑን ያይ ዘንድ ወደደ፥ አየም። በእምነትም እየሠራ ዳነ። «አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ፥ አየም ደስም አለው» (ዮሐ. 8፡56) በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ክርስቶስ አብርሃም ስለ ቀኑ እንደ አወቀና እንዲሁም ወደ ምድር መምጣቱን የማዳኑንም ሥራ እንዳወቀ ይመሰክራል።

እስራኤላውያንም በምድረ በዳ እንደሚመጣው አዳኝ አድርገው ያምኑበት ነበር። «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፥ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፥ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና ያም ዓለት ክርስቶስ ነበር።» (1ኛ ቆሮ. 10፡3፥4)።

በኢሳ. 53 በሙሉ በትንቢት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስቃይና ሞት እንዲሁም ስለ ጠፉት ደኅንነት ያደረገውን የሚገልጽ ጽሑፍ ሰፍሮአል።

በእስራኤል ብዙ ሃይማኖቶች አሉ፥ ነገር ግን የደኅንነትን መንገድ አያውቁም። በተመሳሳይ መንገድ ዛሬም ብዙ ሰዎች በስመ-ክርስቲያን እየተጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ በቤታቸው ያላቸውና ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱ፥ ነገር ግን የደኅንነትን መንገድ የማያውቁ አሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በፍጹም ልባቸው ቢሹት እንደሚያገኙት ይናገራል፤ (ዘዳ. 4፡29፤ ምሳሌ 8፡17፤ ኤር. 29፡13፤ የሐዋ. ሥራ 17፡26፥ 27)። ማንኛቸውም ጥበብንና ማስተዋልን የሚሹ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሥጋዊና መንፈሳዊ ብርሃን ይሆንላቸዋል። ሰዎች ከኃጢአታቸው መመለስን አይወዱም። ለዚህ ነው እንግዲህ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ለመንፈሳዊ ነገር የታወሩት። ሄኖክ ምድር በውኃ ከመስጠምዋ በፊት ሊመጣ ስላለው ጊዜ ተናግሮ ነበር (ይሁዳ 14፡15)። ኢዮብም ወደፊት ሊሆን ስላለው ትንሣኤ ስለሚያውቅ ተናግሮ ነበር (ኢዮብ 19፡25-27)። እነዚህ አምስቱን የሙሴን መጽሐፍ ማጥናታችንን ስንቀጥል በብሉይ ኪዳን የተገለጸው የደኅንነት ትምህርት ይበልጥ እየተገለጠልን ይሄዳል።

32. እግዚአብሔር ለቃየን ተጨማሪ ዕድል እንደሰጠውና ቃየን ፈቃደኛ ቢሆን ኖሮ ምን ያህል መልካም ያደርግ እንደነበረ አሳይ። ቃየን መልካም አለማድረጉ ካልቀረ ኃጢአት በደጁ ለምን አድብታ እንደቀረችም አሳይ። ዕብ. 9፡22፤ 10፡1፤ 4፡10-12፤ ዘፍ. 4፡5-7።

መልስ።

ቃየን ያቀረበውን መሥዋዕት እግዚአብሔር ስላልተቀበለለት ተቆጣ። እግዚአብሔርም አሁንም ቢሆን መልካም የማድረግ ዕድል እንዳለው ሊገልጽለት አትቆጣ ብሎ አዘዘው (ዘፍ. 4፡7)። መልካም ማድረግ ያልነውም አቤል እንዳደረገው የደም መሥዋዕት በእምነት ማቅረብ ነው። ቃየን «በሴትዋ ዘር ማለት በሚመጣው አዳኝ ባለማመን የደም መሥዋዕትን በእምነት ባለማቅረቡ ኃጢአት በደጁ እንዳደባች ቀረች። ንስሐ ወይም እምነት እስከአልኖረው ድረስ ኃጢአቱ አይከደንለትም ወይም አይሰረይለትም። ለብሉይ ኪዳን ዘመንም ሆነ ለአዲስ ኪዳን ዘመን ሰዎች ከፈሰሰው ከክርስቶስ ደም በቀር የኃጢአት ይቅርታ አያገኙም» (ዕብ. 9፡12፥ 14፥ 22፤ 10፡1፥ 4፥ 10-12)።

33. ቃየን ለምን አቤልን ተቆጣው?

መልስ።

ቃየን የተቆጣው እግዚአብሔር ሃይማኖታዊ ሥራውን ስላልተቀበለው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በእምነት የቀረበውን የአቤልን የደም መሥዋዕት ስለተቀበለ የቃየን ቁጣ ወደ አቤል ዞረ። በሐሰተኛ ሃይማኖት የቀረበው ወይም በሥራ ሃይማኖት የቀረበው ቃየን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን አቤልን ገደለው። የቃየን ሥራ ተንኮል የተሞላ ነበር። ምክንያቱም ምንም እንኳ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ቢያቀርብ በኃጢአቱ አልተናዘዘም ነበር (ዘፍ. 4፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡12)። እስከ አሁንም ጊዜ ድረስ በኃጢአታቸው ያልተናዘዙና ደኅንነትን በእምነት በክርስቶስ ደም ያልተቀበሉ ሃይማኖታዊ ሰዎች የእግዚአብሔርን ልጆች እየገደሉ ነው። ማቴ. 23፡33-38፤ ሉቃ. 11፡50፥ 51 ተመልከት። እነዚህ የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔርን ሊጎዱት ስለማይችሉ በተቻላቸው ጊዜ የእግዚአብሔርን ልጆች ይጎዱአቸዋል።

34. ዘፍ. 4፡7 መልካም ማድረግ ሲል እግዚአብሔር ምን ማለቱ ነው?

መልስ።

ዘፍ. 4፤ ሉቃ. 15፡7፤ የሐዋ. ሥራ 3፡19 ተመልከት። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጊዜ መልካም ብሎ የሚጠራው ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ሲናዘዝ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ለደኅንነቱ በክርስቶስ ደም በሚያምን ጊዜ ነው (ዮሐንስ 6፡28፥29)። ማንም ኃጢአቱን ያልተናዘዘ ወይም ያላመነ ሰው ሃይማኖታዊ መልካም ሥራው በእግዚአብሔር ፊት እንደመርገም ጨርቅ ነው (ኢሳ. 64፡6) የአቤል ሥራ ጥሩ ነው። «መልካም አድርጎአል» ምክንያቱም ስለ ተናዘዘና ስለ አመነ ነው (ዕብ. 11፡4) እስራኤላውያን እንኳን በኃጢአታቸው ሳይናዘዙ

ወይም ሳያምኑ የሚያቀርቡትን የደም መሥዋዕት አልተቀበለም (ኢሳ. 1፡1-18፤ 1ኛ ሳሙ. 15፡22፤ መዝ. 50(51)፡16፥ 17፤ ሆሴዕ 6፡6፤ ማቴ. 9፡13፤ ዕብ. 9፡9)። ኃጢአተኛ የክርስቶስን ደኅንነት የሚቀበለው መሥዋዕቱን በሚያቀርብ ጊዜ ነው። ምክንያቱም በኑዛዜና በእምነት የሚቀርበውን የደም መሥዋዕት ብቻ ነው እግዚአብሔር የሚቀበለው። በዚህም አድራጎቱ በእምነት ወደ ክርስቶስ ሲመለከት ደኅንነትን ያገኛል። ይህም ደግሞ «የእግዚአብሔር መልካም አድራጎት» ሲሆን እግዚአብሔር ቃየንን የፈለገው ይህን እንዲያደርግ ነው።

35. ሀ. በዘፍ. 4፡11፥ 12፥ 16፥ 17 እንደተገለጸው ቃየን በምድር ላይ ሲኖር እንደተረገመ ሁሉ ዕድሜውን በምን ዓይነት ኑሮ አሳለፈ?

መልስ።

1. እግዚአብሔር በዘፍጥረት 4፡7 ላይ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ቃየን በኃጢአት ላይ እንዲነግሥ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ኃጢአት ነገሠበት። ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ያልሆነና በኃጢአት ላይ መንገሥ የማይችል ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።

2. ቃየንም የወንድሙ ገዳይ ሆነ (ዘፍ. 4፡8፤ ማቴ. 15፡19)።

3. ቃየንም ሰላምና እረፍት የሌለው ሕይወት እንዲኖር ተረገመ (ዘፍ. 4፡11፥ 12፤ ይሁዳ 11-13)።

4. ቃየንም እግዚአብሔር ይህን የመሰለ ዕድል ሲሰጠው ይህን በሚያህል የራሱ ፈቃድ ባርነት በመገዛት ሳይናዘዝ ቀረ። እርሱም «ከጌታ ፊት ተለይቶ ወጣ» (ዘፍ. 4፡16)። ስለዚህ በመጀመሪያ ጊዜ ወደዚህ ምድር በመወለድ የመጣው ሰው በፈቃዱ ጠፋ።

5. ቃየንም ከተማን ሠርቶ በልጁ ስም ሞክሼ ሄኖሕ ብሎ ጠራው። እርሱም እግዚአብሔርን ሳይሆን እራሱን አከበረ (ዘፍ. 4፡17)። እርሱም በኩራትና በትዕቢት ኖረ።

6. ከቃየንና ከልጆቹ የተነሳ በኋለኛው ጊዜ የነበሩ ሰዎች በውኃ ተጥለቅልቀው እንዲጠፉ ተደረገ። የእግዚአብሔርም ልጆች ከመንገዱ ስተው እንዲሄዱ አደረጉዋቸው። የሰውም ክፋት በምድር ላይ እየባሰ ሄደ። የቃየንም ልጆች የእግዚአብሔር ጠላት ሆኑ። ልጆች ያባቶቻቸውን ባሕርይ ይከታተላሉ (ዮሐ. 8፡24፤ ሮሜ 10፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡12)።

35. ለ. ቃየን ሊድን አይችልም ነበርን?

መልስ።

ቃየን በሃይማኖታዊ ሥራው ያቀረበው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘቱን ከአየ በኋላ በዘፍጥረት 4፡7 ላይ እንደተጠቀሰው

እግዚአብሔር ሊድንበት የሚችልበትን ዕድል ሰጠው (ዘፍ. 4፡7)። እግዚአብሔር የሰዎች ኃጢአት ምንም ያህል ታላቅ ቢሆን ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይፈልጋል (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። ቃየን እግዚአብሔር የሰጠውን ደኅንነት እምቢ አለ (ዘፍ. 4፡16)። ዛሬም ብዙ የልዩ ልዩ ሃይማኖት ክፍል ሰዎች አንድ ብቻ የሆነና በእምነትና በንዛዜ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ደኅንነት እምቢ ብለዋል። እነርሱም ቃየን እንዳደረገው እንዲያድናቸው በየግል ሃይማኖታቸው ይመካሉ። በክርስቶስ ዘመን የነበሩ ሃይማኖታዊ ሰዎች የሆኑ ፈሪሳውያን በኃጢአታቸው መናዘዝ ስላልፈለጉ ኢየሱስ ክርስቶስን ክደው ጠፉ።

36. ዘፍጥረት 4፡19-24 ከላሜህ ዘመን ሁናቴ ማለት ከግብረገባዊና ከማኅበራዊ ኑሮ ምን እንማራለን?

መልስ።

1. በላሜሕ ዘመን ግብረገባዊ ኑሮ በፊቱኑ በጣም ዝቅ ብሎ ነበር።

ሀ. እግዚአብሔር አንድ ሰው አንድ ሚስት ብቻ እንድትኖረው ነው ሐሳቡ፥ ላሜሕ ግን ሁለት ሚስቶች አገባ። ላሜሕ ከቃየን ቤተሰብ ነው (ዘፍ. 4፡17፥ 18)።

ለ. ላሜሕ የራሱን ሕይወት ለማዳን አልሞት ባይ ተጋዳይ ሆኖ ሌላውን ሰው ገደለ። እርሱም «እኔ ጎልማሳውን ለቁስሌ ብላቴናውንም ለመወጋቴ ገድዬዋለሁ» አለ (ዘፍ. 4፡23) እርሱን ያጠቃውንና ያቆሰለውን ሰው ገደለ። ይህም ደግሞ በዚያን ዘመን ጊዜው አደገኛ ስለሆነ የሰው ሕይወት ጥበቃ እንዳልነበረው ያሳያል።

2. የቃየን ልጆች በተለያዩ ሥራዎች ላይ ችሎታና ጥበብ ነበራቸው። እነርሱም የሙዚቃ መሣሪያዎችን በመሥራት ይጫወቱባቸው ነበር (ቁጥር 21)። እነርሱንም ከነሐስና ከብረት ይሠሩ ነበር። (ቁጥር 22)።

36. ዘፍጥረት 4፡24 አንብብ። ላሜሕ ለምን እንዲህ ሲል ተናገረ?

መልስ።

«ቃየን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል፤ ላሜሕን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ።» ቃየን ምንም በደል የሌለበትን ሰው ሲገድል ተቅርቋሪ ወይም ረዳት የሌለው መስሎት ነበር። ቃየን በልቡ ነፍሰ ገዳይ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ቃየንን የሚበቀል ሰባት እጥፍ ይቀጣል አለ (ዘፍ. 4፡15)። ላሜሕ ግን ያጠቃውን ክፉ ሰው ገደለ። እርሱ ግን እንደ ቃየን ከልቡ ነፍሰ ገዳይ አይደለም። ስለዚህ አልሞት ባይ ተጋዳይ በመሆን ነፍሱን ስለአዳነ ሌላ ሰው ቢበቀለው እግዚአብሔር 70 ጊዜ 7 እጥፍ ተበቃዩን ይበቀለዋል ብሎ አሰበ።

38. «ሴት» የሚባለው ስም ትርጉሙ ምንድር ነው? 4፡25፥ 26።

መልስ።

ሔዋንም ሦስተኛውን ልጅዋን ሴት አለችው። የስሙም ትርጉም «ምትኩ» ማለት ነው። እግዚአብሔርም ሴት የአቤልን ሥፍራ እንዲይዝ ምትክ አድርጎ ሰጣቸው። ምናልባት ሔዋን ይህንን ስም ያወጣችለት ሴት እንደ አቤል የእግዚአብሔርን መንገድ ሲከተል ካየች በኋላ ይሆናል።

39. ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በምድር ላይ ምን ዓይነት ሁለት ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ? ቁጥር 26

መልስ።

የሴት ልጆችና የቀሩት የአዳም ልጆች እግዚአብሔር እንደተከተሉ አያጠራጥርም። «ከዚያም በኋላ ሰዎች የጌታን ስም መጥራት ጀመሩ።» ቁጥር 26። በዚያን ጊዜም እንዳሁኑ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ አማኞችና የዓለም ልጆች የሆኑ (የማያምኑ) ነበሩ። በማርቲን ሉተር ትርጉም እንደተጻፈው «የጌታን ስም ማስተማር ጀመሩ» ይላል። አማኞች ባሉበት ሥፍራ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እየተሰበከ ነው።

40. ዛሬ የቃየንና የሴት ሥራና ኑሮ በዘሮቻቸው ማለት በአሁኑ ትውልድ ሕይወት እንዴት ይታያል?

መልስ።

ዛሬም የማያምኑት ሰዎች እንደ ቃየን ዘሮች የራሳቸውን እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አያደርጉም። እነርሱም ቃየን በክርስቶስ ሞት በማመን ንስሐ ለመግባት እምቢ እንዳለና እንደተረገመ እነርሱም እምቢ ብለው ከደዋል። የዛሬዎቹም አማኞች በሴት ዘመን እንደነበሩት አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ከመንፈስ ስለተወለዱ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ኃጢአት ማድረግን ሲተው የዓለም ልጆች ደግሞ ኃጢአትን ለማድረግ ይናፍቃሉ።

## ምዕራፍ 5ን አንብብ።

41. ሀ. አዳም በምን አምሳል ነው የተፈጠረው? ይህስ ምን ማለት ነው?

መልስ።

አዳም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ (ዘፍ.5፡1)፥ ይህም ማለት እንደ እግዚአብሔር ንጹሕ ቅዱስና ያለ ኃጢአት ነበር። አዳም በኃጢአት ከወደቀ በኋላ በእኛ ላይ በተዛመተውና እኛ በለበስነው ዓይነት የኃጢአት አካል አልተፈጠረም። እግዚአብሔርም የሚወደውን እንዲመርጥና እንዲገዛ የራሱን ምርጫ ሰጥቶታል።

41. ለ. ሴት በማን አምሳልና መልክ ነው የተወለደው? 5፡3 ይህስ ምን ማለት ነው?

መልስ።

ሴት የተወለደው አዳም ከወደቀ በኋላ የሆነውን አምሳልና ባሕርይ ይዞ ነው። እርሱም አዳም ከመውደቁ በፊት የነበረውን ኃጢአት የሌለበትን ተፈጥሮ ይዞ እንደ አዳም በቅድስና የተፈጠረ ሳይሆን አዳም ከወደቀ በኋላ የወረሰውን ኃጢአተኛ አካልና ተፈጥሮ ይዞ ነው የተወለደው። ሴት ከመጀመሪያው ጀምሮ ኃጢአተኛ ስለሆነ ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ታጥቦ መዳንና አዲስ ፍጥረት መሆን አለበት (ዘፍ. 3፡15-21)።

42. ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩት ሰዎች የመዳንን መንገድ ያውቁ ነበርን? ዕብ. 11፡2-7፤ ይሁዳ 14፡15፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡5።

መልስ።

ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩት ሰዎች የመዳንን መንገድ ማወቅ ቢፈልጉ ኖሮ መረዳት ይችሉ ነበር። ይህም ማለት እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶአቸው በነበረው በክርስቶስ ሞት አምነው ይድኑ ነበር ማለት ነው።

አቤል የዳነው በእምነት ነበር (ዕብ. 11፡4)። እምነቱም ስለ ኃጢአቱ በሚሞተው በክርስቶስ ነበር። ስለዚህ ነው እንግዲህ የደም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀረበው። እግዚአብሔርም ለአዳምና ለሔዋን እንስሳ በማረድ ቆዳውን አልብሶአቸው በዘፍጥረት 3፡15 ላይ የክርስቶስን የመሥዋዕትነት ተስፋ በመስጠት የደኅንነትን መንገድ አሳይቶአቸዋል። አቤልም የደኅንነትን መንገድ በአዳምና በሔዋን በኩል ተማረ። በዕብ. 11፡4 እንደተብራራው ዛሬም ቢሆን አቤል የደኅንነት መንገድ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት ብቻ እንደሆነ ይመሰክርልናል። ዛሬም ቢሆን የመዳን መንገድ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም በማመን ነው። አቤል እስከ ዛሬ ድረስ የመዳንን መንገድ ከመሰከረልን እኛም በተመሳሳይ መንገድ እንደምንድን ያውቅ እንደነበረ ያረጋግጣል። (ዕብ.11፡5፥6)። ከጥፋት ውኃ በፊት ይኖር የነበረው ሄኖክ የዳነው በእምነት ነው። ምክንያቱም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብ. 11፡5፥6)። ሄኖክ አሁን እንኳ ገና ወደፊት ሊሆን ስላለው ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት የሚሰብክ ሰባኪ ነበር። (ይሁዳ 14፡15)። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር በወንጌል ሊናገረው ስላቀደው ነገር ለሕዝቡ ሳይናገር በጨለማ እንዳልተዋቸው ያረጋግጣል። ማለት (የደኅንነትን) መንገድ ወንጌል ስለሚለው ቃል በዚሁ መጽሐፍ ላይ ወደፊት የምታገኘውን የ74ኛውን ጥያቄ መልስ ተመልከት።

ኖኅ «የጽድቅ ነገር ሰባኪ ነበር።» (2ኛጴጥ.2፡5)። ንጹሑ የደኅንነት መንገድ የጥፋት ውኃ ከመምጣቱ በፊት ለሚጠፉት መስበክ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ሰባክያን የሆኑት እንደነ አዳም ሴትና ልጆቹ (ዘፍ. 4፡26) ሄኖክ፥ ኖኅ የመሳሰሉት እስከ 1000 ዓመት አቅራቢያ የኖሩ ናቸው። ምክንያቱም እውነተኛውን የወንጌል መልእክት ስለሚያውቁና እግዚአብሔር እራሱ አስቀድሞ ሳይለወጥ እንዳለ እውነተኛውን የደኅንነት መንገድ ስለሰጣቸው

ነው። ማቱሳላ ከተወለደ በኋላ አዳም 243 ዓመት ኖረ፥ ማቱሳላም እስከ የጥፋት ውኃ ዘመን ኖረ። ሁሉ አንድ ዓይነት ቋንቋ ይናገሩ ነበር።

ይህም ማለት በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች ሁሉ ወንጌልን ያውቃሉ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ለማወቅ ቢፈልጉ ኖሮ ሁሉም ስለ ወንጌል ማወቅ ይችሉ ነበር። ዛሬም ደግሞ ወንጌል በየስፍራው ሁሉ ይሰበካል፥ ሰዎችም ለማወቅ ከፈለጉ ማወቅ ይችላሉ። የሚገርመው ግን በየዕለቱ በሬዲዮ ወንጌል በሚሰበክበት ከተማ የሚኖሩ ሰዎች እንኳ ስለ ወንጌል አለማወቃቸው ነው። ምክንያቱም ለማወቅ ስለማይፈልጉ ነው።

43. የትኛው የአዳም የዘሩ ሐረግ ነው በምዕራፍ 5 ላይ የተጠቀሰው?

መልስ።

በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት የሴት ወገኖች ናቸው፤ ምክንያቱም እነርሱ አማኞች ስለነበሩ ይሰብኩ ነበር። (የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ) እነርሱም በምድር ሊጠብቁ ይገባቸው ነበር። ኖኅ የሴት ዘር እንደመሆኑ እኛም ደግሞ ነን።

44. ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩት ሰዎች ምን ዓይነት መንፈሳዊ ደስታና ልምምድ እንደነበራቸው ለመረዳት የሄኖክ ሕይወት በመንፈሳዊ ብርሃናዊ ኑሮው ምን ያሳይ ነበር? ዕብ. 11፡5፤ ይሁዳ 14፡15።

መልስ።

ሄኖክ እግዚአብሔር ሊወስደው እስከሚችል ድረስ ወደ እግዚአብሔር በእምነት በጣም ቀርቦ ነበር (ዘፍ. 5፡24፤ ዕብ. 11፡5፥ 6)። እርሱም አልሞተም ነበር፥ ነገር ግን እካሉ ተለውጦ ወደ ሰማይ ተወሰደ (ዕብ. 11፡5)። እርሱም አሁን እንኳ ገና ስላልሆነው ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ማለት ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ ወደ ዓለም መምጣትና ዓለምን ስለ መፍረድ ይሰብክና ትንቢት ይናገር ነበር። (ይሁዳ 14፥ 15)። ይህም ደግሞ በዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች በቂ የወንጌል ብርሃንና ደኅንነት እንዲያገኙ ያሳያል። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በደኅንነት በኩል በጨለማ ውስጥ አልተዋቸውም ነበር። በዘፍጥረት ውስጥ የተጠቀሰው የ74ኛውን ጥያቄ መልስ ተመልከት። በሄኖክ ዘመን የነበሩት ሰዎች እጅግ በጣም መጥፎዎች ነበሩ። ሄኖክ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ለ300 ዓመት ተጓዘ። ይህም ደግሞ እኛም ብንሆን ከፈለግን በዚህ በጥቂት ዘመናችን በኃጢአት በረከሰ ዓለም ውስጥ ስንኖር ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ እንችላለን። ምናልባትም እግዚአብሔር ሄኖክን ለውጦት ወደ ሰማይ ወስዶት ይሆናል። ምክንያቱም ስለ መጨረሻው ዘመን የሚገልጸው መልእክቱ እውነት እንደሆነ ለሰዎች ለማሳየት ነው። ከዚህ በቀር እግዚአብሔር ሄኖክን የወሰደው ጌታ በዳግመኛ ምጽአቱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ማለት ሙሽራይቱን ወደ ራሱ ሊወስዳት ያለውን ሥልጣንና ኃይል ለማሳየት ነው። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ከጥፋት ውኃ አስቀድሞ ሕዝቡቹ በባሪያው

አማካይነት የመዳንን መልእክት እንዲያምኑ ፈቃዱ ነበር። ዕብ. 11:5፥ 6 ተመልከት።

45. በዚያን ጊዜ የሰው የሕይወቱ ዘመን ምን ያህል ነበር? እነርሱስ በክፉና በመልካም ነገር ላይ ምን አስተያየት አላቸው? ዘፍ. 6:1-7 አንብብ።

መልስ።

ሰዎች በዚህ ጥቂት ዘመን ውስጥ ማለት 1600 ዓመት ውስጥ እንዲህ የተበላሹት ስለ ዕድሜአቸው እርዝማኔ ነው። እነርሱም ወደ ሺህ ዓመት የሚጠጋ ዕድሜ ይኖሩ ነበር። በእርኩሰት የሚተጋ ሰው በሕይወት በቆየ ቁጥር ኃጢአቱን እየጨመረና በክፋቱ እየባሰ ይሄዳል። በዕድሜ የመቆየታቸውም ነገር ሌሎችን በክፋት ለመሳባቸው አመቺና ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላቸዋል (ዘፍ. 6:5)። ሰው እግዚአብሔርን አልታዘዝ ካለ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሰውዬውን ከመውቀስ ያቆማል። ከዚያም ኃጢአተኛው እየደነደነ ልቡ እየከረረ ይሄድና ክፋቱም እየጨመረ ይሄዳል። ጌታም «መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም» ይላል (ዘፍ.6:3)።» የአማኞች በዕድሜ መቆየት ከእግዚአብሔር ጋር እንደመራመዳቸው የበለጠ ፍጹም እየሆነ ያድጋል።

46. በዘፍጥረት 5:29 ላይ የአማኞች የልብ መቃተትና ተስፋ ስለሆነ ነገር ምን ታገኛለህ?

መልስ።

ዓለም እጅግ ኃጢአተኛ ስለሆነች ሰዎች በከባድ ሥራና ኃዘን ጥረው ግረው እንዲኖሩና ኑሮአቸውን እንዲገፉ እግዚአብሔር ምድርን ረገማት። ብዙ በሥራ ላይ መቆየት ለኃጢአት ጥቂት ጊዜ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ኃጢአተኞች ደግሞ በክፉ ሥራቸው ሕይወት ለአማኞች ከባድና መራራ እንዲሆንባቸው ያደርጉባቸዋል። የአማኞች ተስፋ የተመሠረተው እግዚአብሔር ይመለሳል ብሎ ተስፋ በሰጣቸው በሚመጣው አዳኝ ነው። ላሜሕ ልጁን ኖኅ ብሎ ስም አወጣለት፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ በእርሱ በኩል እንደሚፈጽም ስለአመነ ነው። ከኖኅም የዘር ግንድ ሐረግ አዳኙ ጌታችን መጣ። መከራ በከበደና በተጫናቸው ጊዜ ያን ጊዜ ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መጽናናት ይሻሉ።

47. ማቱሳላ ስንት ዓመቱ ነበር?

መልስ።

969 ዓመቱ ነበር (ዘፍ. 5:27)።

48. የኖኅ ልጆች እነማን ነበሩ?

መልስ።

የኖኅ ልጆች ካም ሴምና ያፌት ነበሩ (ዘፍ. 5፡32)። ሴም ክርስቶስ ሰው ከሆነበት ዘር የሆነ የተመረጡት የነገዶች አባት ነው። ከዚህም በቀር የዓረብ ነገድ የሆኑት ሁሉ የሴም ዘሮች ናቸው። ከእነዚህም ነገዶች ጥቂቶቹ በሰሜን አፍሪካ ከሚገኙ የካም ነገዶች ጋር ተደባልቀዋል (ዘፍ. 10፡21-31)።

ካም በመሠረቱ የአፍሪካውያን ሰዎች አባት ነው። ዘፍ. 10፡6-20። ያፌትም በመሠረቱ የኤውሮፓውያን ሰዎች አባት ነው። ጥቂቶቹ የካም ነገዶች እንደ ከነዓንና አምሩድ በሚባሉ አገሮች ይኖራሉ። ጥቂቶቹ የያፌት ነገዶችም ደግሞ በፐርሺያና በሕንድ ይኖራሉ።

ዘፍጥረት ምዕራፍ 6 አንብብ።

49. በመጨረሻ ይህ ኃጢአትን የተሞላ ሰብአዊ ተፈጥሮ እንዴት ያለውን የእግዚአብሔር ቁጣ አመጣ?

መልስ።

የእግዚአብሔር ልጆች የማያምኑትን ማግባት ሲጀምሩ ዓለም በፍጥነት ለፍርድ የምትታጨድ መከር ሆነች (ዘፍ. 6፡2-5)። ከዚያም በኋላ ሰዎች ስለ ኃጢአት የሚያስብ ብቻ ሆነው የመንፈስ ቅዱስን ማስጠንቀቂያ ወደፊት የማይሰሙ ሆኑ (ዘፍ. 6፡5፥ 11-13)። ልጆች በተፈጥሮ ያላመኑትን ቤተሰቦቻቸውን ይከተላሉ። ምክንያቱም ልባቸው በተፈጥሮ በኃጢአት የተሞላ ስለሆነ ነው። እንደዚሁም ሁሉ ያላመኑትን የሚያገቡ ሰዎችም በእምነታቸው ጠንካሮች አይደሉም፤ ምክንያቱም በእምነታቸው ጠንካሮች ቢሆኑ ኖሮ እንዲህ ባላደረጉም ነበር። ይህ ሰይጣን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ልጆች ለማጥፋት የሚሞክርበት መንገድ ነው።

አብርሃም ልጁ ያላመነችውን ሴት እንዲያገባ አልፈቀደለትም ነበር (ዘፍ. 24፡3፥ 4)። ይስሐቅም አልፈቀደም ነበር። ዘፍ. 28፡1፤ ዘዳግም 7፡3፥ 4። ደግሞ ኢያሱ 23፡12፥ 13፤ ዕዝራ 9፡12፤ ነህምያ 13፡25 ተመልከት። እግዚአብሔር የአዲስ ኪዳን አማኞችን ደግሞ ያላመኑትን እንዳያገቡ ይከለክላል (2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)። ምክንያቱም በኃጢአት ላይ ወድቀው ቤተ ክርስቲያንን እንዳያጠፉ ነው። አንዳንዶችም በዘፍ. 6፡2 እንደተመለከተው ሴቶች መላእክትን ስላገቡ ከዚህ የተነሳ ልጆቻቸው ኃይለኞች ሆኑ ብለው ያስተምራሉ (ቁጥር 4)። የዚህ ጥቅስ ትክክለኛው ትርጉም የእግዚአብሔር ልጆች ማለት አማኞች ዓለማዊ ሴቶችን አገቡ ማለት ነው። ልጆቻቸውም እግዚአብሔርንም አልፈሩም፤ ከዚህም የተነሳ ደስ የሚያሰኛቸውን ሁሉ በማድረግ የእግዚአብሔርን አሳብ ሁሉ ተቋቋሙ። መንፈስ የሆነ መልአክ ሊወልድ ወይም ሊዋለድ አይችልም (ማቴ. 22፡29፥ 30)። መላእክት ሊወልዱና ሊዋለዱ አልተፈጠሩም፥ መንፈስም ስለሆኑ ሥጋ መሆንም አይችሉም።

50. እግዚአብሔር በቁጣው ጊዜ እንኳ እንዴት ቁጣውን በጸጋው ለወጠ? ዘፍ. 6፡3።

መልስ።

እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ፍርዱን ቢያወርድ እንኳ ለሰዎች ሁሉ ማምለጫውን ሰጥቶአቸዋል። እርሱም ኃጢአታቸውን ተናዘው እንዲመለሱ 120 ዓመት ሰጥቶአቸዋል። በዚያን ዘመንም ኖኅ መርከብ እየሠራ በሥራና በቃል ስለሚመጣው ፍርድ እየመሰከረ የደኅንነትን መንገድ ይናገር ነበር (ዘፍ. 6፡3።) በ2ኛ ጴጥ. 2፡5)። «የጽድቅ ሰባኪ ተብሎ ተጠርቶአል።»

51. ሰው በኃጢአቱ ሳይናዘዝ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሕይወቱ ይቀጥላልን?

መልስ።

ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ምክርና ትግል አልሰማ ሲሉ መንፈስ ቅዱስ ለፍርድ ይተዋቸዋል። ዘፍ. 6፡3 «ጌታም መንፈሴ ዘወትር አከታትሎ ከሰው ጋር አይታገልም፥ እርሱ ሥጋ ለባሽ ነውና ይላል።» ይህ ነገር ዛሬም በእውነት የሚሆን ነገር ነው። ኢሳ. 63፡10፤ 45፡9፤ ማቴ. 12፡31፤ ማር. 3፡29፤ 1ኛ ሳሙ. 16፡14፤ መዝ. 50(51)፡11 ተመልከት። መንፈስ ቅዱስ በሰው ሕይወት ውስጥ እስከታገለ ድረስ ለዚያ ሰው የመዳን ተስፋ አለው።

52. ኖኅ በምን መሠረት ነው በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ያገኘው?

መልስ።

«ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ» (ዘፍ.6፡8፥9)። ሁለት ሰዎች ካልተስማሙ አብረው አይሄዱም (አሞጽ 3፡3)። ኖኅ የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም አምኖ ተቀበለ። ኖኅም ከመርከብ በወጣ ጊዜ እንስሳ በመሠዋት የነበረውን እምነት አሳየ (ዘፍ. 8፡20፥21)። በዕብራውያን 11፡6 ፥7 ኖኅ በእምነት እንደዳነ ተጠቅሶአል። እምነት ባይኖረው ኖሮ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችልም ነበር። ኖኅም «በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ (ዕብ. 11፡7)። ከአዳም ጊዜ ጀምሮ ሰው የሚድንበት ሌላ መንገድ ስለሌለ በክርስቶስ ደም ካልሆነ በቀር መዳኛ መንገድ የለም።

53. ኖኅ በምስክርነቱ በዘመኑ የነበሩትን ሰዎች እንዴት እንደኮነናቸው አሳይ። ዕብ. 11፡7፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡5።

መልስ።

እግዚአብሔር ዓለምን በውኃ አጠፋለሁና መርከብ ሥራ ባለው ጊዜ ኖኅ ሳይጠራጠር በእግዚአብሔር አመነ። ስለዚህ መርከብ እየሠራ የደኅንነትን መንገድ ለሚጠፉት ይሰብክ ጀመር። እርሱም በ2ኛ ጴጥ. 2፡5 የጽድቅ መልእክት ሰባኪ ተባለ። ስለዚህ በሥራውና በምስክርነቱ በዘመኑ የነበሩትን ሰዎች

ኮነነ። ሁልጊዜ ሰዎቹ የሚሠራውን መርከብ እያዩ መልእክቱን ይሰሙ ነበር። እነርሱም መኮነናቸውን በጆሮአቸው እየሰሙ በዓይናቸው ይመለከቱ ነበር። ዛሬም አማኞች በመንፈሳዊ እርምጃቸውና በምስክርነታቸው ዓለምን ይኮንናሉ። ሰዎች እውነተኛ አማኞችን ሲያዩ በመርከብ በሚመስለው በክርስቶስ ሆነው ባይድኑ እንደሚኮነኑ ይገነዘባሉ።

54. ሙሴ ከዘፍጥረት ላይ የጻፈውን መምሪያ ከየት ያገኘ ይመስልሃል?

መልስ።

የዘፍጥረት መጽሐፍ ከሙሴ በፊት የነበረውን የሰውን ታሪክ የያዘ ነው። ሙሴ ራሱ ምን እንደሚጽፍ አያውቅም ነበር። ነገር ግን ከቤተሰቦቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች የሰማውን አልጻፈም። ከሰው ወደ ሰው የተነገሩት ነገሮች ከጊዜ ብዛት ዓላማቸውን ስተው ልክ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ስለዚህ አሁን የዘፍጥረት መጽሐፍ ያልተሳሳተ ትክክለኛ መጽሐፍ መሆኑን የምንረዳው ክርስቶስ ራሱ ከዚህ ታሪክ ጠቅሶ ስላስተማረ ነው (ማቴ. 19፡4-6፤ 24፡37-39፤ ማር. 10፡4-9፤ ሉቃ. 11፡49-51፤ 17፡26-29፥ 32፤ ዮሐ. 7፡21-23፤ 8፡44፥ 56፤)። በ2ኛ ጢሞ. 3፡16 ላይ እንደተነገረው «የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ሁሉ የተሰጡት በእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ነው።» እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ከሙሴ ጋር በተራራ ላይ 40 ቀንና 40 ሌሊት ቆየ። በሕግ መጻሕፍት ላይ መጻፍ የሚገባውን ሁሉ ከእርሱ ተቀበለ። የፍጥረትን ታሪክና ሕግጋትን የእግዚአብሔር ቃል በትክክል እንደሚያስረዳው ከእግዚአብሔር ተቀብሎ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ጻፈው።

55. የጥፋት ውኃው ታሪክ ምን ያህል ያጠቃልልና እስከ መቼስ ድረስ ቀጥሎ ነበር?

መልስ።

ጎርፉ ያጥለቀለቀው ምድርን ሁሉ ሲሆን ተራራን ሁሉ እስኪሸፍን ድረስ ሞልቶ ነበር (ዘፍ. 7፡12፥ 17-24)። ዝናቡም 40 ቀን ከዘነበ በኋላ ውኃው ሳይጎድል በምድር ላይ 150 ቀን ቆየ። ኖኅም በመርከብ ውስጥ አንድ ዓመት ከ10 ቀን ቆየ (ዘፍ. 7፡17-24፤ 8፡1-14)። ኖኅም በተወለደ በ600 ዓመቱ ከሁለት ወር ከሰባት ቀን ወደ መርከቡ ገባ (ምዕ. 8፡13፥ 14)። ኖኅም በተወለደ በ601 ዓመት ከሁለት ወር ከ27 ቀን ከመርከብ ወጣ። ውኃው በሞላ ከላይ የመጣ ሳይሆን የምድር ምንጮችም ተከፍተው ከሥርም ይጎርፍ ነበር (ዘፍ. 7፡11)። ይህን የሚያህል የውኃ ጎርፍ ከላይ ሲወርድ ከምድርም ውኃ ወደላይ ይፈልቅ ነበር።

56. ሀ. የመርከቡን በር የዘጋው ማን ነበር? ዘፍ. 7፡16።

መልስ።

እግዚአብሔር ራሱ የመርከቡን በር ዘጋው። የምሕረቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ኖኅ ራሱ የመርከቡን በር ይከፍትላቸው ነበር።

56. ለ. እግዚአብሔር በሩን በሚዘጋበት ጊዜ ሰው በፈቃዱ በሩን መክፈት ይችላልን?

መልስ።

እግዚአብሔር በሩን በሚዘጋ ጊዜ ማንም ሰው ሊከፍት አይችልም። ሰዎቹ በኃጢአታቸው ተናዘው ለመመለስ 120 የምሕረት ዓመት ተሰጥቶአቸው ነበር። እነርሱም ኖኅ መርከቡን ሲሠራና መልእክቱን ሲሰብክ በዓይናቸው እያዩ በጆሮአቸው ይሰሙ ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ከመስማት እምቢ ስላሉ ተጨማሪ ምሕረትን አላገኙም። ሰዎች ውኃውን ባዩ ጊዜ ወደ መርከቡ ለመግባት እንደሮጡ አያጠራጥርም። ከውጭም ሆነው የመርከቡን በር እየመቱ ኖኅን በመጥራት «አሁን ከፈትልን እናምናለን» ሳይሉ አይቀሩም። ኖኅም ምናልባት እግዚአብሔርን እየተጣራ ሰዎቹ ለመዳን መጥተዋልና ከፈትላቸው እያለ በሩን ለመክፈት ሳይታገል አይቀርም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ምሕረትና የመንፈስ ቅዱስን ልመና እምቢ ካሉ በኋላ ወደፊት ተጨማሪ ምሕረት የለም። እግዚአብሔር ከፍርድ እንጂ ከኃጢአታቸው ለመዳን የማይፈልጉትን አፋዊ አማኞች በመርከቡ ውስጥ ሊቀበላቸው አልፈለገም።

ዛሬም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ማንኛውንም ነገር ግልጽ አድርጎ ካስረዳቸው በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ልመና አልሰማ ብለው ደኅንነትን እምቢ አሉ።

እነዚህም መንፈስ ቅዱስን የሚሳደቡና የሚያንቋሽሹ ናቸው። ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ይተዋቸዋል፤ ከእንግዲህ ወዲያም የደኅንነትን መንገድ የሚከፍትላቸውም አያገኙም (ማቴ. 12፡31፥ 32፤ ማርቆስ 3፡28-30)።

57. በመርከቡ ውስጥ ሆነው የዳኑ ስንት ናቸው?

መልስ።

በመርከቡ ውስጥ ሆነው የዳኑት ስምንት ሰዎች ናቸው። እነርሱም ኖኅና ሦስት ልጆቹ ካም ሴምና ያፌት ከነሚስቶቻቸው ነበሩ (ዘፍ. 7፡7)።

ምዕራፍ 8ን አንብብ።

58. መርከቡ በምን ተራራ ላይ ሊያርፍ ወረደ?

መልስ።

መርከቡ ዛሬ የሩሲያ፥ የቱርኮችና የኢራቅ ድንበር በሆነው በአራራት ተራራ ላይ አረፈ (ምዕ. 8፡4)።

59. ኖኅ በመጀመሪያ ጊዜ ከመርከቡ እንደወጣ ምን እንዳደረገና ያደረገው ነገር ምሳሌነት ምን እንደሆነ አብራራ።

መልስ።

ኖኅ መሠውያ ሠርቶ በመሠውያው ላይ የሚቃጠል መሥዋዕትን ለጌታ አቀረበ (ዘፍ.8፡20፥ ዘፍ. 8፡21)። እግዚአብሔር ኖኅ ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ያለውን እምነት ባየ ጊዜና (በሚቃጠል መሥዋዕት በክርስቶስ ያለውን እምነት በገለጠ ጊዜ) እግዚአብሔር ደስ አለው። እግዚአብሔርም የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕቱንም አሸተተ። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር በኖኅ መሥዋዕት በእርሱ ያለውን እምነት ተመልክቶ ሊሆን ያለውን የክርስቶስን ሞት አየ፤ ወይም አሸተተ። ትርጉሙም በ2ኛ ቆሮ. 2፡15 ጳውሎስ እንደጠቀሰው በክርስቶስ ባለን እምነት የተነሣ ለእግዚአብሔር «ጣፋጭ ሽታ» ነን። ደግሞም በኤፌሶን 5፡2 ላይ እንደገና ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን መሥዋዕት አድርጎ ሲሰጥ እኛ እንድንድን ለእግዚአብሔር «የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት» አድርጎ ራሱን እንዳቀረበ ያመለክታል። ስለዚህ እግዚአብሔር ኖኅ ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ሞት ማመኑን አይቶ ደስ አለው።

ንጹሕ ካልሆነ እንስሳና አዕዋፍ ከእያንዳንዱ አንዳንድ ጥንድ ወደ መርከቡ ሲያስገባ ከንጹሖቹ እንስሳትና አዕዋፋት ግን ሰባት ጥንድ እያደረገ ወደ መርከቡ አስገባ፤ ለዚህ ነው እንግዲህ ኖኅ ለመሥዋዕት የሚያቅርባቸውን እንስሳት ያገኘው (ዘፍ. 7፡2-3)።

## ምዕራፍ 9 አንብብ።

60. በኖኅና በእግዚአብሔር መካከል ለቆመው ቃል ኪዳን መሠረትና ቀንበር ሰጠው። ዘፍ. 8፡20-22፤ 9፡11።

መልስ።

በክርስቶስ ደም መሠረት ላይ ማለት ኖኅ በእምነት ባቀረበው በሚቃጠል የመሥዋዕት ደም እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶ ዓለምን ዳግመኛ በውኃ እንደማያጠፋ ተናገረ (ዘፍ. 8፡21፤ 9፡11)። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ሰዎች ከጥፋት ውኃ በፊት በነበሩበት ኃጢአትና ርኩሰት እንዳይጠመዱ እግዚአብሔር ሌላ የመዳኛ መንገድ አዘጋጀ (ዘፍ. 8፡21፤ 9፡1-17)።

1. እግዚአብሔር ምድርን እንዲገዛ ለአዳም ትእዛዝ እንደሰጠው ለኖኅም ተመሳሳይ ትእዛዝ ሰጥቶታል (ዘፍ. 8፡21፤ 9፡1፥ 2)።

2. ሰዎች ሌላውን ሰው ከመግደል እንዲፈሩና እንዲጠነቀቁ ነፍሰ ገዳይ የሆነ ሰው እንዲገደል ትእዛዝ ተሰጠ (ዘፍ. 9፡5 ፥6)። ይህ ሕግ የተሰጠው ከጥፋት ውኃ በፊት አልነበረም።

3. የሰውም ዕድሜ አጭር ሆነ (መዝ. 89(90)፡ 10)። ይህም አመጸኞችና ኃጢአተኞች በኃጢአታቸው እየጨመሩና እየባሱ በመሄድ ሌሎችንም ክፋት እንዳያስተምሩና እንዳያበላሹአቸው ዕድሜአቸውን ለማሳጠር ይጠቅማል።

4. ሕዝቡም በተለያየ ቋንቋና ቀለም እንዲሁም ዘር የተከፋፈለ ነበር። ከእነዚህ ነገድ አንዱ በኃጢአትና በርኩሰት ሲሰለጥን ሌላው ዜጋ ተነስቶ ያጠፋው ነበር። ከጥፋት ውኃ በፊት ሕዝቡ ሁሉ አንድ ቋንቋ ነበረው። ሰዎች ክፋት እየጨመሩና እየባሱ እንዲሄዱ ካደረጋቸው ነገር አንዱ ይህ ነው (ዘፍ. 11፡1፥ 6)።

61. የኪዳኑ ምልክት ምን ነበር?

መልስ።

የኪዳኑ ምልክት ቀስተደመና ነበር (ቁጥር 13 ዘፍ. 9፡8-17)።

62. ከጥፋት ውኃ በፊት ቀስተደመና ዝናብና ጉም ነበርን? ዘፍ. 2፡5፥ 6፤ 9፡14-16።

መልስ።

ከጥፋት ውኃ በፊት ዝናብ ያለ አይመስልም። ጭጋግ ከምድር እየተነሳ መሬትን ያጠጣት ነበር። ዝናብ በሌለበት ደመናና ቀስተደመና አይኖርም (ዘፍ. 2፡5 ፥6)። በዘፍጥረት 9፡14-16 እንደተጠቀሰው ቀስተደመና አዲስ ነገር ነበር። ደመናም በፊት ያልታየ አዲስ ነገር ነበር። እግዚአብሔር ኖኅ ሊሞት ባለው በክርስቶስ ማመኑን ስለአየ ዓለምን ዳግመኛ በውኃ እንደማያጠፋ ለኖኅ ቃል ኪዳን ገባለት። በክርስቶስ ከሚኖረን እምነት የተነሳ ፍርድ አይኖርብንም። እስከ ዛሬ ድረስ ቀስተደመናን በምናይበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን ብቻ ከፍርድ እንዳዳነን እንድናስብ ይፈልግብናል (ዮሐ. 3፡18፥ 36፤ 5፡24)።

63. በካም ላይ የተወሰነበት ርግማን ነበረን? ዘፍ. 9፡18-29።

መልስ።

በዘፍ. 9፡18-29 በካም ላይ የተባለ ምንም ዓይነት መርገም የለም። ኖኅ ታናሹ ልጁ ያደረገውን ባወቀ ጊዜ ተናዶ ይረግመው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በዚህ ፋንታ በከነዓን ላይ ትንቢት እንዲናገር አድርጎታል። የካም ልጅ የሆነው ከነዓንም በአባቱ ኃጢአት ምክንያት አልተረገመም (ሕዝ. 18፡20፤ ዘዳግ. 24፡16)። እያንዳንዱም ሰው ስለየግል ኃጢአቱ ይፈረድበታል። ከነዓን እግዚአብሔር ለተመረጠው ሕዝቡ የጠበቀውን ምድር ለራሱ እንደሚወስድና ተቀናቃኝ እንደሚሆን አስቀድሞ አውቆት ነበር። ከነዓናውያን በጣም ክፉዎች እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ስላወቀ ከነዓናውያንን አጥፍቶ ምድሩን ለእስራኤላውያን መስጠት ነበረበት። ስለዚህ ይህ ትንቢት በመጽሐፈ ኢያሱ ተፈጸመ።

64. በከነዓን ላይ የወደቀው ርግማን ከነዓን እግዚአብሔርን የመከተል ነጻነት አጥቶ በረከትን እንዳይቀበል አደረገው? ዘዳ. 24፡16፤ ሕዝ. 33፡11፤ 18፥ 20።

መልስ።

እግዚአብሔር ሁሉን መባረክና ማዳን ይፈልጋል። ከነዓን ቢፈልግ ኖሮ የእግዚአብሔርን ደኅንነትና በረከት ይቀበል ነበር። የራሱን ፍላጎትና ፈቃደኝነት ተከተለ። ስለዚህ ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ከነዓን የሚመርጠውን አስቀድሞ ስላወቀ የከነዓንን ፍርድ አስቀድሞ ይናገር ነበር። ሰዎችም ሁሉ መዳን ከፈለጉ ይድኑ ነበር። ይህም የእነርሱ የግል ፍላጎት ነው። ዘዳ. 24፡16፤ ሕዝ. 18፥ 20፤ 33፡11፤ ኤር. 31፡30 ተመልከት። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ሊድኑ እንደሚፈልግ የሚገልጸውን ለመረዳት ሕዝ. 33፡11 እና 2ኛ ጴጥ. 3፡9 ተመልከት። «ጌታ ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲመጡ እንጂ ማንም እንዲጠፉ አይፈልግም።»

65. ሴምና ያፌት የተቀበሉት በረከት ምንድር ነው? ዘፍ. 9፡26፥ 27።

መልስ።

1. የዘፍጥረት 9፡26 ትክክለኛው ትርጉም እንደሚለው «የሴም ጌታና አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ» ይላል። በዚህ ቦታ ጌታ የሆነው ክርስቶስ ተባረከ። ክርስቶስ በሴም ዘር በኩል ወደ ምድር ስለሚመጣ በዚህ ሥፍራ በረከትን ተቀበለ። ከነዓንም የሴም አገልጋይ ይሆናል ተባለ። ይህም ትንቢት ተፈጸመ። የሴም ዘር የሆኑትን ከነዓናውያን እስራኤላውያን አጠፉአቸው። በምድሩም ላይ የተረፉት ከነዓናውያን የእስራኤላውያን ባሪያዎች ሆኑ።

2. «እግዚአብሔርም ያፌትን ያስፋ» (ዘፍ. 9፡27)። ይህም ተፈጽሞአል። የያፌት ዘር የሆኑት ኤውሮፓውያን ወይም ነጮች በዓለም ውስጥ በየትኛውም ሥፍራ ይገኛሉ። እነርሱም ኤውሮፓውያን አውስትራልያንና ሌሎችም ብዙ አገሮች ሞልተዋል። «እርሱም በሴም ድንኳን ያድራል።» የያፌት ልጆች የሴም እንግዶች ናቸው። የኢየሱስ ክርስቶስ እንግዳዎች ማለት ደግሞ ከሴም ዘር የተወለዱት ናቸው። የኤሮፓውያን ዜጎች ሁሉ የክርስቲያንን ሃይማኖት ተቀብለዋል። ወንጌሉም ወደ ሁሉም መጥቶአል። ሆኖም በነፍስ ወከፍ አዳኙን አልተቀበሉም። የዚህም ትርጉም ያፌት የሴም ወገን የሆነውን አዳኝ ተቀብሎአል ማለት ነው። እርሱንም ያመልኩታል። በሴምም ድንኳን ያድራሉ።

«ከነዓን ግን የእርሱ አገልጋይ ይሆናል።» ከነዓናውያን ብቻ ሳይሆኑ የካም ነገዶች በሙላ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንኳን የያፌት አገልጋዮች ነበሩ። ኢትዮጵያውያን ግን በከፊል የሴም ወገን ስለሆኑና በዚህም ማረጋገጫ ቋንቋቸው ስለሚመሰክር ከባርነት ፈጽሞ ነፃና ገለልተኛ ናቸው። በአፍሪካ አህጉርም ከሚገኙት አብዛኞዎቹ ዜጎች ኢትዮጵያውያን ብቻ ክርስቲያኖች ነበሩ።

## ምዕራፍ 10 እና 11 አንብብ።

66. ሀ. በዚህ ምዕራፍ የኖኅ ነገድ በምን ሦስት ታላላቅ ክፍሎች ተከፈሉ?

መልስ።

ሦስቱ ታላላቅ ነገዶች

1. ሴማውያን የሴም ነገዶች ናቸው። ለእነርሱም እግዚአብሔር በተለይ ምዕራባዊውን እስያ ሰጥቶአቸዋል።

2. ካማውያን የካም ነገዶች ናቸው። ለእነርሱም እግዚአብሔር አፍሪካን ሰጥቶአቸዋል።

3. ያፌታውያን የያፌት ነገዶች ናቸው። ለእነርሱም እግዚአብሔር ኤውሮፓን ሰጥቶአቸዋል። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር በኖኅ ትንቢት እየበዙ እንደመሄዳቸው መጠን ሌላውንም የምድር ክፍል ሰጥቶአቸዋል።

66. ለ. የትኛው ጥቅስ ነው ስለ እያንዳንዱ የሚገልጸው?

መልስ።

በም. 10፡2-5 ያለው ጥቅስ ስለ ያፌት ዘር ይገልጻል። ከም. 10፡6-20 ስለ ካም ይገልጻል። ከም. 10፡21-32 ስለ ሴም ዘር ይገልጻል።

67. እግዚአብሔር ለአዳምና ለኖኅ ምን ትእዛዝ ሰጣቸው? ዘፍ. 1፡28፤ 9፡1።

መልስ።

እግዚአብሔር አዳምንም ሆነ ኖኅን እንዲባዙና ምድርን እንዲሞሉ አዘዛቸው። ትክክለኛው እንደገና «መተከልና» ዳግመኛ ተተክሎ እንደገና መሙላት ነው። እግዚአብሔር ለአዳም ይህን ትእዛዝ የሰጠው አዳም ከመፈጠሩ በፊት ሰይጣን ስለወደቀና ምድር ስለተበላሸች ነው። (ለሰባተኛው ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ተመልከት)። ስለዚህ አዳም እንደገና ተተክሎ ምድርን መሙላት አለበት። ለኖኅ ደግሞ ይህ ትእዛዝ የተሰጠው ከጥፋት ውኃ በኋላ እንደገና አዲስ ሆኖ ስለጀመረ ነው። ትእዛዙ ዓለምን ሁሉ መሙላት ነው። ይህም ማለት ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና በምድር ሁሉ ላይ ተበታትነው ምድርን ሁሉ ይዘው በፍጥረታት ሁሉ ላይ እንዲገዙ ነው (ዘፍ. 1፡29፤ 9፡2፥ 7)።

68. ሰዎቹ በገዛ ፈቃዳቸው አልታዘዝም ብለው ምን አደረጉ? ዘፍ. 11፡1-4።

መልስ።

እግዚአብሔር እስከ ሩቅ ቦታ ድረስ ወጥተው እንዲሰራጩና ምድርን ሁሉ ለራሳቸው እንዲያደርጉ አዘዛቸው፤ ሰዎችም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመከላከል ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፥ በምድር

ላይ ሳንበታተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ (ምዕ. 11፡4)። እነርሱም እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ አድማ አደረጉ። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያለመቀበል ኃጢአት ነው። ያለመታዘዝ ኃጢአት ከአዳም ውድቀት ጀምሮ እስከ አሁን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጠላትነትን አስቀምጦአል። ሰው መንፈሳዊ ዓይኑ ስለታወረ በገዛ ፈቃዱ አለመታዘዝን መረጠ። ቢታዘዝ ኖሮ ደኅንነት የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተቃረነ።

69. እግዚአብሔር ሰዎቹ እንዲታዘዙት እንዴት ያስገድዳል? ዘፍ. 11፡5-9።

መልስ።

ዘፍ. 11፡5 እግዚአብሔር ሕዝቦች ከጥፋት ውኃ በፊት በአንድነት ሆነው ከመጠን በላይ ኃጢአትን እንደሚያደርጉ አስተዋለ። ስለዚህ እግዚአብሔር አንዱ የሚናገረው ለሌላው እንዳይገባው ቋንቋቸውን ለያየው፥ ከዚያም ተለያይተው በምድር ሁሉ ተበታተኑ (ዘፍ. 11፡9)።

የሴም ነገዶች አንድ ዓይነት ቋንቋ ሆኖ በተለያዩ ቋንቋዎች የተከፈለ ቋንቋ ተሰጣቸው። ሆኖም ቋንቋው ተቀራራቢ የሆነ ግንኙነት አለው። ይህም እውነት እንደሆነ በአሁኑ ጊዜ እንኳን የሴማቲክ ቋንቋዎች መቀራረብ ይመሰክራል። እንደ ሴማቲክ ቋንቋዎች ያፌታዊውም ቋንቋ ይቀራረባል። እነዚህ ሦስት ታላላቅ ቋንቋዎች በየበኩላቸው በተለያዩ ብዙ ቋንቋዎች ተከፍለዋል። በአሁኑ ጊዜ በምድር ላይ 3000 የሚሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ (ዘፍ. 10፡5፤ 20፡31፥ 32)።

70. በዚህ ፍርድ ውስጥ የእግዚአብሔር ምሕረት እንዴት ይታያል?

መልስ።

ሰዎቹ ዳግመኛ ክፉዎች ሆነው እንደገና ደግሞ ሁሉም እንዳይጠፉ እግዚአብሔር በብዙ ቋንቋና ነገድ ከፋፈላቸው። ከጥፋት ውኃ ወዲህ አንዱ ነገድ ለፍርድ የተዘጋጀ ሲሆን ሌላው ነገድ ተነስቶ ይቀጣቸው ነበር። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለመቅጣት ሶርያውያንን አስነስቶ ተጠቀመባቸው። ይሁዳንም ለመቅጣት በባቢሎናውያን ተጠቀመ። ባቢሎናውያንንም ለመቅጣት በሜዶ ፋርሳውያን ተጠቀመ። መጽሐፍ ቅዱስም እንደዚህ ባሉት ምሳሌዎች የተሞላ ነው። ስለዚህ ይህ የቋንቋ መለያየት ነገር ሰው ዳግመኛ እንደ ጥፋት ውኃ ዘመን በታላቅ ፍርድ እንዳይጠፉ የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚያሳይ ምልክት ነው። የእስራኤል ነገድ በእግዚአብሔር ተመርጦ በአሕዛብ መካከል በመኖር የእግዚአብሔር ደኅንነት መስካሪ እንዲሆን ተደረገ (የሐዋርያት ሥራ 17፡26፥ 27፤ ዘዳ. 32፡8፥ 9)።

71. ይህ ቋንቋ እየተሻሻለ መጣ ወይስ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ፍጹም የሆነ ቋንቋ ሰጣቸው?

መልስ።

በዘፍ. 11፡7-9 እንደተገለጠው እግዚአብሔር ለየቤተሰቡና ለየወገኑ በአንድ ጊዜ አንድ ዓይነት የተለያየ ቋንቋ ሰጥቶአቸዋል። ሕዝቦቹ በአንድ ጊዜ ቋንቋቸው ስለተለያየ አንዱ የሚለው ሊገባው አልቻለም። ከዚህም የተነሳ ሥራቸውንም ሊሠሩ አልቻሉም። ስለዚህ በያለበት ተበታተኑ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቋንቋ በየአንጻሩ የተለያየ ሆነ።

72. ምድር ለተለያዩ ሰዎች የተከፋፈለችው በምን ደንብና ሥርዓት ነው? ዘዳ. 32፡8፥ 9።

መልስ።

እግዚአብሔር ወገኖችን ሲከፋፍልና ምድራቸውን ሲሰጣቸው ወንጌል ከማንኛቸውም የራቀ እንዳይሆን ሕዝበ እስራኤል በመካከላቸው እንዲኖሩ አደረገ። ለዚህም ለእያንዳንዱ ወገን በፈለገበት ቦታ እርስት እንዳከፋፈላቸው ይታያል። ለያፌት ኤውሮፓን ለሴም እስያን ለካም ደግሞ አፍሪካን ሰጠ። ምድረ ከነዓንን እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ለዘለዓለም ርስት አድርጎ ጠብቆላቸዋል። ስለዚህ የእነዚህ ሦስት ታላላቅ ወገኖች መኖር እውነት ነው። ስለዚህ ወንጌል በእነዚህ በሦስቱም ወገኖች አቅራቢያ መገኘት አለበት። ወደዚያም ምድር ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ። ከዚያም ምድር ኢየሱስ ክርስቶስ ለ1000 ዓመት በሰላም በአሕዛብ ሁሉ ላይ ወደፊት ይገዛል (የሐዋ. ሥራ 17፡26፥ 27)።

73. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የጠበቀላቸው ምድር የትኛው ነው? ዘፍ. 15፡18፤ ዘጸአት 23፡31፤ ዘዳግም 11፡24፤ ሕዝ. 47፡18።

መልስ።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከነዓን ያተባለውን ምድር ነው ርስት አድርጎ የጠበቀላቸው ይህም ምድር የሚገኘው በታላቁ ባሕር በስተምሥራቅ በሚገኘው የባሕሩ ዳር ነው። እንደተሰፋውም ቃል እግዚአብሔር ከግብጽ ባሕር አንስቶ እስከ ቀይ ባሕር ማለት እስከ (ኤርትራ ባሕር) ከዚያም በምስራቅ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ከሊባኖስ ይዞ እስከ ሶሪያና እስከ ፋርስ ሸለቆ ነው። እስራኤላውያን እስከ አሁን ድረስ ይህንን ምድር አልያዙም፥ ነገር ግን ኢየሱስ በምድር 1000 ዓመት ሊነግሥ ሲመጣ ይህን የተባለላቸውን ምድር በሞላ ይወርሳሉ።

74. እግዚአብሔር ምድርን ለምን እንደዚያ ከፋፈላት? የሐዋ. ሥራ 17፡26፥ 27።

መልስ።

እግዚአብሔር ምድርን እንደዚያ የከፋፈላት እስራኤል በአሕዛብ መካከል እንዲሆኑና የደኅንነት የምስራች የሚያውጀው ወንጌል ከሰዎች እንዳይርቅ ነው። ስለዚህ ማንም በቅርብ የደኅንነትን መንገድ ቢፈልግ እዚያው በቅርቡ የደኅንነትን መንገድ እንዲያገኝ ነው።

ወንጌል የሚለው ቃል ትርጉም የምስራች ወይም መልካም ዜና ማለት ነው። ይህም መልካም ዜና ለሚፈልጉ ሁሉ ደኅንነት በክርስቶስ በኩል እንዳለላቸው የሚያውጅ ነው። ይህም መልካም ዜና ወይም ወንጌል ለአዳም እንኳን ተሰጥቶአል። በኋላም የዮሐንስ፥ የማቴዎስ፥ የሉቃስና የማርቆስ ወንጌላት የክርስቶስን የምድራዊ ሕይወቱን ታሪክ ስለያዙ አራቱ ወንጌላት ተብለው ተጠሩ። መጽሐፍ ቅዱስ በሞላ ለሰው የሚሆነውን መልካሙን ዜና ይዞአል። በሚከተለው ወንጌል በሚለው አርዕስት በመግለጫው ላይ ተመልከት።

75. እግዚአብሔር የባቢሎንን አገር ለየትኛው ወገን ነው የሰጠው? ዘፍ. 10፡21-32፤ 11፡27፥ 28።

መልስ።

ባቢሎን ከሴም ወገን ለሆኑት ለአሶራውያን የተሰጠ ነው። ከአርፋክሳድ ዘር ማለት ከሴም ወገን የሆነው አብርሃምም ከባቢሎን አገር ከዑር ነው የመጣው፥ ያም ምድር የከለዳውያን አገር ተብሎ ይጠራል፤ የቀድሞው ስም ሬሴን ይባል ነበር (ዘፍ. 10፡9-11)።

76. እንደ ዘፍ. 10፡6-11 በየስፍራው ከተበታተኑ በኋላ በባቢሎን ውስጥ ማን አረፈባት?

መልስ።

ለሴም ወገን የተሰጠው ባቢሎን የካም ዘር በሆነው በናምሩድ ተያዘ።

77. እንዴት ይህ ምድር በሌላ ወገን መያዝ ቻለ?

መልስ።

ዘፍ. 10፡11 በቁጥር 11 ላይ እንደተገለጠው ናምሩድ ምድሩን በኃይል ያዘ። ናምሩድ ወደ ከተማዋ በገባ ጊዜ ከሴም ወገን የሆነው አሴር ባቢሎንን ለቅቆ በስተ ሰሜን በሚገኘው ምድር አረፈ። አሶር ለምለሙን የሬሴን ምድር ለቅቆ ጠፍ ወደሆነው ወደ ሰሜናዊው ምድር የሄደው ፈቅዶ አይደለም።

78. በዘፍጥረት 10፡8፥ 9 ስለናምሩድ በተገለጠው ክፍል ስለ ዓለም መንግሥታት ምን ታስተውላለህ?

መልስ።

ናምሩድም «በምድር ላይ ኃያል መሆንን ጀመረ» (ዘፍ.10፡8)። ይህም ማለት ኃያል ተዋጊና ገዢ ሆነ ማለት ነው። አሦራውያንንም ነድቶ አስወጣቸው። እርሱም በጌታ «ፊት ኃይለኛ አዳኝ» ነበር። ይህም ሲተረጎም «በጌታ ላይ ኃይለኛ አዳኝ ነበር ማለት ነው።» እርሱም አልታዘዝ በማለት ጌታን እምቢ አለ (ቁጥር 9)። በምድር ሲነገር እንደሚሰማው ናምሩድ በእግዚአብሔር ላይ ያምጽና ይከፋ ጀመር። የቁጥር 9 አድራጎቱም በየስፍራው ሁሉ የታወቀ ሆነ። እርሱም በተከታታይ ከእርሱ በኋላ የመጡትን የዓለም ነገሥታት ጠባይ ይዞ ነበር።

1. ሌሎቹን ወገኖች እግዚአብሔር ከሰጣቸው ምድር አስወጣቸው (ዘፍ. 10፡10፥ 11)።

2. እርሱም በፊቃዱ እግዚአብሔርን አልታዘዝ አለ።

3. የእግዚአብሔርንም ፊት ተጻፈረ።

4. እርሱም እንደ እግዚአብሔር ይመለከ ነበር። የጥንትም ታሪክ የባቢሎናውያን አምላክ እንደሆነና እንደ እግዚአብሔርም ይመለክ እንደነበር ይነግረናል። ናምሩድም ከጥንት የዓለም ነገሥታት የመጀመሪያው ነበር። ሐሰተኛው ክርስቶስም የመጨረሻው የዓለም ገዢ ይሆናል። ከጥፋት ውኃ ጀምሮ እስከ 44000 ዓመት በዓለም ላይ አራት የዓለም ነገሥታቶች ብቻ ነበሩ።

79. እንደ ዘፍ. 10፡13-20 የትኛው የሴማውያን ምድር ነው በኋላ በካም ነገዶች የተወሰደው? መዝ. 105(106)፡22 ተመልከት።

መልስ።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የጠበቀላቸው ምድር የካም ነገድ በሆኑት በከነዓናውያኖች ስለተወሰደ የከነዓናውያን ምድር ተብሎ ተጠራ።

80. ሀ. ስለ እነዚህ ወገኖች ምን ትንቢት ተተንብዮ ነበር? ዘፍ. 9፡25፥ 27።

መልስ።

የተተነበየው ትንቢት ከነዓናውያን የሴም ነገዶች ባሪያ እንደሚሆኑ ነው።

80. ለ. በኋለኛው ጊዜ እነዚህ የሴም ነገዶች ወደምድራቸው ተመልሰው በመኖራቸው ትንቢቱ እንዴት ተፈጸመ?

መልስ።

እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ እንደወጡ ከነዓናውያንን አጥፍተው ከሞት የዳኑትን ባርያ አደረጉዋቸው። እግዚአብሔር ምድሩን ለእስራኤላውያን ለመስጠት ቃል እንደገባላቸው ለእስራኤላውያን ሰጣቸው። ከነዓን እግዚአብሔር ሳይሰጠው ምድሩን ስለያዘ ለዘሮቹ የእግዚአብሔርን ፍርድ አቆያቸው።

81. ለሴም የተሰጠው የተለየ ስም ምን የሚል ነበር? ሴም ለምን በዚህ ስም ተጠራ?

መልስ።

ሴም «የዔቦር ልጆች ሁሉ አባት ተባለ።» የዔቦር ልጆች የተባሉት ዕብራውያኖች ናቸው። እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘራቸው የተወለደው እግዚአብሔር የመረጣቸው እስራኤላውያን ናቸው። በቁጥር 24 እንደተጠቀሰው ዔቦር የሚለው ስም ትርጉም «መሻገር» ማለት ነው። ሴም የእነዚያ የተሻገሩ ወይም ያለፉት ሰዎች አባት ነው። ዔቦር የሚለው ስም ደግሞ በበኩሉ የተተነበየ

ነው። በኋለኛውም ጊዜ አብርሃም ኡር ከተባለው ከከለዳውያን አገር አቋርጦ ወደ ከነዓን መጥቶአል። እስራኤልም በተአምራት የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ከነዓን ገብተዋል። በኋላም እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ በእግዚአብሔር ተአምር ተሻግረው ምድሩን ለመውረስ ገብተዋል። የዔቦርም ልጅ ፋሌቅ ይባላል። ምድሪትዋም የተከፈለችው በፋሌቅ ዘመን ነበር (ዘፍ. 10፡25)። ትርጉሙም ምናልባት የሰው ዘር በተለያዩ ቋንቋዎች መከፋፈል ይሆናል። ከዚያም ምድር በመካከላቸው ተከፋፍላ የሚኖሩበት ምድር ተገልሎ ተሰጣቸው (ዘፍ. 11፡1-9)።

ሳይንስ ግን አሕጉሮች በሞላ አብረው የነበሩ ሳሉ በኋላ ነው የተከፋፈሉት ይላል። አሜሪካም ከኤውሮፓና ከአፍሪካ ጋር አንድ የነበረ አህጉር ነበር ይላሉ። የአህጉሩ ቅርፅ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ላይ የተጣመሩ እንደነበሩ ይመስላል። ይህም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችን ምድር በፋሌቅ ዘመን እንደተከፋፈለች አድርገው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ምናልባት በዘፍጥረት ዘመን ምድሪቱ ስትከፋፈል አህጉሮቹ ቀስ በቀስ እየተነጣጠሉ ሄደው ይሆናል። ይህ በዘፍጥረት 10፡25 ላይ የተነገረው ነገር በአንድ ሰው የሕይወት ዘመን የተፈጸመ ነው። በፋሌቅ ዘመን የተደረገው የመሬት መከፋፈል ለሰው ልጆች የዘርና የጎሳ እንዲሁም የቋንቋና የመኖሪያ ስፍራ የመከፋፈል ምክንያት ነው።

ዘፍጥረት 11፡10 እስከ 12፡4 አንብብ።

82. እግዚአብሔር አብርሃምን ለምን እንደጠራው ከኢያሱ 24፡1-3 ያለውንና በዘፍ. 12፡1-4 በመጥቀስ አስረዳ።

መልስ።

1. በኢያሱ 24፡1-3 እግዚአብሔር አብርሃምን በምድር ሕዝብ ሊያደርገውና ከዘሩም ለራሱ በምድር ነገድን ሊያደርግ ፈለገ። «እግዚአብሔርም ዘሩን አበዛለት።»። (ቁጥር 3)። ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ወገኖች እንዲሆኑ ሌላ አማልክትን ከሚያመልኩ ከሌሎች አሕዛብ መለየት አለባቸው (ቁጥር 2)። ስለዚህ እግዚአብሔር አብርሃምን ከአሕዛብ መካከል ጠርቶ ለራሱ የተለየ ወገን እንዲሆን አደረገው።

2. እግዚአብሔር በአብርሃም ዘር የዓለምን አሕዛብ ሁሉ ሊባርክ ፈለገ (ዘፍ. 12፡3)። ኢየሱስ ክርስቶስም ከአብርሃም ዘር መምጣት ነበረበት። ስለዚህ እግዚአብሔር አብርሃም ቅዱስ የሆኑ ዘሮች እንዲያፈራና መልካሙን ዜና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲያደርሱ ሰዎችም ደኅንነትን እንዲያገኙ አብርሃምን መረጠው። ሁለቱም ማለት ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠን በአብርሃም ዘር በኩል ነው።

83. አብርሃም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አጠናቆ ፈጽሞአል? ዘፍ. 12፡1-4 እና 11፡31፥ 32 ተመልከት።

መልስ።

በዘፍ. 11፡31፥ 32 እንደተጠቀሰው የአብርሃም አባት የከለዳውያንን ምድር ለቆ ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር ከነዓን ለመሄድ የተነሳ ይመስላል። ነገር ግን በምዕራፍ 12፡1 ላይ እግዚአብሔር ማንንም ሳይጨምር አብርሃምን ብቻ ወደ ከነዓን እንዲሄድ እንደጠራው በግልጽ ይታያል። ይኸውም በኃላፊ ጊዜያት ነው። «እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፤» እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ ከነዓን አገር እንዲሄድ ጠራው፤ ሆኖም በጉዞው ቤተሰቦቹ ሁሉ ቢከተሉት ከእርሱ ጋር ከነዓን ሊገቡ አልቻሉም። ከዚያም በሐራን አርፈው አብርሃምም አባቱ እስከ ሞተ ድረስ በዚያው ዘገየ። አንድ ከእግዚአብሔር የተጠራ ሰው ምድራዊ በኩራቱን ካላበረከተ ለሙላት መጠራቱን አላሟላም ማለት ነው።

የአብርሃም አባት በሞተ ጊዜ እግዚአብሔር ገና በከለዳውያን አገር በዑር ሳለ ያደረገለትን ጥሪ ለማሟላትና ለመታዘዝ ነፃ ሆነ። አብርሃም አሁንም የወንድሙን ልጅ አስከትሎ ወደ ከነዓን በመሄዱ አሁንም ሌላ ተጨማሪ ጥፋት አድርጎአል (12፡4፥ 5)። ሎጥ በከነዓን አገር ለአብርሃም ኃዘንና ችግር ብቻ ሆኖበታል። በዚህ ሁሉ ከመጀመሪያው አብርሃም እግዚአብሔርን በሙላት እንዳልታዘዘ እናያለን። እግዚአብሔር ደግሞ አብርሃምን «ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ» ብሎ አዘዘው። እርሱ ግን ከአባቱና ከአባቱ ቤተሰብ ኋላም ከሎጥ አልተለየም።

84. ሀ. በአብርሃም ኪዳን ውስጥ ዋናውና ጎላ ብሎ የሚታየው ምን ኖሮአል? ዘፍ. 12፡1-3።

መልስ።

1. ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ (ቁጥር 2)።

2. በዘርህም የዓለም አሕዛብ በሞላ ይባረካሉ (ቁጥር 3)። ይህ በሙሉ ተፈጽሞአል። አብርሃም ታላቅ ሕዝብ ሆኖአል፥ እነዚሁም የእስራኤል ነገዶች ናቸው። የእስራኤል ክብር ከምንም ጊዜ ይልቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ለ1000 ዓመት ሲገዛ ዳግመኛ ሲመጣ እጅግ ታላቅ ይሆናል። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብዙ ሕዝቦች እንደተባረኩ የቀሩትም ወደፊት ይባረካሉ። ምክንያቱም ከእያንዳንዱ ወገንና ሕዝቡ ጥቂቶቹ እንደተባረኩ እንደዚሁም ደግሞ ስለሚድኑ ነው (ማቴ. 24፡14፤ ራእይ 5፡9፥ 10)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለ1000 ዓመት በምድር ሲገዛ በአሕዛብ ላይ በሞላ በሰላም ይገዛል።

84. ለ. እግዚአብሔር አብርሃምን በመጥራት ይህ ተስፋ የእግዚአብሔርን ውጥን እንዴት ያሳያል?

መልስ።

እግዚአብሔር መጀመሪያውኑ የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ጠብቋል። ይህንንም አገር የመረጠው አዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘራቸው በኩል ወደ ምድር

ለሚመጣው ሕዝቦች ነው። ያም ምድር ወንጌል ከእግዚአብሔር እንዳይርቅ ልክ በትክክለኛው ስፍራ መካከል ነው (የሐዋ. ሥራ 17፡26፥ 27)። በአዳኙ በክርስቶስ በኩል የዓለም ሕዝቦች በሙሉ መባረክ አለባቸው። እግዚአብሔርም አብርሃምን የዚያ ሕዝብ አባት እንዲሆን ጠራው።

84. ሐ. ከሥላሴዎች በየትኛው አምላክ ነው ይህ ኪዳን ቀጥታ ከአብርሃም ጋር የተካሄደው?

መልስ።

ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ያካሄደው እግዚአብሔር ወልድ ነው። እግዚአብሔር ምንም ጊዜ ከሰው ጋር ግንኙነት ማድረግ ሲፈልግ ሁልጊዜ አንድነቱን የሚፈጽመው በሥላሴዎች አንዱ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ክርስቶስ ገና በሥጋ ወደ ምድር ባልመጣበት ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርገው በእርሱ በኩል ነው።

1. ኢየሱስ «ቃል የነበረውና በኋላም ሥጋ ሆኖ በእኛ መኃል ያደረው ነው» (ዮሐ. 1፡1፥ 2፥ 14)። እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ብቻ ስለሚናገር ቃል ተባለ። የእግዚአብሔርን ዕቅድና ፈቃድ ለሰዎች የሚያሳየው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አንተ የልቤን ምሥጢር፥ አሳብ የምትረዳው በምናገረው ነገርና በጽሑፍ በምገልጸው ነገር ነው። በተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዕቅድ እንዲሁም አሳብ መረዳት የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። እግዚአብሔር አብ የሚናገረው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ብቻ ነው። ስለዚህ ክርስቶስ «ቃል» ተባለ። ማቴ. 11፡27 ተመልከት።

2. በብሉይ ኪዳን ዘመን አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን አይተውት ቃሉንም ሰምተዋል። በዮሐንስ 6፡46 ላይ ግን ኢየሱስ «አብን ማንም አላየውም» ብሎአል። በዮሐ. 1፡18 ደግሞ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው የለም። ሆኖም ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎአል (ዘፍ. 32፡24፥ 25፥ 30)። ሙሴም ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ተነጋግሮአል (ዘጸአት 33፡11፤ ዘኁልቁ 14፡14፤ ዘዳግ. 5፡4› 34፥ 10)። ኢሳይያስም ጌታን በመቅደስ ውስጥ ሆኖ አየው (ኢሳ. 6፡1)። ኢየሱስም ይህንኑ ነገር በዮሐ. 12፡41 ላይ አጽንቶታል። በ1ኛ ነገሥት 22፡19 ነቢዩ ጌታን እንዳየ ይናገራል። ያዩትና የሰሙት እግዚአብሔር አብን አይደለም። እነርሱ ያዩት የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር ሠራተኛ የሆነውን የእስራኤልን ንጉሥ ክርስቶስን ነው (ኢሳ. 6፡5)። ኢየሱስ እራሱ መቼም ቢሆን አብን ያየው ማንም የለም ብሎአል።

የጌታ ክብርም እጅግ ታላቅ ስለሆነ ማንም አይቶት በሕይወት አይኖርም። ስለዚህ እርሱ ከሰው ጋር ሲገናኝ ክብሩን ሸሽጎ ነው። ከአሁን ቀደምም ክብሩን ለመሸሸግ ብሎ በደመና ተከልሎ ወርዶአል። ሰው ወደ ፀሐይ በሚመለከትበት

ጊዜ የፀሐይዋ ብርሃን ዓይኖቹን ይጎዱታል። ነገር ግን በጥቁር መስተዋት አድርጎ ፀሐይን ቢመለከት የፀሐይዋን ጠቅላላ አካል መመልከት ይችላል። የፀሐይዋም ብርሃን ስለተከለለ ዓይኖቹ አይጎዱም።

3. እግዚአብሔር ወልድ በሰው አምሳልና መልክ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊትም የእስራኤል ንጉሥ ነበር። ከዚያም በአህያና በአህያይቱ ውርንጫ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ እራሱን በንጉሥ መልክ አቅርቦአል። ማለት ግርማውና ክብሩ በሥጋ በተሸፈነ ጊዜ ማለት ነው (ማቴ. 21)። በሚመጣው በ1000 ዓመት የሰላም ግዛቱም ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል። ደግሞም በዳዊት ዙፋን ይቀመጣል። እርሱም ለዘለዓለም አምላካቸው ነው። እግዚአብሔር አምላካቸውም በንጉሣቸው በክርስቶስ በኩል በሙሴ እጅ መራቸው። ከአብርሃም ጋርም ቃል ኪዳን የገባው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (የእስራኤል ንጉሥ ስለሆነው ስለ ክርስቶስ ለማጥናት የዚህን መጽሐፍ ትምህርት በተከታታይ በመግለጫው ላይ ተመልከት።)

4. እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርገው በልጁ በኩል ብቻ አይደለም። ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ የመፍጠርንም ነገር ሁሉ ሠርቶአል። ዮሐ. 1፡3፤ ዕብ. 1፡2፤ ኤፌ. 3፡9፤ ቆላ. 1፡16 ተመልከት።

85. እግዚአብሔር ከሰው ጋር አስቀድሞ የገባቸውን ቃል ኪዳኖችና የሰጣቸውን ስጦታዎች በቅደም ተከተል ዘርዝር። ዘፍ. 2፡17፤ 3፡15፤ 8፡20-22፤ 12፡1-3።

መልስ።

1. ዘፍ. 2፡17 ከአዳም ጋር የገባው ቃል ኪዳን የታዘዝክ እንደሆን በሕይወት ትኖራለህ፤ ያልታዘዝክ እንደሆነ ግን ትሞታለህ የሚል ነው።

2. ዘፍ. 3፡15 በኃጢአት ከወደቀ በኋላም እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል። «የሴትዋ ዘር» የሆነው ክርስቶስም በሰይጣን ላይ ለመፍረድ መምጣት ነበረበት። ኃጢአታቸውን ተናዘው ለሚያምኑ ሁሉ በክርስቶስ ደም ከበደል ሁሉ መንጻትና መገላገልን አግኝተው ደኅንነትን ማግኘት ይችላሉ። የዚህም ኪዳን ምልክት ደም ነው። በእግዚአብሔር ፊት የአዳምና የሔዋን እራቁትነት በቆዳ እንዲሸፈን የእግዚአብሔር እጅ ደምን አፈሰሰ (ዘፍ. 3፡21)። ይህም የክርስቶስ ሞት ምሳሌ ነው። ተሰፋ ተሰጥቶ በነበረው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ኃጢአታቸው ተሸፈነ።

3. ዘፍ. 8፡20-22 ይህ ቃል ኪዳን ደግሞ ከኖኅ ጋር የተገባ ነው። ኖኅ ወደፊት ሊሆን ያለውን የክርስቶስን ሞት ተመልክቶ በእምነት የደምን መሥዋዕት ስላቀረበ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ዳግመኛ በውኃ ያለማጥፋቱን ቃል ኪዳን ገባለት።

4. ዘፍ. 12፡1-3 አብርሃም አገሩንና ዘመዶቹን ትቶ እግዚአብሔር ወደሚያሳየው ምድር የሄደ እንዴሁ እግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገውና በዘሩም የዓለም አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ቃል ኪዳን ገባለት። ያም ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመጣ በፊቱኑ ታውቆ ነበር። ነገር ግን በማን በኩል እንደሚመጣ አልታወቀም ነበር።

86. በአብርሃም ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ምን አዲስ ነገር ገለጠ?

መልስ።

በዚህ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ክርስቶስ በአብርሃም ዘር በኩል እንደሚመጣ ገለጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስ በአንዱ በአብርሃም ዘር በኩል እንደሚመጣ የታወቀ ሆነ። ይህ ነገር በሌላው ኪዳን ውስጥ በመጀመሪያ አልተገለጠም ነበር።

ምዕራፍ 12፡5-20 ያለውን አንብብ።

87. ሀ. በምዕራፍ 12፡7 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ምን ነበር?

መልስ።

እግዚአብሔር አብርሃምን ታላቅ ሕዝብ ሊያደርገው ተስፋ ከገባለት ይህ ሕዝብ የሚኖርበት ምድር ሊሰጠው ይገባል። በምዕራፍ 12፡7 እንደተጠቀሰው ለአብርሃም የከነዓን ምድር ተስፋ ተሰጠው።

87. ለ. አብርሃም ለእግዚአብሔር ምን መልስ ሰጠው? ምዕ. 12፡8።

መልስ።

አብርሃም ወደ ተራራ ወጥቶ «በዚያ ለጌታ መሠውያን ሠራ።» ይህም አድራጎቱ በዚያ አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች አብርሃም እውነተኛ አምላክን ብቻ እንደሚያገለግል ምስክር ነው። መሠዊያውንም በተራራ ላይ የሠራው ሁሉ እንዲያዩ ነው።

ከዚህም በቀር አብርሃም መሠውያውን ሲሠራ እንደ እግዚአብሔር ተስፋ ሊመጣና ሊሰዋ ባለው በክርስቶስ ማመኑን ለእግዚአብሔር ሲመሰክር ነው። በዚህ እምነት መሠረት ላይ ተመርኩዞ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ገባ። አሁን አብርሃም ተስፋውን አድሶ ሊመጣ ባለው በክርስቶስ አምኜ እቆማለሁ፤ ወደኋላም አልመለስም አለ።

88. አብርሃም ወደ ግብፅ በሄደ ጊዜ ምን ኃጢአት አደረገ?

መልስ።

1. በምድሩ ላይ ረኃብ በሆነ ጊዜ አብርሃም ምን ማድረግ እንደሚገባውና የት መሄድ እንዳለበት እግዚአብሔርን አልጠየቀም። ነገር ግን በገዛ ፈቃዱ ወደ

ግብፅ ሄደ። ግብፅ የዓለም ምሳሌ ናት። አብርሃም ከእግዚአብሔር ርዳታን በመጠየቅ ፋንታ ከዓለም ርዳታን ፈለገ። ይህም ደግሞ ወደ መከራ አመጣው። ዛሬም ብዙ አማኞች መከራ በሚገጥማቸው ጊዜ ርዳታን ከዓለም ይፈልጋሉ። ነገር ግን እግዚአብሔርን ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ምን እንደሚሻላቸው ርዳታን አይጠይቁም። ይህ ደግሞ በኃጢአት ላይ መውደቅ ነው። (ያዕቆብ 4፡13-15፤ 2ኛ ነገሥት 18፡21፤ ኢሳ. 30፡2÷ 3፤ 31፡1)።

2. አብርሃም ሚስቱ ሣራ ቆንጆ ስለሆነች ግብፃውያን ገድለውኝ ይወስዱብኛል ብሎ ፈራ። ስለዚህ ሣራ እህቱ ነኝ እንድትል ነገራት። እርግጥ ሁለቱም አንድ አባት ቢኖራቸውም በእናት አይገናኙም ነበር፤ ነገር ግን አብርሃም ሣራ ሚስቱ እንዳልሆነች ለግብፃውያን ሊያስረዳ ፈለገ፥ እርሷም ኃጢአት በሆነው ነገር ተታለለች (ዘፍ. 20፡12)።

3. እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ አብርሃምን ታላቅ ሕዝብ ባደረገው ነበር። ነገር ግን አብርሃም ግብፃውያንን ፈርቶ ይገሉኛል በማለቱ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ሙሉ እምነት ስለሌለው እንግዲህ አብርሃም ከተገደለ እንዴት እግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብ ሊያደርገው ይችላል?

አብርሃም ቶሎ ብሎ ወደ ጌታ ዘወር አለ። ግብፅንም ለቆ እግዚአብሔርን በመጀመሪያ ጊዜ ወዳናገረበት ሥፍራ ተመለሰ። በዚያም እግዚአብሔርን እንደገና ጠራ። እርሱም እግዚአብሔርን ባለማመን ካሳዘነና ከታለለ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት ሕይወቱን አስተካከለ (ዘፍ. 13፡1-4)።

ምዕራፍ 13፡1-9 አንብብ።

89. አብርሃምና ሎጥ በምድሩ ፊት ጥሩ ምሳሌነት ያለውን ምስክርነት አስቀርተዋልን? 13፡7።

መልስ።

አብርሃምና ሎጥ የእግዚአብሔር ሰዎች ይባሉ ነበር። አብርሃምም በተራራው ላይ መሠውያን በሠራ ጊዜ በምድሩ ሕዝቦች ፊት ስለ እውነተኛው አምላክ የሚቃጠል መሥዋዕት በማቅረብ ምስክርነት ሰጥቶ ነበር። ነገር ግን በአብርሃምና በሎጥ እረኞች መካከል የተደረገው ጠብ ያንን ምስክርነት አጠፋ። ቁጥር 7 የአብርሃምና የሎጥን መንጎች በሚጠብቁት መካከልም ጠብ ሆነ ይላል። «በዚያም ዘመን ከነዓናውያንና ፌርዛውያን በዚያች ምድር ተቀምጠው ነበር።» ይህም ማለት እነዚህ ሰዎች ጠቡን ስለተመለከቱ የእግዚአብሔር ሰዎች ነን በሚሉት ላይ ያስተያየታቸውን ፍርድ ሳይሰጡ አይቀሩም። (1ኛ ተሰ. 5፡22 ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ።)

90. ሀ. ለሎጥ ውድቀት የመጀመሪያ እርምጃ ምን ነበር? ዘፍ. 13፡5-11።

መልስ።

የመጀመሪያውን የሎጥን ውድቀት እርምጃ ሳንዘረዝር በመጀመሪያው ሎጥ በእምነቱ ያለማዳትን እንመልከት። አብርሃም ወደተለያዩ አዳዲስ ስፍራዎች በሄደ ቁጥር በዙሪያው ለሚገኙ ሰዎች በሞላ ይመሰክር ነበር። በተራራም ላይ መሰውያ ሠርቶ የሚቃጠል መሥዋዕት አቅርቦአል። ሎጥ ግን እንዲህ ያለውን ምስክርነት በጭራሽ አቅርቦ አያውቅም። ማንም በክርስቶስ ማመኑን የማይመሰክር አማኝ በጣም ደካማ ስለሆነ በቀላሉ ይወድቃል። በሕይወቱም ፈጽሞ አሸናፊ ክርስቲያንም አይሆንም። በሮሜ 10፡10 ላይ «ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል» የሚል እናነባለን። ይህም ማለት በእምነት ድኖአል ማለት ነው። የመጀመሪያው እርምጃ አሸናፊ ለመሆን ከኃጢአት ኃይል መዳን ነው። «በአፉም መስክሮ ይድናልና!» ይህም ከኃጢአት ኃይል የመዳን ደኅንነት ነው። ኃጢአትን ድል በማድረግ መንገድ ላይ መሄድ እንደጀመርክ በምትመሰክርበት ጊዜ በእምነት ለማደግ ያ መንገድ በእያንዳንዱ ክርስቲያን እርምጃ መወሰድ አለበት።

ወደታች አዘቅዝቆ ለመውረድ የሎጥ የመጀመሪያው ኃጢአት የገንዘብ ፍቅር ነው። አብርሃም ከለምለሙና ብዙ ሣር ከሚገኝበት ውኃ ገብ መሬትና ከደረቁና ትንሽ ሣር ካለበት ከተራራማው ምድር መካከል ምርጫ እንዲያደርግ ሎጥን ሲጠይቀው ሎጥ ብዙ ሣርና ውኃ የሚገኝበት ዝቅተኛ ምድር ለራሱ መረጠ። 1ኛ ጢሞ. 6፡9፥ 10 አንብብ።

90. ለ. ወደ ውድቀት ያደረሰው ሁለተኛው የሎጥ እርምጃ ምን ኖሮአል? ዘፍ. 13፡12፡13።

መልስ።

ሁለተኛው ሎጥን ወደ ውድቀት ያደረሰው እርምጃ ኃጢአትን ያለመፍራቱ ነው። የሰዶም ሰዎች በኃጢአት በጣም የረከሱ ነበሩ። ሎጥም ኃጢአትን ሳይፈራ ወደዚያች ከተማ ድንኳኑን አዘዋወረ። ልጆቹ በከተማው ነዋሪዎች ኃጢአት እንዳይበላሹ እንዳይተባበሩ ሎጥ ድንኳኑን ከከተማው በጣም አርቆ መትከል ነበረበት (መዝ. 1፡1፥2)። በከተማው አቅራቢያ ወተት፥ አይብ፥ ቅቤ፥ ቆዳና የመሳሰሉት ነገሮች ሳይሸጡ አይቀሩም። ኃጢአትን እንዳይፈራ ያደረገው የገንዘብ ፍቅር ነው።

91. እግዚአብሔር ሎጥን ምን ብሎ አስጠነቀቀው? ዘፍ. 14።

መልስ።

በ2ኛ ጴጥ. 2፡8 እንደምንመለከተው ሎጥ ጻድቅ ሰው ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰይጣን ወጥመድ ሊያወጣው ፈለገ። አራቱ የምሥራቅ ነገሥታት ከአምስቱ በሚዳማው የጨው ባሕር አጠገብ ከሚኖሩት ነገሥታት ጋር ጦርነት አደረጉ (ዘፍ. 14፡1፥ 2፥ 8)። የሰዶምና የገሞራ ነገሥታቶች ተሸንፈው በእነዚህ በሁለቱ ከተማዎች የሚገኙት ነገሮች በሞላ በምሥራቆቹ ነገሥታት ተዘርፎ ተወሰደ። እነርሱም ሎጥንና ያለውን ሁሉ አብረው ወሰዱ (ቁጥር 12)።

አብርሃም ይህን እንደሰማ የእርሱ የሆኑትን ከ318 ሰዎች ጋር ሆኖ ተከታተላቸው። እርሱም ነገሥታቶቹን ከመታ በኋላ ሎጥን ነፃ አወጣው። ይህም የሆነው ኃጢአት ባለበት የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ ሎጥን ለማስጠንቀቅ ነው። ሎጥም ማስጠንቀቂያውን ንቆ በኃጢአት ወደታች ለመውረድ በኃጢአቱ ለመቀጠል ወደ ሰዶም ሄደ።

92. ሀ. ወደ ውድቀት ያደረሰው ሦስተኛው የሎጥ እርምጃ ምን ነበር? ዘፍ. 19፡1።

መልስ።

ሎጥን ወደ ውድቀት ያደረሰው ሦስተኛው እርምጃ የምቾትና የመዝናናት ፍቅር ነበር። እርሱም በዚያች ጥፉ በሆነች ከተማ መኖር ጀመረ። እርሱም የዚያች ከተማ ጥፉነት በልጆቹ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት አላስተዋለም። ምናልባትም ሚስቱና ሴቶች ልጆቹ የሰው ልብ የሚሻውን ነገር በሞላ በገንዘባቸው ለመግዛት ስለሚችሉ በዚህ ኑሮው ምቹ ባልሆነ ድንኳን ውስጥ ከመቀመጥ በዚች ከተማ እንዲኖር ደጋግመው ጪቅጭቀውት ይሆናል።

በሦስተኛው ቁልቁል በሚያመራው ውድቀት ውስጥ የራስን ክብር የመሻት ኃጢአት ይታያል። ሎጥ በከተማዋ በራፍ ተቀምጦ ነበር። ይህም ስፍራ የከተማው ሽማግሌዎች የከተማውን ወንጀለኞች ለመፍረድ የሚቀመጡበት ቦታ ነው። ከዚህ ከክፉ ከተማ ሸሽቶ በመውጣት ፋንታ በክፉዎቹ ላይ ለመፍረድ የሚያስችለውን የሽምግልና ክብር ለመሻት ከአገሩ ሽማግሌዎች ጋር ተቀመጠ።

92. ለ. ወደ ውድቀት ያደረሰው አራተኛው የሎጥ እርምጃ ምን ኖሮአል? ዘፍ. 19፡32-36።

መልስ።

ሎጥ ያለውን ክብር ሁሉ ሲጥል በመናዘዝ ፋንታ ኃዘኑንና የልቡን ጭንቀት ለመርሳት ጠጥቶ ሰከረ። ከዚያም እርሱ ሳያውቅ ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ልጆችን ካባታቸው ወለዱ። እነርሱም በኋላ ሕዝብ ሆነው የእግዚአብሔር ጠላቶች የሆኑትን ሞአብና አሞንን ወለዱ።

ጻድቁ ሎጥ የዓለምን ፍላጎትና የገንዘብን ፍቅር ስለተከተለ ሌሎች የሚወድቁበት እንቅፋትና መሰናክል ሆነ (ያዕ. 1፡14፥ 15)። ሎጥ የዓለማዊ ክርስቲያኖች ምሳሌ ሲሆን አብርሃም ደግሞ የመንፈሳዊ ክርስቲያኖች ምሳሌ ነው።

93. የሎጥ ሚስት ለምን ተፈረደባት? በልቧ የተሰወረው ኃጢአት ምን ኖሮአል? ዘፍ. 19፡17-26፤ ሉቃ. 17፡31-33።

መልስ።

የሎጥ ሚስት ልብ በተረገሙት በዓለም ነገሮች ላይ ነበር። ከተማውና በከተማው ውስጥ ያለው ነገር በሙላ ስለተፈረደበት ሎጥና ቤተሰቦቹ ዘወር ብለው እንዳይመለከቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር። አማኝም በኃጢአቱ በተናዘዘና በአመነ ጊዜ ከዓለም ሸሽቶ ወደ ክርስቶስ መሄድ አለበት። ምክንያቱም ዓለም ስለተፈረደባት ነው። ሰውዬውም የሚያፈቅረው ነገር በዓለም ውስጥ ኖሮት ወደ ዓለም ቢመለስ ከዓለም ጋር ይፈረድበታል። እርሱም አፍአዊ አማኝ ብቻ ስለሆነ ነው። አንዳንድ ጊዜ ባለቤት የሆነ ሰው በሚድን ጊዜ ቤተሰቦቹ በሙላ አብረው ሄደው እኛም አምነናል ይላሉ። ነገር ግን አልተናዘዙም። እነርሱም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኳ ቢመጡ ኃጢአታቸውን ሊተዉ አይፈልጉም፤ ስለዚህ በእነዚህ ሰዎች በሎጥ ሚስት ላይ የደረሰው ፍርድ ይመጣባቸዋል።

የሎጥ ሚስት የልብዋ አሳብ በሙላ ወደዚያች ከተማ ኃጢአት ስለሆነ ወደኋላ ተመለከተች። ቤትዋና ንብረትዋ ዕቃዋ በሙላ በዚያ ከተማ ነበር። አንዳንዶቹም ሴቶች ልጆችዋ አግብተው የሚኖሩት በዚያች ከተማ ነበረ። እርሷ ሕይወትዋን ለማዳን ይህንን ሁሉ ቸል አላለችም ነበር።

ፍቅራችን በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ ከሆነ ክርስቶስን መቀበል አንችልም። ስለዚህ በሄድንበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ይከተለናል። ዘመዶቻችን በዓለም ውስጥ ሆነው ከዓለም ለመውጣት እምቢ ቢሉ እንኳ እኛ ብቻችንን ወደ ክርስቶስ መምጣት አለብን (ዘፍ. 19:14፥ 15)።

94. ሎጥ ዓለምንና ገንዘብን ቢወድ እንኳ ምን ትርፍ አገኘ?

መልስ።

ሎጥ ለጥቂት ጊዜ በከተማዋ ውስጥ በድሎት በሀብትና በክብር ተዝናና። እግዚአብሔር ሎጥን ወደ ንስሐ ሊያመጣው ሀብቱንና ድሎቱን ለማራቅ ያለውን ንብረትና ክብት በሙላ ከከተማው ጋር በአንድነት አጠፋ። ከሴት ልጆቹ ጋር በዋሻ በሚኖርበት ጊዜ ክብሩን አስገፍፎ ነበር። በከተማው የሚኖሩትን ሰዎች ያገቡት ልጆቹ ግን ከከተማው ጋር ተፈረደባቸው። ባለቤቱ ሞተች፥ በሁለቱም ሴቶች ልጆቹ ልብ ደግሞ የሰዶም ኃጢአት ነበረ። ይህም የሎጥ ገንዘብን የመውደድና ኃጢአትን ያለመፍራት ፍሬ ነው። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ለዘለዓለም ያለሽልማት ይኖራል። የእርሱ ምስክርነት ቤተሰቦቹን እንኳን ማዳን አልቻለም (2ኛ ጴጥ. 2:6-8)። ዛሬም ከኃጢአት የማይሸሹ አማኞች በእግዚአብሔር ፊት ለዘለዓለም ባዶ እጃቸውን ያለ ሽልማት ሲቀሩ ምናልባትም ቤተሰቦቻቸውም ያልዳኑ ይሆናሉ።

95. ከምዕራፍ 12 እስከ 22 ድረስ ባለው ክፍል ላይ ተመርኩዘህ አብርሃም በእምነቱ እያደገ እንደሄደ በቅደም ተከተል ግለጥ። ገላ. 3:8፤ ዮሐ. 8:56-58፤ ዘፍ. 11:31-12:5 ተመልከት።

መልስ።

1. እግዚአብሔር አብርሃምን ከዑር ወደ ከለዳውያን አገር እንዲሄድ ጠራው (ዘፍ. 12፡1)። ነገር ግን አባቱና ቤተሰቦቹ በሞላ ተከትለውት ወደ ከነዓን ስላመሩ አብርሃም ከነዓን ሳይደርስ በካራን ተቀመጠ (ዘፍ. 11፡31፤ የሐዋ. ሥራ 7፡2-4)። ይህም የሆነበት ምክንያት ለእግዚአብሔር በፍጹም ልብ ባለመታዘዙ ነው።

በኋላም አብርሃም ከካራን ለቆ ወደ ከነዓን ሲሄድ በገዛ ፈቃዱ ሎጥን አስከትሎ ሄደ። እግዚአብሔር ሎጥን ስላልጠራው በዚያ አገር የልብ ኃዘንና የመጥፎ ምስክርነት ምክንያት ሆኖአል። አንድ ጊዜም አብርሃም ከ318 ሰዎች ጋር ብቻ ሆኖ ሎጥን ከአራት ኃይለኛ ነገሥታት እጅ አድኖታል። ይህም የእምነትን ሥራ ያሳያል። አብርሃም በእግዚአብሔር እርዳታ ተማምኖ ነበር (ዘፍ. 14፡14-24)።

2. ዘፍ. 13፡9 እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር በሞላ ለአብርሃም ሊሰጠው ተስፋ ገባለት። አብርሃምም የእግዚአብሔርን ተስፋ በማመኑ ከከነዓን ምድር የትኛውን እንደሚፈልግ ለሎጥ ምርጫ ሰጠው (ዘፍ. 13፡14-17)። በኋላም እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር በሞላ ለዘሮቹ ሰጠ። አብርሃም ሎጥ እንዳደረገው የሥጋን መንገድ አልተከተለም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድና መንገድ ተከተለ። እርሱም ወደ አዳዲስ ቦታ ሁሉ በተዘዋወረ ቁጥር ለእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ባካባቢው ላሉት ሰዎች ለመመስከር መሠውያ ይሠራ ነበር። አብርሃም እንደዚህ ዓለም ሰዎች የመሆን ፍላጎት አልነበረውም (ዘፍ. 12፡7፥ 13፥ 18)።

አብርሃም እግዚአብሔር ቃል ስለገባለት በሁሉ ነገር እንደሚጠነቀቅለት ያምን ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም እኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካደረግን እግዚአብሔር የምንፈልገውን ነገር በሙሉ እንደሚሰጠን በማቴዎስ 7፡31-34 ባለው ክፍል ላይ መክሮናል። ለእግዚአብሔር መኖር የእኛ ፋንታ ነው። እግዚአብሔር ተስፋ ስለገባለን የምንለብሰውንና የምንበላውን ሊሰጠን ደግሞ የእርሱ ፋንታ ነው።

3. ዘፍ. 14፡14-24 አብርሃም በእግዚአብሔር የእርዳታ ተስፋ ስላመነ አራቱን ኃይለኛ የምሥራቅ ነገሥታት አልፈራም። እርሱም በ318 ሰዎች ብቻ ረታቸውና ድል አደረጋቸው።

አብርሃምም ምንም ዓይነት የዓለምን ብልጽግና ሊቀበል አልፈለገም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠውን ብቻ መቀበል ፈለገ። ስለዚህ የሰዶም ንጉሥ ያበረከተለትን ስጦታ አልቀበለም አለ (ዘፍ. 14፡21-24)። ዛሬ ይህን የመሰለውን ብልጽግና አልፈልግም የሚሉ አማኞች ብዙ አይደሉም።

በእግዚአብሔር ርዳታ አብርሃም የዓለምን ብልጽግና እንዳልተቀበለ እግዚአብሔር በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር በዘፍጥረት 15፡1 ላይ

የተጠቀሰውን ቃል ተናገረ። አብርሃም ሆይ፥ አትፍራ 1. እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ። 2. ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው አለው። እግዚአብሔር የሚሰጠን ዋጋ እምነት ነው።

4. በዘፍ. 12፡2 ላይ እግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገው ለአብርሃም ተስፋ ሰጥቶታል። ነገር ግን በዘፍ. 15፡3 እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር የሚያደርገው ተአምራታዊ ሥራ የአብርሃም እምነት በጣም ትንሽ ነበር። አብርሃምም አገልጋዩና ወራሹ እንዲሆን ፈለገ፤ ምክንያቱም አብርሃም በሰብዓዊ ችሎታው ልጅ የማግኘት ኃይል ስለሌለው ነው። ከቁጥር 4-6 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለታል። እርሱም እግዚአብሔር በተአምራት ልጅ እንደሚሰጠው አመነ።

በዘፍ. 15፡8 ላይ አብርሃም ከነዓንን እንደሚወርስ እግዚአብሔር የማረጋገጫ ምልክት እንዲሰጠው ፈለገ። ምልክትን መፈለግ እምነተደካማነትን ያሳያል። ከቁጥር 19-21 ያለውን አንብብ። እግዚአብሔርም አብርሃምን መሥዋዕት እንዲያዘጋጅ ጠየቀው። ይህን እንደአደረገ አብርሃም እግዚአብሔርን ይጠብቅ ጀመር። እግዚአብሔር ግን መልስ ከመስጠት ዘገየ። እግዚአብሔርም በዚህ ዘሮቹ ከነዓንን ሳይወርሱ ብዙ እንደሚቆዩ ለአብርሃም አመለከተው። 400 ዓመት ወሰደባቸው (ቁጥር 13)። እግዚአብሔር ግን ተስፋውን ይፈጽማል። ለእኛም አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ተስፋ ሳይፈጸምልን ይዘገያል።

አብርሃም እየጠበቀ ሳለ ወፎች መሥዋዕቱን ሊበሉ መጡ። አብርሃምም አባረራቸው። እኛም እግዚአብሔርን እየጠበቅን ሳለን የጥርጥር ወፎች ይመጡብናል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እርግጥ ስለሆነ ጥርጥርን በሞላ ማባረር አለብን። የእርሱም የተስፋ ቃል ሳይፈጸምልን አይቀርም።

የምድጃው ጢስ እስራኤል በግብፃውያን እጅ እንደሚሰቃዩ የሚያሳይ ምልክት ነው (ቁጥር 17)። ብርሃኑም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነው። የእግዚአብሔር ልጆች በምድር መከራ ሲቀበሉ የእግዚአብሔር ተስፋ በመካከላቸው ብርሃን ሆኖ ያበራላቸዋል።

5. ሣራ ልጅ ለመውለድ በጣም አርጅታ ነበር። ምዕራፍ 16፡16 በዚያን ጊዜ አብርሃም 86 ዓመቱ እንደነበረ እናነባለን (ዘፍ. 16፡4-6)። በዚህ ሁናቴ ሣራ 76 ዓመት ሆኖአታል ማለት ነው። የ76 ዓመት ሴት ልጅ ለመውለድ አትችልም። እግዚአብሔር ግን ተስፋ የሰጠው ከአብራኩ የወጣ የራሱ ልጅ እንደሚኖረው ነው። አብርሃምም እግዚአብሔር የገባለት ቃል የሚፈጸመው ሌላ ሚስት ካላገባ በቀር በሌላ መንገድ የማይፈጸም መሰለው። አብርሃም እግዚአብሔር ተአምር እንደሚያደርግ እስከ አሁን አላመነም ነበር። ስለዚህ አብርሃም የእግዚአብሔር ፈቃድ መስሎት የእግዚአብሔር ተስፋ እንዲፈጸም አጋርን ሚስት አድርጎ ወሰዳትና ወንድ ልጅ ወለደችለት። አብርሃም ለራሱ ቅሬታ እግዚአብሔርን ትንሽ ለመርዳት ሞከረ። አማኝ እምነት በጎደለው ጊዜ እራሱን ለማጽናናት እግዚአብሔርን መርዳት የሚገባው ይመስለዋል። ከአጋር

የተወለደው እስማኤል እስከሞተበት ቀን ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት የእስራኤላውያን ጠላት ነበር። የእስማኤል ዘር የሆኑት ዓረቦችም ዛሬ የምድራዊዎቹ የአብርሃም ዘሮች ዋና ጠላቶች ናቸው።

6. ዘፍ. 17፡1-19፤ 18፡18፥ 19 አንብብ። እግዚአብሔር አብርሃምን ከእንግዲህ ወዲያ ስሙ አብርሃም እንጂ አብራም ተብሎ አለመጠራቱን ነገረው። አብራም ማለት ትልቁ አባት ማለት ሲሆን አብርሃም ማለት ደግሞ የብዙ ሕዝብ አባት ማለት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አብርሃምን ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁ ስላለው ነው (17፡5)።

በምዕራፍ 17፡15 ደግሞ እግዚአብሔር ሦራ ሣራ ተብላ መጠራት አለባት አለ። ሣራ ማለትም ልዕልት ማለት ነው። እግዚአብሔር ቃል የገባው ከሣራ በሚወለደው ልጅ በኩል ነው። ነገር ግን አብርሃም እስከ አሁን በዚህ በእግዚአብሔር ተአምራታዊ ነገር ለማመን እምነቱ አልጠነከረም። እርሱም እንደ እኔ ያለው የመቶ ዓመት ሰው ልጅ ሊወለድለት ይቻላልን? አለ። ዘጠና ዓመት የሆናት ሣራስ ልጅ አርግዛ መውለድ ይቻላታልን? (ቁጥር 17)። አሁንም በቁጥር 18 ላይ አብርሃም እስማኤል በእግዚአብሔር የተመረጠው ልጁ እንደሆነ አድርጎ ተስፋ ያደርግ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሣራ ልጅ ትወልዳለች ብሎአል። ቁጥር 19 «ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘለዓለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ።» በምዕራፍ 18፡17-19 ያለውን ክፍል አንብብ። በእግዚአብሔር ፊት አብርሃም ታማኝና አማኛ ሰው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ከእርሱ ምንም ነገር አልሰወረም።

7. ምዕራፍ 20 (17፡16፤ 19፥ 20፡2፥ 11) አንብብ። አብርሃም ወደ ጌራራ በሄደ ጊዜ አሁንም ሰዎች በሚስቱ ምክንያት ይገሉኛል ብሎ ፈራ። ስለዚህ እንደ ገና አሁንም «እህቴ ናት አለ።» በምዕራፍ 17፡16፥ 19 አብርሃም ሚስቱ ሣራ ልጅ እንደምትወልድለት የሚናገር ተስፋ አለለት። በዚህ ጊዜ ግን እምነቱ በጣም ጥቂት ስለሆነ እግዚአብሔር ይገለኝ ይሆናል ብሎ ፈራ። እርሱም የሞተ እንደሆን ከሣራ የሚወለድለትን ልጅ የማያገኝ ሊሆን ነው። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አላመነም። ሰው እምነቱ በደከመ ጊዜ ፈሪ ይሆናል። የጌራራ ንጉሥ የነበረው አቤሜሌክ ሣራ ውብ ስለነበረች ሚስቱ እንድትሆን ፈለገ። ሣራና አብርሃም በዕድሜአቸው አርጅተው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በተአምር የልጅነት መልክ ስለሰጣቸው ሣራ በዘጠና ዓመትዋ ወጣት ትመስል ነበር። ሣራ ከሞተች በኋላም አብርሃም ከሚስቱ ከኬቱራ ልጆችን ወለደ። በምዕራፍ 17፡17 እንደተገለጠው በዚህ ጊዜ አብርሃም ልጆችን ለመውለድ በጣም አርጅቶ ነበር።

8. ዘፍ. 22፡1-12፤ ዕብ. 11፡17-19። ብዙ ዓመታቶችም አለፉ፥ አብርሃምም አረጀ። ከዚያም እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት ፈተነ። እግዚአብሔር አብርሃምን በልጁ በይስሐቅ በኩል ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገውና ቃል ኪዳንም ከይስሐቅ ጋር እንደሚያቋቁም ተስፋ ገብቶለት ነበር። ሆኖም ልጁን ይስሐቅን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብለት አዘዘ። በዚህን ጊዜ ግን አብርሃም እግዚአብሔር በይስሐቅ በኩል ሊፈጽመው

ቃል ኪዳን የገባውን ቃል እንደሚፈጽም አመነ። ስለዚህ አብርሃም እግዚአብሔር ይስሐቅን ከሞት እንኳ ሊያድነው እንደሚችል አምኖ መሥዋዕት ሊያደርገው ይዞት ሄደ። እግዚአብሔር ይስሐቅን ታላቅ ሕዝብ ሊያደርገው ከፈለገና እንዲሁም ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ ከፈለገ ይስሐቅ በሕይወት መኖር አለበት። ስለዚህ የእግዚአብሔር ተስፋ እንዳይቀር ከሞት መነሳት አለበት። ይህ እውነተኛ እምነት ነው። ዕብ. 11፡17፥ 19 አንብብ። ይህም በደንብ ያብራራል።

ይስሐቅ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕት ባቀረበው ጊዜ ወጣት እንጂ ልጅ አልነበረም። ስለዚህ ደኅና ጎበዝ ስለነበረ መሥዋዕት ከመሆን ሊከላከልና እምቢ ሊል ይችል ነበር። ይስሐቅ ይህ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ስላወቀ ለሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። ኢየሱስ ክርስቶስም ለአባቱ ፈቃድ ለሞት እንኳ የታዘዘ ሆኖአል (ፊልጵ. 2፡5-8)።

አብርሃም በልቡ ይስሐቅን ገና ድሮ መሥዋዕት አድርጎት ነበር። ስለዚህ እንደ አብ ይመስላል። ሮሜ 8፡32፤ ዮሐ. 3፡16፤ በዘፍ. 22፡13 የተጠቀሰው በግ የምትክነት ምሳሌ ነው። በጉ በይስሐቅ ፋንታ መሥዋዕት ሆነ። ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ምትክ የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ ተሰውቶአል (ዕብ. 10፡5-10)። አብርሃም በእምነቱ እያደገ በሄደ ጊዜ በጣም ይወዳቸው የነበሩትን አራት ነገሮች መተው ነበረበት።

1. ሕዝቡንና አገሩን ትቶ መሄድ ነበረበት (ዘፍ. 12፡1፤ ማቴ. 10፡34-39፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)።

2. አብርሃም በተፈጥሮ በጣም ያቀርበው ከነበረውና ለውርስ ካበቃው አማኝ ዘመዱ መለየት ነበረበት (2ኛ ጴጥ. 2፡7፥ 8፤ ዘፍ. 13፡1-18)። «ለውርደቱ ምክንያት ከሆነው» አማኝ መሳይ ሰው ፈጽሞ መለየቱ በዘፍ. 15፡1-3 እንደተገለጠው አብርሃም ከሎጥ ይልቅ ባርያው እንዲወርሰው ፍላጎት እንዲያድርበት አድርጎታል (2ኛ ጢሞ. 2፡20-21)።

3. ለልጁ ለእስማኤል የነበረውን ዕቅድ መተው ነበረበት (ዘፍ. 17፡17፥ 18)።

4. ይስሐቅንም አሳልፎ መስጠት ነበረበት፥ «የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን» (ዘፍ. 22፡1-19፤ ዕብ. 11፡17፥ 18፤ 11፡8-11)።

96. ከዘፍ. 17 ጋር አንድነት ያለውን የግዝረትን ትርጉም ከሮሜ 4፡1-12 እና ከሮሜ 2፡28፥ 29 ጠቅሰህ አስረዳ።

መልስ።

አብርሃም ሁለት ዓይነት ዘር ነበረው።

1. የተፈጥሮ ዘሮች እስራኤላውያን ናቸው (17፡1-8)። ለእነርሱም እግዚአብሔር እንዲኖሩበት ምድረ ከነዓንን ሰጥቶአቸዋል። ዘፍ. 13፡14-17 ተመልከት። እነርሱንም እንደ ምድር አሸዋ አበዛቸዋለሁ አለ። እግዚአብሔር ከእነርሱም ጋር ክርስቶስ በእነርሱ ዘር በኩል እንደሚመጣና የዓለምም አሕዛብ ሁሉ በእርሱ እንደሚባረኩ ቃል ኪዳን ገባ (ሮሜ 3፡1-3)።

እነርሱም ለዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር የደኅንነት ምስክሮች እንዲሆኑ ቅዱሳን መሆን ስላለባቸው የካህን ወገን ተባሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር ጣዖትን ከሚያመልኩት ከቀሩት አሕዛቦች ሁሉ እንዲለዩ ፈለገ። እግዚአብሔርም ከሌሎች የመለያቸውን ምልክት ሰጣቸው። ማለት እግዚአብሔር በተለይ ከእስራኤል ወገን ጋር እንደሆነ የሚያሳይ ምልክት ነው። ያም ኪዳን በእግዚአብሔርና በአብርሃም የሥጋ ወገኖቹ ከሆኑት ጋር ብቻ ነበር። እርሱ የወንዶች ልጆቹና ወገኖቹ ግዝረት ነው (ዘፍ.17፡10-12)። «የቁልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ፤ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል።» (ዘፍ. 17፡10-12)። እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘሮች ምድራዊና ሥጋዊ ወገኖቹ እንዲሆኑ መረጣቸው። እነርሱም የሥጋ ምድራዊ ወገኖቹ እንደመሆናቸው ሁሉ ሥጋዊና ምድራዊ ኪዳን ከእነርሱ ጋር አድርጎ ነበር። ያውም ወንዶቻቸውን ሁሉ እንዲገርዙ የሚል ነበር።

እግዚአብሔር የሥጋን ግዝረት ምልክት እንዲሆን የመረጠበት ምክንያት እስራኤላውያን ጣዖት ከሚያመልኩት ሕዝቦች ጋር በጋብቻ ተጣምረው በጣዖቶቻቸው አምልኮ እንዳይረከሱ ነው። እግዚአብሔር ለሥጋዊና ምድራዊ ሕዝቦቹ የሥጋዊን የግዝረት ምልክት ሰጣቸው። ምክንያቱም ከአረመኔውና ከጣዖት አምላኪው ሕዝብ ከሥጋዊ ትብብርና አንድነት እንዲለዩ ነው።

2. አብርሃም እንደ እራሱ በእምነት የጸኑ መንፈሳዊ ዘሮች ደግሞ አሉት። እነርሱም ደግሞ እንደ ሰማይ ከዋክብት ሊበዙ ይገባል (ዘፍ. 15፡5)። ከእነዚህም ጋር እግዚአብሔር ቃል ኪዳን አለው፤ ያም ደግሞ የልብ ግዝረት ምልክት ነው። ይህም ግዝረት ከልብ ውስጥ ኃጢአትና ከዓለም ርኩሰት ሁሉ የሚለይ ነው። እነዚህም መንፈሳውያን የእግዚአብሔር ዘሮች ከዓለም ሕዝብ ሁሉ ማለት ከነገድና ከቋንቋ ሁሉ ናቸው። እነዚህም የዘለዓለም ሕይወትን የሚያገኙት ወገኖቹ ብቻ ናቸው (ሮሜ 4፡11፥ 12)።

እነዚህ የእግዚአብሔር ሥጋዊ ወገኖች የሆኑት እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር መንፈስ ተወልደው መንፈሳዊ ዘሮቹ ባይሆኑ ምንም እንኳ ሥጋዊ ግዝረት ቢኖራቸው እንደማንኛውም ከመንፈስ ዘር እንዳልሆነ ሰው ለዘለዓለም ይጠፋሉ። ስለዚህ ከእግዚአብሔር የዘለዓለም ሕይወትን ደግሞ እንዲቀበሉ ስለፈለገ እስራኤላውያን ሥጋዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ዘሮቹም እንዲሆኑ ይወዳል። የልብም ግዝረት እንደሚያስፈልጋቸው በነቢያትም ሆነ በሕግ ተነግሮላቸዋል (ዘዳ. 20፡6፤10፡16፤ ኤር. 4፡4፤ 32፡39፤ ሕዝ. 11፡19፤ 36፡26፤)። ስለዚህ የሥጋ ግዝረት በእግዚአብሔርና በምድራዊ

የሥጋ ወገኖቹ መካከል ብቻ የተደረገ የኪዳን ምልክት ነው። ይህንንም እነርሱ የዳኑም ቢሆኑ ያልዳኑ ያደርጉታል። ሥርዓቱም የተሰጣቸው ጣዖትን ከሚያመልኩ አሕዛብ ጋር በጋብቻ እንዳይጣመሩና የጣዖትንም አምልኮ ከመካከላቸው ማራቅ ያለባቸውን ኪዳን እንዲያስታውሳቸው ነው። ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ (ሮሜ 4፡11)። አብርሃም እግዚአብሔርን ስለአመነ የእግዚአብሔር ወገኖች አባት እንዲሆን መረጠው ይህም ደግሞ አብርሃም በእግዚአብሔር የተመረጡት ምልክት ነው። እርሱም ታላቅ ሕዝብ ለመሆን የቻለው ከእምነቱ የተነሳ ነው። የአብርሃም ልጆችም ገና ሕፃን ሳሉ ከፉና በጎ ሳይለዩ ይገረዙ ነበር። ይህም የሥጋ ግዝረት ለዳኑትም ሆነ ላልዳኑት ምድራዊ ሕዝቦቹ ለእስራኤላውያን ለምልክት ያህል ብቻ የተሰጣቸው ነው።

የልብ ግዝረት ምልክት ግን የተሰጠው በመንፈስ ዳግመኛ ለተወለዱት ለእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ነው (ቆላ. 2፡11፤ ፊልጵ. 3፡3፤ ሮሜ 2፡28፥ 29)።

አብርሃም በሥጋ ሳይገረዝ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ስላመነ ጻድቅ በመሆኑ ዳነ (ሮሜ 4፡3፥ 10፥ 11፥ 12)። ግዝረት ከደኅንነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ስለዚህ አይሁዶች ስለግዝረት ለአሕዛብ ሲያስተምሩ ጳውሎስ አሕዛብ በእምነት እንጂ በሃይማኖት ሥራ ደኅንነት እንደሌለ አውቆ ከአሕዛብ ያመኑት እንዳይገረዙ ከለከለ። የሐዋ. ሥራ 15፡5-19 አንብብ። ቁጥር 5፡10፥ 19፥ 20፥ 24፥ 28፤ የሐዋ. ሥራ 21፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡18፤ ገላ. 5፡2፥ 6፤ 6፡15።

የእግዚአብሔር የዘለዓለም ልጆች ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ የልብ ግዝረት ያላቸው ብቻ ናቸው (ሮሜ 2፡28፥ 29)። እነርሱም የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆቹ ናቸው።

<u>ዋና ዋና ነገሮች</u>።

ሀ. እግዚአብሔር አብርሃምን ስለ እምነቱ ምድራዊ ሕዝቡ እንዲሆን መረጠው።

ለ. እግዚአብሔር የግዝረትን ምልክት ለአብርሃምና ለቤተሰቡ እንዲሁም ለምድራዊ ዘሮቹ ሁሉ ሥጋዊ ምልክት አድርጎ ሰጣቸው። ምክንያቱም እነዚህ ሕዝቦቹ በአሕዛብ ኃጢአት እንዳይጠላለፉና እንዳይረከሱ ነው።

ሐ. ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ከአሕዛብ ወገን የዳኑት አማኞች እንዳይገረዙ ወሰኑ። የሐዋ. ሥራ 15፡5-19፤ (ቁጥር 5፡10፥ 19፥ 20፥ 24፥ 28) የሐዋ. ሥራ 21፡21፤ ገላ. 2፡3፤ 5፡2፥ 6፤ 6፡15፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡18።

መ. የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆች ከዓለማዊነትና ከዓለም ኃጢአት የሚለይ የልብ ግዝረት አለባቸው (ሮሜ 2፡28፥ 29፤ ፊልጵ. 3፡3፤ ቆላ. 2፡11፤ ዘዳ. 30፡6፤ 10፡16፤ ኤር. 4፡4)።

ሠ. እስራኤላውያንም ቢሆኑ ለመዳን ከፈለጉ እነርሱም የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆች መሆን አለባቸው። በሥጋ እንደተገረዙትም አሕዛብ የልብ ግዝረት ሊኖራቸው ይገባል። (ዘዳ. 10፡16፤ 30፡6፤ ኤር. 4፡4)።

ረ. ዛሬም ቢሆን አማኞች ለሃይማኖት ሥርዓት ሲሉ የተገረዙ እንደሆነ እንደ ጳውሎስ ዘመን በእነርሱም እንደ ኃጢአት ይቆጠርባቸዋል። ከዚህም በቀር የዓለማውያን ወግ አምሮአቸው ቅንጦሽ ስለአስፈኛቸው ቢገረዙም እንደ ኃጢአት ይቆጠርባቸው ነበር (ዕብ. 13፡12-14)።

ሴቶችን መግረዝ ግን ሁልጊዜ ኃጢአት ነው። ሴትንም ስለመግረዝ የሚናገር ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ የለም። ይህ ቀድሞ በሰይጣን የተጀመረ ሥራ ነው። ሴትን የሚገርዙ ሰይጣንን የሚያመልኩ ብቻ ናቸው። አማኝ የሆነ ሰው የሰይጣንን ወግና ልማድ በሞላ ካልተወ በቀር የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ዋጋ አይቀበልም።

97. ሀ. መንፈሳዊውንና ለ. ምሳሌያዊውን የይስሐቅን መሥዋዕትነት ግለጽ። ዕብ. 11፡17-19 ተመልከት።

መልስ።

ሀ. መንፈሳዊ ዓይነት፡-

አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል አመነ። እግዚአብሔርም ቃል የገባው በይስሐቅ በኩል ታላቅ ሕዝብ እንዲያደርገው ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ይስሐቅ አንድ ልጅ እንኳን ሳይወልድ አብርሃምን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ ሰዋልኝ ብሎ አዘዘው። የእግዚአብሔር ተስፋ የማይዛባና እውነተኛ ስለሆነ ቢታረድ እንኳ ይስሐቅን ያስነሳው ነበር። ይህም እውነተኛው እምነት ነው። እግዚአብሔር የሚናገርህ ነገር ምንም ያህል ከባድና አስቸጋሪ መስሎ ቢታይህ እንኳ በእምነት ታዘዘው።

ለ. ምሳሌያዊው ዓይነት፡-

1. የሞሪያም ተራራ (ዘፍ. 22፡2) የጎልጎታ ተራራ እንደሆነ ታምኖአል። (ቀራንዮ) ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ መሥዋዕት የሆነበት ቦታ በአብርሃም ዘመን የኢየሩሳሌም ከተማ ገና አልተቋቋመም ነበር። መልከጼዴቅ የሳሌም ንጉሥ በሚኖርበት ቦታ በኋለኛው ዘመን የኢየሩሳሌም ከተማ እንደተሠራበት ይታመናል።

2. አብርሃም ለገዛ ልጁ ሳይራራለት ለሁላችን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር አብ ይመሰላል (ሮሜ 8፡32፤ ዮሐንስ 3፡16)።

3. ይስሐቅ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። አብርሃም መሥዋዕት ባደረገው ጊዜ ሕፃን ልጅ ሳይሆን ጎረምሳ ነበር። ስለዚህ አባቱን ሊከላከል ሲችል በፈቃዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም አባቱ ሲያስረው ታዘዘ። ኢየሱስ ክርስቶስም ቢሆን ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ (ፊልጵ. 2፡5-8) ይስሐቅ እግዚአብሔር ስለ እርሱ የገባውን ተስፋ ያውቅ ነበር። ይህንንም ከአብርሃም እንደሰማ አይጠረጠርም። እርሱም ደግሞ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ጠብቆ ከሞት እንኳ እንደሚያስነሳው ያውቅ ነበር።

4. በጉ (ዘፍ. 22፡13) የምትክነት ምሳሌ ነው። በይስሐቅ ምትክ በጉ ታረደ። ስለ እኛም ምትክ ክርስቶስ ሞተ (ዕብ. 10፡5-10)።

5. በአብርሃም ልብ ይስሐቅ ገና ድሮ ሞቶ ነበር። ምክንያቱም አብርሃም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ወዲያውኑ በሠዋው ነበር። ስለዚህ እንደ አብርሃም አሳብ ይስሐቅ ከሞት ተነስቶ ከእግዚአብሔር እጅ ዳግመኛ ተቀብሎ በወሰደው ነበር (ዕብ. 11፡19)። እግዚአብሔርም ክርስቶስን የወሰደው ከሞት ከተነሳ በኋላ ነው። ከሞተም በኋላ ሕያው ሆኖ ተነስቶ ከአብ ጋር ለዘለዓለም ይኖራል።

### ምዕራፍ 23 እና 24ን አንብብ።

98. በምዕራፍ 24 ላይ አብርሃም ቤተሰቦቹን በመግረዝ የግዝረትን ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር እንደጠበቀ አመልክት። (ቁጥር 1-4 ተመልከት።)

መልስ።

አብርሃም ልጁ ይስሐቅ በኃጢአት ከሚኖሩት ከነዓናውያን ጋር በኃጢአት እንዳይተባበር ሚስት ከእነርሱ መኃል ወስዶ እንዲያገባ አልፈቀደለትም። ስለዚህ ለይስሐቅ ሚስት ለማግኘት እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ከወገኖቹ መካከል ሚስት እንድትመጣለት መልእክተኛ ወደ ካራን ተላከ። እርሱም ለመለየት የተቀበለው የግዝረት ምልክት ስላለው ቃል ኪዳኑን ጠበቀ (ዘፍ. 24፡3፤ 28፡1፤ ዘዳ. 7፡1-4፤ ኢያሱ 23፡12፥ 13፤ ዕዝራ 9፡12፤ ነህምያ 13፡25፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)።

### ምዕራፍ 25 እና 26ን አንብብ።

99. በምዕራፍ 25-37፡1 ያሉት ቁጥሮች ሁለት ታላላቅ ክፍሎች አሉዋቸው። እነዚህም በምዕራፍ 36 የዔሳው ታሪክ ሲሆን በምዕ. 25፡19-36፡29 ደግሞ የያዕቆብ ታሪክ ነው። ለምንድ ነው ከዔሳው ታሪክ ይልቅ የያዕቆብ ታሪክ የላቀው?

መልስ።

እግዚአብሔር ያዕቆብን የመረጠበት ምክንያት ያዕቆብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሚሆንና ከዘሩም ክርስቶስና ደኅንነት ለጠፉት ሕዝቦቹ ስለሚመጣ ነው። እግዚአብሔር ያዕቆብ ቀስ በቀስ እንዴት የእምነት ሰው እንደሆነና በኋላም

በመጨረሻ የእስራኤል አባት የመባልን ችሎታ እንዳገኘ ያመለክታል። ያዕቆብ እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ለዓለም ደኅንነትን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ የመረጠው ታላቅ ሰው ነው። ዔሳው ግን እግዚአብሔር ያልተጠቀመበት የዚህ ዓለም ሰው ብቻ ነበር። ስለዚህ ነው እንግዲህ ስለ እርሱ ጥቂት ብቻ የተጻፈው።

100. በምን መሠረት ላይ ነው የአብርሃም ቃል ኪዳን ወደ ይስሐቅ ተዘዋውሮ የጸናው? ዘፍ. 18፡19፤ 26፡5፥ 24።

መልስ።

እግዚአብሔር የአብርሃምን ኪዳን በይስሐቅ ላይ ያጸናው በአብርሃም እምነት ስለተራመደ ነው። አብርሃም የእግዚአብሔር ሰው እንደመሆኑ መጠን ልጁን ይስሐቅን በእምነት ጎዳና ማሳደጉ ስለማይቀር ኪዳኑ ያለምንም ነቀፋ ከአብርሃም ወደ ይስሐቅ ሊተላለፍ ችሎአል። «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም» (ምሳሌ 22፡6)።

እንደዚሁም ልጆች ያሉዋቸው ቤተሰቦች ደግሞ ልጆቻቸውን በጌታ ፍርሃት ቢያሳድጉአቸው እነርሱንም ጌታ ሊባርካቸው ይችላል።

101. ይስሐቅ እራሱ የእምነት ሰው እንደሆነ አመልክት። ምዕ. 28፡1-4።

መልስ።

ይስሐቅም እንደ አባቱ እንደ አብርሃም የእግዚአብሔርን ኪዳን ሊጠብቅና ከዓለም ተለይቶ ንጹሕ ሊሆን ይፈልግ ነበር። ስለዚህ ይስሐቅ ያዕቆብ ከነዓናዊ ሴት አግብቶ ምናልባት ኃጢአትን ወደ ቤተሰቡ እንዳያዛምትና ቤተሰቡን በዓለም ኃጢአት እንዳይበክል ልጁ ከነዓናዊት ሴት እንዲያገባ አልፈለገም፤ ከዚህም በቀር ይስሐቅ የመለየት ምልክት የሆነውን የግዝረትን ቃል ኪዳን እንዲጠብቅ ይፈለግበት ነበር። ስለዚህ እውነተኛውን አምላክ ከሚያመልኩት ወገኖቹ ማለት ከሃራን ሰዎች ሚስት እንዲያገባ ያዕቆብን ላከው። ይህም ደግሞ ይስሐቅ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበረና የልጁን እግዚአብሔርን አለመታዘዝ የማይፈቅድም እንደነበረ ያሳያል። በ2ኛ ቆሮ. 6፡14-18 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ትእዛዝ ተመልከት።

ዔሳው ሁለት ኬጢያዊ ሴቶች ባገባ ጊዜ ይስሐቅ በነገሩ አዝኖ ነበር (ዘፍ. 26፡34፥ 35)። በዘፍ. 26፡17-25 ደግሞ ይስሐቅ የሰላም ሰው እንደነበረ እናያለን።

102. ሀ. ያዕቆብና ዔሳው ገና ሳይወለዱ ስለ እነርሱ ምን ትንቢት ተተንብዮ ነበር? ዘፍ. 25፡23።

መልስ።

ያዕቆብና ዔሳው ገና ሳይወለዱ የተነገረላቸው ትንቢት ታናሹ ከታላቁ ስለሚያይል ታላቁ ለታናሹ እንደሚገዛ ነው።

102. ለ. ይህ ትንቢት ከአብርሃም ጋር ለተገባው ኪዳን ምን ድጋፍ ይሰጣል?

መልስ።

ይህ ትንቢት እግዚአብሔር የአብርሃምን ኪዳን ሊያወርሰውና በዘሩም የዓለምን አሕዛብ በሞላ ሊባርክ የይስሐቅን ታናሹን ልጁን ያዕቆብን እንደመረጠ ያሳያል።

102. ሐ. የያዕቆብ ቤተሰቦች ይህንን ስለ ያዕቆብ የተነገረውን ትንቢት ፈጽሞ እንዳልረሱ የሚያስረዳ ቢያንስ ቢያንስ ምን አንድ ማረጋገጫ አለህ?

መልስ።

የያዕቆብ እናት ርብቃ በዘፍጥረት 25፡23 ላይ ስለ ልጅዋ የተነገረውን ትንቢት ፈጽማ አልረሳችም ነበር። ይስሐቅ ዋናውን ምርቃት ለዔሳው ሊሰጥ ባለ ጊዜ ርብቃ ዋናው ምርቃት ለያዕቆብ እንዲሰጥ ያዕቆብን በማጭበርበሩ ሥራ ረዳችው። እግዚአብሔርን ይህን ምርቃት ለያዕቆብ እንደሰጠው ታውቅ ነበር። እርሷም በእምነትዋ ስለደከመች እግዚአብሔርን ለመርዳት ስለቃጣች በቤተሰቡ ላይ በሙሉ ታላቅ ኃዘንን አስከተለች። ዘፍ. 27 አንብብ።

103. ያዕቆብ የተስፋውን ቃል ኪዳን እንደገዛ ያስመሰለበትና ወደ ካራን ያሸሸው የቀድሞ ጠባዩ እንደሆነ ምን ማረጋገጫ ይገኛል? ምዕ. 25፡28-34፤ ምዕ. 27።

መልስ።

1. ያዕቆብ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እንዲፈጸምለት ፈለገ። በውልደት ዔሳው ታላቅ ስለሆነ እንደ ደንቡ በረከቱን መቀበል የሚገባው እርሱ ነበር። ያዕቆብ አሁንም በእምነቱ ደካማ ስለሆነ በረከቱን በአታላይነት መንገድ ሊቀበል ፈለገ። ያዕቆብ ለበረከቱ በጣም ስለጓጓ ለብኩርናው ግድ ካልነበረው ከዔሳው ገዛው (25፡28-34)።

2. ዔሳው በረከትን ሊቀበል በቃጣ ጊዜ ያዕቆብ ለበረከቱ በጣም ጓጉቶ ስለነበር ፈጥኖ በማወናበድ ተቀበለ (ምዕራፍ 27)።

3. ያዕቆብ ከአብርሃም ቃል ኪዳን እራሱን ለማግለል ስላልፈለገ ከከነዓን ሴቶች አንድዋን እንኳን አላገባም። እግዚአብሔር ሊሰጠው ተስፋ የገባለትን ነገር ለመቀበል መጓጓቱ መልካም ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ሊሰጠው በሚፈልግበት መንገድ እንደሚሰጠው ቢተማመነው መልካም ነበር። ያዕቆብ በሥጋዊ መንገድ ስለተጠቀመ ከዚህ የተነሳ ብዙ ኃዘን ደረሰበት።

104. በምን ዓይነት ሁናቴ ነው ቃል ኪዳኑ የጸናለት? ዘፍ. 28፡10-22።

መልስ።

ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ሸሽቶ ወደ ካራን በኮበለለ ጊዜ አንድ ቀን ምሽት በውጭ ተኝቶ ነበር። በሕልሙም አንድ ከምድር ተነስቶ ጫፉ ሰማይ የሚደርስ መሰላል አየ። እግዚአብሔርም በመሰላሉ ጫፍ ላይ ሆኖ ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን አጸናለት። መላእክትም ከእግዚአብሔር ዘንድ በመሰላሉ ላይ ወደ ላይና ወደታች ይመላለሱ ነበር። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔር መላእክት እንደሚጠብቁትና እንደሚያገለግሉት ማረጋገጫ ነው። ያዕቆብም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ በታውን «ቤቴል» ብሎ ጠራው። ትርጓሜውም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው። ከዚያም በኋላ ያዕቆብ እግዚአብሔር ከሰጠው አንድ አሥረኛውን መልሶ እንደሚሰጠው ለእግዚአብሔር ተስፋ ገባ።

105. ሀ. ቃል ኪዳኑ በጸናለት ጊዜ ያዕቆብ የስንት ዓመት ሰው ነበር? መልሱን ከሚከተሉት ጥቅሶች ለማግኘት ሞክር። ዘፍ. 41፡46፥ 47፥ 53፤ 45፡6፤ 47፡9፤ 31፡41፤ 30፡25-28።

መልስ።

ያዕቆብ ወደ ካራን በሸሸ ጊዜና ቃል ኪዳኑ በጸናለት ጊዜ የ77 ዓመት ሰው ነበር። የዕድሜው መጠን በሚቀጥለው መንገድ ሊታወቅ ይችላል። ዮሴፍ በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ የ30 ዓመት ሰው ነበር። (ዘፍ. 41፡46)። ያዕቆብ ወደ ግብጽ በመጣ ጊዜ 39 ዓመት ሆኖት ነበር። ሰባት የጥጋብ ዓመቶች ነበሩ (ዘፍ. 41፡47፥ 53)። ያዕቆብ ወደ ግብጽ ከመምጣቱ በፊት ሁለት የረኃብ ዘመን ነበር (ዘፍ. 45፡6)። በጠቅላላው ዮሴፍ በፈርዖን ፊት እስከቆመ ቀን ድረስ ወደ ግብፅ ከመጣ 9 ዓመት ሆነው ማለት ነው። ስለዚህ ያዕቆብ ወደ ግብፅ በመጣ ጊዜ ዮሴፍ የ39 ዓመት ሰው ነበር። ያዕቆብ ግን በዚያን ጊዜ 130 ዓመት ሆኖታል (ዘፍ. 47፡9)። ዮሴፍ በተወለደ ጊዜ ያዕቆብ ላባንን 14 ዓመት አገልግሎት ነበር (ዘፍ. 30፡25-28)። መንጋ ለማገድ ደግሞ ሌላ 6 ዓመት በተጨማሪ አገለገለው፤ በጠቅላላው ያዕቆብ ላባን ለ20 ዓመት ያህል አገልግሎታል (ዘፍ. 31፡41)።

ዮሴፍ በተወለደ ጊዜ የያዕቆብ ዕድሜ ምን ያህል እንደነበረ ለማወቅ ከፈለግን ከያዕቆብ ዕድሜ የዮሴፍን ዕድሜ መቀነስ ይኖርብናል። ከ130 ላይ 39 ሲቀነስ 91 ይቀራል። ስለዚህ ዮሴፍ በተወለደ ጊዜ ያዕቆብ 91 ዓመቱ ነበር ማለት ነው። ዮሴፍ ሳይወለድ ከ14 ዓመት በፊት ያዕቆብ ወደ ካራን በሚጓዝበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳንን ተቀበለ (ዘፍ. 30፡25-28)። ይህም 14 ዓመት፥ ከ91 ዓመት ላይ መቀነስ አለበት። በዚህን ጊዜም 77 ዓመት ይቀራል። ያዕቆብ ከዔሳው ሸሽቶ በነበረ ጊዜና እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ባጸናለት ጊዜ 77 ዓመቱ ነበር ማለት ነው።

105. ለ. ያዕቆብ ቀደም ብሎ ያላገባበት ምክንያት ምንድር ነው?

መልስ።

ያዕቆብ ለሕይወቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለፈለገ እግዚአብሔርን ታዘዘ። በስፍራው የሚገኙት የከነዓን ሴቶች ብቻ ስለሆኑ ያዕቆብም ከእነርሱም አንዷን ቢያገባ እግዚአብሔር ደስ እንደማይለው ስላወቀ ሳያገባ ቀረ። ስለዚህ እግዚአብሔር እስከ ሰጠው ድረስ ሚስት ሳያገባ ኖረ።

106. ያዕቆብ ያለ እግዚአብሔር አመራር በስሕተት የተቀበለው ነገር ምንድን ነው?

መልስ።

ያዕቆብ እግዚአብሔርን ያምን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር አቀነባብሮ እንደሚፈጽምለት አልተማመነውም ነበር። እግዚአብሔር ተስፋ የገባለትን ነገር ለማግኘት በራሱ ተማመነ እርሱም እግዚአብሔር እስኪሰጠው ድረስ ታግሶ አልጠበቀም። ስለዚህ በእግዚአብሔር ሳይሆን በራሱ ተማምኖ እግዚአብሔር ያቀደለትን መልካም ዕቅድ ስላጠፋ ታላቅና ብዙ የእግዚአብሔር በረከት ቀረበት። በዘፍ. 47፡9 ያዕቆብ ሲናገር «የሕይወቴ ዘመኖች ጥቂትም ክፉ ሆኑብኝ» ብሎአል።

107. እግዚአብሔር ያዕቆብ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲያውቅ ያደረገበትን ግልጽ መንገድ አመልክት። ዘፍ. 28፡10-15፤ ም. 31-32፡1፥ 2፤ 28፡12፥ 13፤ ም. 32፤ 25፡1-4።

መልስ።

ያዕቆብ እግዚአብሔር የአብርሃምን ቃል ኪዳን ተስፋ እንደሰጠው ያምን ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ተስፋውን እንደሚሰጠው የሚያረጋግጥ በቂ እምነት አልነበረውም። በዚህ ፋንታ ግን ተስፋውን በራሱ ኃይል በማጭበርበር ሊቀበል ሞከረ። በመጀመሪያ ብኩርናውን ትክክል ባልሆነ ጊዜያዊ ነገር ገዛ (ዘፍ. 25፡27-34)። ከዚያም በረከቱን በማጭበርበር ተቀበለ (ዘፍ. 27)።

ምሳሌ፡- አንድ ቤተሰብ ለልጃቸው አንድ ጥሩ ስጦታ ቢያዘጋጁለትና ልጁም ስጦታው ለእርሱ እንደሆነ ቢያውቅ ነገር ግን ልጁ ስጦታው ሳይሰጠው በፊት ሄዶ እራሱ ቢወስድ ይህ አድራጎት ቤተሰቦቹን በጣም ያሳዝናቸዋል። ይህ ነው እንግዲህ ያዕቆብ በእግዚአብሔር ላይ የፈጸመው። በረከቱ የእርሱ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሳይሰጠው በፊት በገዛ እጁ ሰርቆ ወሰደ። ያዕቆብ የእግዚአብሔርን በረከት ይፈልግ ነበር፥ ነገር ግን እምነቱ በጣም ጥቂት ነበር። እርሱም እግዚአብሔር ሊሰጠው ተስፋ ከገባለት በኋላ ሌላ ሰው የሚወስድበት መስሎት ፈራ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች አባት ለመሆን እምነትን መማር ነበረበት። ሆኖም እግዚአብሔር አስተማረው፤ በመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር በብዙ ትዕግሥትና ፍቅር አስተማረው።

1. የአብርሃም ኪዳን ለያዕቆብ በሕልም ጸናለት (ምዕራፍ 28፡10-15)። እግዚአብሔር ያዕቆብን በእምነቱ ለማበረታታትና በእግዚአብሔርም ላይ እምነት እንዲኖረው ለማድረግ የገባለትን ቃል ኪዳን በሕልሙ አሳየው። ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እግዚአብሔር ከሰጠው ከአሥር አንድ መልሶ ለእግዚአብሔር እንደሚሰጥ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባ።

2. በምዕራፍ 31 እንደተጠቀሰው ያዕቆብ እግዚአብሔር በከብቶች እንደባረከው ያውቅ ነበር (ዘፍ. 31፡5፥ 7)። ይህ ራሱ ለያዕቆብ በእግዚአብሔር ላይ ለመተማመን ይበቃው ነበር። ነገር ግን ያዕቆብ አሁንም ቢሆን በሙላት በእግዚአብሔር ተስፋ አልተማመነም ነበር።

እግዚአብሔር ያዕቆብን በሰላም መልሶ ወደ አገሩ እንደሚያመጣው ተስፋ ሰጥቶት ነበር (ምዕ. 28፡15)። ነገር ግን ካራንን ለቆ ወደ ከነዓን የሚሄድበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ ያዕቆብ ላባ እንድሄድ አይለቀኝም ብሎ ፈራ። ያዕቆብ እግዚአብሔር መልሶ ወደ ከነዓን እንደሚያገባው ተስፋ ተቀብሎአል፤ ነገር ግን ከካራን ተደብቆ ሸሸ (ምዕራፍ 31፡14-55)። (ቁጥር 20) ያዕቆብ ከላባ በሸሸ ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ላባን እንዳይነካው በማስጠንቀቅ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን አሳይቶታል (ዘፍ. 31፡24፥ 42)።

3. ያዕቆብ በጥቂት እምነቱ በመንገድ ላይ ሳለ እንኳ እግዚአብሔር መላእክት ሊጠብቁት በአጠገቡ እንዳሉ አሳየው (ምዕራፍ 32፡1፥ 2)። ይህም ደግሞ እምነቱን ለማጠንከር ነበር። ያዕቆብ የእግዚአብሔር መላእክት በምዕራፍ 28፡12፥ 13 ሲያገለግሉት አይቶአል። ስለዚህ እግዚአብሔር ያንን ነገር አሁን አስታወሰው።

4. ዔሳው ያዕቆብን ለማጥፋት ከ400 ሰዎች ጋር መጣበት። ያዕቆብ አሁንም የእግዚአብሔርን ተስፋ በሙላት ስላልተማመነ ፍርሃት ያዘው። ምዕራፍ 32፡10 ላይ ያዕቆብ እግዚአብሔር ወደ አገርህ መልሼ አመጣሃለሁ የሚለው የእግዚአብሔር ተስፋ ወደ አገሩ ሀብታም አድርጎ በመለሰው ጊዜ ስለተፈጸመ ትዝ አለው። ስለዚህ እግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ ብሎ ተስፋ እንደሰጠው አሳሰበው (ዘፍ. 32፡11፥ 12)። አሁን ዔሳው እርሱንና ቤተሰቦቹን ለመግደል ቢመጣ የተነገረለት የተስፋ ቃል ባልተፈጸመም ነበር። ስለዚህ በእግዚአብሔር ተስፋ ተማምኖ ማረፍ ነበረበት። ሆኖም እስከ አሁንም ይፈራ ነበር። እምነት ባለበት ቦታ ምንም ዓይነት ፍርሃት አይኖርም።

አሁንም ያዕቆብ በሥጋ ክንድ እንጂ በእግዚአብሔር አልተማመነም። ምክንያቱም የዔሳውን ቁጣ ለማብረድና ለመለማመጥ የእንስሳት ገጸበረከት አቀረበለት። ከዚህም በቀር ሠራዊቶቹን ለሁለት ከፈላቸው፥ ምክንያቱም ዔሳው የመጀመሪያውን ሠራዊት ከመታ ሁለተኛው ሠራዊት ያመልጣል በሚል አሳብ ነው (ዘፍ. 32፡7፥ 8)። አሁንም ቢሆን ያዕቆብ በሥጋ ይታመናል።

5. እግዚአብሔር ያዕቆብ በእግዚአብሔር በመተማመን ብቻ እንጂ በሌላ መንገድ ከውስጡ ሊወጣ የማይችልበት ወጥመድ ውስጥ አገባው። በዚህ ላይ ያዕቆብ በራሱ ኃይል ተማምኖ በዔሳው እጅ ይወድቅ እንደሆን ወይም በእግዚአብሔር ተማምኖ እንደተስፋው ከወጥመድ ያመልጥ እንደሆን ምርጫ ተሰጥቶታል፤ ሌላ ለያዕቆብ የቀረለት ምርጫ ፈጽሞ አልነበረም።

በዘፍ. 32፡24-30 ያለውን ክፍል አንብብ። ያዕቆብ ሕይወቱን ለማዳን የሚችለውን ነገር ሁሉ ካደረገ በኋላ ለመጸለይ ሄደ (ቁጥር 24)። በዚያን ሌሊት ያዕቆብ ብቻውን ተወው። ትግሉም በእግዚአብሔር በመተማመንና ፍርሃት በሞላበት በራሱ ችሎታ በመተማመን በሚያደርገው ነገር መካከል ነው። አንድ ሰው ከያዕቆብ ጋር ይታገል ነበር። ያም ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነበር። እግዚአብሔር አብ በብሉይ ኪዳን ዘመን በልጁ በኩል ካልሆነ በቀር በግል ከሰው ጋር ግንኙነት ያደረገበት ጊዜ የለም (ምዕ. 32፡30)። እግዚአብሔር ያዕቆብ በሥጋ መተማመኑን ትቶ በእርሱ ብቻ እንዲታመን ይፈልግ ነበር። ያዕቆብ እራሱን በሞላ ለእግዚአብሔር መስጠት አልቻለም ነበር። ሥጋዊው ተፈጥሮው ይህን ከማድረግ ወደኋላ ይለው ነበር። የያዕቆብ የዘወትር ስሕተቱ በራሱ ችሎታ መተማመኑ ነበር። እግዚአብሔር በሰላም ወደ ከነዓን መልሶ እንደሚያመጣው ተስፋ ገብቶለት ነበር። አሁን ያዕቆብ እግዚአብሔር ተስፋውን እንዲፈጽም በእግዚአብሔር ቃል ተማምኖ ማረፍ ነበረበት። ነገር ግን አደጋን ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ተስፋ ላይ የነበረውን እምነት ትቶት ሄደ።

እግዚአብሔር ያዕቆብን ባላሸነፈው ጊዜ ማለት የያዕቆብን አለማመን ሊያላቅቀው ባልቻለ ጊዜ ያዕቆብ በእግዚአብሔር ተማምኖ በሙላት በእግዚአብሔር ላይ ስላልተማመነ እግዚአብሔር ሹሉዳውን ነክቶ አንድ እግሩ አንካሳ እንዲሆን አደረገው (32፡25)። በዚያን ጊዜ ዔሳው የመጀመሪያውን ሠራዊት ቢመታበት ኖሮ ያዕቆብ ከሁለተኛው ሠራዊት ጋር ተደባልቆ በሸሸ ነበር። ስለዚህ ወደፊት በምንም መንገድ መሸሽ አይችልም። ከእንግዲህ ወዲያ ከዔሳው እጅ ማምለጥ ስለማይቻል በእግዚአብሔር መተማመን ብቻ ቀርቶለታል።

እግዚአብሔርም ራስክን መርዳት የምትችል ከሆነና የማላስፈልግህ ከሆነ «ልቀቀኝና ልሂድ አለው» (ቁጥር 26)። ሸሹቱ አመልጣለሁ በሚለው ዕቅድህ ተጠቀም። በዚህን ጊዜ ያዕቆብ እግዚአብሔር ብቻ ተስፋው ስለነበረ እግዚአብሔርን ሊለቅቅ አልፈለገም። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ያዕቆብን እስራኤል ብሎ ጠራው። ቁጥር 28 «ከእግዚአብሔርና ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና።» ያዕቆብ ደክሞ ለሥጋ አልተሰጠም ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ጨብጦና ተመርኩዞ ሥጋን እስኪያሸንፍ ድረስ አጥብቆ ስለታገለ ነው። ከዚያን በኋላ የትግሉ ጊዜ ስለአበቃ ያዕቆብ ሰላምን አገኘ። እግዚአብሔርም በተአምራታዊ መንገድ ያድነኛል ብሎ አመነ። ያም ተአምራት እንዳለው ሆነ።

ያዕቆብ መልሺ በሰላም ወደ ከነዓን አመጣሃለሁ ያለውን እግዚአብሔርን ስለተማመነ እግዚአብሔር የዔሳውን ልብ ለወጠ። ዔሳውም 400 የጦር ሰዎች ይዞ የመጣው ያዕቆብን ለመበቀል ነበር። ይህ ባይሆን ኖሮ እነዚህን ሰዎች ሁሉ ይዞ ባልመጣም ነበር። ዔሳው በመንገድ ላይ ሳለ ያዕቆብ በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔር የዔሳውን ልብ ለወጠ። ሁለቱም ወንድማማቾች በሰላምና በፍቅር ተገናኙ። ምንም ያህል ሁናቴው የማይቻል ቢመስልም ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻለዋል። አንተ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረግህ እመነው፥ እግዚአብሔርም በማንኛውም ሁናቴ ውስጥ ይጠብቅሃል።

6. ምዕራፍ 34 ያዕቆብ በሥጋው በተማመነና በተጓዘ ቁጥር ልጆቹ ጥሩ ምስክርነትና ምሳሌነት ስላላዩበት ክፉ ሰዎች በመሆን አደጉ። በምዕራፍ 34 ላይ እንዳየነው ሁሉ ያዕቆብ በኃጢአቱ ከመናዘዙ በፊት እንኳ ብዙ በሥጋው የዘራውን የኃጢአት መከር አጭዶአል። አባቶች የኃጢአተኛ ሕይወታቸውን ፍሬ ከልጆቻቸው ያመርታሉ። ጥሩ ምስክርነት የሌላቸው የአማኝ ቤተሰቦችም በሎጥ ሕይወት እንደደረሰው ከልጆቻቸው የኃዘንን መከር ይሰበስባሉ።

ያዕቆብ በምዕራፍ 32 በጵኒኤልና በምዕራፍ 35 በቤቴል ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ባስረከበ ጊዜ የዮሴፍ የስድስት ዓመት ልጅ በመሆኑ በመንፈሳዊ ሕይወት እያደገ ስለሄደ በኋላም መንፈሳዊ ሰው ሆነ (ምሳሌ 22፡6)።

7. ምዕራፍ 35፡1-4 እግዚአብሔር የአብርሃምን ቃል ኪዳን ለያዕቆብ ከሰጠው ከ20 ዓመት ወዲህ ነው ያዕቆብ ወደ ቤቴል የሄደው፤ በዚያም ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለ። ስለ ቤተሰቦቹ በሞላ ደግሞ ኃላፊነት አለበት። ቤተሰቦቹን በሞላ በእውነተኛ ልብ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ለማድረግ ጣዖታትን በሞላ እንዲያስወግዱ አዘዘ። ከዚህም በቀር ልብሳቸውን እንዲያጸዱና ንጹሐን እንዲሆኑ አዞአቸዋል። እግዚአብሔርን በእውነት ልናመልክ ከፈለግን በልባችን ጣዖታት እንዲኖሩ መፍቀድ አይኖርብንም። ጣዖት ማለትም ከእግዚአብሔር አልቀን የምንወደው ነገር ነው። እርሱም ሁልጊዜ በአእምሮአችን መለስ ብለን ልናየው የምንፈልገው ነገርና ከእግዚአብሔር ጋራ ሳለን አንድ ዓይነት መጋረጃና ገደብ የሆነ ነገር ነው። ከዚህም በቀር በእግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ በአካልና በልብሰም ቢሆን ንጹሕ ሆነን መገኘት ይገባናል (ምዕራፍ 35፡2)።

ነገር ግን ያዕቆብ ሊያጠፋቸው ይገባ የነበሩትን ጣዖታት ፈጽሞ አላጠፋቸውም ነበር። ነገር ግን በዋርካ ስር ሸሸጋቸው (35፡4)። እርሱም እንደገና ሁልጊዜ እዚያ ሊያገኛቸው ይችላል። አማኞችም በልባቸው ያመልኳቸው የነበሩትን ጣዖታት ካራቁ በኋላ ፈጽመው አያጠፉአቸውም። ምክንያቱም በልባቸው ውስጥ አሁንም ለእነዚህ ነገሮች ጥቂት ፍቅር ስላላቸው ነው። በዚህ መንገድ እንግዲህ ወደ እነዚህ ጣዖታት መመለስ በጣም ቀላል ነው። እግዚአብሔር ዳግመኛ ወደ እነርሱ የመመለስ ዕድል እንዳይኖርና ፈጽመን

እንድናጠፋቸው ይፈልጋል። እግዚአብሔርም እርሱ እንደጠላቸው እኛም እንድንጠላቸው ይፈልጋል።

## ምዕራፍ 37-50 አንብብ።

108. ሀ. ከምዕራፍ 37 የሚጀምረው ክፍለ ትምህርት ምንድን ነው?

ለ. የዚህ ክፍል ዋና ባለ ታሪክ ማን ነው?

መልስ።

ሀ. ትምህርቱ ስለ «ያዕቆብ ትውልድ» ነው (37፡2)።

ለ. የዚህም ክፍል ዋንኛው ባለ ታሪክ ዮሴፍ ነው። ከያዕቆብ ልጆች ሁሉ ዮሴፍ ጻድቅ ስለነበረ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ወደ ግብፅ መሄጃ መንገድ እንዲያዘጋጅና እነርሱም በዚያ ታላቅ ሕዝብ እንዲሆኑ ዮሴፍን መረጠው።

109. ዮሴፍ ጶጢፋርን ሲያገለግል ሳለ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደነበረ እንዴት ተገለጠ? (39፡1-6)። የግዞቱ ጊዜስ እንዴት ነበር? (39፡21-23)።

መልስ።

እግዚአብሔር ዮሴፍ የሚሠራውን ነገር ሁሉ ባረከለት፤ ምክንያቱም የጶጢፋር ንብረት በሞላ በዮሴፍ እጅ ስለ ነበር ነው። እግዚአብሔርም የጶጢፋርን ቤትና እርሻውን ሁሉ ባረከ (ምዕራፍ 39፡4፥ 5)። እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር የመሆኑ ማረጋገጫ ለዮሴፍ ጥሩ ማበረታቻ ነበር።

ዮሴፍ ወደ ግዞት በተጣለ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረና የሚሠራውን ሁሉ ስለሚባርክለት ዮሴፍ በእስር ቤት ባለው ሥራ ላይ ሁሉ ኃላፊ ሆነ።

የእግዚአብሔር ልጆች ያለ ጥፋታቸው በስድብና በእስር መከራ ሲቀበሉ እግዚአብሔር ሁሉንም ይባርካቸዋል። ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ እስር ቤት በታሠሩ ጊዜ የእስር ቤቱ ዘበኛና ቤተሰቦቹ ዳኑ። ከዚህም በቀር በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመ (የሐዋርያት ሥራ 16)።

110. እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘፍ. 15፡13 ላይ የገባውን ቃል ኪዳን በዮሴፍ ተጠቅሞ ምን በማድረግ ፈጸመው?

መልስ።

እግዚአብሔር አብርሃምን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ማለት የአብርሃምን ዘር በእንግድነት አገር ለ400 ዓመት አገልጋዮች እንደሚሆኑና ከዚያም እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ከባርነት እጅ አውጥቶ ገዝተዋቸው የነበሩትን ሕዝቦችም እንደሚቀጣ ለአብርሃም ነግሮት ነበር (ዘፍ. 15፡13፥ 14)።

ስለዚህ እግዚአብሔር አሁን ከያዕቆብ ልጆች የራሱን ሕዝብ ማቋቋም ጀመረ። በዮሴፍም ተጠቅሞ ወደ ግብፅ የሚመራቸውም ጊዜ ደረሰ። ሰይጣንም የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማደናቀፍ ዮሴፍን ለማጥፋት በጣም ሞክሮ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ዘወትር አሸናፊ ነው።

ሀ. ዮሴፍም ወደ ግብፅ ተሸጠ። ግብፅ እስራኤላውያን ታላቅ ሕዝብ የሚሆኑባት አገር ነበረች (ዘፍ. 37)።

ለ. ዮሴፍም የፈርዖን ባለሟል ለሆነው ለጶጢፋር ተሸጠ (ዘፍ. 39፡1-18)። ዮሴፍም ከፈርዖን ባለሟል ሚስት ከጶጢፋር ጋር ግንኙነት አደረገ።

ሐ. ዮሴፍም ወደ ግዞት ተጣለ (ዘፍ. 39፡19-23)። ሰይጣን ሊያጠፋው ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር ግን ዓላማውን ለማሟላት ተጠቀመበት።

መ. ዮሴፍ ወደ ፈርዖን ፊት እንዲመጣ የፈርዖን አሽከሮች በእስር ቤት የተጣሉት በእግዚአብሔር አመራር ነው (ዘፍ. 40 እና 41)።

ሠ. እግዚአብሔር የፈርዖንን ሕልም እንዲተረጉም ለዮሴፍ ጥበብን ስለሰጠው ዮሴፍ የፈርዖን ሁለተኛ ገዢ ሆኖ በግብፅ ላይ ተሾመ (ዘፍ. 41)።

ረ. ሰባቱ የረኃብ ዘመን በመጣ ጊዜ የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመግዛት ከከነዓን ወደ ግብፅ መጡ (ዘፍ. ምዕራፍ 42-44)።

ሰ. ዮሴፍም ወንድሞቹ በወንድማቸው ላይ ስላደረጉት በደል ሲጸጸቱና ሲናዘዙ ተመልክቶ የልባቸውን መለወጥ አስተዋለ (ምዕራፍ 42፡21፥ 22፤ 44፡16-34)።

ሸ. ዮሴፍም ለወንድሞቹ ተገለጠላቸውና አባቱንና ቤተሰቦቹን በሙላ ወደ ግብፅ እንዲያመጡ ላካቸው (ምዕራፍ 45)።

ቀ. እግዚአብሔርም ያዕቆብ ወደ ግብፅ እንዲሄድ አበረታታው (ዘፍ. 46፡1-4) የያዕቆብ ሙላ ቤተሰቡና ወገኑ በሙላ ወደ ግብፅ ሄደው በጌሴም ምድር ተቀመጡ (ዘፍ. 20፡20)። የዮሴፍም ወንድሞች በዮሴፍ ላይ ክፉ አድርገውበት ነበር። እግዚአብሔር ግን ለመልካም አደረገው። ሰይጣንም በክፉ ሥራው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሊያጠፋ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሥራ ተስፋፋ።

111. ሀ. እግዚአብሔር ለምን ዓይነት ሁለት ዓላማ ነው የእስራኤል ልጆች ወደ ግብፅ እንዲሄዱ ያደረገው? ዘፍ. 15፡16፤ 46፡3-5።

መልስ።

1. እግዚአብሔር መጀመሪያውኑ ምድረ ከነዓንን ለእስራኤላውያን ለመስጠት አቅዶ ነበር። ከነዓናውያኖችም ምድረ ከነዓንን ወስደው የሚኖሩበት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ነበረ። ሆኖም እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነ

ከነዓናውያንን የኃጢአታቸው ጽዋ እስኪሞላ ድረስ አልፈረደባቸውም ነበር። እግዚአብሔር አብርሃምን አሞራውያንንና ከነዓናውያንን (እስዋሃለሁ ያለው ሳይፈረድባቸው ከ400 ዓመት በፊት ነበር።) ስለዚህ ከነዓናውያኖች ንስሐ መግባት ቢፈልጉ ኖሮ አስቀድመው ንስሐ በገቡ ነበር። እግዚአብሔርም ኃጢአታቸው ከ400 ዓመት በኋላ እንደሚሞላ ያውቃል። ከዚያም እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከነዓናውያንን አጥፍተው ምድሩን እንዲወርሱ ወደ ከነዓን መራቸው (ዘፍ. 15፡16)። እስራኤላውያንም ከነዓናውያንን ለማጥፋት በግብፅ ሳሉ ሊዋለዱና ሊባዙ ይገባ ነበር።

2. ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እስራኤላውያን በፍጥነት ታላቅ ሕዝብ ሆነው ከቀሩት ኃጢአተኛ ሕዝብ የተለዩ እንዲሆኑ ነበር። እስራኤላውያን በከነዓን ቢኖሩ ኖሮ ከከነዓናውያን ጋር ይደባለቁና እራሳቸውን ከእግዚአብሔር ሕዝብነት ያገልሉ ነበር። የያዕቆብ ልጆችም ገና ድሮ የከነዓንን ሴቶች ማግባት ጀምረው ነበር (ዘፍ. 46፡10፤ 38፡2)።

እስራኤላውያን ከሌላ ሕዝብ ተለይተው ለማደግና ለመባዛት የሚችሉት በግብፅ ብቻ ነው። እስራኤላውያን በግብራቸው እረኞች ናቸው። ስለዚህ በግብፃውያን ዘንድ እረኛና በግ እንደ ርኩስ ስለሚቆጠር ይጸየፉአቸዋል። በዚህ ምክንያት ግብፃውያን እራሳቸው እንኳ ከእስራኤላውያን ተለይተው ይኖሩ ነበር (ዘፍ. 46፡31-34፤ 43፡32፤ ዘጸአት 8፡26፤)። ዮሴፍም ወንድሞቹ እረኛ እንደሆኑ በሌላ አሕዛብ የጣዖት አምልኮ ሳይበከሉ ለብቻቸው በመኖር እንዲበዙ ለምለሙን የጌሴምን ምድር ስጠን ብላችሁ ፈርዖንን ጠይቁት ብሎ ነገራቸው (ዘፍ. 46፡3-5)።

111. ለ. ያዕቆብ ወደ ግብፅ ሊሄድ አቅራቢያ እግዚአብሔር ምን ተጨማሪ ማረጋገጫ ሰጠው? ዘፍ. 46፡4።

መልስ።

ያዕቆብ እግዚአብሔር የሰጠው ከነዓንን እንጂ ግብፅን እንዳልሰጠው በአእምሮው እያሰበ ነበር። በዚህ ምክንያት ወደ ግብፅ ለመሄድ አይፈልግ ይሆናል። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ያዕቆብን ወደ ግብፅ እንዲሄድ አዘዘውና እኔም ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፤ ከዚያም እኔ እመልስሃለሁ በማለት ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ማረጋገጫ ሰጠው።

111. ሐ. ያዕቆብ ልክ በሚሞትበት ቀን ዮሴፍን ያስማለው ስለምን ነበር? ዘፍ. 47፡30-31።

መልስ።

ያዕቆብ ዮሴፍን በከነዓን እንጂ በግብፅ እንዳይቀብረው ጠየቀው። እግዚአብሔርም ተስፋ የገባላቸው ግብፅን ሳይሆን ከነዓንን ነው። አብርሃምና ይስሐቅ የተቀበሩት በከነዓን ነው። ስለዚህ ያዕቆብም እንዲረሱት አልፈለገም (ዘፍ. 47፡30፥ 31፤ 49፡29-33)።

112. ያዕቆብ የሞተ ዕለት ዮሴፍንና ልጆቹን የባረካቸው በረከትና ምርቃት ጥቅሙ ምንድን ነው? ዘፍ. 48፤ 49፡22።

መልስ።

ያዕቆብም የዮሴፍ ልጆች ምናሴና ኤፍሬም የእርሱ ልጆች መሆን እንዳለባቸው ትንቢት ተነበየ፤ የዮሴፍ ሁለቱ ልጆች ከእስራኤል ነገድ ውስጥ እንደ ሁለቱ ሆነው ተቆጠሩ። የዮሴፍ ልጆች እንደ ሁለት ነገድ ሲሆኑ የያዕቆብ ልጆች ግን እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ነገድ ሆነው ተቆጠሩ (ዘፍ. 48፡5)።

ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች በመረቃቸው ጊዜ ቀኝ እጁን በታናሹ በኤፍሬም ላይ በማድረግ ታላቅ እንደሚሆን ሲያመለክት በታላቁ በምናሴ ላይ ደግሞ ግራ እጁን ጭኖ ከታናሹ እንደሚያንስ አሳወቀ። ስለዚህ ኤፍሬም ከእስራኤል ነገዶች ዋንኛውና ታላቁ ሆነ።

113. ስለ ይሁዳ የተነገረውን ትንቢትና የትንቢቱን ምሳሌ አብራራ። ዘፍ. 49፡8።

መልስ።

ያዕቆብም ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ዘር እንደሚመጣ ትንቢት ተናገረ (ዘፍ. 49፡10)። በሕጉ መጽሐፍ ውስጥ ማለት በዕብራውያን «ሳሌም» ተብሎ ይጠራል። ትርጓሜውም «የሰላም ንጉሥ» ወይም «የእረፍት ቦታ ማለት ነው።» በአማርኛም መጽሐፍ ቅዱስ «ገዢ» ተብሎ ተጠቅሶአል። ስለዚህ እርሱ በክርስቶስ ላመኑት ሁሉ የእረፍት ቦታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምና አንድነት ሰጠን። ዳግመኛ ሲመጣ ደግሞ ዓለምን በሰላም ለ1000 ዓመት እንደሚገዛ ንጉሥ ሆኖ ይመጣል። የዓለም ሕዝብ ሁሉ ሊታዘዙው ይገባል። «በትረ መንግሥትም ከይሁዳ እጅ አይለይም።» የይሁዳ አንበሳ ነገሥታት በሞላ የመጡት ከይሁዳ ነገድ ከሆነው ከዳዊት ዘር ነው። የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ በናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን ተማርኮ የተወሰደው ነው (2ኛ ዜና 36፤ 2ኛ ነገሥት 24 እና 25)። ሁለተኛውና እውነተኛው የይሁዳ ንጉሥና በዳዊት ዙፋንም ለዘለዓለም የሚነግሠው ከይሁዳ ዘር የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው (ሉቃ. 1፡32፥ 33፤ ኢሳ. 9፡7፤ ዳንኤል 2፡44፤ 7፡13፥ 14፤ ራእይ 11፡15)።

በዘፍጥረት 49፡24 ላይ ያዕቆብ ዮሴፍን በመረቀበት ቦታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእስራኤል እረኛና ድንጋይ ተብሎአል። በዚህ ላይ ያዕቆብ የሚተነብየው ክርስቶስ «ከያዕቆብ አምላክ ዘንድ» እንደሚመጣ ነው። እርሱም በይሁዳ ዘር በኩል እንዲመጣ ከሰማይ ተልኮአል።

114. ዮሴፍ ከመሞቱ በፊት ወንድሞቹን ምን አስማላቸው? ዘፍ. 50፡24-26፤ ዘጸአት 13፡19።

መልስ፡፡

ዮሴፍም እንደ ያዕቆብ በከነዓን እንዲቀብሩት እስራኤላውያንን አስማላቸው፡፡ እግዚአብሔር እንደገባው ቃል ኪዳን እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ከነዓን እስከመራቸው ድረስ አጥንቱ በግብፅ እንዲቆይ ነገራቸው፡፡ ከዚያም የወጡ ዕለት አጥንቱን ይዘው ሄደው በከነዓን እንዲቀብሩት ቃል ገብተዋል፡፡ የዮሴፍ አጥንት እስራኤል በግብፅ በኖሩበት ዘመን ሁሉ ከነዓን እግዚአብሔር ቃል የገባላቸው አገራቸው እንደሆነ የሚያሳስባቸው ምልክት ነበር፡፡ ከዚህም በቀር አጥንቱ እነርሱ በግብፅ አገር እንግዶች እንደሆኑና አንድ ቀንም ጌታ ከግብፅ አውጥቶ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ እንደገባላቸው ቃል ኪዳን መርቶ ወደ ከነዓን እንደሚያስገባቸው ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ የዮሴፍ አጥንት በመካከላቸው ተገኝቶ ዘወትር ባያስታውሳቸው ኖሮ እስራኤላውያን እግዚአብሔር በለምለምዋ ምድር ትኖራላችሁ ያላቸውን ተስፋ ወዲያውኑ በዘነጉት ነበር፡፡

115. ከዮሴፍ ሕይወት ያገኘኸው ጠቃሚ ትምህርት ምንድን ነው?

መልስ፡፡

ከዮሴፍ ሕይወት በጣም ጠቃሚው ትምህርት ዮሴፍ በልቡና በአካሄዱ ጻድቅ ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ ዮሴፍ ከመፈተኑ በፊት ኃጢአትን ላለመሥራት በልቡ ቁርጥ አሳብ ነበረው፡፡ ስለዚህ ኃጢአት የሆነውን አሳብ በሞላ አልቀበል አለ፡፡ በዚህ ምክንያት ብቻ (ዘፍ. 39፡9) «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገርና ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት አደርጋለሁ ለማለት ቻለ፡፡» ማንኛውም ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ስለሆነ እግዚአብሔር አማኞችንም ቢሆን ስለ ኃጢአታቸው ይቀጣቸዋል፡፡ እነርሱም ፈጥነው በመናዘዝ ንስሐ ካልገቡ ከእግዚአብሔር የተግሣጽ እጅ አያመልጡም (ዕብ. 12፡6-10፤ ራእይ 3፡19፤ ማቴ. 5፡24-26)፡፡ ዮሴፍ ልቡንና አእምሮውን በንጽሕና ስለጠበቀ እግዚአብሔር በግሩም ሁኔታ ተጠቅሞበት ባረከው፡፡

116. ዮሴፍ በምን መንገድ ነው የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው?

መልስ፡፡

1. ክርስቶስም ሆነ ዮሴፍ ሁለቱም በአባታቸው የሚወደዱ ነበሩ (ዘፍ. 37፡3፤ ማቴ. 3፡17፤ ዮሐ. 3፡35፤ 5፡20)፡፡

2. ሁለቱም በወንድሞቻቸው የተጠሉ ነበሩ (ዘፍ. 37፡4፤ ዮሐ. 15፡25)፡፡

3. የሁለቱም ወንድሞች ሊገድሉዋቸው አድመውባቸዋል (ዘፍ. 37፡18፤ ማቴ. 26፡3-4)፡፡

4. ሁለቱም በወንድሞቻቸው በገንዘብ ተሸጡ፡፡

5. የሁለቱም ከፍተኛ ደረጃቸው በወንድሞቻቸው የተካዱ አድርጎአቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሲያስረዳ ዮሴፍ ደግሞ ወንድሞቹ ወድቀው እንደሚሰግዱለት ነግሮአቸዋል (ዘፍ. 37፡8፤ ማቴ. 21፡37-39፤ ዮሐ. 15፡24፥ 25)።

6. ዮሴፍም እንደ ክርስቶስ በግብፅ ተደብቆ ነበር። ያውም ፈርዖን ሊገድለው በፈለገ ጊዜ ነው (ማቴ. 2፡13-15) በሆሴዕ 11፡1 እንደተነበየው «ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት» ይላል። ይህም ትንቢት መፈጸም ነበረበት። እስራኤል ከግብፅ ተጠርተው እንደወጡ ክርስቶስም ከግብፅ ተጠርቶ ወጥቶአል (ማቴ. 2፡15)።

7. ሁለቱም ጻድቃኖች ስለሆኑ የእግዚአብሔርን በረከት በመከራ ውስጥ አልፈው ተቀበሉ።

8. ሁለቱም ደግሞ ጻድቃኖች ስለነበሩ ብዙ ስቃይና መከራን ተቀበሉ።

9. ሁለቱም ለአሕዛቦች በረከት ሆነው ነበር (ዘፍ. 41፡1-45)።

10. ሁለቱም ከአሕዛብ ወገን ሙሽራዎችን አትርፈዋል (ዘፍ. 41፡45፤ የሐዋርያት ሥራ 15፡14፤ ኤፌ. 5፡31፥32)።

11. ዮሴፍ ከንጉሡ ፈርዖን በስተቀኝ ተቀመጠ። ኢየሱስም በአብ ቀኝ ተቀምጦአል (ማቴ. 16፡19፤ ዕብ. 1፡3)።

12. ዮሴፍ ብዙ የተራቡትን ሰዎች መግቦ ብዙ ነፍስ ከሞት እንዳዳነ ኢየሱስም መንፈሳዊ ምግብ ሰጥቶ ብዙ ሰዎችን ከዘለዓለም ሞት ሕይወታቸውን አድኖአል።

13. ዮሴፍ በወንድሞቹ ስለተጠላ የወንድሞቹንና የብዙዎቹን አሕዛብ ሕይወት ከረኃብ ሞት አዳነ። ኢየሱስም በወገኖቹ በመጠላቱ የብዙዎቹ አይሁዶችና አሕዛብ አዳኝ ሆነ።

14. ዮሴፍ የግብፅን አሕዛብ በምቾት ሲመግብ ወንድሞቹ በከነዓን ይራቡ ነበር። ኢየሱስም አሕዛብን በመንፈሳዊ ምግብ እየመገባቸው ሳለ ወድሞቹ አይሁዶች ያለ ወንጌል ናቸው።

15. የዮሴፍ ወንድሞች በፊቱ እስከተናዘዙ ድረስ አሳብና ኃጢአት እንዲሁም በኃዘንና በመከራ እንደኖሩ የክርስቶስ ወንድሞች የሆኑት አይሁዶችም በኢየሱስ ክርስቶስና በዳግም ምጽአቱ አምነው ካልተናዘዙ በስተቀር በኃዘንና በመከራ ይኖራሉ (ዘካርያስ 12፡10)።

16. ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ታረቀ። ከዚያም በኋላ ከፍ ከፍ አደረጋቸው። እንደዚሁም ክርስቶስ ለዕብራውያን ወንድሞቹ ይህንኑ ያደርግላቸዋል (ዘፍ. 45፡1-15፤ ዘዳግም 30፡1-10፤ ሆሴዕ 2፡14-18፤ ሮሜ 11፡1፥ 15፥ 25፥ 26።)

17. ዮሴፍ ወዲያውኑ እራሱን ለወንድሞቹ እንደገለጠ ክርስቶስም አይሁዶችን በታላቅ መከራቸውና ስቃያቸው ጊዜ ይገለጽላቸውና ያድናቸዋል። (ዘካርያስ 12፡10፤ ዮሐ. 19፡37፤ ዘካርያስ 13፡6፤ የሐዋ. ሥራ 1፡9-11)።

# አሪት ዘጸአት።

## ዘጸአት ምዕራፍ 1-6 ያለውን ክፍል አንብብ።

1. ሀ. የዘፍጥረት መጽሐፍ የእስራኤልን ልጆች የትና በምን ያልተፈጸመ ተስፋ ተዋቸው?

መልስ።

በዘፍጥረት መጽሐፍ መጨረሻ ላይ እስራኤል በግብፅ አገር ውስጥ ጌሴም በሚባለው ስፍራ እንደነበሩ እናነባለን። እነርሱም እስከዚያ ጊዜ ድረስ እንኳን ብዙ ሕዝቦች አልነበሩም። ከዚህም በቀር እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ከነዓን የተባለውን ምድር አልወረሱም ነበር።

1. ለ. በዘፍጥረትና በዘጸአት መካከል ያለው መጣመር ምንድን ነው?

መልስ።

በዘፍጥረት መጽሐፍ የእስራኤልን ሕዝብ አመጣጥና አጀማመር እናነባለን። በዘጸአት ግን አንድ ትልቅ ሕዝብ ሆነው እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ግብፅን ለቀው እንደወጡ እናነባለን።

2. ሀ. ምን ያህል የሚሆኑ የያዕቆብ ትውልዶች ናቸው ወደ ግብፅ የገቡት?

መልስ።

ወደ ግብፅ የገቡት የያዕቆብና የልጅ ልጆቹ ቁጥር 70 የሚያህል ነበር (ዘጸአት 1፡5፤ ዘዳግም 10፡22)። በሐዋርያት ሥራ 7፡14 ግን 75 የሚሆኑ ሰዎች ወደ ግብፅ እንደገቡ እናነባለን። በዚህም ምንም ዓይነት ስሕተት የለም። ዘጸአት 1፡5 እነዚህ ሰባዎቹ የያዕቆብ የግል ልጆቹ እንደነበሩ በግልጽ ያስረዳል። «ከያዕቆብም ጉልበት የወጡት ሰዎች ሁሉ ሰባ ነፍሶች ነበሩ።» ይህም ማለት የያዕቆብንና የወንድ ልጆቹን ሚስቶች ሳይጨምር ነው። በሐዋርያት ሥራ 7፡14 ላይ ግን የተገለጸው ከልጆቹ ሚስቶች ጋር ሲደመር ነው። ስለዚህ ነው እንግዲህ ቁጥራቸው 75 የደረሰው። ለምን አምስት ሚስቶች ብቻ እንደነበሩ አናውቅም። ምናልባትም ብንያም በዚያን ጊዜ አላገባ ይሆናል። ምናልባትም አንዳንዶቹ የያዕቆብ ልጆች ያገቡዋቸው የከነዓን ሴቶች በከነዓን ቀርተው ይሆናል። ስለዚህ ምንም የምናውቀው ነገር የለም።

2. ለ. በምን ዓይነት ሁናቴ ነበር በመጀመሪያ ጊዜ በግብፅ ውስጥ የኖሩት?

መልስ።

እስራኤል በግብፅ ውስጥ የኖሩት መልካምና ለም በሆነ ምድር ላይ ነው።

2. ሐ. ይህ ሁናቴ በዘፍጥረት 46፡3 ላይ ያለውን ነገር በምን ዓይነት መንገድ ያሟላል?

መልስ።

በዘፍጥረት 46፡7 ላይ እግዚአብሔር ያዕቆብን ዘርህን በግብፅ ውስጥ ትልቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ ብሎ ቃል ገብቶለታል። ከምድሩ ሀብታምነት የተነሳ የእስራኤል ልጆች በፍጥነት እየተባዙ ሄዱ። በጠፍ ምድር ማለት ምግብ እንደልብ በማይገኝበት ስፍራ ችጋርና በእህል ዕጦት በሽታ ስለሚሆን ሕፃናት ያልቁና ለሕዝብ መባዛት እንቅፋት ወይም ገደብ ይኖራል (ዘጸአት 1፡7)።

3. ሀ. በዘጸአት 1፡8 ላይ እንደተጠቀሰው በመንግሥቱ ላይ ምን ዓይነት ታላቅ ለውጥ ሆነ? ይህስ ሁኔቴ በሐዋርያት ሥራ 17፡26፥ 27 እግዚአብሔር ከአንድ ሕዝብ ጋር ያደረገውን ነገር እንዴት ያብራራል?

መልስ።

በግብፅ ዮሴፍን ያላወቀ አዲስ ንጉሥ ተነሣ (ዘጸአት 1፡8)። እርሱም እስራኤላውያንን በማስጨነቅና በግፍ ባሪያ አደረጋቸው በሐዋርያት ሥራ 17፡26፥ 27 ባለው ክፍል ላይ እግዚአብሔር አስቀድሞ ከአንዱ ሰው ደም ማለት ከኖኅ የዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲመጡ አቀደ። አሁን በሕይወት ያሉ ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ በዓለም እንዲኖሩ ስላቀደ ነው። እግዚአብሔርም ለሕዝቡ መኖሪያ ስፍራ ሰጥቶ ድንበር ከልሎላቸዋል። እግዚአብሔርም ሕዝቦቹ ወንጌልን ለመስማት እንዲችሉ የት መኖር እንደሚገባቸው አስቀድሞ ወስኖአል (የሐዋርያት ሥራ 17፡26፥ 27)። እግዚአብሔርም በሕዝቡ መካከል ለራሱ መኖሪያ ቦታ አዘጋጀ። ምክንያቱም እግዚአብሔር በሚጠቀምባቸው ሰዎች ውስጥ ሆኖ ለሕዝቡ ሁሉ የደኅንነትን የምስራች እንዲያደርሱ ነው። እግዚአብሔር ለራሱ መኖሪያ የጠበቃት ምድረ ከነዓን ስትሆን ሕዝቦቹም እስራኤላውያን ናቸው። በምሥራቃዊ እስያ የሚኖሩት ሕዝቦች ከኖኅ የተወለደው የሴም ነገዶች ናቸው። ከምዕራብ በኩል ደግሞ የያፌት ነገዶች ለሆኑት ለአውሮፓውያን እግዚአብሔር መኖሪያ ሲሰጥ ከከነዓን ደቡባዊውን ክፍል ደግሞ አፍሪካውያን ለሆኑ የካም ነገዶች መኖሪያ አድርጎ ሰጣቸው።

የካም ልጅ የሆነው ከነዓን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እግዚአብሔር ምድር ሄደ። ሆኖም በኋለኛው ዘመን ከዚህ ምድር ተባሮ ወጣ። በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ምርጦቹ የሆኑትን የእስራኤልን ሕዝቦች በግብፅ ውስጥ እያበዛቸው ነበር። ምክንያቱም የከነዓንን ምድር ለእስራኤላውያን ሊሰጣቸው ስለፈለገ ነው። እነርሱም ከምቾቱ የተነሳ ቶሎ እንዲባዙ በሚያደርጋቸው በጣም ለምና ሀብታም በሆነው በግብፅ ምድር ጌሴም በሚባለው ስፍራ ይኖሩ ነበር።

እዚህ ላይ ተመልከቱ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ የግብፅን ገዢ በመለወጥ እስራኤል ወደ ግብፅ እንዲገቡ እንዳደረገና እንዲሁም ደግሞ ገዢውን ቀይሮ እስራኤል ከግብፅ እንዲወጡ እንዳደረገ።

## እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ግብፅ እንደመራ።

ግብፃውያን ከካም ዘር ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው የካም ልጅ የምጽራይም ልጆች ናቸው። እስራኤላውያን ግን ከሴም ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ወገን ናቸው። በግብፃውያን ዘንድ እረኛ እንደ ርኩስ ነገር ስለሚቆጠር ግብፃውያን እስራኤላውያን እረኞች ስለነበሩ ይጸየፉአቸው ነበር (ዘፍጥረት 46፡31-34፤ 43፡32፤ ዘጸአት 8፡26)። በዚህ ምክንያት እስራኤላውያን ከግብፅ ጋር በጋብቻ በመጣመር በጣዖታቸው ሳይጠላለፉ በቅድስና ለመኖርና ለመባዛት ችለዋል። ይህን ለመረዳት በዘፍጥረት 111. ሀ ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ተመልከት።

## ምዕራፍ 1 ና 2

አይሁዶች የሆኑት (እስራኤላውያን) በግብፃውያን ዘንድ እንደ ርኩስ ስለሚታዩ ግብፃውያን እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ ግብፅ የሚገቡበትን መንገድ አዘጋጀ። በአብርሃም ዘመን ማለት ኢየሱስ ከመወለዱ ከ2000 ዓመት በፊት የሴም ነገዶች በምሥራቅ በኩል ግብፃውያንን ወርረው ለ400 ዓመት ገዙአቸው። እነርሱም ሄክሶስ ወይም «የእረኞች ነገሥታት» ይባሉ ነበር። በዮሴፍ ዘመን ግብፅን ይገዛ የነበረው ንጉሥ ከሴም ወገን ነበር። እርሱም ያለ ምንም ቅሬታ ነበር እስራኤላውያን በግብፅ እንዲኖሩ የጋበዛቸው። ለእስራኤሎች መንገድ እንዲያዘጋጅላቸው እግዚአብሔር ነበር ይህንን የእረኞች ንጉሥ ለግብፃውያን የሰጣቸው። የግብፅ ንጉሥ እስራኤላውያን በግብፅ እንዲኖሩ ፈቀደላቸው። ነገር ግን ግብፃውያን እስራኤላውያንን በርኩሰታቸው እንዳይበክሉ ከእስራኤላውያን ተገልለው ይኖሩ ነበር።

እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ ከዘመናት መጀመሪያ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን የሚያስገባበት ጊዜ ሲደርስ እስራኤላውያን ጌሴምን የመሰለ ለምለምና ፍሬያማ ምድር ለቀው መውጣት ባልፈለጉም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከግብፅ አገር እንዲወጡ አስገደዳቸው። ለዚህም እግዚአብሔር የእረኞች ንጉሥ እንዲሸነፍና የእስራኤላውያንን መጠላት የወደደ ግብፃዊ የሆነው የካም ንጉሥ ግብፅን እንዲገዛ አደረገ፤ እርሱም ዮሴፍ ማን እንደነበር የማያውቅ ንጉሥ ነው (ዘጸአት 1፡8)። ይህንንም በማድረግ እስራኤላውያን በደስታ የግብፅን አገር ለቀው እንዲወጡ አደረገ። ጭቆናና መከራ መቀበል ብቻ ነበር እስራኤላውያንን ከግብፅ እንዲወጡና ወደ ከነዓን እንዲሄዱ ያደረጋቸው። በሐዋርያት ሥራ 17፡26ና 27 እግዚአብሔር ጊዜው እስኪደርስ ድረስ ምድራቸውን ጠብቆ ሊያወርሳቸው እንደሚችል እናነባለን። እስራኤላውያንም ወደ ከነዓን በገቡ ጊዜ የወንጌል መልእክት ወደ ሁሉ ሰው እንዲቀርብ በመካከላቸው ሆኖ ይመሰክር ነበር።

3. ለ. የእነዚህን ነገሥታት መለዋወጥ ምክንያት በማድረግ በእስራኤል ላይ የደረሰው መከራ እንዴት በረከት ሊሆንላቸው ቻለ?

መልስ።

ይህ በግብፅ የደረሰባቸው መከራ እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ተስፋ ወደ ገባላቸው ወደ ምድረ ከነዓን እንዲገቡ አድርጎአቸዋል። ከመከራ የተነሳም ንጉሣቸው ክርስቶስን መከተል ተማሩ። (ስለ ንጉሡ ክርስቶስ የሚገልጸውን መግቢያ ተመልከት።) ዛሬም መከራ እንዲሁ ክርስቲያኖችን ከዓለም ለይቶ ክርስቶስን እንዲከተሉ ያደርጋቸዋል። ግብፅ ያሁኑ የከፋው ዓለም ምሳሌ ስለሆነች ከዚያ ሸሽቶ መውጣት ነበረባቸው (1ኛ ዮሐንስ 2፡ 15-17)።

4. ሀ. እግዚአብሔር ሕዝቡቹን ነፃ እንዲያወጣለት ማንን ነበር ያስነሳው? ደግሞስ ግብፃውያን እስራኤላውያንን ባስጨነቁአቸው ጭንቀት ያ ነፃ አውጫቸው ሰው ምን ተማረ? (የሐዋርያት ሥራ 7፡21፥ 22።)

መልስ።

እስራኤልን ነፃ ለማውጣት እግዚአብሔር ሙሴን አስነሳ። ከሚቀበሉት የመከራ ዓይነት አንዱ የእስራኤላውያንን ወንዶች ልጆች መግደል ነበር። ሙሴንም የፈርዖን ሴት ልጅ ባገኘችው በወንዝ ዳር በቅርጫት ውስጥ ተሸሽጎ ነበር። እርሷም በሐዋርያት ሥራ 7፡21 ላይ እንደተገለጸው አንስታ ለንጉሥ ቤተሰብ ደረጃ ስለአበቃችው እስራኤልን ለመግዛትና ለመምራት የሚያስችለውን ትምህርት ተማረ። ዘጸአት ምዕራፍ 2 አንብብ።

ሰይጣን እስራኤልን ለማጥፋት ፈልጎ ነበር፥ ነገር ግን እግዚአብሔር መሪያቸውን ለማሰልጠን ሲል መከራ እንዲያመጣባቸው ፈቀደለት። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሰይጣን በእግዚአብሔር ልጆች ላይ መከራን ያመጣል። ይህ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሕዝቡቹ መከራ እንዲቀበሉ ባላደረገም ነበር።

4. ለ. የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሔር የተመረጠ የእግዚአብሔር መሣሪያ መሆኑ ለዚህ ሰው እንዴት ተገለጸለት? ይህስ ሰው የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንዴት ተረጎመው? የትርጉሙ ውጤትስ ምን ጥፋት አስከተለ? የሐዋ ሥራ 7፡23-25፥ 35።

መልስ።

ሙሴ 40 ዓመት በሆነው ጊዜ በሕዝቡቹ ለመታወቅ ጉጉት ነበረው። ይህም ማለት እርሱ እራሱ እስራኤልን ነፃ እንዲያወጣ እግዚአብሔር እንደመረጠው አውቆአል ማለት ነው። እናቱ ባሳደገችው ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳንና ነፃ እንደሚያወጣቸው ሳትነግረው እንዳልቀረች አያጠራጥርም (ዘጸግም 2፡ 1-10)። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት የወሰደው እስራኤል ነፃ ለማውጣት እንዲችል ትምህርት ሊያስተምረው እንደሆነ ምናልባት ተገንዝቦ ይሆናል።

ሙሴ እግዚአብሔር እንዲመራው በትዕግሥት አልጠበቀም። እርሱም እስራኤልን በራሱ ጥበብና ችሎታ ነፃ ለማውጣት ፈለገ። ስለዚህ ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ የሚያደርገው በእርሱ በኩል እንደሆነ እንዲያውቁ አንድ ግብፃዊና አንድ እስራኤላዊ ሲጣሉ ለእስራኤላዊው ረድቶ ግብፃዊውን ገደለው። ውጤቱም ሕይወቱን ለማዳን ሙሴ እንዲሸሽ አድርጎታል (ዘጸአት 2፡11-25)።

5. ሀ. ከሥላሴዎች ማንኛው ነው ሙሴን በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ያናገረው?

መልስ።

እግዚአብሔር ወልድ (ክርስቶስ) ሙሴ ሊያደርገው የሚገባውን አስታወቀው። እርሱም የእስራኤል ንጉሥ ስለሆነ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእርሱ በኩል ብቻ የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎችን ይገናኝ ነበር። በዘፍጥረት ውስጥ በ4ኛውና በ84ኛው ሐ ላይና በመግቢያው ላይ ብትመለከት በሚገባ ተብራርቶ ተገልጾአል።

5. ለ. ለምንድነው እኔ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ ያለው? ዘጻግም 3፡6፥ 15-17።

መልስ።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ምድረ ከነዓንን ለዘራቸው ለመስጠት ተስፋ ገብቶላቸው ነበር። ስለዚህ ሙሴን ይህንን ተስፋ ሊያስታውሰው የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ ብሎ እራሱን ገለጸለት። እግዚአብሔርም ሙሴን መሣሪያ በማድረግ የገባውን ቃል ኪዳን በእርሱ በኩል ሊፈጽም ሙሴን እንደመረጠው ነገረው። ሙሴም በዚህን ጊዜ ከግብፅ ሸሽቶ ከወጣ ወዲህ በምድረ በዳ 40 ዓመት ሆኖት ነበር። ያውም አሁን በጠቅላላው የ80 ዓመት ዕድሜ ሰው ሆኖአል።

## ምዕራፍ 6

6. በዘጸአት 6፡3-8 ያለውን ክፍል ከዘፍጥረት 12፡1፤ 22፡14-16፤ 24፡27 ና 42፤ 26፡24 ና 25፡28፥ 28፤ 13፡16፥ 20፥ 21 ባገኘኸው ጥናት ተመርኩዘህ አብራራው።

መልስ።

እግዚአብሔር ሙሴን ለአብርሃምና ለይስሐቅ እንዲሁም ለያዕቆብ «ኤልሻዳይ» በቂው አምላክ ሆኖ እንደታወቃቸው ነገረው (ዘጸአት 6፡3)። ነገር ግን ለእነርሱ «ያለና የነበረ የማይለወጥም እግዚአብሔር (ያህዌህ) እንደ መሆኑ አልታወቃቸውም ነበር።»

ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ እንደ መገለጹ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ማድረግ እንደሚችል ሆኖ ነው። ዓለምን የፈጠረ እርሱ ነው። ከዋክብቶችንም ሆነ ምድርን ይገዛል። የራሱ የሆኑትን ሁሉ የሚጠብቅ እርሱ ነው። ጠላቶቹንም ይቀጣል። እርሱንም ማንም ሊቋቋመው ስለማይችል የእርሱ የሆኑ ሁሉ ይደገፉበታል። እርሱም ለሚታመኑት ሁሉ «በቂውና ሁሉን የሚችል አምላክ ነው።»

በዘፍጥረት 12:1-3 እንደምናነበው እግዚአብሔር በተአምር አብርሃም የሚኖርበትን ምድር ከሰጠው በኋላ ትልቅ ሕዝብ በማድረግ የዓለምን ሕዝብ ሁሉ በዘሩ ይባርካል (በዘፍጥረት 22:14-16)። እግዚአብሔር ለሰው ደኅንነት የሚሆነውን መሥዋዕት አቅርቦአል (በዘፍጥረት 24:27፥ 42)። እግዚአብሔር የአብርሃምን ባሪያ በተአምር መርቶ ለይስሐቅ ሚስት እንዲያመጣለት አድርጎአል (በዘፍጥረት 26:24፥ 25፥ 28)። እግዚአብሔር ይስሐቅን የሚባርከው የሚጠብቀውና መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ የሚሰጠው አምላክ መሆኑን ያስረዳል (ዘፍጥረት 28:13፥ 15፥ 16፥ 20፥ 21)። እግዚአብሔር ለያዕቆብ መልካሙን ሁሉ በመስጠት እየባረከ ሊጠብቀው ችሎአል። እርሱም በቂውና «ሁሉን የሚችል አምላክ» ነው።

በዘጸአት 6:3 እግዚአብሔር በተለያዩ ስሞች መታወቅ ፈለገ። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ሊያወጣቸው ስላሰበ ለእርሱ መንፈሳዊ ምስክሮች አድርጎ ሊያቆማቸው ስለወደደ እግዚአብሔርን መከተልና መታዘዝን መማርና ዓላማውንም ማሟላት ይኖርባቸዋል። እነርሱም ፈቃዱን ተቀብለው እግዚአብሔር ሲጠቀምባቸውና ዓላማውን በእነርሱ በኩል ሲያከናውን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የሚገዛቸውና የሚታዘዙት ሕዝቦቹ እንደሆኑና አምላካቸው እንደሆነ ሊያሳውቃቸው ይወዳል።

በዕብራይስጥ ቋንቋ እግዚአብሔር ያህዌ በመባል ይጠራል። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን በዘፍጥረት 22:14 ላይ (ያህዌ) ተብሎ ተጽፎአል። ይህም ቃል ጌታ ማለት ሲሆን ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ልንጠቀምበት አይገባም። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን ሁለቱም ማለት እግዚአብሔር የሚለውና (ያህዌ) የሚለው ቃል ሁለቱም እግዚአብሔር በሚለው ስም ተጽፈዋል። በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ዓለምን የፈጠሩት (ሥላሴዎች) እግዚአብሔር ተብለው በዚህ ስም ተጠቃለዋል። እግዚአብሔር አብ ማንኛውንም ነገር በሠራው በልጁ በኩል ዓለምንና በዓለም ያለውን ነገር ሁሉ ፈጥሮአል (ኤፌሶን 3:9 ዮሐንስ 1:3፤ 10:14፤ ቆላስይስ 1:6፤ 1ኛ ቆሮ. 8:6፤ ዕብ. ምዕ. 1 ና 2)። በኋላም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴን በማናገር እስራኤሎችን ለማሰልጠን ተባበራቸው። እርሱም ጌታቸውና ንጉሣቸው ማን እንደሆነ ያውቁ ዘንድ እራሱን በተለያዩ ስሞች አስታወቃቸው። ከዚያም እኔ ጌታ (ያህዌ) ነኝ ብሎ እራሱን ጠራ። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ያህዋ የተባለው ስም እግዚአብሔር ተብሎ ተጽፎአል። ስለዚህ ስለ ሥላሴዎች ያህዌ ወይም ያህዋ ተብሎ ስለሚጠራው ስለ ልጁ እንደሆነ በሥራቸው ለይተን ማወቅ ይኖርብናል። ለሰዎች በሥጋ

የተገለጸው፥ ሰዎችን ያናገረው፥ እስራኤልን የመራው ልጁ ነው። እርሱም በዓይን ታይቶ ሲናገርም በጆሮ ተሰምቶአል (ዘጸአት 24፡10፥ 11፤ ኢሳይያስ 6፡5፤ ዘዳግም 5፡24፤ ዘጸአት 33፡11፤)። እግዚአብሔር አብን ማንም አይቶት አያውቅም (ዮሐንስ 1፡18፤ 3፡31፥ 32፤ 6፡46፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡16)። በዘጸአት 6፡3 እግዚአብሔር ወልድ እስራኤላውያን እንደ ጌታቸውና እንደ ንጉሣቸው አድርገው እንዲያውቁት ይፈልጋል። ስለዚህ አምላክ ሳለ እንደ ጌታ ያውቁት ዘንድ ያህዌ በመባል ጌታቸው መሆኑን ገለጸ። ይህ ክርስቶስ ያህዌ የተባለው (እግዚአብሔር) ነው። እርሱም በሚቀጥሉት ጥቅሶች ተገልጾአል። ኢሳ. 6፡3ን ከዮሐንስ 12፡40፥ 41፤ ኢሳ. 40፡3 ከማቴ. 3፡3፤ ዘኁልቁ 21፡6፥ 7 ከ1ኛ ቆሮ. 10፡9፤ መዝሙር 23(24)፡7-10 ከ1ኛ ቆሮ. 2፡8፤ ደግሞም ከያዕቆብ 2፡1 ጋር ኢሳ. 44፡6 ከራእይ 1፡17፥ 18፤ ምሳሌ 16፡4 ከቆላስይስ 1፡16፤ መዝ. 96(97)፡9 ከዮሐ. 3፡31፤ ኢዩኤል 2፡32ና ሮሜ 10፡13 አመዛዝነህ የእነዚህ መጻሕፍት ተከታይነት ተመልከት።

ተጨማሪ አሳብ።

በዘጸአት 3፡14 እግዚአብሔር ለሙሴ ስሙን ሲነግረው «እኔ ነኝ» አለው። ይህም ስም እግዚአብሔር ሁልጊዜ አንድና የማይለወጥ መሆኑን ያስረዳል። እርሱም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ያው ነው። እርሱ ሁልጊዜ እርሱ ነው። መጀመሪያና መጨረሻ የለውም። ያለ አንዳች ርዳታ በራሱ ኃይል ይኖራል። እርሱም የሰው ድጋፍ አያስፈልገውም (ኢሳ. 41፡4፤ 44፡6፤ 48፡12፤ ራእይ 22፡3)። እግዚአብሔር በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ በተገለጠ ጊዜ ቁጥቋጦው አይቃጠልም ነበር (ዘጸአት 3፡1ና 3)። ይህም ደግሞ በእስራኤል ይመስላል። እግዚአብሔር እስራኤልን ከመረጠ ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን ሊያጠፋቸው በጣም ይጥራል። ስለዚህ እስራኤል ብዙ ጊዜ እንደ እሳት በሆነ መከራ ውስጥ ይገባሉ። ነገር ግን ፈጽሞ አይጠፉም። ከአሁን ቀደም የተለያዩ ብዙ ሌሎች ሕዝቦች ጠፍተዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባው ቃል ኪዳን ስላለ ቃል ኪዳኑን ለመፈጸም ዕቅድ ስላለው ማንም ሊያጠፋቸው አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዊት ዙፋን ለሺህ ዓመታት ሲቀመጥ ከእርሱ ጋር ይነግሳሉ።

1. ግብፃውያን እስራኤላውያንን በግብፅ ሊያጠፉዋቸው ብዙ መከራ አሳይተዋቸዋል። ነገር ግን ከግብፅ ነፃ ሆነው ወጡ።

2. ወደ ባቢሎንም ተማርከው ሄደው ነበር፤ ነገር ግን በነፃነት ተመለሱ።

3. በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ አይሁዶች ሁሉ እንዲገደሉ ተፈርዶባቸው እንደ ነበረ እናነባለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አዳናቸው።

4. በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ስድስት ሚሊዮን አይሁዶች ተገደሉ። ይህም ማለት አይሁዶች ሁሉ እንዲጠፉ ነበር፤ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ የእስራኤል ነገዶች አሉ፥ በተለያዩም አገሮች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዳውያን ይኖራሉ።

5. በመጨረሻውም ዘመን የክርስቶስ ጠላት ማለት ክርስቶስን ተቃዋሚው እስራኤላውያንን ፈጽሞ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ይሞክራል። በዚህም እንደ እሳት በሚነድ መከራ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑ እስራኤላውያን ይገደላሉ። በዚህን ጊዜም ከስቃያቸው የተነሳ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ ሲጮኹ ክርስቶስ ከሰማይ ወርዶ ያድናቸዋል (ዘካርያስ 13፡8፥ 9፤ ሚልክያስ 3፡2-4፤ ኢሳ. 48፡9፥ 10፤ ራእይ 12፡1-5)።

## ምዕራፍ 7 ና 9

ዘጸአት ምዕ. 7፡1 እስከ ምዕ. 13-16 ያለውን ክፍል አንብብ።

7. ሀ. በሙሴና በፈርዖን መካከል ለመረታታት በተደረገው መከራከርና ትግል ከሙሴና ከፈርዖን በላይ ተዋጊዎቹ እነማን ነበሩ?

መልስ።

በዚህ ላይ እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክለኛዎቹ ተከራካሪዎች እግዚአብሔርና ሰይጣን ናቸው። እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለዓለም ምስክሮች እንዲሆኑ ወደ ከነዓን ሊመራቸው ይፈልጋል። የዓለም አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከእነርሱ ወገን በምድረ ከነዓን መወለድ አለበት። ስለዚህ እግዚአብሔር ፈርዖን እስራኤላውያን እንዲለቃቸው ለሙሴ ተአምራት የሚያደርግበትን ኃይል ሰጠው። ሰይጣንም የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማድረስ በተቻለው መጠን ባለው ችሎታ ሁሉ እስራኤላውያን በግብፅ ለማስቀረት ሞክሮ ነበር። ሰይጣንም በግብፅ ለሚገኙት ጠንቋዮችን አስማተኞች ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዳይለቃቸው የሚቻለውን ተአምራት እንዲያደርጉ ሰጥቶአቸው ነበር።

7. ለ. የግብፅ አስማተኞችና ጠንቋዮች እስራኤልን ለማሰናከል እንዲህ ያለውን ተአምራት ያደርጋሉ ተብሎ ይገመት ነበርን? መልስህን አብራርተህ ግለጽ።

መልስ።

ሰይጣን እስራኤልን ወደ ከነዓን እንዳይገቡ ለመከላከል ያደረገው ጥረት ምንም ጊዜ አድርጎት የማያውቀው ዓይነት ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል ኪዳን እንዳይፈጽም ለማድረግ ብዙ ጣረ። እስራኤል እግዚአብሔር እንደሚፈልግባቸው ለዓለም ምስክሮቹ እንዳይሆኑና ታላቅ ሕዝብም እንዳይሆኑ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም እንዳይመጣ ለማገድ ነበር። ስለዚህ ነው ሰይጣን ያለውን ኃይል ሁሉ ለግብፅ ጠንቋዮች ሰጥቶ ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዳይለቅ ልቡን ያደነደነው።

8. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ለማውጣት በግብፃውያን ላይ ስለመጣው ፍርድ ምን ምክንያት ነበር የሰጠው? ዘጸአት 7፡5፤ 9፡16፤ 15፡13-16።

መልስ።

እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ አስቃቂ ፍርድ ያመጣበት የመጀመሪያው ምክንያት ግብፃውያን እውነተኛው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እንዲያውቁ ነው። ኃጢአታቸውን ተናዘው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ይፈልጋል (ዘጸአት 7፡5)። ውጤቱም ብዙዎቹ ግብፃውያን ግብፅን ለቀው እግዚአብሔርን ወይም ክርስቶስን በምድረ በዳ እንዲከተሉት አድርጎአቸዋል (ዘጸአት 12፡38)።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በዓለም ያሉ ሕዝቦች ሁሉ እውነተኛውን እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ነው። ማንኛቸውም ሰዎች መዳን ከፈለጉ እግዚአብሔርን የት እንደሚያገኙት ማወቅ ይችላሉ (ዘጸአት 9፡16)።

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ማንኛውም ሕዝብ እስራኤልንን ለመቃወም እንዲፈራ ነው (ዘጸአት 15፡13-16)። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገላቸውን ታላቅ ነገር ሰምተው ጥቂት ከነዓናውያን ከጥፋት ድነዋል። ለምሳሌ ያህል ረዓብንና ቤተሰቦችዋን እንመልከት (ኢያሱ 2፡9-14፤ 6፡17፤ ዕብ. 11፡31)።

9. በግብፅ ላይ የደረሰውን መቅሰፍት ጥቅስ በመስጠት በቅደም ተከተል ግለጽ። ዘጸአት 9-12።

መልስ።

1. ዘጸአት 7፡19-25 ውኃው ወደ ደም ተለወጠ።
2. ዘጸአት 8፡1-15 እንቁራሪቶች።
3. ዘጸአት 8፡16-19 ቅማል።
4. ዘጸአት 8፡20-31 ዝንቦች።
5. ዘጸአት 9፡1-7 በእንስሳት ላይ የደረሰው በሽታ።
6. ዘጸአት 9፡8-21 በሰውና በእንስሳ ላይ እባጭ።
7. ዘጸአት 9፡22-26 በረዶና እሳት።
8. ዘጸአት 10፡1-20 አንበጣ።
9. ዘጸአት 10፡21-23 ጨለማ።
10. ዘጸአት 11፡4-10፤ 12፡29፥ 30 የበኩር ልጆች መሞት።

10. ሀ. ይህ መቅሰፍት በግብፃውያን ላይ ምን ችግር አመጣባቸው?

ለ. በፈርዖን በራሱ ላይስ? ዘጸአት 9፡27፤ 10፡7-16፤ 12፡33-38።

መልስ።

1. የዚህ የመቅሰፍት ችግር በግብፃውያን ላይ የደረሰው ግብፃውያን ኃጢአተኛ መሆናቸውን እንዲረዱ ወይም እንዲገነዘቡ ነበር።

2. እውነተኛው አምላክ ማን እንደሆነ እንዲማሩ ነው። «ፈርዖንም በዚህ ጊዜ በደልኩ፤ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፥ እኔና ሕዝቤም ኃጢአተኞች ነን አለ» (ዘጸአት 9፡27፤ 10፡26፥ 27)። ንስሐ የገባውም ከልቡ አልነበረም። ነገር ግን ከፍርድ ለማምለጥ ብቻ ስለፈለገ ነው። ዛሬም ብዙ ሰዎች ከሲኦል ፍርድ ለማምለጥ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ከኃጢአታቸው ለመዳን አይፈልጉም። ንስሐቸውም ከልብ ስላይደለ ይጠፋሉ።

3. ግብፃውያን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ፈቃደኞች እንዲሆኑ አድርጓአቸዋል (ዘጸአት 10፡7፤ 12፡33)።

4. ብዙ ግብፃውያን ከእስራኤላውያን ጋር ምድረ ግብፅን ለቀው ወጥተዋል። ከመቅሰፍቱ የተነሳ ብዙ ግብፃውያን ወደ ምድረ በዳ በመጓዝ የእግዚአብሔር ሰዎች ሆነው ተቆጥረዋል (ዘጸአት 12፡38)።

11. እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ እንዴትና ለምን አደነደነ? ዘጸአት 3፡19፤ 4፡21፤ 5፡2፤ 7፡2፥ 3፥ 22፤ 8፡21፤ 9፡7፥ 12፥ 24፤ 10፡1፥ 2፥ 16፥ 17፥ 26፥ 27፤ 11፡10፤ 14፡8።

መልስ።

ከመጀመሪያው ፈርዖን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቢመርጥ ኖሮ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበትን መንገድ በሙሉ በሰጠው ነበር። ነገር ግን ፈርዖን በዚህ ፋንታ በእንቢተኛነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማድረግ ልቡን ዘጋ።

ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ እግዚአብሔር ፈቃደኛ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)። እርሱን ለመገናኘት ለሚመጡት ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት ስለሚሰጣቸው የመዳን ዕድል ይገጥማቸዋል። ፈርዖንም ፈቃደኛ ቢሆን ኖሮ ይድን ነበር። በተመለከተው ኃይልና ተአምራት እንዲሁም በሙሴ ምስክርነት እውነተኛውን እግዚአብሔርን አውቆ ይድን ነበር። እርሱ እራሱ እንደመሰከረው ኃጢአተኛ መሆኑን ያውቅ ነበር (ዘጸአት 9፡27፤ 10፡16)። ፈርዖን እራሱ ከመጀመሪያው ልቡን በእግዚአብሔር ላይ አደንድኖ ነበር፥ ስለዚህ ፈርዖን ልቡን እስከመጨረሻ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ስለዘጋ የአምላኩን ደኅንነት አጣ። በዚህም እግዚአብሔር የዘመኑን ሰው ለማስጠንቀቅ ተጠቀመበት። እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ የባሰ አደነደነው፤ ምክንያቱም ሌሎች ሰዎች በእርሱ ላይ በደረሰው ነገር እውነተኛውን እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ነው።

1. የእስራኤል ትውልዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡና እንዲያውቁት እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አደነደነው (ዘጸአት 10፡1፥ 2)።

2. እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ያደነደነው ግብፃውያን ሁሉ ወደ እውነተኛው እግዚአብሔር እንዲመለሱ ነው (ዘጸአት 14፡4)።

3. እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ያደነደነው የዓለም ሕዝቦች ሁሉ እውነተኛውን እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ነው (ኢያሱ 2፡9-11፤ 4፡23፥ 24፤ ዘዳግም 2፡25፤ ኢያሱ 4፡24)። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ የእግዚአብሔር ክንድ ታላቅ እንደሆነ ያውቁ ዘንድ እግዚአብሔር ፈርዖን ለዘላለም እንዲጠፋ አልፈለገም። ነገር ግን ፈርዖን እግዚአብሔርን መቃረን መረጠ። እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያውቃል። ስለዚህ እግዚአብሔር የዓለም ሰዎች ይህንን አይተው በእርሱ አምነው እንዲድኑ ፈርዖን የግብፅ ንጉሥ ካደረገው በኋላ ይህንን ሁሉ ድንቅና ተአምር አደረገ።

12. የፋሲካን ሥርዓት አብራራ ዘጸአት 12፡3-28።

መልስ።

1. እስራኤሎች የመጀመሪያው ወር በገባ በአሥረኛው ቀን የበግ ወይም የፍየል ጠቦት ከመንጋው መኃል መርጠው ለብቻው ይለዩታል (ዘጸአት 12፡2፥ 3)።

2. ጠቦቱም ነውር የሌለበት መሆን አለበት (ዘጸአት 12፡5)።

3. ጠቦቱም በመጀመሪያው ወር አሥራ አራት ቀን ድረስ ይጠበቅ ነበር (ዘጸአት። 12፡6)።

4. እርሾውን ሁሉ ከቤታቸው ማውጣት አለባቸው። እርሾ ያለበት ምግብ ቢበሉ የሞት ፍርድ ይሆንባቸዋል። ሰባት ቀን ሙሉ እርሾ የሌለበት ምግብ መብላት አለባቸው (ዘጸአት 12፡15፥ 19፥ 20)።

5. እስራኤል የሆኑ ሁሉ በአንድነት በሌሊት ጠቦት ያርዱ ነበር (ዘጸአት 12፡6)።

6. እስራኤላውያን የጠቦቱን ደም በመዝጊያው ጉበን ላይና በሁለቱ መቃን ላይ መርጨት ነበረባቸው (ዘጸአት 12፡7፥ 22)። ያም ደም ከሞት ፍርድ ያድናቸው ነበር። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም ከዘለዓለም ሞት ያድናል (1ኛ ዮሐ. 1፡7፤ ማቴ. 26፡28፤ ሮሜ 5፡9፤ ራእይ 1፡5፤ 7፡14)።

7. የጠቦቱንም ሥጋ መዝጊያው በደም በተረጨው ቤት ውስጥ ሆነው መብላት አለባቸው (ዘጸአት 12፡7)።

8. ሥጋውንም በዚያው ሌሊት ቅቅሉን ወይም ጥሬውን ሳይሆን ጥብሱን መብላት አለባቸው። (ዘጸአት 12፡8፥ 9)።

9. ሥጋውንም ከመራራ ቅጠል ጋር መብላት አለባቸው (ዘጸአት 12፡8)።

10. ቢቻላቸው በዚያ ሌሊት ምንም ሳያስቀሩ መብላት አለባቸው፤ ከተረፋቸው ግን የተረፋቸውን ሁሉ በእሳት ያቃጥሉታል (ዘጸአት 12፡10)።

11. የጠቦቱን አጥንት መስበር የለባቸውም (ዘጸአት 12፡46)።

12. ወገባቸውን ታጥቀው ጫማቸውን ተጫምተው በትራቸውን እንደያዙ መመገብ አለባቸው። በፍጥነትም መብላት አለባቸው (ዘጸአት 12፡11)።

13. እግዚአብሔርም የጠቦት ደም በመዝጊያቸው መቃን ያልረጩትን የግብፃውያንን የበኩር ልጆች ሊገድል በዚያች ሌሊት የሞት መልአክ ተላከ (ዘጸአት 12፡12፥ 13)።

13. የክርስቶስ መሥዋዕት ከፋሲካ ጋር የሚመሳሰልበት በምንድን ነው? በሰፊው አብራራ። 1ኛ ቆሮ. 5፡6፥ 7፤ ማቴ. 26፡17፥ 18፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23-29፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፥ 19።

መልስ።

በ1ኛ ቆሮ. 5፡6፥ 7 ክርስቶስ ፋሲካችን ተባለ፤ በ1ኛ ጴጥ. 1፡18፥ 19 ደግሞ የእግዚአብሔር በግ ነው። እንደ እነዚህ ቁጥሮች ፋሲካው የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ያሳያሉ።

1. ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ለዓለም ኃጢአት እንዲሞት ተመረጠ (ዮሐ. 1፡29-36፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡19፤ ራእይ 13፡8፤ 22፡1-3፤ ራእይ 5፡6፥ 12፤ ኢሳይያስ 53፡7)።

2. ያ በግ በመጀመሪያው ወር በ10ኛው ቀን ለመሥዋዕትነት እንደተለየ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚያው ቀን ለመሥዋዕትነት ተለይቶ ለመቃብሩ ሽቶ ተቀባ (ማቴ. 26፡12፤ ዘጸአት 12፡3)።

3. ጠቦቱ ነውር የሌለበት መሆን አለበት (ዘጸአት 12፡5)። የእግዚአብሔር በግ የሆነው ክርስቶስም ደግሞ ምንም ኃጢአት አልነበረበትም። እርሱም በሰው አምሳል የተገለጸ አምላክ ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

4. ጠቦቱም የመጀመሪያው ወር በገባ ከ10ኛው ቀን እስከ 14ኛው ቀን ተጠብቆ በ14ኛው ቀን ይታረድ ነበር (ዘጸአት 12፡6)። ኢየሱስ ክርስቶስም በመጀመሪያው ወር በ10ኛው ቀን ለመቃብሩ የሚሆነውን ሽቱ ተቀብቶ ለሞት በመለየት የመጀመሪያው ወር በገባ በ14ኛው ቀን ተሰቀለ (ማቴ. 26፡6-13)።

5. ማንኛውም እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ ጠቦት ያርድ ነበር (ዘጸአት 12፡6)። እስራኤላውያን ሁሉ በአንድነት ከከተማው ክርስቶስን እየተከተሉ ስቀለው ስቀለው በማለት ለሞት አሳልፈው ሰጡት (ማቴ. 27፡20-23፤ ዮሐንስ 19፡6)።

6. እስራኤላውያን የጠቦቱን ደም በመዝጊያው ላይና ከመዝጊያው በላይ በመቃኑ ላይ ይረጩ ነበር (ዘጸአት 12፡7-22)። ደሙም ከሞት ፍርድ ያድናቸዋል። እንደዚሁም ሁሉ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከዘለዓለም ሞት ያድናል (1ኛ ዮሐ. 1፡7፤ ማቴ. 26፡28፤ ሮሜ 5፡9፤ ራእይ 1፡5፤ 7፡14)።

7. በመዝጊያው ላይ የተቀባው ደም መቅሰፍቱን እንዲከላከልላቸው የጠቦቱን ሥጋ በቤት ውስጥ ሆነው መብላት ነበረባቸው (ዘጸአት 12፡7)። እኛም ደግሞ ከዘላለም ፍርዱ ለማምለጥ እራሳችን ከክርስቶስ ደም ሥር መከለል እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል። ያለበለዚያ ግን የእግዚአብሔር ፍርድ በላያችን ላይ ይወርድብናል። በክርስቶስ ሞት ከሆነው ደኅንነት በቀር ሌላ ምንም ከፍርድ የምናመልጥበት መንገድ የለንም። እኛ ነፃ እንድንወጣ እርሱ ለእኛ ምትክ ተተክቶ ፍርዱን ተቀብሎልናል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡24፤ ዮሐንስ 6፡22-59)።

8. እስራኤላውያኖች በእሳት የተጠበሰውን ሥጋ መብላት ነበረባቸውን (ዘጸአት 12፡8 ና 9)። እሳትም የፍርድ ምሳሌ ነው። በእኛ ኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር የእሳት ፍርድ በክርስቶስ ላይ ወረደ (ኢሳ. 53፡5፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡24)።

9. ጠቦቱንም ከመራራ ቅጠል ጋር መብላት ነበረባቸው (ዘጸአት 12፡8)። እርሱ ቅዱስ ሆኖ ምንም ስሕተት ሳይኖርበት ስለእኛ ኃጢአት መሞቱ ለክርስቶስ መራራ ፍርድ ነው። (አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?) አንድ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ተናዞ ከኃጢአቱ ሲመለስ ከክርስቶስ ጋር ይሞታል። ይኸም ደግሞ ለሥጋ መራራ ነው (ሮሜ 8፡13)። የዘለዓለምን ሕይወት ለማግኘት ለኃጢአት መሞት አለብን። ከዚያም መስቀሉን ተሸክመን የዓለምን ስድብ መቀበል ይኖርብናል (ዕብ. 13፡12፥ 13)።

10. እስከ ጠዋትም ከጠቦቱ ሥጋ ምንም መቅረት የለበትም። የተረፈም ካለ በእሳት መቃጠል አለበት (ዘጸአት 12፡10)። እስራኤሎች የጠቦቱን ሥጋ ከበሉ በኋላ ለመንገዳቸው ብርታትን ተቀበሉ። እንደዚሁም ደግሞ ከበጉ ደም በታች ያሉት ብቻ ናቸው ብርታትን የሚቀበሉት። ከደሙ በታች ላልሆኑ ግብፃውያን ከጠቦቱ ሥጋ ለመብላት አይፈቀድላቸውም። በክርስቶስ ደም የዳኑ አማኞች ብቻ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከክርስቶስ ጋር ለመራመድ ከክርስቶስ ብርታትን ይቀበላሉ፥ ግንም በክርስቶስ ደም ያልዳነ ሁሉ ከክርስቶስ መብል ሊቀበል አይችልም (ፊልጵ. 4፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡10)።

11. ከጠቦቱ አጥንት እንዳይሰብሩ ተከልክለው ነበር (ዘጸአት 12፡46)። ክርስቶስ በተሰቀለበት ቀን ከእርሱ ጋር ተሰቅለው የነበሩት ሁለት ሰዎች ቶሎ እንዲሞቱ አጥንቶቻቸውን ሰበሩዋቸው። ወታደሮቹ የክርስቶስን አጥንት ደግሞ ለመስበር ወደ እርሱ ሲጠጉ እርሱ ከዚያ በፊት ቶሎ ሞቶ ስለነበር አጥንቱን አልሰበሩትም። ስለዚህ ክርስቶስን መትተው አልገደሉትም። ነገር ግን እራሱ

በፈቃዱ ሕይወቱን ሰጥቶ ሞተ (ዮሐ. 19፡31-37፤ 19፡30፤ 10፡11፤ 15፡17ና 18)። «እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሳት ሥልጣን አለኝ . . .»

12. እስራኤላውያን ወገባቸውን ታጥቀው ጫማቸውን ተጫምተው ምርኩዛቸውን ይዘው ከግብፅ ተጉዘው ለመውጣት ተዘጋጅተው ነበር (ዘጸአት 12፡11)። ማንኛውም ክርስቶስን በእውነት ከልቡ የተቀበለ አማኝ ሁሉ እንዲሁ ከዓለም ለመለየት ዝግጁ ይሆናል። እርሱም በዚህ ምድር እንግዳና መፃተኛ ሆኖ በመኖር መንግሥተ ሰማይ እስኪገባ ድረስ ክርስቶስን ይከተላል። ይኸውም እስራኤላውያን ክርስቶስን ተከትለው ምድረ ከነዓን እስከገቡ ድረስ እንደተከተሉት ማለት ነው።

13. እነርሱም በግብፅ ላይ ከሚመጣው ፍርድ ለማምለጥ በፍጥነት መብላት ነበረባቸው (ዘጸአት 12፡11)። ግብፅም በዚህ ዓለም ትመሰላለች። ዓለምም ወደ ፊት ተፈርዶባት ትቀጣለች። ስለዚህ ማንኛውም በዓለም ላይ ሊመጣ ካለው ፍርድ ለመዳን በፍጥነት ከዚህ ዓለም እርኩሰት ተለይቶ ለደኅንነቱ ወደ ክርስቶስ መሸሽ አለበት (ማቴ. 3፡7)።

14. ዘጸአት 12፡12፥ 13 ግብፃውያን ከደሙ ሥር እራሳቸውን ባለመሸሸጋቸው በሞት መልአክ ተፈረዱ። እንደዚሁም ዛሬ ሰዎች እራሳቸውን ከክርስቶስ ደም በታች አድርገው ከዚህ ዓለም ኃጢአት ባይሸሹ በመጨረሻው ዘመን በእግዚአብሔር ፍርድ ከሚጠፋው ዓለም ጋር አብረው ይጠፋሉ (ዮሐንስ 3፡18)።

## ክርስቶስን ፋሲካችን አድርገን እንዴት እንደምንቀበል። 1ኛ ቆሮ. 5፡6-8።

ፋሲካ ምሳሌ በመሆን የደኅንነትን መንገድ ያሳየናል።

1. እስራኤላውያን አስቀድመው እርሾውን ሁሉ ከቤታቸው ማስወጣት አለባቸው። በቤታቸውም ውስጥ ጥቂት እርሾ እንኳን እንዳይገኝ፥ ቤታቸውን በማጽዳት እርሾውን ሁሉ ማስወገድ አለባቸው (ዘጸአት 12፡15)። «እርሾውን ሁሉ ከቤትህ ማስወገድ አለብህ» (ቁጥር 19)። «ሰባት ቀን በቤታችሁ እርሾ አይገኝ» (13፡7)። «ሰባት ቀንም ሙሉ ቂጣ እንጀራ ትበላለህ፥ በአንተም ዘንድ እርሾ ያለበት እንጀራ አይታይ። በድንበርህም ሁሉ እርሾ አይታይ።» እስራኤሎችም በፍጥነት በቤት ውስጥ ያለውን እርሾ አስወገዱ፥ ምክንያቱም እርሾ በቤቱ የተገኘና የበላ ሰው ሞት ይፈረድበት ነበር (ዘጸአት 12፡15)።

እርሾ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኃጢአት ይመሰላል። አሁንም ቢሆን ማንኛውም ሰው ከዘለዓለም ፍርድ ለመዳን ቢፈልግ ከሚያውቀው ኃጢአቱ በሙላ መለየት አለበት። ልቡንም መመርመርና ከኃጢአትም ለመዳን መወሰን አለበት። ይህም ንስሐ መግባት ይባላል። ኃጢአቱን በልቡ ሰውሮ ከሰወረው ኃጢአቱ መላቀቅ ባይሻ የሞት ፍርድ በራሱ ላይ አለበት። ከእስራኤላውያን መኃል አንዱ

በፋሲካው ምሽት እርሾ ወይም እርሾ የተቀላቀለው እንጀራ በቤቱ ቢያኖር ወይም ቢበላ ኖሮ የጠቦቱ ደም ከእግዚአብሔር መቅሰፍት አይስውረውም ነበር። እንደዚሁም ደግሞ ማንኛውም ሰው ሊለየው የማይወደውን ኃጢአት በልቡ ሰውሮ ከኃጢአቱ ለመላቀቅ ባይወድ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአቱ አያድነውም። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው «ሕዝቦቹን ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው ነው።» (ማቴ. 1፡21)። ማንም ከኃጢአቱ ለመዳን የማይወድ ሰው ሁሉ ስለ ኃጢአቱም ከሚመጣበት ፍርድ ለመዳን አይችልም። «ይህም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ሊል ይችላል!» ሆኖም እራሱን ያታልላል (ማቴ. 7፡21-23)። ማንም እርሾ ያለበትን ምግብ የበላ ሁሉ ከጠቦቱ ሥጋ አይበላም ነበር።

ይህን ቢያደርግ የሞት ፍርድ ይፈረድበት ነበር! እንደዚሁም ማንም በፈቃዱ ኃጢአቱን በልቡ ቢሰውር ክርስቶስ ያድነኛል ብሎ ተስፋ አያድርግ። ብዙ ሰባኪዎች ሰዎች ኃጢአታቸውን ተናዘው እንዲያምኑ ባለማድረጋቸው ሰውን ያታልላሉ። እምነትን ብቻ ይሰብካሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን «በኃጢአታችሁ ተናዛችሁ እመኑ» ይላል።

2. እስራኤላውያን በየበሩ መቃንና ከበሩ በላይ ያለውን መቃን ደም መርጨት ነበረባቸው። ከዚያም በኋላ የፋሲካውን ጠቦት በቤት ውስጥ ሆነው ይበላሉ። እኛም ደግሞ አሁን የፋሲካችን በግ በሆነው በክርስቶስ ደም ሥር እራሳችንን እኑረናል። ምክንያቱም ኃጢአታችንን ስለተናዘዝን ኃጢአታችን በክርስቶስ ላይ ሆኖ በመስቀል ላይ እንደተፈረደበት እናምናለን። ደሙም የፈሰሰው ስለ ኃጢአታችን እንደሆነ እናምናለን። እኛም በእምነት ድነናል። በኃጢአታችን ፍርድ በክርስቶስ ላይ ተፈርዶአል።

3. እስራኤላውያን ከጠቦቱ ሥጋ የበሉት (ንጉሣቸውን ክርስቶስን) ተከትለው ከግብፅ ሲወጡና በምድረ በዳ ሲጓዙ ኃይል ይሆንላቸው ዘንድ ነው። እኛም ደግሞ የክርስቶስን ሞት በእምነት ስንቀበል መንፈሳዊ ብርታት ከክርስቶስ ይሰጠንና ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለን ከዓለም እንወጣለን፥ ከዓለም ነገር ሁሉ እንለያለን። እኛም ከዚህ ሕይወታችን በረሐ ተጉዘን ምድረ ከነዓን እንገባለን።

4. እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ፍርድ በግብፅ ላይ እንዳንዣበበ ስላወቁ በፍጥነት ግብፅን ለቀው ወጡ! አሁንም ማንኛውም ሰው መዳን ቢፈልግ የእግዚአብሔር ፍርድ ሳይወርድበት አስቀድሞ በፍጥነት ኃጢአቱን ተናዞ በክርስቶስ አምኖ መዳን አለበት። እራሱንም ለማዳን ከዓለምና ከኃጢአቱ ጋር ያለውን አንድነት ማቋረጥ ይኖርበታል። በልቡ ጥቂት በዓለም ቀዛ ከተደሰትኩ በኋላ ኃጢአቴን ትቼ ወደ ጌታ እመለሳለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው ለግብር-ይውጣ ክርስቲያን መስሎ ከኖረ በኋላ ተመልሶ ወደ ጥፋቱ ያዘግማል።

5. የተገረዙት ብቻ ነበሩ ከፋሲካው ጠቦት መብላት የሚችሉት (ዘጸአት 12፡48)። ግዝረት እስራኤላውያን ምድራዊ ወገኖቹ እንደሆኑ ምልክት ይሆንላቸው ዘንድ የተሰጣቸው ነው። ይህም ምልክት የተሰጣቸው እራሳቸውን

ከዓለም ርኩሰትና ጣዖት ገልለው በኃብቻና እግዚአብሔርን በማያስከብር ነገር ከዓለም ጋር እንዳይጠላለፉ ነው። እኛም ደግሞ ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕዝቦቹ ነን። የእኛም ግዝረት የልብ መገረዝ ነው (ሮሜ 2፡29፤ ቆላስይስ 2፡11)። እኛም ከዓለም የተለየነው ከልብና ከሥጋ ከሆነ ኃጢአት ነው። እኛም ከልብ ከዓለምና ከሥጋ ጋር ያለንን ተባብሮ ካላቋረጥን የፋሲካችን በግ ከሆነው ከክርስቶስ መብላት አንችልም። እስራኤሎች የሥጋ ግዝረት ሳይኖራቸው ከጠቦቱ መብላት እንደማይችሉ ሁሉ እኛም ደግሞ የልብ መገረዝ ሳይኖረን በእምነት ፋሲካችን ከሆነው ከክርስቶስ መብላት አንችልም። እኛ እንደምናምነው ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ማለት ከዓለም ከሥጋ ፈቃድና ከኃጢአት ሁሉ መለየት ማለት ነው። አፍአዊ ክርስቲያን (አማኝ) ከክርስቶስ መብላት አይችልም፥ ሰው ሁሉ ክርስቶስን መቀበል ይችላል፥ ነገር ግን በኃጢአቱ ተናዞ ከኃጢአቱ ካልተለየ መዳን አይችልም። ሁሉም ከፋሲካው ጠቦት መብላት ይችላሉ፥ ነገር ግን አስቀድመው መገረዝ አለባቸው።

14. የፋሲካን በዓል በቀጥታ ከእስራኤል ጋር ያቋቋመው ከሥላሴዎች ማንኛው ነው?

መልስ።

ፋሲካን ያቋቋመው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በኋላም የሰው ልጅ ይህን የመሰለውን መሥዋዕት ማቅረብ ስላለበት ራሱ ከአብ ዘንድ መጥቶ በፈቃዱ ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ። ፋሲካም ለእስራኤላውያን የተሰጠው ክርስቶስ ሊያድናቸው ስለ ኃጢአታቸው እንደሚሞት በእምነት እንዲያዩ ነው (ገላትያ 3፡24)። በዘፍጥረት ለ84ኛው ሐ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ተመልከት።

15. እስራኤል ከእግዚአብሔር ወይም ከያህዌ ጋር እንዴት ወደአለ አዲስ ሕብረት ገቡ?

መልስ።

አሁን እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሰዎች ለመሆን በደም ተገዝተዋል።

1. ያህዌ (እግዚአብሔር) እስራኤላውያንን ከግብፅ እስራት ያስለቀቃቸው ክርስቶስ ነው።

2. እርሱም ወደ ምድረ ከነዓን የሚመራቸው መሪ ሆኖአቸዋል።

3. ከክፉ ነገር ሁሉ የሚከላከልላቸው ጠባቂአቸው ሆነላቸው።

4. እርሱም ሊታዘዙት የሚገባ በዓይን የማይታይ ንጉሣቸው ሆነ። ይህም አሁን ባሉት አማኞችና በክርስቶስ ይመሰላል። (ስለ ክርስቶስ ንጉሥነት የሚገልጸውን የዚህን መጽሐፍ መግቢያ ተመልከት።)

1. ክርስቶስ አማኞችን ሁሉ በደሙ ገዝቶአቸዋል (1ኛ ጴጥሮስ 1፡18፥ 19)። ከዘለዓለም ጥፋት አድኖአቸዋል። በዚህ በክፉ ዓለም ካለው የኃጢአት ኃይል አድኖአቸዋል።

2. ክርስቶስ ሕዝቦቹን ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም በፍጹም ደስታ ወደሚኖሩበት ስፍራ በዚህ ዓለም ውስጥ የሚመራቸው መሪ ነው።

3. አሁንም ክርስቶስ መንፈሳውያን ሕዝቦቹን የሚጠብቅ እረኛ ነው። እርሱም ሊያጠፉቸውና ሊያሳዝናቸው ከሚወደው ከሰይጣን ውጊያ ያድናቸዋል።

4. ክርስቶስ የማይታይ የአማኞች ሁሉ ጌታና ንጉሥ ነው። እርሱንም አማኞች ሁሉ ሊታዘዙት ይገባል።

16. ሀ. ለመታሰቢያ የሚደረገውን የፋሲካን እራት እንዲበሉ የተፈቀደላቸው እነማን ናቸው? ዘጸአት 12፡43-49።

መልስ።

ወንዶቻቸው የተገረዙ ቤተሰቦች ብቻ ከፋሲካው መብላት ይችላሉ። እነርሱም እስራኤላውያን ሆኑ ወይም እንግዶች ወይም ባሪያዎች ምንም ልዩነት የለውም። ደኅንነት ለሁሉ የተሰጠ ነው። አሁንም ማንም አይሁዳዊ ቢሆን ወይም ከአሕዛብ ወገን ወይም ባሪያ ቢሆን ነፃ ሕዝብ ኃጢአቱን ከልቡ ተናዞ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ቢቀበል ይድናል። ይህንን የሚያደርጉ ሁሉ የልብ ግዝረት አላቸው። እነርሱም ከሥጋና ከዓለም ከሆነው ነገር ሁሉ ተቋርጠዋል (ቆላስይስ 2፡11፤ ሮሜ 2፡29፤ 4፡1-4)። እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ምድራዊ ልጆች እንደመሆናቸው ሁሉ አማኞች ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆች ናቸው። ማንኛውም ከዘለዓለም ጥፋት ለማምለጥ የሚወዱ እስራኤላውያን ደግሞ የልብ ግዝረት ሊኖራቸው ይገባል። የእግዚአብሔር ምድራዊ ልጆች መሆናቸው ከዘለዓለም ጥፋት ሊያድናቸው አይችልም። የሥጋ ግዝረት የልብ ግዝረት ምሳሌ ነው።

16. ለ. ለምንድን ነው ሌሎች ሰዎች የዚህ በዓል ተካፋዮች የማይሆኑበት ምክንያት?

መልስ።

እነዚህ የተገረዙት ብቻ ናቸው ከዓለም እንደተለዩ ለማስታወቅ የግዝረት ምልክት የሚቀበሉት። ግዝረቱን የተቀበሉት ሰዎች ከማንኛውም ዘር ቢሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች ስለሆኑ ከፋሲካው ጠቦት የመመገብ መብት አላቸው። ሌሎቹ ግን የሚያመልኩት ሐሰተኛውን አምላክ ነው። በሌላ አንጻር ደግሞ እነዚህ ልባቸውን ተገርዘው ከዓለም ኃጢአት የተለዩ ብቻ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። እነርሱም ከክርስቶስ መብላት ይችላሉ። እነርሱም የዘለዓለም ሕይወትንና መንፈሳዊ ብርታትን በክርስቶስ ሞት ውስጥ ይቀበላሉ። ስለዚህ

የልብ ግዝረት የሌላቸው ሁሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ሊሆኑና የዘለዓለም ሕይወትን ሊቀበሉ አይችሉም። እነርሱም ሌላ አምላክ አላቸው፥ እርሱም ዓለምና ኃጢአት ነው።

17. ሀ. ምዕራፍ 13 ለምንድን ነው እግዚአብሔር ከሰውም ሆነ ከእንስሳ የመጀመሪያው እንዲሰጠው የፈለገው? ዘጸአት 13፡2፤ 12፡15፤ ዕብ. 12፡23፤ ገላትያ 4፡7፤ ሮሜ 8፡17፤ ያዕ. 1፡18።

መልስ።

የመጀመሪያው ልጅ ሁልጊዜ ወራሽ ነው። ግብፅ በዚህ ዓለም ትመሰላለች። ይህ ኃጢአትን የተሞላ ዓለም ከእግዚአብሔር የሚወርሰው ሞትን ነው። በዓለም የሚመሰለው የግብፅ የመጀመሪያ ወራሽ የሆነ ወንድ ልጅ ሁሉ ሞትን እንደወረሰ እንደዚሁም ዓለም ሞትን እንደሚወርስ መዘንጋት አያሻም።

ከእግዚአብሔር ሕዝቦች የተወለደ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። እነርሱም በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ተገዝተው የዘለዓለምን ሕይወት ከሚወርሱ ሰዎች ጋር ይመሰላሉ።

አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ልጆች ናቸው። እነርሱም የእግዚአብሔር ወራሾች በመሆን የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሳሉ (ዕብ. 12፡23፤ ገላ. 4፡7፤ ሮሜ 8፡17፤ ያዕቆብ 1፡18)።

17. ለ. እግዚአብሔር ማንኛውንም የመጀመሪያ ልጅ ለራሱ የመውሰድ መብት እንዳለው ለማሳየት ሰዎቹ ምን ማድረግ አለባቸው? ዘጸአት 13፡2፥ 12፥ 15፤ ዘኍልቁ 18፡14-17፤ ዘጸአት 34፡20፤ ሉቃስ 2፡22-24።

መልስ።

ማንኛውም ከሚበላ እንስሳ የተወለደ ሁሉ ለጌታ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል። ከማይበላው እንስሳ ማለት እንደ አህያ ካለ እንስሳ የተወለደው ግን በበግ ይለወጣል፥ ተለውጦም የመጣው በግ በምትክነት ይታረዳል። በአህያው ምትክ የሚታረድ በግ ባይገኝ አህያው ራሱ አንገቱ ተጠምዝዞ ይገደላል (ዘጸአት 13፡13)። እርሱም ከማይበሉት እንስሳ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። ነገር ግን ንጹሕ ባለመሆኑ በእግዚአብሔር ፊት አንገቱ ተጠምዝዞ በመገደል ይፈረዳል። ይህም ደግሞ አፍአዊ አማኝ ብቻ በሆኑት ሰዎች ይመሰላል። እርሱም የእግዚአብሔር እንደሆነ ተቆጥሮ ነበር፤ ነገር ግን ወደ ጥፋቱ ስለተመለሰ ንጹሕ ባለመሆኑ በእግዚአብሔር ፊት በሞት ይቀጣል።

ለቤተሰቡ የተወለደ ወንድ ልጅ (ዘጸአት 13፡15) ሁሉ በገንዘብ መገዛት አለበት (ዘኍልቁ 18፡16)። ኢየሱስ ለቤተሰቦቹ የመጀመሪያ ልጅ ነበር። ስለዚህ ቤተሰቦቹ ይህንኑ አድርገውለት ነበር (ሉቃስ 2፡22-24)።

እስራኤላውያንም ለልጆቻቸው እንደምስክርነት ይሆንላቸው ዘንድ ይህንን መጠበቅ ነበረባቸው። ልጆቻቸውም «ለምን ይህን ታደርጋላችሁ?» ብለው ሳይጠይቋቸው አልቀሩም (ዘጸአት 13፡14)። በዚህን ጊዜ አባት የሆነው ሰው የኃጢአት ዋጋ ሞት እንደሆነና ከኃጢአቱም የሚያድነው አዳኝ እንዳለው ለማስታወቅ ጥሩ አጋጣሚ ይሆንለታል። የደኅንነትን መንገድ ለልጆቹ ለማሳየት በጣም ይቀልለታል። ይህም የተደረገው በዘመን ሁሉ እስራኤል እግዚአብሔርም የነፃ ደኅንነቱን ለሁሉም እንደሰጠ ለማስታወቅ ነው።

ዘጸአት 13፡ 17፥ 18፥ 27 ያለውን ክፍል አንብብ።

18. እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ በምንና እንዴት ተመርተው ነው?

መልስ።

እግዚአብሔር (ክርስቶስ) እስራኤላውያንን ቀን በደመና አምድ ሌሊት በእሳት አምድ እያደረገ መንገዳቸውን በፊታቸው ያበራላቸው ነበር። እስራኤላውያን መንገዱን ማወቅ አላስፈለጋቸውም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በሚመራቸው መንገድ በታዛዥነት መከተል ብቻ ነበር የፈለጉት። እንደዚሁም ዛሬ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት ሁሉ በታዛዥነት የእግዚአብሔርን አመራር መከተል ብቻ አለባቸው።

እግዚአብሔርም ከአደጋ እየጠበቀ በጥንቃቄ ወደ ፍሬአማነት በመምራት በመጨረሻ ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። የእግዚአብሔር ልጆች በራሳቸው መንገድ በሚጓዙበት ጊዜ ብቻ ነው በሰይጣን ወጥመድ የሚወድቁት። እስራኤላውያን መንገዱን እንደማያውቁና ወይም ነገ የት እንደሚሄዱ እንዳልተገነዘቡ ሁሉ እኛም ደግሞ የወደፊቱን አናውቅም። መጪውን እግዚአብሔር ብቻ ስለሚያውቅ ከአደጋ እየጠበቀን ይመራናል (ዘጸአት 13፡21፥ 22)።

19. እስራኤላውያን ይህን በመሰለ መሪ በሚመሩበት ጊዜ መሪያቸው የሆነው እግዚአብሔር በመንገዳቸው ተአምራትን ያደርግ ይሆን ተብሎ ይጠበቅ ነበርን?

መልስ።

እግዚአብሔር አምላካቸው በክርስቶስ መሪያቸው ከሆነ የእስራኤልን የሕይወታቸውን አመራር አቅዶ የያዘው እርሱው ነው፤ ስለሆነም ሰይጣን ከማንኛውም ነገድ ይልቅ ሊያጠፋቸው የሚሻ ጠላት እንደመሆኑ ሁሉ እግዚአብሔር ደግሞ ከማንኛውም ነገር ይልቅ ረዳታቸው እንደሆነ እንረዳለን። በዚህ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል በሚደረገው ውጊያ እግዚአብሔር ለእስራኤሎች የሚያደርገውን ድንቅና ተአምራት ለማየት መጠበቅ ይኖርብናል።

እንዲሁም እግዚአብሔር ለአማኞችም ዛሬ ደግሞ ተአምራትን ያደርጋል። ስለዚህ ሰይጣን ዓለማዊውን ክርስቲያን ከሚያጠቃ ይልቅ ታዛዡን ክርስቲያን

በጣም ያጠቃዋል። ምክንያቱም ታዛዥ ክርስቲያን ከእርሱ ጋር በኃይል ስለሚዋጋ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ከማንም ይልቅ ለዚህ ለታዛዥ አማኝ ይከላከልለታል።

20. በቀይ ባሕር መሃል ስለማቋረጥ የሚናገረውን ክፍል አብራራ። ዘጸአት 13፡16-14፡31።

መልስ።

እግዚአብሔር፥ ክርስቶስ ቀጥታውን እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን አልመራቸውም፤ ምክንያቱም በዚያ የሚኖሩት አሞራውያን፥ ከነዓናውያን፥ ፍልስጥኤማውያን ተዋጊዎች ስለነበሩ ነው። እስራኤላውያን ግን ባርነትን እንጂ ጦርነትን አያውቁም ነበር። ክርስቶስንም የተከተሉት ለጥቂት ቀናት ብቻ ነበር። እነርሱም በእምነታቸው ገና ሕፃናት ስለሆኑ በእግዚአብሔር ኃይል ታምነው ጠላታቸውን ከመግጠም ይልቅ መሸሽን ይመርጡ ነበር (ዘጸአት 13፡16)።

እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን እምነት ሊያስተምራቸው በኤርትራ ባሕር አካባቢ ወደ ምሥራቅና ወደ ደቡብ መራቸው። እግዚአብሔርም የፈርዖን ልብ እንዲደነድንና እስራኤልን መልሶ ባሪያ የማድረግ አሳብ እንዲኖረውና እንዲከታተላቸው አደረገ። እግዚአብሔርም ይህን ያደረገው እስራኤላውያን በእግዚአብሔር መታመንን እንዲማሩና ሌሎችም አሕዛቦች እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር እንዳለ እንዲያውቁና እንዲፈሩት ለማድረግ ነው (ኢያሱ 2፡9፥ 11፤ ዘጸአት 14፡31)።

የግብፅ ወታደሮች ተከታትለው ቀይ ባሕር አጠገብ ደረሱባቸው። እስራኤሎችም ምንም የሚያመልጡበት መንገድ አልነበራቸውም። ከኋዋላቸው ግብፃውያን ከፊታቸው ደግሞ ቀይ ባሕር ተጋርጦባቸው ነበር። እነርሱም በወጥመድ ውስጥ ነበሩ። በዚያም ጊዜ ሊያደርጉት የሚችሉት አንድ ነገር ብቻ ነበር። ያውም ወደ ላይ አንጋጠው አምላካቸው የሚያደርገውን ተአምራት በጸሎት መንፈስ ሆነው መጠበቅ ነበር። በዚያች ሌሊት በሙሉ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ግብፃውያን ወደ እስራኤላውያን እንዳይቀርቡ በእሳት ዓምድ ውስጥ ሆኖ በእስራኤልና በግብፅ መካከል ነበር (ዘጸአት 14፡13-20)።

ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ እጆቹን በባሕሩ ላይ ዘረጋ ባሕሩም ለሁለት ተከፈለ (ዘጸአት 14፡21)። በግራና በቀኝም ባሕሩ እንደ ግድግዳ ሆኖ ቆመ። ከዚያም በኋላ እስራኤላውያን ልጆቻቸውንና ከብቶቻቸውን አስከትለው በዚያ ጭቃና ድጥ በተኛበት መሬት ላይ ተራምደው መሻገር አልቻሉም። ስለዚህ እግዚአብሔር ኃይለኛ የምሥራቅ ነፋስ አስነስቶ ጭቃውንና ድጡን ሌሊቱን ሙሉ እንዲያደርቅላቸው አደረገ (ዘጸአት 14፡22-29)። እግዚአብሔርም እንዲሁ ለሚወዳቸው ሁሉ ዘወትር መንገዳቸውን ያዘጋጃል።

እስራኤላውያንም ውኃው በግራና በቀኛቸው እንደ ግድግዳ ቆሞ በደረቅ መሬት ተሻገሩ። ግብፃውያንም ተከተሉዋቸው። እግዚአብሔር ግብፃውያን

በመኃሉ እንዲሰናከሉ ከፋኛ አወካቸው። ይሄኔም እስራኤላውያን ተሻግረው በባሕር ዳር እንደቆሙ ሙሴ እጁን በባሕሩ ላይ ሲዘረጋ ባሕሩ በፈርዖን ወታደሮች ሁሉ ላይ ተከደነባቸው (ዘጸአት 14፡23-29)። አሁንም ቢሆን በእግዚአብሔር ሰዎችና ሥራ ላይ እንቅፋት በሆኑት ላይ አሰቃቂ ፍርድ ይፈርድባቸዋል።

21. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚህ ምዕራፍ በስተቀር በሌላ ቦታ የዚህ የባሕር መከፈል በተፈጥሮ በየጊዜው የሚሆን ነገር ነው ወይስ እግዚአብሔር በተአምራት ያደረገው ነገር ነው? የሚከተለውን ተመልከት፤ ዘጸአት 14፡20፥ 31፤ 15፡3-10፤ ኢያሱ 2፡10፤ 4፡23፤ ነህምያ 9፡9-11፤ መዝሙር 105(106)፡9፥ 21፥ 22፤ 135(136)፡13-15፤ የሐዋርያት ሥራ 7፡36፤ ዕብራውያን 11፡29።

መልስ።

እንዳንድ ሰዎች እስራኤሎች ቀይ ባሕርን በተሻገሩበት ስፍራ ውኃው ጥልቅ ስላልሆነ ነፋስ ባሕሩን በቀላሉ የሚያስወግድበት ቦታ ስለሆነ ባሕሩን ያለምንም ችግር መሻገር ይቻላል ብለው ይከራከራሉ። ይህም በተፈጥሮ የሚደረግ ነገር ነው እንጂ ተአምራት አይደለም ይላሉ። ነገር ግን ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ጥቅሶች ሁሉ በነፋስ ሳይሆን በእግዚአብሔር ተአምራት የተደረጉ እንደነበር ይገልጻሉ።

1. እግዚአብሔር የላከው የምሥራቅን ነፋስ ነበር። የሰሜን ነፋስ ብቻ የኤርትራን ባሕር ማስወገድ ይችል ነበር፤ ምክንያቱም የኤርትራ ባሕር በቁመቱ በሰሜንና በደቡብ መካከል ስለተዘረጋ ነው። ውኃውም ከተከፈለ በኋላ የምሥራቅ ነፋስ በመንገዳቸው ላይ ያለውን ድጥና ጭቃ ያደርቀው ነበር (ዘጸአት 14፡21)።

2. በዘጸአት 14፡21፥ 22፥ 31 ላይ ውኃው በግራና በቀኛቸው እንደ ግድግዳ እንደቆመ እናነባለን፤ ውኃውን በስተቀኛቸው ያቆመው ነፋስ ቢሆን ኖሮ በስተግራቸው የውኃ ግድግዳ ባልነበረም ነበር። ከዚህም በስተቀር በነፋስ ግፊት ውኃ እንደ ግድግዳ መቆም አይችልም።

3. ውኃውንም ወደኋላ የገፋው የነፋሱ ኃይል ቢሆን ኖሮ እስራኤላውያኖችንም ወደኋላ በገፋቸው ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ የነፋሱን ግፊያ መቋቋም ባልቻሉም ነበር። ነፋሱ ግን እስራኤላውያን በጭቃ ላይ እንዳይሄዱ ምድሩን አደረቀላቸው።

## ከምዕራፍ 15 እስከ 17።

22. ከቀይ ባሕር አንስተው እስከ ሲና ተራራ ድረስ ሲጓዙ እግዚአብሔር ምን ሌላ መለኮታዊ ተአምራት አድርጎ እስራኤላውያንን እረዳ? ምዕራፍ 15-17።

በመኃሉ እንዲሰናከሉ ከፋኛ አወካቸው። ይሄኒም እስራኤላውያን ተሻግረው በባሕር ዳር እንደቆሙ ሙሴ እጁን በባሕሩ ላይ ሲዘረጋ ባሕሩ በፈርዖን ወታደሮች ሁሉ ላይ ተከደነባቸው (ዘጸአት 14፡23-29)። አሁንም ቢሆን በእግዚአብሔር ሰዎችና ሥራ ላይ እንቅፋት በሆኑት ላይ አሰቃቂ ፍርድ ይፈርድባቸዋል።

21. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚህ ምዕራፍ በስተቀር በሌላ ቦታ የዚህ የባሕር መከፈል በተፈጥሮ በየጊዜው የሚሆን ነገር ነው ወይስ እግዚአብሔር በተአምራት ያደረገው ነገር ነው? የሚከተለውን ተመልከት፤ ዘጸአት 14፡20፥ 31፤ 15፡3-10፤ ኢያሱ 2፡10፤ 4፡23፤ ነህምያ 9፡9-11፤ መዝሙር 105(106)፡9፥ 21፥ 22፤ 135(136)፡13-15፤ የሐዋርያት ሥራ 7፡36፤ ዕብራውያን 11፡29።

መልስ።

አንዳንድ ሰዎች እስራኤሎች ቀይ ባሕርን በተሻገሩበት ስፍራ ውኃው ጥልቅ ስላልሆነ ነፋስ ባሕሩን በቀላሉ የሚያስወግድበት ቦታ ስለሆነ ባሕሩን ያለምንም ችግር መሻገር ይቻላል ብለው ይከራከራሉ። ይህም በተፈጥሮ የሚደረግ ነገር ነው እንጂ ተአምራት አይደለም ይላሉ። ነገር ግን ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ጥቅሶች ሁሉ በነፋስ ሳይሆን በእግዚአብሔር ተአምራት የተደረጉ እንደነበር ይገልጻሉ።

1. እግዚአብሔር የላከው የምሥራቅን ነፋስ ነበር። የሰሜን ነፋስ ብቻ የኤርትራን ባሕር ማስወገድ ይችል ነበር፤ ምክንያቱም የኤርትራ ባሕር በቁመቱ በሰሜንና በደቡብ መካከል ስለተዘረጋ ነው። ውኃውም ከተከፈለ በኋላ የምሥራቅ ነፋስ በመንገዳቸው ላይ ያለውን ድጥና ጭቃ ያደርቀው ነበር (ዘጸአት 14፡21)።

2. በዘጸአት 14፡21፥ 22፥ 31 ላይ ውኃው በግራና በቀኛቸው እንደ ግድግዳ እንደቆመ እናነባለን፤ ውኃውን በስተቀኛቸው ያቆመው ነፋስ ቢሆን ኖሮ በስተግራቸው የውኃ ግድግዳ ባልነበረም ነበር። ከዚህም በስተቀር በነፋስ ግፊት ውኃ እንደ ግድግዳ መቆም አይችልም።

3. ውኃውንም ወደኋላ የገፋው የነፋሱ ኃይል ቢሆን ኖሮ እስራኤላውያኖችንም ወደኋላ በገፋቸው ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ የነፋሱን ግፊያ መቋቋም ባልቻሉም ነበር። ነፋሱ ግን እስራኤላውያን በጭቃ ላይ እንዳይሄዱ ምድሩን አደረቀላቸው።

## ከምዕራፍ 15 እስከ 17።

22. ከቀይ ባሕር አንስተው እስከ ሲና ተራራ ድረስ ሲጓዙ እግዚአብሔር ምን ሌላ መለኮታዊ ተአምራት አድርጎ እስራኤላውያንን እረዳ? ምዕራፍ 15-17።

መልስ።

1. ምዕራፍ 15፡23-26 የማራ መራራ ውኃ ተፈወሰ።

2. ምዕራፍ 15፡27 እግዚአብሔር ለእስራኤል ውኃና ጥላ በመስጠት አሳረፋቸው።

3. ምዕራፍ 16፡2-13 የሚበሉት ሥጋ ለእስራኤላውያን ተሰጣቸው።

4. ምዕራፍ 16፡14-36 ለምግባቸው መና ተሰጣቸው።

5. ምዕራፍ 16፡26-36 የማረፊያቸው ሰንበት ተሰጣቸው።

6. ምዕራፍ 17፡1-7 ውኃ ከዓለት ውስጥ ተሰጣቸው።

7. ምዕራፍ 17፡8-16 አማሌቃውያንን ድል አደረጉ።

23. በማራ መራራ ውኃ መፈወስና በውኃው አጠገብ በተደረገው ፍርድና ሥርዓት መካከል ምን አንድነት አለ? ዘጸ. 15፡23-26።

መልስ።

1. እስራኤላውያን በበረሃ አቋርጠው እንደወጡ ሁሉ እኛም ደግሞ በዚህ ዓለም ባለው የሕይወታችን በረሃ ክርስቶስን ተከትለን እንጓዛለን። በበረሃው ውስጥ የነበረው መራራ ውኃ በዚህ ዓለም የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች በዚህ የምድር ሕይወታቸው ከሚገጥማቸው መራራ ሕይወት ጋር ይመሳሰላል። የዚህ ዓለም ሰዎች ለእረፍት ለሰላምና ለእርካታ እየተጠሙ ናቸው። ዓለምም የሚሰጣቸው ሃይማኖትና ደስታ ሁሉ መራራ ነው። የተጠማችውንም ነፍስ ለማርካት ከቶ አይችሉም።

2. ወደ ውኃው የተጣለው ዛፍ የክርስቶስ በመስቀል ላይ የመሞት ምሳሌ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ዘዳግም 21፡22፥ 23፤ ገላትያ 3፡13፤ የሐዋርያት ሥራ 5፡30፤ 10፡39፤ 13፡29፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24፤ ራእይ 22፡2። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለሞተልን መራራውን ነገር ሁሉ አንስቶልናል። ስለዚህ እኛም የዓለምን መራራ ውኃ ከመጠጣት ይልቅ ሰላም ደስታና እርካታን የሚሰጠንን የመንፈስ ቅዱስን ውኃ እንጠጣለን።

እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይባሉ ነበር። እነርሱም ለ3 ቀን ያህል በሞቃቱ በረሃ ውስጥ ከተጓዙ በኋላ በጣም ደከሙ፥ እጅግም ተጠሙ። ከዚያም ያንጎራጉሩ ጀመር። ዛሬም የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሁ አንዳንዴ ብስጭትጭት እያሉ ተስፋ ለመቁረጥ ይቃጣቸዋል። ነገር ግን በዚያ ጊዜ ወደ አዳኛቸው መስቀል ቢመጡ ጣፋጭ ውኃ ጠጥተው በመከራ ውስጥ እንኳ ሳሉ ያርፋሉ። ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ እስር ቤት ታስረው በመከራ ውስጥ እንኳ ሳሉ መራራውን የእስር ቤት ችግር ተቋቁመው ጣፋጩን ውኃ በመጠጣት

ያገኙትን ሰላምና ደስታ የሚገልጸውን ታሪክ ተመልከት። (የሐዋ. ሥራ 16፡16-40።)

3. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዘዘው ትእዛዝ በዘጸአት 15፡25-66 ባለው ክፍል ላይ ይገኛል። ማብራሪያውም እጅግ በጣም ቀላል ነው።

ሀ. እስራኤላውያንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆኑ።

ለ. ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ፋንታ በሙሴ ላይ አጉረመረሙበት።

ሐ. እግዚአብሔርም መራራውን ውኃ ጣፋጭ በማድረግ ወደ እርሱ በመምጣት የሚገኘውን እርካታ በምሳሌ አሳያቸው።

መ. እግዚአብሔርም ከአሁን ጀምራችሁ ከእኔ ጋር በቅርብ ብትራመዱና ብትታዘዙኝ በሚያስፈልገው በረከት ሁሉ እባርካችኋለሁ አላቸው።

ሠ. እነርሱም ባይታዘዙትና አሻፈረኝ ቢሉት አባት እልከኛውንና የማይታዘዘውን ልጁን ቀጥሎ ታዛዥ እንደሚያደርገው ሁሉ ይቀጣቸዋል። ባይታዘዙት ግብፅን እንደቀጣ ይቀጣቸዋል። ግብፃውያን በእልህ እግዚአብሔርን ስለተቋቋሙት በመቅሰፍት፥ በበሽታ፥ እንዲሁም በመጨረሻ በሞት ቀጣቸው። እስራኤላውያንም እንደ ግብፅ ከእግዚአብሔር ጋር እልህ ቢያያዙና የማይታዘዙ ከሆኑ እስራኤልን የተጻረሩትን ግብፃውያን እንደቀጣቸው እነርሱንም በበሽታ ይቀጣቸዋል። ነገር ግን እስራኤላውያን ከታዘዙት ከተቀጡበት ሕመማቸው ይፈውሳቸዋል። እንደገና ቁጥር 26ን አንብብ። እግዚአብሔርም ከታዘዛችሁኝ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላመጣባችሁም አላቸው። «እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና።» በዚህ ላይ ያለው ቅጣት ልጆቹ ስለታዘዙት ቀረላቸው።

በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ብዙ መከራ ሕመምና ኃዘን የሚመጣባቸው በኃጢአታቸው ምክንያት ነው። እግዚአብሔርም የሚቀጣቸው በኃጢአታቸው እንዲናዘዙ ነው። ይህም በ1ኛ ቆሮ. 11፡27-32 በግልጽ ታይቶአል (2ኛ ሳሙ. 7፡14፥ 15፤ 12፡13፥ 14፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡5፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡20፤ ዕብራውያን 12፡7)። በሽታ ሁሉ በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ አይደለም። የግብፃውያን በሽታ ግን ለቅጣት የመጣ ነበር። እግዚአብሔር የሚታዘዙትን ልጆቹን አይቀጣም። ይህም ማንም ሊገባው የሚችል ቀላል ነገር ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እግዚአብሔርን በሚታዘዙት ጊዜ ሰላምና ደስታ ይኖራቸዋል። ነገር ግን የማይታዘዙ ከሆኑ ግን ይቀጣሉ።

በቁጥር 26 ላይ እግዚአብሔር «እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና» ብሏል። እግዚአብሔር የሚታዘዙትን ልጆች መፈወስ ደስታው ነው። እርሱም የችግራቸው ምክንያት አለመታዘዝ ባይሆን እንኳ ከንጹሕ ልብ የመነጨውን ጸሎት ይሰማል።

ምዕራፍ 15፡27 እግዚአብሔር በበረሃ የነበረውን ውኃ ከፈወሰ በኋላ 12 ምንጭ አድርጎ ለ12ቱ ነገድ በማዳረስ በቂ ውኃ እንዲኖራቸው አድርጎ

ሰጥቶአቸዋል። ከዚህም በቀር 20ዎቹ የዘንባባ ዛፎች ለጥላና ለማረፊያ ሆኑላቸው።

በዚህ ክፉ ዓለም ምክንያት ከነችግራችን ወደ እግዚአብሔር መምጣትን ስንማር እግዚአብሔር መራራውን ውኃ ወደ ጣፋጭነት ይለውጥልናል። በዚህ በሚጠላን ዓለም ውስጥ በቂ ውኃ በመስጠት ወደ እረፍትና ጥላው ይመራናል (ዮሐንስ 4፡14)።

24. እስራኤላውያን ባደረጉት ጉዞ ውስጥ በእግዚአብሔር መታመንን እንዲማሩ በቅደም ተከተል የደረሱባቸው አጋጣሚ ችግሮችና ሁኔታዎች ምን ነበሩ?

መልስ።

እግዚአብሔር እስራኤላውያን በፍጹም ልባቸው እንዲታመኑበት ስለሚፈልግ አውቆ እምነትን እንዲማሩ በዚህ በተባለው መንገድ መራቸው።

1. ግብፃውያን እስራኤላውያንን በኋላቸው በሚከተሉዋቸው ጊዜና የቀይ ባሕር በፊታቸው ባጠራቸው ጊዜ የሚያደርጉት ሲጠፋቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰምቶ በተአምራት መውጫውን አዘጋጀላቸው።

2. በማራም የገጠማቸው መራራ ውኃም በክርስቶስ ብቻ የሚገኘውን ጣፋጭነት እርካታ እንዲማሩ አድርጎአቸዋል። እግዚአብሔርንም ቢታዘዙት ለቅጣት ከመጣባቸው በሽታ እንደሚፈወሱ አወቁ፤ ስለዚህ በመታዘዝ ጤና ሰላምና እረፍት ይገኛል።

3. እስራኤላውያን በመጀመሪያ የት እንደሚሄዱ አላወቁም ነበር። እግዚአብሔርም ሲመራቸው በፍጹም ልባቸው ተማምነው መከተል አለባቸው። የደመና ዓምድ በቀን፥ የእሳት ዐምድ በሌሊት፥ በፊታቸው ሲሄድ እስራኤላውያን በቀን ሆነ ማታ ይከተሉ ነበር። ዐምዱም በሚቆምበት ጊዜ ግን ድንኳናቸውን ይተክሉ ነበር። ያለ ምንም ጥያቄ እግዚአብሔርን (ክርስቶስን) መከተል ተማሩ። የእግዚአብሔርንም ክብር በደመናው ውስጥ ስለሚያዩ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደነበረ ያውቁ ነበር (ዘጸአት 16፡10)።

4. እስራኤላውያንም ስለ ምግባቸው ደግሞ በእግዚአብሔር መታመንን መማር አለባቸው። ያጉረመረሙትም የሚበላ ሥጋና ምግብ ስላልነበራቸው ነበር። እነርሱም በሚቸግራቸው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን መጠየቅ እንጂ ማጉረምረም እንደሌለባቸው ተነገሩ (ምዕራፍ 16፡2-13)። በመሸም ጊዜ እግዚአብሔር ለምግባቸው ድርጭቶችን ሰጣቸው።

5. ዘጸአት 16፡14-22 እግዚአብሔርም ከሰማይ መና የሚባለውን እንጀራ ሰጣቸው። በዚህ ላይ የእግዚአብሔርም ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን መጠየቅ እንጂ ማንጎራጎር እንደሌለባቸው መማር ይኖርባቸዋል።

በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር በደስታ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል (ማቴ. 6፡25-34፤ 7፡7-11)።

6. እግዚአብሔርም እምነትን ሊያስተምራቸው ከዓለት ውኃን አፍልቆ ሰጣቸው (ዘጸአት 17፡1-7)።

7. አማሌቃውያን እየወጉአቸው በመከራ ውስጥ በነበሩ ጊዜ እግዚአብሔር በጋለ ሁኔታ እንዲጸልዩ አስተማራቸው (ዘጸአት 17፡8-16)።

መና በክርስቶስ ይመሰላል።

1. መና እስራኤል በልተው በሕይወት እንዲኖሩ ከሰማይ የተሰጣቸው ምግብ ነው። እንደዚሁም ኢየሱስ ነፍስ ሁሉ ከእርሱ ተመግባ የዘለዓለም ሕይወት ይኖራት ዘንድ ከሰማይ የተላከ እውነተኛ መና ነው (ዮሐንስ 6፡22-59)። የሰውነት ምግብ በአፍ እንደሚበላ ሁሉ የነፍስ ምግብ ደሞ በእምነት ይወሰዳል።

2. እስራኤላውያን ማለዳ ፀሐይ ከመውጣትዋ አስቀድመው መናቸውን ይለቅሙ ነበር። ያለዚያ ግን ፀሐይ ያቀልጥባቸዋል። በጠዋት ያልተነሱ ሰነፎች ሁሉ ይራባሉ። እኛም ለቀኑ ሁሉ የሚሆነንን መንፈሳዊ ስንቅ ለመቀበል በጠዋት ተነስተን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ካነበብን በኋላ መጸለይ ይኖርብናል። ይህንን ማድረግ የማይችሉ ሰነፎች ግን ምንም መንፈሳዊ ጥንካሬ አይኖራቸውም። እግዚአብሔርም ለሰነፎች መንፈሳዊ ጥንካሬን አይሰጥም።

3. ከመሬት የሚለቀመው መና በጣም ትንንሽ ከመሆኑ የተነሳ እስራኤላውያን ተንበርክከው መናቸውን ይለቅሙ ነበር። የሚለቅሙትም መና ለዕለት የሚበቃ ነበር። ጸሎትም ከልብ የሚደረግ ከሆነ ቀላል ሥራ አይደለም። ጸሎት ከባድ ሥራ ባይሆን ኖሮ ለዕለቱ ለሚገጥመን ፈተና መቋቋሚያ በቂ ኃይል ከክርስቶስ ባልተቀበልን ነበር።

4. እስራኤላውያን በጣም ሕፃናት ለሆኑ በጣም ላረጁና ለታመሙ ሁሉ መና ይለቅሙላቸው ነበር። እኛም ደግሞ ለሌሎች መስጠት እንድንችል ከእግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መቀበል ይገባናል። ከዚህም በቀር በነፍሳቸው ለጠፉ ደኅንነትን መስበክና በመንፈስ ደካሞች ለሆኑት መንፈሳዊ እርዳታ የመስጠት ኃላፊነት አለብን።

5. እስራኤል ከመና በቀር ሌላ የሚያስፈልጋት ነገር የለም። እኛም ደግሞ ክርስቶስ ብቻ ያስፈልገናል። እርሱ ለደኅንነትም ሆነ ለእኛ በእርሱ ለምንጓዘው ልጆቹ ብርታት በቂአችን ነው።

6. አንዳንዶች ሰዎች በማግሥቱ ሌላ መና እንደሚሰጣቸው እምነት አልነበራቸውም። ስለዚህ ከሚያስፈልጋቸው በላይ ይለቅሙ ነበር። ከዚህ የተነሳ ጠዋት ምግቡ ተልቶ ይገማ ነበር። አንዳንድ አማኞችም ለወደፊት ለሚያስፈልጋቸው ነገር በእግዚአብሔር አይታመኑም። ለሥጋቸውም ብቻ ስለሚጨነቁ ለሥጋቸው የሚጠቅመውን ነገር ብቻ ይሰበስባሉ። እነዚህም

መንፈሳውያን አይባሉም። ምስክርነታቸውም ተበላሽቶአል። ስለዚህ ለሌሎች ጥሩ ምስክሮች አይሆኑም (ዘጸአት 16፡20)።

7. እስራኤላውያን በሰንበት ቀን መና እንዲለቅሙ አልተፈቀደላቸውም ነበር። ሰባተኛው ቀን የእረፍት ቀን ነበር። ማንም በሰባተኛው ቀን የሚሠራ ሰው በድንጋይ ተወግሮ ይገደል ነበር። ሰባተኛው ቀን ወደ ደኅንነት ከሚመራው መንገድ ጋር ይመስላል። እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ በስድስት ቀን ውስጥ ፍጹም አድርጎ ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ በሰባተኛው ቀን ከሥራው እንዳረፈ ሁሉ እንደዚሁም እግዚአብሔር የደኅንነትን ሥራ በሙሉ ሠርቶ ጨርሶ ፍጹም አድርጎታል። እኛም በዚህ ላይ ጥቂት እንኳን መጨመር አንችልም። እኛ ግን ማድረግ የምንችለው ደኅንነትን በእምነት ተቀብለን ማረፍ ብቻ ነው። ማንም ክርስቶስ ሠርቶ በጨረሰው ሥራ ላይ የራሱን ሥራ ለማከል የሚሞክር ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆናል። ምክንያቱም ክርስቶስ ሠርቶ በጨረሰለት ሥራ ስለአላመነ ነው። በዘጸአት ውስጥ በ44ኛው ጥያቄ ላይ ስለ ሰባተኛው ቀን የተወሳውን ተመልከት።

8. ምዕራፍ 17፡1-17 እስራኤል ዳግመኛ ውኃ ባጡ ጊዜ እንደገና ለማጉረምረም ፈጽሞ አልፈቀዱም፤ በዚህ ፋንታ ግን ውኃ እንዲሰጣቸው ዓይናቸውን ወደ እግዚአብሔር አቅንተው ተመለከቱ። እግዚአብሔርን በሙሴ በኩል ስለጠሩት እግዚአብሔር ልመናቸውን ሰምቶ በተአምር ከዓለት ውስጥ ውኃን ሰጣቸው። እግዚአብሔር አስፈላጊ ከሆነ አሁንም ቢሆን በተአምር የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ በእምነት ብንጠይቅ ሊሰጠን ይችላል።

እስራኤላውያን ገና በእምነት ከግብፅ መውጣታቸው ነው። እነርሱም ገና በደሙ ተገዝተው በእምነታቸው እንደ ሕፃን ልጆች ናቸው። ሕፃን አንድ ነገር ሲያስፈልገው አይጠይቅም፥ ነገር ግን ዝም ብሎ ያለቅሳል። እስራኤላውያንም እንደዚሁ አንድ ነገር በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ከእግዚአብሔር ጠይቆ ከመቀበል ይልቅ እንደ ሕፃን እየተበሳጩ ያለቅሳሉ። ሕፃናት ልጅ ያላቸው ቤተሰቦች ሕፃኑ ልጅ ሲያለቅስ በትዕግሥት እንደሚሆኑ ሁሉ እግዚአብሔርም እስራኤላውያን ሲናደዱና ሲያለቅሱበት በትዕግሥት ይመለከታቸው ነበር። ይህም ሲሆን ጥያቄያቸውን በአግባቡ አያቀርቡም፥ ሆኖም እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል። እስራኤላውያን በሲና ተራራ ለሁለት ዓመት ከቆዩና የእግዚአብሔርን ሕግ ከሙሴ ከተማሩ በኋላ በእምነታቸው በጣም ማደግ ነበረባቸው። ከዚያ በኋላ ግን በእግዚአብሔር ላይ እንቢተኛ በሆኑ ጊዜ እግዚአብሔር ክፉኛ ቀጣቸው። ሕፃን አድጎ እንቢተኛና እልከኛ በሚሆንበት ጊዜ ቤተሰቦቹ ትልቅ ልጅ ሊያደርጉት ይቀጡታል። እግዚአብሔር በቀድሞ ጊዜ እስራኤላውያንን በቀጣበት ዓይነት ቅጣት ዛሬም ልጆቹን ይቀጣል (ዕብራውያን 12፡5-15)።

ከዓለት የፈለቀው ውኃ ትርጓሜ (ዘጸአት 17፡1-7)።

በእነዚህ በሚከተሉት ጥቅሶች እንደተገለጸው ዓለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1ኛ ቆሮ. 10፡4፤ ማቴ. 21፡42፤ የሐዋ. ሥራ 4፡11፤ ኤፌ. 2፡20፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡4-6፤ ዘዳ. 2፡34፥ 35፤ ኢሳ. 28፡16፤ ዘዳ. 32፡41)። ሙሴ በበትር በመታው ጊዜ እስራኤላውያን እስኪጠግቡ ውኃ ያፈለቀው ድንጋይ በክርስቶስ ይመሰላል። እስራኤላውያንም የዚህ የድንጋይ ምሳሌ ምን እንደሆነ ስለተማሩ ያውቃሉ። የዚህም ትርጉም መንፈስ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮ. 10፡4 ላይ በጳውሎስ እጅ ስለ እስራኤል ጽፎአል። «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፥ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ።» እስራኤላውያን ስለ ክርስቶስ ያውቃሉ። ከእርሱም መንፈሳዊ መጠጥ ጠጥተዋል።

ሙሴም ዓለቱን በመታው ጊዜ ከዓለቱ ለእስራኤል ሁሉ የሚበቃ ውኃ ፈለቀ። ኢየሱስም ስለ እኛ ኃጢአት በሽመል ተመቶ ስለ ኃጢአታችን ተፈረደበት። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ሁሉ ኃጢአት ስለሞተ ለሚፈልጉ ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት ሊሰጣቸው በቂ የሆነ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከእርሱ ይፈልቃል።

ዮሐንስ 4፡14 ማንም ከክርስቶስ ኢየሱስ የሚጠጣ ሁሉ በውስጡ የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ይኖረዋል። ለእርሱና ለሌሎችም የሚበቃ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከእርሱ ይፈልቃል። እርሱም ሌሎቹ የዘለዓለምን ሕይወት እንዲያገኙ የሚረዳቸው ምስክርነት አለው። ይህንንም ለማድረግ እራሱን አያስገድድም። ምክንያቱም ከውስጡ ምንም ሳያግደው ስለሚጎርፍ ነው። አልፎ አልፎ የማይፈልቅበት ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ሲያዝንና ዓለማዊነትና አለመታዘዝ በአማኙ ሕይወት ሲነግሥ ነው። ስለዚህ ይህ እንዳይሆን በ1ኛ ተሰ. 5፡19 «መንፈስን አታጥፉ» ተብለን ስንመከር በኤፌ. 4፡30 ደግሞ «የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» በመባል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል።

ዮሐንስ 7፡37-39 ባለው ክፍል ዓለቱ ክርስቶስ ከእርሱ እንዲጠጡ ሁሉንም ይጋብዛል። ያም ውኃ በቁጥር 39 እንደተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ ነው።

1. (ቁጥር 38) የሚያምን ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል።

2. ለሚቀበል ሁሉ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከእርሱ ይፈልቃል።

3. የሕይወት ውኃ ምንጭ እንጂ ትንሽ ጭላጭ ውኃ አይደለም።

4. ይህም ለሚያምኑ ሁሉ ማለት ለገበሬዎች፥ ለነጋዴዎች፥ ለሴቶችም ጭምር ነው እንጂ ለሰባኪያን ብቻ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በሚያዝንበት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች ፍሬ ቢስ ይሆናሉ። ስለዚህ «ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።» (ኤፌሶን 4፡30)።

25. አማሌቃውያንን ድል ለመንሳት ምን ያስፈልጋል? ዘጸአት 17፡8-16።

መልስ።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን ሊመራቸው ፈለገ፤ ነገር ግን ሰይጣን እስራኤላውያንን ተቃወማቸው። እግዚአብሔርም የዔሳው የልጅ ልጅ የነበረውንና አሁን እስራኤልን ሊቋቋም ታላቅ ሕዝብ የሆነውን የአማሌቅን ነገድ አስነሳ። እስራኤላውያን ከአማሌቃውያን ጋር ሲዋጉ ሙሴ አሮንና ሖር ወደ ተራራ ወጡ። ሙሴ እጁን ለጸሎት መዘርጋት ደክሞት ሲመልስ አማሌቃውያን ያሸንፉ ነበር። ሙሴ ግን እጁን አጠንክሮ ወደላይ በመዘርጋት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ደግሞ እስራኤላውያን ያሸንፉ ነበር። ከዚያም ሙሴ ድንጋይ አምጥቶ በላይ ከተቀመጠ በኋላ አሮንና ሖር እጆቹን ወደ ላይ በደገፉለት ጊዜ እስራኤላውያን ድል አደረጉ።

1. ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማጥፋት በሚዋጋበት ጊዜ እግዚአብሔር ብቻ ድል ሊያደርገው ይችላል። ሙሴ ባይጸልይ ኖሮ እስራኤላውያን ባላሸነፉ ነበር።

2. እንደዚሁም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ላይ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ታላቅ ጦርነት አለ። የእግዚአብሔርም ሰዎች ባላቸው ኃይልና ችሎታ ሰይጣንን ድል ለማድረግ በጸሎት መታገል አለባቸው፥ ይህም ኃይለኛውን ጠላታችንን ድል ለማድረግ የምንዋጋው መንፈሳዊ ጦርነት ነው (ኤፌ. 6፡12)።

3. እስራኤልም ባላቸው ኃይል ሁሉ እስከ ማታ ተዋጉ። ማናቸውም እውነተኛ አማኝ ሁሉ እንደዚሁ ተስፋ ባለመቁረጥ በሥራው በመግፋት ጠላትን ድል እስኪያደርግ ድረስ መዋጋት አለበት።

4. ጸሎት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ሥራ ብቻ በግሉ በቂ አይደለም። እስራኤላውያን በሚዋጉ ጊዜ እግዚአብሔር የሙሴን ጸሎት ሰምቶ ረዳቸው።

5. ሙሴ ስለደከመው ግድ ርዳታ ያሻው ነበር። ሙሴ እንዳደረገው ሁሉ አንድ ሰው ብቻውን በየጊዜው የሚጸልይ ከሆነ ሰልችቶት ተስፋ ሊቆርጥ ይችላል። የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወይም ሽማግሌ ብቻ የሚጸልይ ከሆነ ጠላት ኃይሉን በመጨመር ሊያሸንፍ ይችላል። ለዚህ ነው እንግዲህ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች የተሸነፉት። አሮንና ሖር ሙሴን እንደረዱት ሁሉ ሁላችንም በጸሎትና በሥራ መረዳዳት ይኖርብናል። ከዚያም እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ ቤተ ክርስቲያናችን በጠላት እንዳትደመሰስ ኃይልና ድል ይሰጠናል። ሰይጣንም በቀላሉ የሚሸነፍ ጠላት አይደለም። እርሱንም ለማሸነፍ ኃይለኛ ውጊያ ማድረግን ይጠይቃል። እስራኤላውያንም ከነዓናውያንን ድል ከማድረጋቸው አስቀድሞ ከሰይጣን ጋር የሚደረገውን ውጊያ መማር ይኖርባቸዋል። የሙሴን እጅ ወደ ላይ አቅንቶ መያዙ የሚያመለክተው ድል የሚገኘው ከእግዚአብሔር ስለሆነ ድል ለማድረግ በጸሎት እግዚአብሔርን መጠየቅ እንደሚያስፈልግ ነው።

ዘጸአት 19፡ 1-24፥ 18 አንብብ።

26. ሀ. እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ወይም በሲና ተራራ ከእስራኤል ጋር ያካሄደውን ኪዳን በጥንቃቄ ጥቀስ። ዘጸአት 19፡3-6።

መልስ።

እስራኤል የእግዚአብሔር የግል የተከበረ ንብረትና የካህናት መንግሥት እንዲሁም ቅዱስ ሕዝብ ለመሆን ለእግዚአብሔር ቃልና ለኪዳኑ መታዘዝ አለበት (ቁጥር 5)። እስራኤልም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል በመሆን አሕዛብን ለደኅንነት ወደ እግዚአብሔር መምራት አለበት። ይህንንም ጥሪ ማከናወን የሚችሉት ለእግዚአበሔር የሚታዘዙና ቅዱስ ሕዝቦች ሲሆኑ ሲችሉ ነው። ለእኛም የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕዝቦች ለሆንነው የተሰጠን ተመሳሳይ ኪዳን ነው፥ 1ኛ ጴጥ. 2፡9፥ 10 ያለውን ክፍል ተመልከት።

26. ለ. ከሥላሴ ማንኛው ነው እነዚህን ቃላት የተናገረው?

መልስ።

የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ልጁ እግዚአብሔር ወልድ ነው። በዘፍጥረት የሚገኘውን የ84 ሀ መልስ ተመልከትና የዚህኛውን መጽሐፍ የመግቢያ ሥራ ቀጥል።

27. ይህ ኪዳን በክርስቶስ በኩል ለዓለም ሁሉ የተሰጠ የማያቋርጥ ጸጋ እንደሆነ አሳይ (ዘጸአት 19፡6)።

መልስ።

እስራኤል ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት ስለሆኑ በሞላ በቤተ መቅደስ ውስጥ ያገለግላሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን እስራኤላውያን ሁሉ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ የሚመልሱ መሆን ይችላሉ። የካህን ሥራ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በመሆን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ነው (ዕብ. 5፤1፥ 2፤ ዘጸአት 28፡30-38፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡20)። የካህን ወገን እንደመሆናቸው መጠን የወገኖቻቸው ኃላፊነት ሲኖርባቸው፥ ግላዊ ሰውም ለሌላው ግለኛ ሰው ኃላፊነት አለበት። እግዚአብሔር ለደኅንነት እስራኤልን ብቻ አልጠራም። እግዚአብሔር ዓለም ሁሉ ሰምቶ እንዲድን ይፈልጋል።

28. እግዚአብሔር (ክርስቶስ) በሲና ላይ ከሕዝቡ ጋር ምን አዲስ ኅብረትን አደረገ?

መልስ።

ክርስቶስ (እግዚአብሔር) እስራኤላውያንን የግል ሕዝቦቹና ከሌላው ሕዝብ ተለይተው የተመረጡና የተጠበቁ አድርጎ ለራሱ ለይቶአቸዋል። እርሱም ከሌላው ሕዝብ ሁሉ የተለዩ የተከበሩ ሀብቶቹ በማድረግ የራሱ የግሉ እንዲሆኑ አድርጎአቸዋል (ቁጥር 5)። እነርሱም ለሌሎቹ ሕዝቦች የዘለዓለምን ሕይወት ጎዳና እንዲያሳዩ የተላኩ የካህናት መንግሥት በሆኑ ነበር። እነዚህ በእውነት

ዳግመኛ በክርስቶስ የተወለዱ መንፈሳዊ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ደግሞ እስራኤላውያን ጥንት ከክርስቶስ ጋር እንደነበራቸው አንድነት ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ አንድነት አላቸው። እነርሱም የክርስቶስ የግል ሀብቶቹ ናቸው። ስለዚህ እነርሱም መንፈሳዊ ሕዝቦቹና ቅዱስ ሕዝቦቹ ለርስቱ የተለዩ ወገኖችና የእግዚአብሔር ካህናት ስለሆኑ በክርስቶስ የሚገኘውን ደኅንነት ለዓለም ሁሉ መናገር አለባቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡9)።

ወንጌልን መስበክ የተሰጠው ለእስራኤል ነበር። እነርሱ አልታዘዝ ባሉ ጊዜ ለአሕዛብ ቤተ ክርስቲያናት ተሰጠ። ክርስቶስ ለ1000 ዓመታት በሰላም በምድር ላይ በሚገዛበት ጊዜ እንደገና ምስክርነቱ ለእስራኤል ተመልሶ ይሰጣቸዋል። በዘፍጥረት ውስጥ ለ74ኛው ጥያቄ መልስ በመሆን የወንጌልን ትርጉም የሚያብራራውን ክፍል ተመልከተህ ትርጉሙን እስከትረዳ ንባብህን ቀጥል።

29. እስራኤል የካህን መንግሥት እንደመሆንዋ ከዓለም ጋር ያላት አንድነት ምንድን ነው? ዘጸአት 28፡30-38፤ ዕብ. 5፡1፥ 2።

መልስ።

ዘጸአት 28፡30 ታላቁ ሊቀ ካህና አሮን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ይቆም ነበር። የልቡም ፍላጎትና መቃጠል ሕዝቦቹን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ነው። ይህ ነው እንግዲህ እስራኤልን በጠቅላላ የካህን ወገን ያሰኛቸው። አሮን 12ቱን የእስራኤልን ነገድ የሚወክሉትን 12 የተከበሩ ድንጋዮች በደረቱ ላይ ባስቀመጠው ሰሌዳ ላይ አኑሯቸው ነበር። በእነዚህም ድንጋዮች መካከል እግዚአብሔር ለእስራኤል ፈቃዱን የሚያስታውቅበት ሁለት ኡሪምና ቱሚም የሚባሉ ነገሮች አሉ። በዚህም ጊዜ ሊቀ ካህኑ ለሕዝቦቹ ይማልዳል። ሊቀ ካህኑም ሁልጊዜ 12ቱንም ነገዶች በእግዚአብሔር ፊት በልቡ ሊሸከማቸው ይገባል። በእግዚአብሔር ፊት ደኅንነት እንዲያገኙና መልካም ጠባይ እንዲታይባቸው ዘወትር በልቡ መቃተት ይኖርበታል። በተመሳሳይ መንገድ እነዚህ ደኅንነትን የተቀበሉት የካህናት መንግሥት የሆኑት እስራኤላውያን ደግሞ በበኩላቸው የካህናት መንግሥት ስለሆኑ ይህ የጠፋ ዓለም ወደ እግዚአብሔር ደኅንነት እንዲመጣ የልባቸው መቃተትና ጭንቀት መሆን ነበረበት።

ዘጸአት 28፡38 የካህናቶች ሁሉ አሳብ ነፍሳትን ለደኅንነት ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነው። ይህም መሆን አለበት። አሮንም ከጥሩ ወርቅ ቅጠል የሚመስል ምልክት ሠርቶ በእርሱም እንደ ማኅተም ቅርጽ «ቅድስና ለእግዚአብሔር» የሚል ቅርጽ የተቀረጸበት በግንባሩ ላይ ማድረግ ነበረበት። እርሱም የሕዝቡን ደኅንነትና ቅድስና ዘወትር በአእምሮው ሊይዝ ይገባል። ለሕዝቡ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቅድስና ማሳየት አለበት። የመሥዋዕቱን ቅድስናና ትርጉም ለሕዝቡ ሊያስተምራቸው ይገባል።

በተጨማሪ ደግሞ የእስራኤል ሕዝቦች የካህናት መንግሥት እንደመሆናቸው መጠን የዓለምን ደኅንነት አዘውትረው በአእምሮአቸው በማከታተል ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ አለባቸው።

ዕብ. 5፡1 ሕዝቦቹ ምናልባት ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁ እንደሆን ሊቀካህኑ ወደ ክርስቶስ ሊመራቸው ይገባል። ሰዎችን በእምነት ወደሚገኘው ደኅንነት በኑዛዜ መምራት አለበት። የራሱን ውድቀት ስለሚያውቅ ለሌሎቹ ማዘንና መራራት ይገባዋል። ይህም ደግሞ የእስራኤል ሕዝቦች ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ለቀረው የዓለም ሕዝብ ማሳየት የሚገባቸው ርኅራኄ መሆን ነበረበት። እነርሱም ለዓለም ሕዝብ መመስከር ነበረባቸው።

30. አሥርቱ ቃላት እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ከሰጠው ሕግጋት ውስጥ አነስተኛ ነው ወይስ ከፍተኛ ደረጃ ይዞአል?

መልስ።

አሥርቱ ቃላተ ኦሪት የሕግጋቶች ሁሉ መሠረት ሆኖ ለእስራኤላውያን የተሰጠ ሕግ ነበር። ሕግጋቶች ሁሉ እንደሚገልጹት ፍጹም መሆን የሚቻለው እግዚአብሔርንና ሰውን በመውደድ ነው (ማቴ. 22፡36-40)።

ምዕራፍ 20፡2-11 የመጀመሪያዎቹን አራቱን ትእዛዛት ይዞአል። እነርሱም ከሁሉ ነገር በላይ እግዚአብሔርን መውደድ እንደሚገባ ያዛሉ። ከቁጥር 12-17 ያለው ክፍል ደግሞ ሰውን እንድንወድ የሚያሳስቡ ስድስት ሕግጋቶችን ይዞአል። ይህም የሙሴ ሕግጋቶች ሁሉ መሠረት ነው። የቀሩት ተጨማሪ ሕግጋቶች ግን እነዚህን ሕግጋቶች ለመፈጸም ምን ማድረግ እንደሚገባና ምን ማድረግ እንደማይገባ ያስረዳሉ (ማቴ. 22፡36-40)። ኃጢአትን የማይሠራው የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስ ቅዱስ እንደሆነ ሕዝቦቹ ደግሞ ቅዱሳን መሆን ነበረባቸው። ሕጉም እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግባቸው አሳይቷቸዋል።

31. እነዚህ ሕግጋቶች የተሰጡት የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑ እስራኤል በምድር እንዲፈጽሙት ብቻ የተሰጣቸው ነው ወይስ ለዘለዓለማዊ ቅድስና የሚመሩ መምሪያዎች ናቸው?

መልስ።

እግዚአብሔርና ሰውን ስለመውደድ የተሰጠው መሠረታዊ ሕግ ለእስራኤላውያን ብቻ የተሰጠ አይደለም። እስራኤላዊም ሆነ ወይም ከአሕዛብ ወገን ማንም ይህንን እግዚአብሔርና ሰውን የመውደድ ሕግ ባይፈጽም ኃጢአተኛና ፍርድ የሚገባው ነው። ይህም ሕግ ዘለዓለማዊ ነው። ይህም ሕግ እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ሰይጣን እግዚአብሔርን መውደዱን አቋርጦ ሌሎችን ነገሮች አልቆ በወደደ ጊዜ ስለተፈረደበት ከመንግሥተ ሰማያት ተነጥሎ ወደ ምድር ተጣለ (ኢሳ. 14፡12-15)። እርሱም አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን መውደዳቸውን ባቋረጡ ጊዜ ሰይጣን ተባለ። (አለመታዘዝ በሌለበት ቦታ ሁሉ ፍቅር ስለሌለ) ተፈረደባቸው። እግዚአብሔር ይህንን ሕግ ለእስራኤላውያን ሰጣቸው፤ ምክንያቱም ቅዱሳን እንዲሆኑ ስለፈለገ ነው (ዘጸአት 20፡2-7)።

በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ተመሳሳይ ሕግ አለን። ኢየሱስም በተራራው ስብከቱ ይህንን ሕግ በልባችን እንዴት አድርገን እንደምንይዘው ነግሮናል (ማቴዎስ ምዕራፍ 5-7)። እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ መውደድ እንደሚገባህና ሰውንም በሙሉ ማፍቀር እንዳለብህ ገልጾአል። ኢየሱስም ይህንኑ ሕግ አድሶ በዮሐ. 13፡34-35 ክርስቶስ እንደወደደን ሌሎቹን ደግሞ መውደድ እንዳለብን ገልጾልናል። ዮሐንስም በ1ኛ ዮሐ. 2፡7፥ 8 ባለው መልእክቱ ላይ ይህቺ ትእዛዝ መጀመሪያውኑ ከሕግጋቶች በፊት የነበረች ናት። በመንግሥተ ሰማያትም ለዘለዓለም ምንም ዓይነት ኃጢአትና ፍርድ የለም ምክንያቱም በዚያ ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን ሰዎች ፍጹም የሆነ ፍቅር ስለሚኖረን ነው።

ሥርዓታዊው ሕግ ዘለዓለማዊ አይደለም። ይህም ሕግ የደም መሥዋዕት፥ በዓላትን የማክበር፥ የሰንበት አከባበር፥ የመብላትና ያለመብላት እንዲሁም የመጠጣት ሕግ ያለባበስና የመሳሰሉት ነው። እነርሱም ስለ ክርስቶስ ሞትና የደኅንነት መንገድ እንዲሁም በቅድስና ስለመመላለስ የሚያስረዱ ምሳሌዎችና መግለጫዎች አሉት። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ ተቀብሮ ከተነሳ በኋላ ሕጎቹ ሁሉ ተፈጽመዋል። ሕግጋቶቹም ተጠብቀው የነበሩት በዚያን ቀን እንዲፈጸሙ እስከዚያን ቀን ድረስ ብቻ ቆይተው ነበር። (ግብረገባዊ ሕግ) ግን ዘለዓለማዊ ነው። ከክርስቶስ የተነሳ ሕጉም ደግሞ በእውነተኛ ክርስቲያኖች ሕይወት ተፈጸሞአል።

32. በአሥሩ ሕግጋት ውስጥ ምን ዓይነት ሁለት ደንቦች ትመለከታለህ?

መልስ።

በምዕራፍ 20፡2-11 ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የሚያደርጓቸውን ሥራዎች እናያለን፥ ከቁጥር 12፡17 ደግሞ ሰዎች ስለ ሰው የሚያደርጉትን ሥራ እንመለከታለን።

33. በመጀመሪያውና በሁለተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ከሕዝቦቹ የሚፈልገው የመታዘዝ ሁኔታ ምን ዓይነት ነው?

መልስ።

የመጀመሪያው ትእዛዝ በዘጸአት 20፡3 ላይ ይገኛል። ሁለተኛው ትእዛዝ ደግሞ ከቁጥር 4-6 ባለው ላይ ሰፍሮአል። እግዚአብሔርም ሕዝቦቹ ከእርሱ በቀር ሌላ ልዩ ልዩ አማልክቶችን እንዳያመልኩ አዟል። ይህ ቀርቶ በእግዚአብሔር አምሳል ወይም ምሳሌ ምንም ዓይነት ሥዕል፥ እንዲሁም ወድቀው የሚሰግዱለት የተቀረጸ ምስል እንዲኖራቸው ፈጽሞ አይፈቅድላቸውም ነበር። ይህ ነው እንግዲህ አእምሮአቸውን ሁሉ ከእግዚአብሔር ላይ አንስቶ ወደ አማልክቶቻቸውና ወደ ሥዕላቸው አድርጎ አምልኮአቸውን ልማዳዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ያደረገው፤ በኋላም እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ በሠሩ ጊዜ ጥጃ እንዳመለኩ ተቆጥረው ፍርዳቸውን ተቀበሉ። አሮንም በዘጸአት 32፡5 ላይ «ነገ የእግዚአብሔር በዓል ነው» ሲል አወጀ። በነጋውም የሚቃጠል መ

ሥዋዕትን፥ የደኅንነት መሥዋዕትን፥ በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ (ቁጥር 6)። ይህን የመሰለውን መሥዋዕት በጥጃው ጣዖት ፊት ስላቀረቡ በቁጥር 4 ላይ እንደተጠቀሰው ሰዎቹ ጥጃ ማምለካቸው ነው። ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ከእግዚአብሔር ይልቅ አሳቡን የሚማርከውና ዘወትር አሳቡን ከእግዚአብሔር ላይ አንስቶ በዚያ በሚያስበው ነገር ላይ ካኖረ ከእግዚአብሔር ይልቅ ያንን የሚያስበውን ነገር ይወዳል ማለት ነው። እርሱም ያንን ነገር ከእግዚአብሔር ይልቅ እንደሚወድ የምናውቀው አሳቡ ሁልጊዜ ወደዚያ ነገር ስለሚወስደው ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚወደውና የሚያስበው ነገር ካለ ያ ነው እንግዲህ የሚያመልከው፤ ጣዖቱና ሥዕሉ እንዲሁም የተቀረጸው ምስሉ፤ እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ ከእግዚአብሔር አልቆ የሚወደው ነገር ካለ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝነው ይህ ነው።

34. ሀ. በዘጸአት 21፡1-23፥ 19 በዓለም ክፍል የተጠቀሰው (ፍርድ) ወይም (ሥርዓት) የእስራኤል ሕዝብ ከሚተዳደርበት ከአሥርቱ የመንግሥቱ መተዳደርያና ሕግጋት ጋር ምን መተባበር አለው?

መልስ።

በዘጸአት 21፡1-23፥19 ባለው ክፍል የተጠቀሰው ሕግ ለእስራኤላውያን የመንግሥት የአስተዳደር ሕግ መምሪያ እንዲሆንና ወንጀለኞች እንዲቀጡበትና ሕግ ተላላፊዎች ሕግን በማፍረሳቸው እንዲፈሩና የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተሰጣቸው ምድር በሰላም እንዲኖሩ ነው። መንግሥቱ በእነዚህ አሥርቱ ትእዛዝ ስለሚያስተዳድራቸው እያንዳንዱ እስራኤላዊ ይህንን ሕግ ግድ መታዘዝ ነበረበት። እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው የበደለውን በግሉ እንዲበቀል አልፈቀደለትም። ይህ የመንግሥቱ ኃላፊነት ነው። እያንዳንዱ እስራኤላዊ ግን በልቡ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈጸም ጠላቶቹን መውደድ አለበት (ዘጸአት 23፡4፤ ምሳሌ 24፡17፤ 25፡21፥ 22፤ ማቴ. 4፡44፤ ሮሜ 12፡20)። ይህ ጥቅስ እያንዳንዱ ሰው በግሉ ሊያደርገው የሚገባውን ነገር ያሳያል። የሚከተለው ጥቅስ ደግሞ የመንግሥቱን ሥራ ያሳያል (ዘጸአት 21፡23-25፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡13፥ 14፤ ሮሜ 13፡1-5)።

34. ለ. እነዚህን ትእዛዛት በየክፍላቸው አከፋፍል።

ምዕራፍ 21፡1-11 ስለ ጌታና ስለ አገልጋዮቹ የሚያስረዳ ሕግ።

ምዕራፍ 21፡12-36 ከብት ወይም ሰው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ ምን መደረግ እንዳለበት የሚገልጽ ሕግ።

ምዕራፍ 22፡1-15 በንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የተሰጠ ሕግ።

ምዕራፍ 22፡16-23፥ 9 በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ለሚደርሰው ግፍ የተሰጠ ሕግ።

ምዕራፍ 23፡10-13 ለእርሻና ለሰንበት የተሰጠ ሕግ።

ምዕራፍ 23፡ 14-19 ስለ ሦስት ባሕላዊ በዓላትና ስለ መከር የተሰጠ ሕግ።

35. እስራኤላውያን ቃል ኪዳናቸውን ቢጠብቁ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ምን ሊያደርግላቸው ቃል ኪዳን ገባ? ምዕራፍ 23፡20-33።

መልስ።

በምዕራፍ 23፡20-24 እስራኤላውያን ቢታዘዙትና ፈቃዱን ቢያደርጉ እግዚአብር በፊታቸው መልአኩን ልኮ መንገዳቸውን እንዲያጠራላቸውና ወደ ከነዓን እንደሚገቡ ተስፋ ሰጣቸው። በቁጥር 20 ና 23 የተገለጸው መልአክ የመላእክት አለቃ የሆነውና በጦርነት ጊዜ ለእስራኤል የሚዋጋ ሚካኤል ነው (ዳንኤል 12፡1)። ኢያሱ ከነዓንን ድል አድርጎ አገሪቷን በያዘ ጊዜ ለጦርነት ተሰልፈው የነበሩትን የእስራኤልን ወታደሮች ለመርዳት የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያሱ ተገለጸለት (ኢያሱ 5፡13-15)። መልአክ ማለት «የተላከ» ማለት ነው። ክርስቶስም በአባቱ የተላከ ነው። ቁጥር 21 እንደሚገልጸው የእግዚአብሔር ስም በመልአክ ውስጥ አለ። ስለዚህ መልአክ በሚልበት ጊዜ ደግሞ ክርስቶስ ማለቱ ሊሆን ይችላል።

እስራኤላውያን ሊያደርጉት የሚገባቸው ዋነኛው ነገር እግዚአብሔርን ማገልገልና መታዘዝ ነው (ምዕራፍ 23፡22፥ 24፥ 25፥ 32፥ 33)። እነዚህን ቢፈጽሙ እግዚአብሔር የሚከተሉትን ስድስት ነገሮች ያደርግላቸዋል።

1. እግዚአብሔር ምድረ ከነዓንን ሊሰጣቸው ነው (23፡23፥ 31)።

2. እግዚአብሔር የሚበሉትን ምግብ ባርኮ ሊሰጣቸው ነው (23፡25)።

3. እግዚአብሔር ሀብታም ሊያደርጋቸውና ከብቶቻቸውንም ሊባርክ ነው (23፡26)።

4. እግዚአብሔር ጤንነት ሊሰጣቸው ነው (23፡25)።

5. እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ ሊሰጣቸው ነው (23፡26)።

6. እግዚአብሔር የጠላቶቻቸው ጠላት ሊሆን ነው (23፡22)።

እስራኤላውያን ኃጢአት ቢሠሩ መልአክ ይፈርድባቸዋል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስም በመልአኩ ውስጥ ስላለ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ በኃጢአት ላይ መፍረድ አለበት (ቁጥር 21)።

36. የኪዳኑ ማኅተም እንዴት እንደታተመ አስረዳ። ዘጸአት 24፡5-8።

መልስ።

እግዚአብሔር ይህን ኪዳን ለእስራኤላውያን ባሳያቸውና በሰጣቸው ጊዜ እስራኤላውያኖች በሞላ በአንድ ቃል «እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ።» (ዘጸአት 24፡3)። በእስራኤልና

በእግዚአብሔር መካከል ውል ተደረገ። ከዚያም ሙሴ መሠዊያ ሠርቶ በላዩ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕትና የደኅንነት መሥዋዕት ለጌታ ያቀርብ ጀመር (ዘጸአት 24:4፥ 5)። ሙሴም የደሙን እኩሌታ በቆሬ ውስጥ አደረገው፤ የደሙንም እኩሌታ በመሠዊያው ላይ ረጨው (ዘጸአት 24:6)። ከዚያም የኪዳኑን መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበው። ሕዝቡም እንደ ገና «እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ እናደርጋለን አሉ» (24:7)። ከዚያም ሙሴ በቆሬ ውስጥ ያለውን ደም በመጽሐፍ ላይና በሕዝቡ ላይ ረጨው (24:8)። ወዲያውም የቃል ኪዳኑ ውል በደም ታተመ።

37. ይህ ማኅተም ምን ያመለክታል? ዕብ. 9:15-22።

መልስ።

በዕብ. 9:15-22 ባለው ክፍል ላይ በደም ስለታተመው ኪዳን ትርጉም ተብራርቷል፤ እስራኤላውያን በገዛ ኃይላቸው ሊጠብቁት የማይችሉትን በጣም ቅዱስ የሆነውን ኪዳን ለመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር ተስማሙ። በመሠዊያው በኪዳኑ መጽሐፍና በሕዝቡ ላይ የተረጨው ደም የክርስቶስ ደም ምሳሌ ነው። ደሙ የተረጨበት መሠዊያ ደግሞ የክርስቶስ ደም በፈሰሰበት መስቀል ይመሰላል። የክርስቶስ ደም በመፍሰሱ ብቻ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አንድነትና ስምምነት ኖረን። ክርስቶስ ባይሞት ኖሮ እስራኤል ይህንን ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር ባላካሄዱም ነበር። ምክንያቱም እስራኤላውያን ኃጢአተኞች ስለሆኑና እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ነው። ይህ ዓይነቱ ቃል ኪዳን የተደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታቸው ወደፊት ስለሚሞትላቸው ነበር።

የደሙ በሕዝቡ ላይ መረጨት ፍቺ (ምሳሌ) ሕዝቡ የተቀበሉትን ኪዳን በራሳቸው ችሎታና ኃይል መጠበቅ ስለማይችሉ የተሰጣቸውን ውል በእምነት ተቀብለው ክርስቶስ በሚሰጣቸው ኃይል ለመፈጸም ነው።

ዛሬም በእውነት ዳግመኛ የተወለዱ አማኞች ሁሉ የሚያደርጉት ይህንኑ ነው። እነርሱም የኃጢአታቸው ፍርድ በክርስቶስ ላይ በሞት እንደተፈረደበት ያለመጠራጠር ክርስቶስን በእምነት እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ይቀበሉታል። ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃንና ልበ - ቅዱሳን ይሆናሉ። በየዕለቱ ጉዞአቸው በራሳቸው ኃይል ሳይሆን በክርስቶስ ርዳታ ኃጢአትን ያሸንፋሉ። እነርሱም የክርስቶስን ደም በእምነት ስለተቀበሉ እንደ እስራኤላውያን በደም የተረጩ ናቸው።

የሕጉ መጽሐፍ በደም የተረጨበት ምክንያት ይህ ቅዱስ ሕግ ሊጠበቅ የሚቻለው ክርስቶስን በመቀበል ብቻ እንደሆነና በክርስቶስም ደም አዲስ ፍጥረት መሆን እንደሚቻል ለማስረዳት ነው።

የእስራኤል ካህናትና ሽማግሌዎች የክርስቶስን ደም በእምነት ለደኅንነታቸው በተቀበሉ ጊዜ እግዚአብሔር (ክርስቶስን) አይተው በሕይወት ኖሩ (ዘጸአት 24:9-11)። መጽሐፍ ቅዱስ ማንም እግዚአብሔር አብን አይቶ በሕይወት

አይኖርም ይላል። ማንም ደግሞ እግዚአብሔርን አይቶ አያውቅም። የእስራኤል ካህናትና ሽማግሌዎችም ክርስቶስን ቢያዩ ኖሮ በሕይወት አይኖሩም ነበር። ምክንያቱም ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ነው። ያም ሆኖ የክርስቶስን ደም ለደኅንነታቸው በተቀበሉ ጊዜ ንጹሐን ሆኑ። እግዚአብሔርን (ክርስቶስን) አይተው አልሞቱም (ዘጸአት 24፡9-11)። (ኤፌ. 2፡13፤ ዕብ. 10፡19፥ 20 ተመልከት።) እስራኤልም ሕጉን ከተላለፉ በኋላ እግዚአብሔርን (ክርስቶስን) ዳግመኛ አላዩትም።

ሙሴም የደሙን ትርጉም በግልጽ አስረድቷቸው እንደነበር አያጠራጥርም። እግዚአብሔርም የሚመጣውን ክርስቶስንና የደኅንነታቸውን መንገድ በግልጽ አሳያቸው። ይህም በገላትያ 3፡24 በጣም ብሩህ ተደርጎ ተገልጾአል። «እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል።» 1ኛ ቆሮ. 10፡4ን ተመልከት።

### ዘጸአት ምዕራፍ 25-29 አንብብ።

38. ከምዕራፍ 25-27 ድረስ ባለው ክፍል ስለምን የሚያስረዳ ትምህርት ነው የተሰጠው?

መልስ።

ምዕራፍ 25-27 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ስለማደሪያው ድንኳንና በውስጡ ስላሉት ዕቃዎች አሠራር የተሰጠው መምሪያ ነው።

ምዕራፍ 25፡1-9 የማደሪያው ድንኳን እንዲሠራ ትእዛዝ ተሰጠ።

ምዕራፍ 25፡10-22 ታቦቱ እንዴት እንደሚሠራ።

ምዕራፍ 25፡23-30 የገጹ ኅብስት ማዘጋጃ ገበታ እንዴት እንደሚሠራ።

ምዕራፍ 25፡31-40 የወርቅ መቅረዝ እንዴት እንደሚሠራ።

ምዕራፍ 26፥ ና 27፡9-19 የማደሪያው ድንኳን የሚሠራባቸው የተለያዩ ነገሮች።

ምዕራፍ 27፡1-9 የናስ መሠዊያ።

ምዕራፍ 27፡20-21 የመብራቱ ዘይት።

የማደሪያው ድንኳን እያንዳንዱ ነገር ሳይቀር በሞላ እንዴት እንደሚሠራ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሰጠ። እያንዳንዱ ሳንቃ ሚንጠና ቀለበት እንዲሁም መጋረጃ እግዚአብሔር እንዳዘዘው መሠራት አለበት። ምክንያቱም እያንዳንዱ ነገር የሚሰጠው ትምህርታዊ ምሳሌነት አለው። እግዚአብሔርም ሙሴን እያንዳንዱ ነገር ልክ እርሱ እንዳዘዘው እንዲሠራ አስጠነቀቀው። እግዚአብሔርም በዘጸአት 25፡9 «እኔ እንደማሳይህ ሁሉ፥ እንደማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ፥ እንዲሁ ሥሩት» አለ።

ዘጸአት 25፡40 «በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ።» በእግዚአብሔር ዘንድ ይህ ሥራ እጅግ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ስለ አሠራሩ አሁንም አሁንም ደጋግሞ አስረድቶአል። ዘጸአት 25፡9፥ 40፤ 26፡30፤ 27፡8፤ ዘኁልቁ 8፡4፤ 1ኛ ዜና 28፡11-19፤ የሐዋርያት ሥራ 7፡44-46 ተመልከት። ይህ ምሳሌ ለእስራኤላውያን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እኛም በትምህርታችን እንደ ምሳሌ አድርገን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። በዕብራውያን 8፡5 ላይ «እነርሱም ሙሴ ድንኳኒቱን ሲሠራ ሳለ እንደ ተረዳ፥ ለሰማያዊ ነገር ምሳሌና ጥላ የሚሆነውን ያገለግላሉ። በተራራው እንደተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበርና»። እያንዳንዱ የማደሪያው ድንኳን ነገር የሰማያዊና የመንፈሳዊ ነገር ምሳሌ ስለሆነ ሕዝቡን ስለሚመጣው አዳኝና የእግዚአብሔር ልጆች በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞ ያስተምራቸዋል።

በዚህ አንጻር የእያንዳንዱን የማደሪያ ድንኳን ክፍልና በእያንዳንዱም ነገሮች የሚሠራው ሥራ የሚሰጠውን ምሳሌ የጠለቀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ካለው ሰው ተረድቶ ለእያንዳንዱ ሥራና ዕቃ ምሳሌ መስጠት በእግዚአብሔር ዘንድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው።

39. ሀ. የማደሪያው ድንኳን የተሠራበት ዋናው ዓላማ ምንድን ነው? ከማንኛው የዚህ ዓለም የመንግሥታት ክፍል ጋር ይመሳሰላል? 20፡8፥ 22።

መልስ።

የማደሪያው ድንኳን የእስራኤል ንጉሥ ለሆነው ለክርስቶስ ማደሪያ ከመሆኑ በላይ ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት ቦታ ነው። ሰዎች ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ ክርስቶስ እንደማንኛችንም የመኖሪያ ቤት ነበረው። በዘጸአት 25፡8፥ 22 እንደተገለጸው እንደማናቸውም የሌላ አገር ነገሥታት የራሱ ቤተ መንግሥት ነበረው። ስለዚህ የማደሪያው ድንኳንም እንደ ምሳሌ ተሠርቶአል ማለት ነው።

1. አሁን ግን ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ይኖራል (ኤፌ. 2፡19-22፤ ማቴ. 18፡20)።

2. ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል (2ኛ ቆሮ. 6፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡19)።

3. በመንግሥተ ሰማያት (ዕብ. 9፡23-24)።

39. ለ. የማደሪያውን ድንኳን ፕላን ለሙሴ የሰጠው ማን ነው? ዕብ. 8፡5፤ ዘጸአት 25፡9።

መልስ።

እግዚአብሔር አምላክ የሆነው ክርስቶስ ራሱ የማደሪያው ድንኳን በትክክል እንዲሠራ ለሙሴ ነገረው። ይህም በዘጸአት 25፡1-9 ታይቶአል። ከዚህም ክፍል በተለይ ቁጥር 9ን አንብብ። እያንዳንዱ የማደሪያው ድንኳን አቀማመጥና

አሠራር ልክ ጌታ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) እንደተናገረው መሠራት ነበረበት። ምክንያቱም በማደሪያው ድንኳን የሚገኘው ነገር ሁሉ የክርስቶስ የመንግሥተ ሰማያትና የደኅንነት መንገድ ምሳሌ ነው (ዕብ. 8፡5)።

## በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ይጠቀሙባቸው የነበሩት ዕቃዎች ትርጉም። ዘጸአት 25፡1-9።

1. ወርቅ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው። የተቀጠቀጠው ወርቅ የእግዚአብሔር ወልድን መከራ መቀበል ያሳያል (ዘጸአት 25፡3)።

2. ብር መዋጀት ነው (ዘጸአት 30፡13-16፤ 38፡25-28)።

3. ናስ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚያመጣው ፍርድ ነው (ዘጸአት 25፡3)።

4. ሰማያዊ ቀለም የመንግሥተ ሰማያት ወይም ከመንግሥተ ሰማያት የሆነ ነገር ምሳሌ ነው (ዘጸአት 25፡4)።

5. ሐምራዊ የንጉሥ ቀለም ነው (ዘጸአት 25፡4)።

6. ቀይ በኃጢአት የሚዋጀን ደም ነው (ዘጸአት 25፡4)።

7. የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር እንከን የሌለበት ሰብአዊነት ነው (ዘጸአት 25፡4፤ ራእይ 19፡8)።

8. የፍየል ጸጉር ክርስቶስ ኃጢአታችንን እንደተሸከመ የሚያሳይ ነው (ዘጸአት 25፡4)።

9. ቀይ የአውራ በግ ቁርበት ክርስቶስ በሞቱ በደም እንደተነከረ ወይም እንደተለወሰ ያሳያል (ዘጸአት 25፡5)።

10. የአቆስጣ ቁርበት የክርስቶስ ንጹሕ እንዳልሆነ መቆጠር፥ እርሱም ስለ እኛ ኃጥዕ ሆነ (ዘጸአት 25፡5)።

11. የግራር እንጨት የበረሃ እንጨት የሆነ ሰብአዊነት ነው (ዘጸአት 25፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

12. ዘይት መንፈስ ቅዱስ ነው (ዘጸአት 25፡6)።

13. ቅመም የእግዚአብሔር አብ በክርስቶስ ደስ መሰኘት ነው (ዘጸአት 25፡6፤ ዘፍጥረት 8፡20፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡15፤ ኤፌ. 5፡2)።

14. የከበሩ ድንጋዮች የማይለወጥ የአማኞች በእግዚአብሔር ፊት የተወደደና ክብሩነት ነው (ዘጸአት 25፡7)።

15. በወርቅ የተለበጠው እንጨት የእግዚአብሔር (የክርስቶስ) ሰው መሆን ነው (ዮሐንስ 1፡14)።

16. አሥራአራቱ ዕቃዎች ሁለት ጊዜ ሰባት ማለት እግዚአብሔር ለሰዎች ሠርቶ የጨረሰላቸውን ሥራ ያመለክታል።

17. ዕጣን የጸሎት ምሳሌ ነው (ራእይ 5፡8)።

40. ሀ. ሙሴ በታቦቱ ውስጥ ምን እንዲያስቀምጥ ነው የተነገረው? ዕብ. 9፡4፤ ዘጸአት 25፡16።

መልስ።

ሙሴ በታቦቱ ውስጥ እንዲያስቀምጣቸው የተነገሩት ነገሮች።

1. በእግዚአብሔር እጅ የተጻፉ አሥርቱ ትእዛዛት ያሉበት የድንጋይ ጽላት (ዘጸአት 16፡21፤ ዕብ. 9፡4)።

2. መና ያለበት የወርቅ መሶብ (ዘጸአት 16፡33፤ ዕብ. 9፡4)።

3. የበቀለች የአሮን በትር (ዘኁልቁ 17፡10፤ ዕብ. 9፡4)።

ታቦቱም በማደሪያው ድንኳን ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳት ሥፍራ ተቀመጠ። በውስጡም የእግዚአብሔር ቃል ነበረበት። የመንፈስ ቅዱስ ቤት መቅደስ የሆነው ቅዱስ ሥፍራ የእግዚአብሔር ልጆች ልብ ነው። በዚህም በልባቸው ውስጥ የክርስቶስ ዙፋን አለ። በልባቸው የሚኖረውም የእግዚአብሔር ቃል በአክብሮት ሆኖ እየታዘዙት መጠበቅ አለበት [መዝሙር 118(119)፡11]።

40. ለ. ሙሴ በታቦቱ ላይ ምን አስቀምጦ ነበር? ዘጸአት 25፡17-21። መልስ።

የስርየት መክደኛው ነበር በታቦቱ ላይ ይቀመጥ የነበረው። በዘጸአት 25፡17-21 ባለው ክፍል ላይ ሙሴ የሥርየቱን መክደኛ እንዴት እንደሚሠራ መምሪያ ተሰጥቶታል። መሰራት የነበረበት ከንጹሕ ወርቅ ነበር። ሁለቱም ኪሩብ ማለት መላእክት በሥርየቱ መክደኛ ጠርዞች ላይ ፊታቸውን አንዳቸው ወደ ሌላው መልሰው ክንፋቸውን በስርየት መክደኛው ላይ ይዘረጋሉ። ሁለቱም ፊታቸውን ትይዩ በማድረግ ጎንበስ ብለው የስርየት መክደኛውን ይመለከታሉ። ይህም የሥርየት መክደኛ የእስራኤል ንጉሥ የሆነው የክርስቶስ ዙፋን ነው።

40. ሐ. ይህ ስፍራ የእስራኤል ንጉሥ ከሕዝቦቹ ጋር የሚገናኝበትና የሚተባበርበት ስፍራ እንደመሆኑ መጠን ምን ጠሊቅ የሆነ ነገር ያስተምረናል? ዘጸአት 25፡22።

መልስ።

የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ክርስቶስ ሕዝቡ እስራኤል በደም፥ በኑዛዜና በእምነት ሊቀርቡት ቢወዱ ምሕረትን ሊያሳያቸው በስርየት መክደኛው ላይ ሆኖ ሊገናኛቸው ይወዳል። እነርሱም በደም፥ በኑዛዜና በእምነት ባይቀርቡት

ይፈረድባቸዋል። ዛሬም ቢሆን ማንም በክርስቶስ ደም በእምነት ወደ እግዚአብሔር ቢቀርብ ምሕረትና ይቅርታን ይቀበላል፤ ነገር ግን ከዚህ በተለየ ሌላ መንገድ ማንም እግዚአብሔርን ሊቀርብ ቢሞክር የሞት ፍርድ በላዩ ይደርስበታል። ሁለቱም ማለት ፍርድና ምሕረት ከአንድ ስፍራ ይመጣል፤ በክርስቶስ ደም በኩል ከሆነው በቀር ሌላ ምንም ዓይነት ደኅንነት የለም።

1. የስርየት መክደኛው የእስራኤል ንጉሥ የሆነው የክርስቶስ ዙፋን ነው።

2. የስርየት መክደኛው በእግዚአብሔር በሚመሰለው በወርቅ ነው የተሠራው።

3. የስርየት መክደኛው የተጋደመበት ታቦት ደግሞ በክርስቶስ ይመሰላል። እርሱም በክርስቶስ ሰብአዊነት በሚመስለው እንጨት የተሠራው ነበር። እርሱም በእግዚአብሔር በሚመስለው በወርቅ ተለብጦአል። ኢየሱስ ክርስቶስም ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

4. በታቦቱም ውስጥ እግዚአብሔር ለሰው የተናገረበት ሕጋዊ ቃል አለበት። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 1፡1-5)።

5. መና ያለበት የወርቅ መሶብ፥ መና ከሰማይ የወረደ እንጀራ ነው። እርሱም የሕይወት እንጀራ ሊሰጠን ከእግዚአብሔር ዘንድ በወረደው በክርስቶስ ይመሰላል (ዕብ. 9፡4፤ ዮሐ. 6፡22-59)።

6. የአቆጠቆጠችው የአሮን በትርም በእግዚአብሔር ዘንድ በእንደራሴነት በሚቀርብልን በሊቀ ካህናችን በክርስቶስ ይመሰላል (ዕብ. 9፡1-15)።

41. ሀ. የማደሪያው ድንኳንና አገልግሎቱ በምን ይመሰላል? ዕብ. 8፡5፤ 9፡11፥ 12።

መልስ።

የማደሪያው ድንኳን በሰማያዊ ነገር ሲመሰል፥ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ የሚደረገው አገልግሎት ደግሞ ክርስቶስ ሰዎችን ለመዋጀት ባደረገው ሥራ ይመሰላል። ሊቀ ካህኑ በሬ፥ በግና ፍየል አርዶ ደማቸውን ይዞ ለሕዝቦቹ የበደል ይቅርታ እንዲሆን ወደ ስርየት መክደኛው እንደሚያመጣ ሁሉ ክርስቶስ ደግሞ ራሱን መሥዋዕት ካደረገ በኋላ የሰው ልጆችን ከኃጢአታቸው ለመዋጀት የገዛ ራሱን ደም ይዞ ከአባቱ ፊት አቀረበው። ራሱን መሥዋዕት ያደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህን ስለሆነ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በራሱ ደም ሰላምን መሠረተ።

41. ለ. የሚመሳሰሉበትን ወይም ምሳሌአቸውን ስጥ።

መልስ።

1. የማደሪያው ድንኳን የሚከተሉት ነገሮች ምሳሌ ነው።

ሀ. የሰማያዊ ነገሮች (ዕብ. 9፡23፥ 24)።

ለ. የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚኖርበት ቤተ ክርስቲያን (ዘጸአት 25፡8፤ ኤፌ. 2፡19-22፤ ማቴ. 18፡20)።

ሐ. የአማኞች (2ኛ ቆሮ. 6፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡19)። በማደሪያው ድንኳን ያሉት ዕቃዎች ሁሉ የክርስቶስ የራሱ ምሳሌዎችና የሰውን ልጆች ለማዳን ያደረገው የሥራው ምሳሌዎች ናቸው።

2. ታቦቱም የተሠራው ከእንጨት ነበር፤ (ሰብአዊነት) በወርቅም ተለብጦ ነበር፤ (እግዚአብሔር) (ዘጸአት 25፡10-16)። የማደሪያው ድንኳን የያዘው ሁሉ በክርስቶስ ይመሰላል።

ሀ. በአማኞች ልብ ያለው የእግዚአብሔር ሕግ ክርስቶስ (ቃል) ነው።

ለ. በታቦቱ ውስጥ ያለው መና የእግዚአብሔር ሕዝቦች በምድረ በዳ ውስጥ የበሉት ምግብ ነው (ዘጸአት 16፡33)። ይህም ምግብ ከሰማይ በወረደው የሕይወት እንጀራ ማለት በክርስቶስ ይመሰላል (ዮሐ. 6፡22-59)።

ሐ. ያቆጠቆጠችው የአሮን በትር በትርዋ ከሞት ወደ ሕይወት ተነስታ እንዳቆጠቆጠች ሁሉ እንደዚሁም ክርስቶስ ከሞት በመነሳት የእግዚአብሔር ሊቀ ካህን ሆኖአል (ዘኁልቁ 17፡10)። እግዚአብሔር የሞተችውን የአሮንን በትር በተአምር ሕይወት ሰጥቷት እንድታቆጠቁጥ በማድረግ አሮንን የእስራኤል ሊቀ ካህን አድርጎ እንደመረጠው ሁሉ እንደዚሁም እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ከመቃብር በማስነሳት ሊቀ ካህን አድርጎ መርጦታል።

3. ዘጸአት 25፡17-22 በታቦቱ ላይ ያለው የስርየት መክደኛ በሰማይ ያለው የክርስቶስ ዙፋን ምሳሌ ነው። በስርየት መክደኛው ፊት ኃጢአት ሁሉ የሞት ፍርድን ይቀበላል። ሊቀ ካህኑ ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ በመናዘዝ ደም ይዞ ወደ ስርየቱ መክደኛ በሚቀርብበት ጊዜ ብቻ ለራሱም ሆነ ለሕዝቡ ምሕረትን ይቀበላል። እርሱም ሆነ ሕዝቦቹ በኃጢአታቸው የተናዘዙት ክርስቶስ መጥቶ እንደሚሞትላቸው ስለ አመኑ ነው (ሮሜ 3፡24-26)።

4. ዘጸአት 25፡23-30 የኅብስቱም ጠረጴዛ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ጠረጴዛውም የተሠራው ከእንጨት ነው። (የክርስቶስ ሰብአዊነት) በወርቅም ተለብጦአል። (የክርስቶስ መለኮታዊነት) ኢየሱስ ክርስቶስም ሰው የሆነ አምላክ ነው። በጠረጴዛውም ላይ 12 ኅብስቶች ነበሩ። እያንዳንዱም ኅብስት ለእያንዳንዱ ለ12ቱ የእስራኤል ነገድ ነው። 12ቱ ኅብስት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ የሚበቃ ምግብ እንደሆነ ያመለክታል።

ጠረጴዛውም ኅብስቱን የሚሸከምበት 4 እግሮች አሉት። ዛሬም በአዲስ ኪዳን ዘመን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የሕይወት እንጀራን የተሸከሙ 4 ወንጌላት አሉን (ቁጥር 30)።

ሀ. ኅብስቱም እንደ ሕይወት እንጀራ በመታየት ለአንድ ሳምንት ያህል በጠረጴዛው ላይ ይቀመጥ ነበር። የሕይወት እንጀራ የሆነው ክርስቶስም ዘወትር መታየት አለበት።

ለ. ከሳምንትም በኋላ ካህኑ በጠረጴዛው ላይ ያለውን ኅብስት በልቶ በምትኩ አዲስ ኅብስት በጠረጴዛው ላይ ያኖራል። ኢየሱስም ሁልጊዜ ለተራበች ነፍስ አዲስና ትኩስ ነው።

ሐ. ተከታታይ ኃይል እንዲሰጣቸው ኅብስቱን የሚመገቡት ካህናቶች ነበሩ። እንደዚሁም አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናቶች ስለሆኑ የክርስቶስን ሥራ በትጋት ለመሥራት አከታትለው ኃይል ከክርስቶስ መቀብል ይችላሉ (1ኛ ጴጥ. 2፡9፤ ራእይ 1፡6)። መና ሕይወትን ሰጥቶአል። ክርስቶስም ከሰማይ የወረደ እንጀራ ነው።

መ. ኅብስቱ የተሠራው ከስንዴ ነበር (ዮሐንስ 12፡24)። ስንዴውም በመከራ ወፍጮ ከተፈጨ በኋላ (ዮሐንስ 12፡27) እንዲበስል ወደ ፍርድ እሳት መጣ (ዮሐንስ 12፡31-33)። ክርስቶስም እኛ ሕይወትና መንፈሳዊ ኃይል እንዲኖረን በዚህ ሁሉ ውስጥ አለፈ (ዕብ. 12፡2፥ 3)።

5. ዘጸአት 25፡31-40 የወርቁ መቅረዝ ደግሞ የዓለም ብርሃን በሆነው በክርስቶስ ይመሰላል። ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ ንጹሕ ወርቅ ነው። ስለዚህም የዓለም ብርሃን ነው።

ሀ. የወርቁ መቅረዝ ከአንድ ሙሉ ወርቅ እንደተሠራ ሁሉ እግዚአብሔር ደግሞ አንድ ነው።

ለ. መቅረዙም ሰባት ቅርንጫፎች አሉት። ሰባት ቁጥርም የፍጹምነት ምልክት ነው። እግዚአብሔርም ፍጹም ነው።

ሐ. በማደሪያው ድንኳን ከእርሱ በቀር ምንም ሌላ ብርሃን የሚሰጥ ነገር የለም። የማደሪያው ድንኳንም ምንም መስኮት የለውም። በመስኮት የሚገባ ማንኛውም የተፈጥሮ ብርሃን ማለት በዚህ ዓለም ጥበብ የሚመሰለው ብርሃን ለእግዚአብሔር ልጆች ልብ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ብርሃን ሊሰጥ ከቶ አይችልም። እርሱም ለእግዚአብሔር እንደሞኝነት ነው። የእግዚአብሔር ልጆችም ንጹሕ ብርሃን ከሚሰጠው ከመንፈስ ቅዱስ ጥበብን ይቀበላሉ። በአማኞች ልብና በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተፈጥሮ ብርሃንና የተፈጥሮ ጥበብ እንደሞኝነት ነው። ለእግዚአብሔር አገልግሎት ትርፍ ያለው ነገር መንፈሳዊ ጥበብ ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡5-16፤ 1፡20)።

መ. ብርሃኑን ማየት የሚችሉት ካህናቶቹ ብቻ ነበሩ። ከእነርሱ በቀር ማንም ሰው በተቀደሰው በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ለመሆን አይፈቀድለትም ነበር። እንደዚሁም ሁሉ መንፈሳዊ ካህናቶቹ የሆኑት አማኞች ብቻ የእግዚአብሔርን

መንፈሳዊ ብርሃን ማየት ይችላሉ። ዓለም ግን ለዚህ መንፈሳዊ ብርሃን ታውሮአል።

ሠ. መቅረዝ ሆኖ በተሠራ ጊዜ ወርቁ በሰው ልጆች ተቀጥቅጦ ነበር። ኢየሱስም የእኛ ብርሃን ለመሆን በፍርድ ተመታ።

ረ. የመቅረዙን መጠን የሚገልጽ ምንም ዓይነት ልክ አልተሰጠም። ከመቅረዙ በቀር በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ያሉት ቁሳቁሶች ሁሉ መጠን ተለክቶ ተገልጾአል። ነገር ግን ብርሃናችን የሆነው ክርስቶስ ግን ውሳኔና መጠን የለውም። መቅረዙ አንድ ሜትር ተኩል ቁመትና አንድ ሜትር ስፋት እንዳለው ይገመታል።

ሰ. በመቅረዞቹ ላይ ሰባት አበባዎችና ሰባት ፍሬዎች ተሰርተውበታል (ዘጸአት 25፡31)። የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ብርሃንም እንደዚሁ ሁልጊዜ መንፈሳዊ ፍሬና አበባ እንድናወጣ ያደርገናል።

ሸ. ለመብራቱ ብርሃን እንዲሰጡ በሰባቱ መቅረዝ የተደረገው ዘይት በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል።

ቀ. ዘጸአት 25፡38 መቅረዙን ለማጽዳት የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች መቅረዙን ሁልጊዜ ንጹሕና የሚያብረቀርቅ ያደርጉታል። የመቅረዙ ማጥሪያ መሳሪያዎች የተሠሩት ከንጹሕ ወርቅ ነው። ወርቅም በእግዚአብሔር ይመስላል። ሰውም መሳሪያዎቹን ይዟአል። በሰው ፈቃደኛነት ብቻ እነዚህ መሳሪያዎች ብርሃኑን ያጸዱታል። እንደዚሁም በራሳችን ፈቃድ ብቻ መንፈስ ቅዱስ አጽድቶን የተሻለ ምስክሮቹ እንድንሆን ያደርገናል። እንግዲህ ይህም የሚወስነው እኛ ለእግዚአብሔር ለማብራት ፈቃደኞች እንደመሆናችንና ላለማብራት ደግሞ ኃጢአትን በልባችን ሰውረን ብርሃናችንን በመሸፈናችን ነው። በዚህ አድራጎታችን መንፈስ ቅዱስ ፈቃዳችንን ይፈጽምልናል።

6. ውስጠኛው መጋረጃ (ዘጸአት 26፡31-35፤ 27፡16-19፤ ዮሐ. 10፡9)። ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳትን ለመለየት በመካከላቸው መጋረጃ ተሰቅሎ ነበር። በቅድስት ውስጥ የዕጣን ማጨሻ የኅብስቱ ጠረጴዛና መቅረዝ አለበት። ካህኖቹም ዕለት ዕለት በቅድስት ውስጥ ሆነው ያገለግሉ ነበር። በቅድስተ ቅዱሳት ውስጥ ግን ያሉት ታቦቱና የስርየት መክደኛው ብቻ ናቸው። እነርሱም የንጉሣቸው የክርስቶስ ዙፋን ነበር። ያ መጋረጃ ሕዝቦቹን ከእግዚአብሔር (ከክርስቶስ) ለይቷል። ሊቀ ካህኑም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ለሕዝቡ የኃጢአት ይቅርታን ለመቀበል ከደም ጋር ወደ ቅድስተ ቅዱሳት ይገባል። ክርስቶስም በመስቀል ላይ በሞተ ዕለት ሁሉ ወደ ውስጥ ማየት እንዲችል መጋረጃው ከላይ እስከ ታች ድረስ ተቀደደ። ይህም ማለት ሕግ አለቀ አበቃለት ማለት ነው። አሁን እንግዲህ ያለምንም ሊቀ ካህን አማላጅነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የተነሳ ማንም በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር መምጣት ይችላል።

መጋረጃው በክርስቶስ ይመሰላል። ይኸውም ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው አንድ መንገድ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ያመለክታል (ዕብ. 10፡20)። መጋረጃውም የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ በሞተ ጊዜ መጋረጃው ተቀደደ። ሰዎችም በቀጥታ እግዚአብሔርን መገናኘት ይችላሉ። ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ተከፍቶልናል።

ሀ. መጋረጃው እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳት ሰዎችን ሁሉ የሚያደርስ አንድ መንገድ ብቻ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም ዓለምን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ አንድ ብቸኛ በር ነው (ዮሐ. 10፡9)።

ለ. በበሩ ላይ መጋረጃው ተሰቅሎ ነበር። ክርስቶስም ተሰቀለ (ዘዳግም 21፡23፤ ገላትያ 3፡13)።

ሐ. የተሰቀለውም በአራት ምሰሶዎች ላይ ነበር (ዘጸአት 26፡23)። የኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ መሰቀል በአራቱ ወንጌላት ከፍ ተደርጎ ተገልጾልናል። ይህም አራቱ ምሰሶ የአራቱ ወንጌላት ምሳሌ እንደሆነ በብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች የሚታመንና የተስማሙበት ነው።

መ. መጋረጃው በወርቅ በተለፉ ኩላቦችና ከብር በተሠሩ ምሰሶዎች ላይ ተሰቅሎ ነበር (ዘጸአት 26፡32)። ወርቁን ማለት እግዚአብሔር አብ ክርስቶስን ስለ እኛ ኃጢአት ፈረደበት። ብር ማለትም የመዋጀቱ ፍቅር ኢየሱስን በመስቀል ላይ እንዲሰቀል አደረገው።

ሠ. መጋረጃውም ሰማያዊ መልክ ነበር። ክርስቶስም ከሰማይ የወረደ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ልጅ ነው። የዮሐንስ ወንጌል በዚህ መልክ ይገልጸዋል።

ረ. የመጋረጃው ሌላ መልክ ደግሞ ሐምራዊ ነበር። ሐምራዊም የንጉሥ መልክ ነው። ኢየሱስም የአይሁድ ንጉሥ ነበር። ማቴዎስም እንደ ንጉሥ ይገልጸዋል።

ሰ. መጋረጃው ደግሞ እንደ ደም ቀይ ነበር። (ቀይ) ኢየሱስም የኃጢአት መሥዋዕት ነበር። ማርቆስም በዚህ መልክ ይገልጸዋል (ዕብ. 9፡22)።

ሸ. መጋረጃውም የተሠራው ከጠራ የተልባ እግር ነው። ኢየሱስም በደል የሌለበት ሰው ሆነ። ይህም ደግሞ በሉቃስ ወንጌል ተገልጧል (ራእይ 19፡8)።

ቀ. መጋረጃውም ለሁሉ የሚበቃ ስፋት አለው። ይኸውም ደግሞ ዓለም ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ቢመጣ ተቀባይነትን ለማግኘት እስከሚችልበት መጠን ድረስ ማለት ነው።

በ. ሁሉም ሰው በኃጢአቱ ቢናዘዝ በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር የመምጣት መብት አለው (ዮሐ. 1፡12)። በዘጸአት 39 ለ ያለውን ጥያቄ መልስ ተመልከት።

7. ዘጸአት 27፡1-8 የናስ መሠዊያ። የናሱ መሠዊያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ምንም በደል ሳለ ራሱን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ባቀረበበት በተሰቀለበት መስቀል ይመሰላል (ዕብ. 9፡14)።

ሀ. መሠዊያው ፍርድን ከሚያመለክተው ከናስ የተሠራ ነበር። መስቀልም እንደዚሁ የፍርድ ምሳሌ ነው። በመስቀል ላይ የሚሰቀለው ወንጀለኛ ነው።

ለ. ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደተደረገ መሥዋዕቱ ደግሞ በመሠዊያው ላይ ይደረግ ነበር።

ሐ. መሥዋዕቱ በመሠዊያው ላይ ሆኖ ይቃጠል ነበር። ኢየሱስም ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ እሳታዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ስለ እኛ ተቀበለ።

መ. ማንም የናሱን መሠዊያ ቸል በማለት ወደ እግዚአብሔር መምጣት አይችልም። ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ አስቀድሞ የኑዛዜ መሥዋዕቱን ማቅረብ ይኖርበታል። እንደዚሁም በመስቀሉ ሥር ሆኖ በእምነት ኃጢአቱን ሳይናዘዝ ማንም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ አይችልም። ስለዚህ በክርስቶስ በኩል ብቻ ካልሆነ ማንም በሌላ በኩል ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ቢሞክር ከእግዚአብሔር ፍርድ በቀር ምሕረትን አይቀበልም። የናስ መሠዊያ በማደሪያው ድንኳን በር ላይ የቆመው በመጀመሪያ የደም መሥዋዕት እንዲቀርብበትና ከዚያም በኋላ እግዚአብሔርን ለማገልገል ወደ እግዚአብሔር መድረስ እንዲቻል ነው።

8. የዕጣን መሠዊያ (ዕጣን) ዘጸአት 30፡1-10። የዕጣኑ መሠዊያ ክርስቶስ የእኛ አማላጅ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። መሠዊያውም ከእንጨት ተሠርቶ በወርቅ የተለበጠ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም ሰውና አምላክ ነው (ዮሐ. 17፡1-26፤ ዕብ. 7፡15)። ጸሎታችንም በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ያርጋል (ዕብ. 13፡15፤ ራእይ 8፡3፥ 4)። አሁን አማኞች ሁሉ ካህናት ናቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡9)። ጸሎታቸውና ምስጋናቸውም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል (ዕብ. 13፡15)። ዕጣንም በጸሎት ይመሰላል። በመሠዊያው ላይ ያለውን ዕጣን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመንፈስ ቅዱስ እሳት ላይ ሆኖ በሚጸለይ ጸሎት ይመሰላል (ሮሜ 8፡26፥ 27)። ልብ በመንፈስ ቅዱስ እሳት በሚፈረድበት ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማል። እሳት በሌለበት ቦታ ወደ ላይ የሚያርግ ጢስ እንደማይኖር ሁሉ ያለ መንፈስ ቅዱስ እሳት የሚጸለይ ጸሎትም አይሰማም።

9. መታጠቢያ ሳህን (መታጠቢያ) (ዘጸአት 30፡17-21)። መታጠቢያው የተሠራው ፍርድን ከሚያመለክት ከናስ ነው። ሳህኑም መታጠቢያውን ውኃ ይዟል። ትርጉሙም ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከበደል ለማንጻት ፍርዳችንን እንደተቀበለ ሲያሳይ ነው። ካህናቱም ለእግዚአብሔር አገልግሎታቸውን ለመስጠት ከመጀመራቸው በፊት በመጀመሪያ አስቀድመው በየጠዋቱ

እግራቸውንና እጃቸውን በመታጠቢያው ውስጥ ይታጠባሉ። ይህም እጥበት የሚመስለው ለደኅንነታችን በክርስቶስ ደም መታጠባችን ሳይሆን በየዕለቱ ለእግዚአብሔር ሥራ ብቁዎች ለመሆን ከጥቃቅን በደላችን ለመንጻት የምናደርገው መታጠብ ነው። ስለዚህ ይህ እጥበት ዕለት ዕለት ከክርስቶስ ጋር ስንራመድ ሳለን ከኃጢአታችን ሁሉ ለመታጠብ የምንቀበለው መታጠብና ይቅርታ ነው። በዮሐንስ 13፡2-10 ባለው ክፍል የተጠቀሰው የእግር መታጠብም ተመሳሳይ ትርጉም የያዘ ነው (ኤፌ. 5፡25-27)። ካህናቱ በቅዱሱ ስፍራ ከማገልገላቸው በፊት እግራቸውንና እጃቸውን መታጠብ ነበረባቸው። እንደዚሁም አማኝ የሆነ ሰውም በየዕለቱ እግዚአብሔርን ከማገልገሉ አስቀድሞ በልብ በአሳብና በአድራጎት ከረከሰበት ነገር ሁሉ መንጻት ይኖርበታል። በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ በኃጢአታችን ምክንያት ካዘነ እግዚአብሔርን ልናገለግል አንችልም (1ኛ ዮሐ. 1፡9፤ ዕብ. 10፡22)።

42. የምዕራፍ 28 ና 29 ትምህርት ምንድን ነው?

መልስ።

ምዕራፍ 28 ና 29 የሚናገረው ስለ ክህነት ነው። ይህም እንዴት ለክህነት እንደሚታጩ ስለ ልብሳቸው፥ እንዲሁም ስለ ሥራቸውና ምግባቸው ነው።

43. ሊቀ ካህኑ የሚሠራው ታላቁ የሊቀ ክህንነት ተግባር ምንድን ነው?

መልስ።

ሊቀ ካህኑ በክርስቶስ ኢየሱስ ይመሰላል። ምክንያቱም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ስለሚማልድ ነው። በደም በመጠቀም ስለ በደላቸው የተናዘዙትን ሰዎች ለይቅርታ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባቸዋል። በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሕዝቡ ለማማለድ ሊቀ ካህኑ ብቻ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ይገባ ነበር። እንደዚሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ በደላችን የፈሰሰውን የገዛ ደሙን ይዞ በሰማይ ባለው ቤተ መቅደስ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ገባ። በዚያም በደላቸውን ለተናዘዙት ኃጢአተኞች ሁሉ ይቅርታን ሊቀበልላቸው ይማልዳል። ከክርስቶስ በቀር በእግዚአብሔር ዘንድ የኃጢአት ስርየትን ሊያስገኝልን የሚችል በእግዚአብሔር የተመረጠ ሌላ ሊቀ ካህን ፈጽሞ የለንም። ከእርሱ በስተቀር ስለ ሰዎች ኃጢአት በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲማልድ የተሰጠ ማንም የለም (1ኛ ጢሞ. 2፡5 ዕብ. 8፡1-6፤ 9፡12፤ ምዕ. 7)።

ከዚህ ጋር አያይዘህ ዘጸአት 30፡7-10 አንብብ።

1. ሊቀ ካህኑ በዕጣኑ መሠዊያ ውስጥ ዕጣን አከታትሎ ያጨሳል፤ ይህም ደግሞ ለሕዝቡ አከታትሎ ለሚያደርገው መማለድ ምሳሌ ነው። የዕጣኑ ጢስ ወደ እግዚአብሔር የሚያርገው በጸሎት ምሳሌ ነው። አሁንም በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ የሚሠራው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዕብ. 7፡25)።

2. ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ መብራቱ እንዲበራ አዘጋጀው (ዘጸአት 27፡20፥ 21፤ 30፡7፥ 8)።

3. ያመቱን ማስተሰርያ ያዘጋጃል (ዘሌዋውያን ም. 16)።

ሀ. ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለዘለዓለም የኃጢአት ስርየት እንዲሆን ራሱን መሥዋዕት አድርጎት እንደሰጠ ካህኑ በየዓመቱ የደም መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ያቀርብ ነበረ (ዕብ. 9፡12)።

ለ. በዓመትም አንድ ጊዜ ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳት ይገባ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም አንድ ጊዜ የራሱን ደም ይዞ በሰማይ በእግዚአብሔር ዘንድ አቅርቦአል (ዕብ. 9፡12)።

ሐ. የተልባ እግር ልብስ ለብሶ ወደ ቅድስተ ቅዱሳት ይገባል። የተልባ እግር የጽድቅ ምሳሌ ነው። ሰው የሆነው ኢየሱስም የጽድቅን ክብር ተጎናጽፎ ወደ ሰማይ አረገ (ዘሌዋ. 16፡4)። የእኛም ኃጢአት በእርሱ ላይ አልቀረም ነበር።

መ. እርሱም የተልባ እግር ልብስ ተጎናጽፎ ከቅድስተ ቅዱሳት ወጣ። ኢየሱስም ሙሽራይቱን ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተመልሶ ይመጣል።

4. ነዶውንም ለመጀመሪያው የመከር ፍሬ በዓል ወስዶ ይወዘውዘዋል (ዘሌዋ. 23፡11)። ይህም የክርስቶስና የጥቂት ቅዱሳን ትንሣኤ ምሳሌ ነው (ማቴ. 27፡52)።

5. እርሱም ሁለት በእርሾ የተጋገሩ ዳቦዎችን አንስቶ በጴንጠቆስጤ ቀን ወዘወዛቸው (ዘሌዋ. 23፡20)። ኢየሱስም ቤተ ክርስቲያናትን ለእግዚአብሔር አቀረበ። እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። ነገር ግን አሁንም በዚህ ኃጢአትን በሚወድ ሥጋ ውስጥ ስለአቀደ በተጋገረው ቂጣ ውስጥ ጥቂት እርሾ ተፈለገ (ዘሌዋ. 23፡17፤ ሮሜ 12፡1)።

6. በመማጸኛው ከተማ ያሉትን ሰዎች ሕይወት ለመጠበቅ ይከላከላል (ዘኍልቁ 35፡25)። ኃጢአተኛ በክርስቶስ ብቻ ሊድን ይችላል። ነፍሰ ገዳዩም ሊቀ ካህኑ እስኪሞት ድረስ በመማጸኛው ከተማ ውስጥ ይቀመጥና ሊቀ ካህኑ ሲሞት ፍጹም ነፃ ይወጣል (ዮሐንስ 8፡36)።

7. ነገሥታትን ሁሉ ይቀባል። ክርስቶስም በምድር ላይ ባሉት ነገሥታት ላይ ሁሉ የነገሥታት ንጉሥ ሆኖ ይገዛል (ሮሜ 13፡1፤ ዳን. 4፡17፥ 25፤ 32፤ 2፡21፤ 5፡21)።

ዘጸአት ምዕራፍ 30 እስከ 40 ያለውን አንብብ።

44. ሰንበት በእግዚአብሔርና (በክርስቶስና) በእስራኤል መካከል ያለ ምልክት እንደሆነና የሰንበትን ትርጉም አብራራ (ዘጸአት 31፡12-17፤ ዕብ. 4፡4-11)። ሰንበት እስራኤላውያንን ምን ያስተምራቸዋል?

መልስ።

በዘጸአት 31፥13 እግዚአብሔር የሰንበትን ትርጉም ይገልጻል። «ይህም በእግዚአብሔርና በሕዝበ እስራኤል መካከል የቆመ የዘለዓለም ምልክት ነው።» ሰንበትም እስራኤላውያን ድነው ወይም አልዳኑ እንደሆነ የሚያሳይ በእግዚአብሔርና በሕዝበ እስራኤላውያን መካከል ያለ ምልክት ነው። ሰንበት በእግዚአብሔርና በመንፈሳውያን ሕዝቦቹ መካከል ማለት የክርስቶስ ቤተ መቅደስ በሆኑ አማኞች መካከል ያለ ምልክት አይደለም። ነገር ግን ይህ የተሰጠው የደኅንነትን መንገድ የሚያሳያቸው ጥሩ ምሳሌ እንዲሆኑ ሥዕላዊ ማስረጃ ለእስራኤላውያን የተሰጠ ነው። «እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ሁሉ አረፈ።» ስለዚህ እስራኤላውያንም ጌታ ዓለምንና በዓለም ያለውን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ በመጨረስ በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ ሁሉ እነርሱም በዚህ ቀን ማረፍ አለባቸው። ከዚህም በቀር ለደኅንነታቸው የሚሆነውን ሥራ ሁሉ ሠርቶ ጨርሶአል። ደኅንነታቸውም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል (በሞቱ) ጨርሶታል። ማንም ደግሞ በዚህ ላይ የሚጨምረው ሥራ የለም። በዚህ ፋንታ ግን በክርስቶስ ተሠርቶ ያለውን ደኅንነት በእምነት ተቀብለው ነፍሳቸውን ማርካት ነው። ሕግ ለእስራኤላውያን የተሰጠው የጠፉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ሲረዱ ወደ ክርስቶስ መጥተው በእምነት እንዲድኑ መሪ እንዲሆናቸው ነው (ገላትያ 3፥24)። እግዚአብሔርም ሃይማኖታዊ የሕግ ሥርዓቶችን በማድረግ ለደኅንነታቸው በዚህ እንዲታመኑ አልፈለገም። እግዚአብሔር ሰንበትን እንዲያከብሩ የሰጣቸው ለማስጠንቀቂያ እንጂ ለደኅነታቸው አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት በኩል የሚድኑበትን መንገድ አዘጋጅቶ ስለሰጣቸው በእምነት ብቻ ስለሚድኑ የእነርሱ ሥራ ከንቱ እንደሆነ ለማስረዳት ነው።

እግዚአብሔርም የሰንበትን ማክበር ትእዛዝ ልኮ በአሥርቱ ቃላት መኃል አኖረው፤ ይህም የተደረገበት ዋናው ምክንያት ሕጎቹን በእምነት በልባቸው እንዲጠብቁ እንጂ በሥራቸው እንዲመኩ አይደለም። ማንም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ካልሆነ በቀር አሥርቱን ትእዛዛት በራሱ ኃይል የመፈጸም ግዳጅ ቢጣልበት እግዚአብሔርን መውደድ አይችልም። ሰንበትም በሚያደርጉት ሥራቸው እንደሚጸድቁ አላመለከታቸውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሥራውን ሠርቶ ጨርሶላቸዋል። እነርሱም በእምነት ተቀብለው ብቻ ማረፍ ነበረባቸው።

አንድ ሰው በሰንበት ቀን የሠራ እንደሆነ የሞት ቅጣት ይቀበል ነበር። ይህም ደግሞ ሕዝቦቹ ለራሳቸው ደኅንነት የሠሩ እንደሆነ እንደሚፈረድባቸው ለማመልከት ነው። ምክንያቱም ሥራው በክርስቶስ መስቀል ላይ ተሠርቶ አልቋል። ማንም በአለቀው በክርስቶስ ሥራ ላይ ለመዳን የራሱን ሥራ ቢያክልበት የክርስቶስ ሥራ በቂ እንዳይደለ የሚገምት ያላመነ ሰው ነው። የኃጢአት ዋጋ የሃይማኖት ሥርዓት ሳይሆን ሞት ነው። በዚያም ሞት ክርስቶስ

ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ተሰቃይቷል። ሥራውም አልቋል። ይህንን እስራኤላውያንም ሆኑ እኛ አምነን መቀበል አለብን።

ምንም እንኳ ሕግ ለእስራኤላውያን የተሰጠ ቢሆንም ለደኅንነታቸው በሕግ ሥራ ስለተመኩ አደጋ ገጥሟቸዋል። ሰንበትም የእግዚአብሔር ምድራዊ ሕዝብ ለሆኑት ለእስራኤላውያን የተሰጠው በሥራ እንዳይመኩና በዚህ ፋንታ ግን ለደኅንነታቸው እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሠርቶ የጨረሰውን ሥራ እንዲቀበሉ ለማስጠንቀቅ ነው። ስለዚህ ዛሬ ሰዎች ሰንበትን በመጠበቅ ለመዳን ቢሞክሩ ወይም በደኅንነታቸው ላይ ተጨማሪ ጽድቅ ለመጨመር ሰንበትን ቢያከብሩ በራሳቸው ሥራ እንጂ እግዚአብሔር ሠርቶ በጨረሰላቸው ሥራ ባለማመናቸው ከፍርድ በታች ናቸው። ምክንያቱም ደኅንነት በእምነት እንጂ በሥራ ስለማይገኝ ነው።

በዕብ. 4:4-11 ባለው ክፍል ላይ ደግሞ በተጨማሪ የሰንበት ትርጉም ተገልጿል። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት የሰንበት እረፍት ትርጉም እስራኤላውያን በኢየሱስ ተመርተው ከነዓን እንደገቡ የሚያመለክት አይደለም (ቁጥር 8)። ዳዊትም ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ ብሎአል (ቁጥር 7)። አሁንም ገና ሌላ እረፍት አለ (ቁጥር 9)። ዳዊት ይህንን ያለው እስራኤላውያን በከነዓን ውስጥ ከኖሩ ከረጅም ዓመታት በኋላ ነው። የሰንበት እረፍት ነፍሳችን በእግዚአብሔር እጅ ማረፏን ያመለክታል። ይህም በሥራ የተገኘ ነገር እንዳልሆነ ለማመልከት እግዚአብሔር ራሱ ሥራውን ጨርሶ አሳያቸው (ቁጥር 10)። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ በሰንበት ቀን እንዳረፈ በሥራቸው እንደማይጸድቁ አውቀው የታከቱትንና በእምነት ለደኅንነታቸው በእግዚአብሔር የሚታመኑትን እግዚአብሔር በዕለተ ሰንበት እንዳረፈ ወደ ሰንበት እረፍት ያስገባቸዋል። ይህውም እረፍት የሚገኘው ክርስቶስ ሠርቶ በጨረሰው በአንድ የእምነት መንገድ ብቻ ነው። ወደዚህ እረፍት መግባት የሚቻለው የራሱ ሥራ ታክቶት ባለቀው በእግዚአብሔር ሥራ የሚያምን ሰው ብቻ ነው። ይህም ሰው መልካም ሥራ የሚሠራው አዲስ ፍጥረት በመሆኑ እንጂ ደኅንነትን ለመቀበል አይደለም። ስለዚህ አማኝ ሁሉ በእምነት ገና ዱሮ ወደ እረፍት ስለገባ የሰንበት ምሳሌነትና ሰንበት ከእንግዲህ ወዲያ አያስፈልገውም። ብዙዎቹ እስራኤላውያን ወደ ሰንበት እረፍት ስላልገቡ ወደ እረፍቱ ለመግባት እንዲችሉ መንገዱን እንዲመራቸው ሰንበት አስፈልጓቸው ነበር።

45. ሀ. ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በተራራው ላይ በነበረ ጊዜ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የተካሄደውን ኪዳን እንዴት አፈረሰ?

መልስ።

ምዕራፍ 32:1-6 እስራኤልም በሌላ አማልክት በእግዚአብሔር ፊት እንዳያመልኩና እግዚአብሔርንም በፍጹም ልባቸውና ኃይላቸው እንዲወዱ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ገብተዋል። ነገር ግን ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር

በተራራው ላይ በሆነ ጊዜ ሕዝቦቹ የጥጃ ጣዖት ሠርተው በፊቱ መስገድ ጀመሩ። በዚህም መንገድ ቃል ኪዳኑን አፈረሱ።

45. ለ. ታዲያ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን እንዴት ተመለከተ?

መልስ።

ምዕራፍ 32:7-10 በእግዚአብሔር ፊት ይህ አድራጎታቸው በሞት ሊያስቀጣቸው የሚገባ ጥፋት ነው።

አሮንና እስራኤላውያን ግን ቃል ኪዳን አፍርሰው ኃጢአት መሥራታቸውን እንደታላቅ ኃጢአት አልቆጠሩትም። እነርሱም ይህ አድራጎታቸው ኃጢአት እንዳልሆነ አድርገው በልባቸው ለራሳቸው ምክንያት ሰጡት። እግዚአብሔርንም በጥጃው ፊት ያመለኩት መሰላቸው (ዘጸአት 32:6)። እነርሱም የሚቃጠል መሥዋዕትና የደኅንነት መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር አቀረቡ። አሮንም «ይህ የእግዚአብሔር በዓል ነው» ብሎ አወጀ (ዘጸአት 32:5)።

ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ለሥዕል ወይም ለተቀረጸ ምስል በሚሰግዱበት ጊዜና በሚጸልዩበት ጊዜ ያ ሥዕል ወይም የተቀረጸ ምስል ጣዖታቸው ይሆናል። መሪያቸውም አሮን በሕዝቡ ፊት ለራሱ ይቅርታ በማድረግ «እግዚአብሔርን በዚህ የጥጃ ጣዖት ፊት እናመልካለን» ብሎ ምክንያት ሰጠ። ሕዝቦቹም በአራተኛው ቁጥር እንደተናገሩት ይህ አምላካችን ነው አሉ። እግዚአብሔር ሕዝቦቹ አምላካቸው እንዲሆን የጥጃውን ምሳሌ ወስደዋል አለ (ቁጥር 8)። በዚህ አንጻር ማንም በሥዕል ወይም በምስል ፊት ወድቆ በመስገድ የሚጸልይ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ጣዖትን እንዳመለከ ይቆጠርበታል (በዘጸአት 20:2-4)። እግዚአብሔርን ይህን ዓይነት አምልኮት በጥብቅ ይከለክላል።

ጥጃው የግብፅ ሃይማኖት ምሳሌ ነው። ይኸውም ግብፅ በዓለም ስለምትመሰል ነው። አማኞችም በቀድሞ ሕይወታቸው የዓለምን ነገር ይናፍቁ ነበር። ይህም ማለት እነርሱም ጥጃ ያመልኩ ነበር ማለት ነው።

45. ሐ. ሙሴ ለሕዝቡ ይቅርታ የጠየቀው በተለይ ምን አሳስቦት ነው? ምዕ. 32 ና 33። 32:11-14፥ 30-35፤ 33:12-17።

መልስ።

ሙሴ ለእስራኤላውያን ይቅርታ ለመጠየቅ የተደገፈው እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በገባው ቃል ኪዳን ላይ ተመርኩዞ ነው (ቁጥር 13)። እግዚአብሔርም እስራኤልን ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርግና በዘራቸውም የዓለምን ሕዝብ እንደሚባርክ ተስፋ ገብቶ ነበር። ዓለምም ይህን አውቃ ነበር። አሁን እግዚአብሔር እስራኤልን ቢያጠፋ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን አልጠበቀም በማለት በእግዚአብሔር ላይ መፍረድ ትጀምራለች። ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዳያጠፋ ከአምላኩ ጋር የተከራከረው የእግዚአብሔር ተስፋ እውነት ስለሆነ ነው (በምዕራፍ 32:7)። እግዚአብሔር

ሙሴን እስራኤላውያንን ያንተ ሕዝቦች አለው። ሙሴም መልሶ በቁጥር 11 ላይ እግዚአብሔርን «ያንተ ሕዝቦች» ናቸው አለው። እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝቦችህ ሲለው እስራኤላውያን ከእንግዲህ ወዲያ ሕዝቦቼ አይደሉም ማለቱ ነው። ሙሴ ግን እግዚአብሔርን ሕዝቦችህ ናቸው ሲለው እንደ እነርሱ ሳይሆን ለአብርሃምና ለይስሐቅ እንደዚሁም ለያዕቆብ እንደገባኸው ቃል ኪዳን ሕዝቦችህ ናቸው ማለቱ ነው።

በምዕራፍ 32፡30-35 እንደተገለጸው ሙሴ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት እግዚአብሔርን ሊማልድ ወደ ተራራ ወጣ። ሙሴ ሕግን ማፍረስ በሞት ፍርድ እንደሚያስቀጣ ያውቅ ነበር። ነገር ግን በቁጥር 32 ላይ «ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው» ብሎ ጠየቀ። ሆኖም እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ሳይፈርድ እንዲሁ ይቅር ብሎ እንደማያልፍ ያውቅ ነበር። ስለዚህ ሙሴ ለእስራኤል ምሕረትን ለመቀበል ፍርዳቸውን በራሱ ላይ ለመውሰድ እራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። በቁጥር 32 ላይ ያለዚያ ግን «ከጻፍከው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ» አለ። ሙሴ ራሱ ኃጢአተኛ ስለሆነ ለኃጢአት ማስተሰርያ ሆኖ መቅረብ አይችልም። እግዚአብሔርም በቁጥር 33 ሙሴን «የበደለኝን እርሱን ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ» አለው።

ምዕራፍ 33 ላይ እግዚአብሔር እስራኤልን በመንገዳቸው ላይ እንደላካቸው እንመለከታለን። ቢሆንም ሙሴ እስራኤላውያን ኃጢአተኞች በሆኑበት ጊዜ ሙሴም እግዚአብሔርን አንድ ጥያቄ ጠየቀው፤ ይኸውም ኃጢአተኛ የሆነው የእስራኤል ሕዝብ እንዴት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊሆን ይችላል ብሎ ጠየቀ (ምዕራፍ 33፡13)። በምዕራፍ 33፡14 ላይ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደሚሆን ነግሮታል። ነገር ግን ሙሴ እግዚአብሔርን ከእስራኤል ጋር ደግሞ የሚሆንበትን ማረጋገጫ ስለፈለገ እግዚአብሔር ከእነርሱም ጋር እሆናለሁ አለው (ዘጸአት 33፡15-17)። እግዚአብሔርም ከእስራኤላውያን ጋር የሚሆንበት ጉዳይ ከምን የተነሣ እንደሆነም ከዚያም በኋላ ከሌላው የዓለም ሕዝብ የተለዩ ነገዶች መሆናቸውን ለሙሴ አሳየው።

46. እግዚአብሔር (ክርስቶስ) በምን ዓይነት ጠባይ ነው ከእስራኤል ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን መልሼ አድሰዋለሁ ያለው? 34፡4-10።

መልስ።

እግዚአብሔርም ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መልሶ ለማደስ ሙሴ ወደ ተራራው እንዲመጣ ጠራው። እግዚአብሔርም ራሱን እንደሚከተለው ገለጸ።

1. ኃጢአትን ይቅር ብሎ ምሕረትን የሚያደርግ።

2. ነገር ግን በደለኛውን ከቶ የማያነጻ አምላክ ነው (34፡6፥ 7)። እግዚአብሔር በደለኛውን እንዳልበደለ አድርጎ ማየት ከቶ አይችልም። ኃጢአት ሁሉ በሞት ይቀጣል። የአንድ ኃጢአተኛ ኃጢአት ኃጢአቱን ተሸክሞ በምትኩ

ፍርድን በሚቀበልለት ሰው ላይ ሲሆን እግዚአብሔር ምሕረትን ያደርግለትና ይቅር ይለዋል። ኃጢአት መፈረድ አለበት። ነገር ግን የበደለኛው ኃጢአት በክርስቶስ ላይ ሆኖ ከተፈረደ ኃጢአተኛው ይቅር ይባላል። ሙሴ በምዕራፍ 32፡32 ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በምትክነት አቅርቦ ነበር። ነገር ግን ያ በቂ አልነበረም። ምትክ መሆን የሚችለው በደል የሌለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መካከል የኖረው ከክርስቶስ ኢየሱስ የተነሣ ነው። ምክንያቱም ኃጢአታቸው ሁሉ በክርስቶስ ላይ ስለነበረ ነው።

ሙሴም እግዚአብሔር በዘጸአት 34፡6፥ 7 ላይ የተናገረውን በሰማ ጊዜ እግዚአብሔርን በግምባሩ ወድቆ አመለከ። ምክንያቱም እግዚአብሔርን በቁጥር 9 የተናገረው ነገር ትርጉም ስለገባው ነው። ሙሴም እግዚአብሔርን እስራኤል አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አንተ በመካከላችን ኑርና ሕዝቦችህ አድርጋቸው። ኃጢአታቸውም በሌላ ሰው ላይ ሆኖ ይቀጣል፥ ከዚያም በኋላ እስራኤል ነፃ ትሆናለች።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ያደሰው እርሱ ክርስቶስ መጥቶ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ስለሚሞት ነው። ከዚህ በስተቀር ቃል ኪዳኑ የሚታደስበት ሌላ መንገድና መነሻ ፈጽሞ የለውም (ዘጸአት 34፡10-17)።

ስለዚህ እስራኤል መምረጥ ይኖርባታል። የማደሪያው ድንኳንም የተተከለው ከሠፈር ወጣ ብሎ ነበር። ሰዎቹም የሚያመልኩት በየድንኳናቸው በራፍ ላይ ሆነው ነበር። እያንዳንዱም በነፍስ ወከፍ ስለ ክርስቶስ መወሰን አለበት። ከዚያም እግዚአብሔር (ክርስቶስ) በመኃላቸው ለመሆን በማንኛውም ሰው ላይ ሳይፈርድ ይመለሳል (ዘጸአት 33፡7-10)። አሁንም ቢሆን ኃጢአትን በልቡ ሰውሮ መንፈስ ቅዱስን በሚያሳዝን አማኝ እግዚአብሔር አይጠቀምበትም። እርሱም በኃጢአቱ ተናዝዞ ከበደሉ ካልራቀ የእግዚአብሔርን ቅጣት ይቀበላል።

47. ሀ. ሙሴ በዚህን ጊዜ በተራራው ላይ ከእግዚአብሔር (ከክርስቶስ) ጋር ለምን ያህል ቀን ቆየ? ደግሞስ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በቆየበት ጊዜ ምን የሚታይ ነገር ተፈጸመ?

መልስ።

ሙሴም ከጌታ ጋር በተራራ ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየ (ዘጸአት 34፡28)። ያን ጊዜ ነበር ሙሴ ሕግጋቶቹን የጻፈው (ቁጥር 27)። እርሱም በዘፍጥረት መጽሐፍ የሆነውን ነገር ፈጽሞ አያውቅም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቅ ስለነበረ ሊጽፍ የሚገባውን ነገረው።

ከእግዚአብሔር (ከክርስቶስ) ጋር አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ስላሳለፈ ፊቱ እጅግ እንዳንጸባረቀ ከተራራው ሲወርድ ሕዝቦቹ ፊቱን ሊያዩት ፈጽሞ አልቻሉም። ስለዚህ ፊቱን በመሸፈኛ መሸፈን ግድ ሆነበት። ያም በልቡ ውስጥ የገባው የእግዚአብሔር ክብር ነው በውስጡ አልፎ በፊቱ ላይ የሚያንጸባርቀው።

አሁንም ቢሆን አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር በኃይል ቀርቦ በዕለት ኑሮው ከእግዚአብሔር ጋር በቅርብ ከተጓዘ ፊቱ ዘወትር ያበራል። ስለዚህ አንድን አማኝ በማየት ከእግዚአብሔር ጋር ምን ያህል የቀረበ ኅብረት እንዳለው ማወቅ ይቻላል (ዘጸአት 34፡27-35)።

47. ለ. ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ የሚገኘው ነገር ይህ ብቻ እንደሆነና ታላቁም ነገር ይኸው ነው ብለህ ነው የምትገምተው?

መልስ።

እንደዚያ ያለው ወደ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) መቅረብ በፊት ላይ ከሚያስከትለው ይልቅ በልብ የሚያስቀረው ለውጥ የላቀ ነው። ፊት በልብ ያለውን ነገር ብቻ ያሳያል። እስጢፋኖስም በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞላ ፊቱ እንደመልአክ ፊት ያበራ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 6፡15)።

47. ሐ. ከዘጸአት እንደተረዳኸው ሙሴ ጌታ ኢየሱስን ምን ያህል የሚያውቀው ይመስልሃል?

መልስ።

ሙሴ ጌታን ፊት ለፊት ያውቀዋል። ሰውም ከጓደኛው ጋር እንደሚናገር አናግሮታል (ዘጸአት 33፡11)።

47. መ. ክርስቶስ በተራራው ላይ በተለወጠ ጊዜ ሙሴ በምን ጉዳይ ላይ ነበር ከክርስቶስ ጋር ይነጋገር የነበረው? ሉቃስ 9፡30-31።

መልስ።

ሙሴና ኤልያስ ከ1500 ዓመት በኋላ ከክርስቶስ ጋር ተገናኝተው የተነጋገሩት በቅርብ ጊዜ ሊሆን ስላለው ስለ ክርስቶስ ሞት ነው። ሙሴ የእስራኤል ሥጋዊ መሪ ሲሆን ኤልያስ ደግሞ መንፈሳዊ መሪያቸው ነው። ክርስቶስ ግን ንጉሣቸው ነው። ንጉሡም እስራኤል በኖረችበት ዘመን ሁሉ ከቶ ኖሯት በማታውቀው ሁለት የተለዩ መሪዎችዋ ጋር ውይይት ያደርግ ነበር። በዓለም ታሪክ ውስጥ ሆኖ ስለማያውቀው ስለ አንድ ታላቅ ነገር ይነጋገሩ ነበር። ያም ጉዳይ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኩል ስለሚያገኘው ደኅንነት እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ጉዳይ (ጎዳና) የሚያወሳ ነበር። ይህም ሙሴ ከመሞቱ በፊት ገና በዓለም ሳለ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ያ ሁሉ የአምልኮት ሥርዓትና እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሁሉ የሚያሳየው ክርስቶስንና የመዋጀቱን ሥራ ነበር።

47. ሠ. ይህን ሁሉ የማወቁ ጉዳይ በክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ላይ ምን አስከተለ? ዕብ. 11፡23-29።

መልስ።

ሙሴ ክርስቶስንና የማዳኑን የተስፋ ኪዳን ሁሉ ስለሚያውቅ እንደዚሁም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያለውን ዘለዓለማዊውን ታሪክ ስለተገነዘበ ምንም የዓለምንና የሥጋን ነገር ሳይቀላቅል እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡናና ኃይሉ አገለገለ። «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበር» (ዘኁልቁ 12፡3)።

ኢየሱስን ከቀድሞ ይልቅ እጅግ እየወደድነውና እያወቅነው ስንሄድ የሥጋ ፍላጎታችንና ዓለምን የመውደዳችን ጉዳይ እየደከመና እየሟሸሸ ስለሚሄድ በእግዚአብሔር ሥራ ይበልጥ ታማኞችና ፍሬአማ እየሆንን እንሄዳለን።

48. ከምዕራፍ 35-40 ያለው ክፍል ምን ያስተምራል?

መልስ።

ከምዕራፍ 35-40 ድረስ ያለው ክፍል ስለ ማደሪያው ድንኳናን የካህናት ልብስ ያብራራል።

49. ሀ. የንጉሡ በሕዝቡ ዘንድ በስፍራው መገኘት ለሕዝቡ እንዴት በቀላሉ ተረዳቸው? ዘጸአት 40፡34-38።

መልስ።

ደመናውም የማደሪያውን ድንኳን ሸፈነው። የእግዚአብሔርም ክብር የማደሪያውን ድንኳን ሞላው። በዚህ ሁናቴ ጌታ በእነርሱ መኃል ለመኖር ወደ ማደሪያው ድንኳን እንደገባ ለሕዝቡ አሳያቸው። የማደሪያውን ድንኳን ቀን ደመና ሲሸፍነው ሌሊት ደግሞ እሳት ይሸፍነው ነበር። በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) በመካከላቸው እንዳለ ይመለከቱ ነበር። ንጉሣቸው ክርስቶስም መንገዱን ሁሉ እስከ ከነዓን ድረስ በእሳትና በደመና ዐምድ ይመራቸው ነበር።

እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ወደ ሰለሞን መቅደስ በተመሳሳይ ሁኔታ ነው የመጣው (2ኛ ዜና 7፡1-3)። ሰውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ለመኖር ወደ ሕይወቱ ይገባል (1ኛ ቆሮ. 6፡19)።

49. ለ. ይህ ምድራዊ መኖሪያው መች ይሆን መለኮታዊ መኖሪያው ለመሆን ምልክት የሚሆንበት?

መልስ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለ1000 ዓመት በምድር ሊነግሥ ሲመጣ በተመሳሳይ ሁናቴ ለሕዝቡ ይገለጣል (ኢሳ. 4፡4-6፤ ዘካርያስ 14፡16-21)።

# ኦሪት ዘሌዋውያን።

ኦሪት ዘጸአት እንደ አዲስ ኪዳን ወንጌላት የመዋጀውን መግለጫ ይሰጣል። ደግሞም የተዋጁት ሕዝቦች እንዴት እንደሚነጹና እንደሚያገለግሉት ይገልጻል። ኦሪት ዘሌዋውያን ደግሞ እንደ አዲስ ኪዳን መልእክቶች ስለ እነዚያ ሰዎች አምልኮ ጉዞና አገልግሎት በይበልጥ ጠለቅ ብሎ ያስረዳል። በዘጸአት እግዚአብሔር ማንም እንዳይቀርበው በተከለከለበት ተራራ ላይ ሆኖ ይናገር ነበር። በዘሌዋውያን ደግሞ በሰዎች መካከል በሚኖርበት የማደሪያው ድንኳን ውስጥ ሆኖ ይናገር ነበር። እዚያም ሆኖ እንዴት አድርገው ከእርሱ ጋር ኅብረት እንደሚኖራቸው ያስተምራቸው ነበር።

የዘሌዋውያን መጽሐፍ መክፈቻ ቃል «ቅድስና» ይባላል። ይህም ቃል 87 ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። መክፈቻ ቁጥሩ ደግሞ ዘሌዋውያን 19፡2 ነው። «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።»

የዘሌዋውያን አከፋፈል።

1. 1፡1-6፥ 7 መሥዋዕቶች።
2. 6፡8-7፡38 የመሥዋዕቶች ሕግ።
3. 8፡1-9፡24 ለእግዚአብሔር መለየት።
4. 10፡1-20 የማስጠንቀቂያ ምሳሌ።
5. ከምዕራፍ 11-15 ለቅዱስ አምላክ የነጹ ሰዎች ሊኖሩት ይገባል።
6. ከምዕራፍ 16-17 እርቅ።
7. ከምዕራፍ 18-22 የእግዚአብሔር ሕዝቦች ኅብረት።
8. ምዕራፍ 23 የይሖዋ በዓሎች።
9. ከምዕራፍ 24-27 መምሪያና ማስጠንቀቂያ።

1. በኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ውስጥ ሌዋውያን ካህናት ያደርጉት የነበረው ሥርዓተ አምልኮ በእስራኤልና በንጉሣቸው መካከል ስላለው ኅብረት ምን ይገልጻል?

መልስ።

ሥርዓታዊው ሕግ ለእስራኤላውያን የተሰጠበት ምክንያት በሚያደርጉት ሥርዓተ ምሳሌነት ወደ እግዚአብሔር እንዴት መቅረብ እንደሚችሉና በእርሱም እንዴት ተቀባይነትን እንደሚያገኙ ለማወቅ ነው። በተለይም በሚያቀርቡት መሥዋዕት ታይቷል። ከዚህም በቀር ይህ ሥርዓት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት

እንዲኖራቸው አሳይቷቸዋል። በተጨማሪ ደግሞ በአጠገባቸው የሚኖረውን እግዚአብሔርን ሳያሳዝኑ እንዴት መኖር እንደሚችሉ አስተምሯቸዋል።

2. ይህ ሥርዓታዊ ደንብ ለእስራኤል የተሰጠው ይህንን ሥርዓት በማድረግ እንዲጸኑ ነው ወይስ ለሌላ የተለየ ጉዳይ የተሰጠ ነው? መዝ. 50(51)፡16-19 እና ኢሳ. 1፡11-18 ተመልከት።

መልስ።

ይህ በመዝ. 50(51)፡16-19 እና በኢሳ. 1፡11-18 የተጠቀሰው ጥቅስ እግዚአብሔር ይህን ሥርዓታዊ ሕግ ለእስራኤላውያን የሰጠው ሥርዓቱን በማድረግ ይጸድቃሉ፥ ወይም ደግሞ ሥርዓቱን በመጠበቅ እግዚአብሔርን ያስደስታሉ ተብሎ እንዳልሆነ በሚገባ ያስረዳል። ይህ ሥርዓታዊ ሕግ ለእስራኤላውያን የተሰጠበት ምክንያት ኃጢአታቸውን በመናዘዝ፥ በእምነት ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ያስተምራቸዋል። እግዚአብሔር እምነትና ኑዛዜ ሳይኖርበት የሚደረገውን ሥርዓተ አምልኮ በዓልና መሥዋዕት እጅግ ይጸየፈዋል (ገላትያ 3፡24)።

በተጨማሪ ደግሞ በመዝ. 4፡5፤ 26(27)፡6፤ 49(50)፡14፤ 50(51)፡16-19፤ ኤርምያስ 7፡21-23፤ ሆሴዕ 6፡6፤ ማቴ. 9፡13፤ 12፡7፤ ሚክያስ 6፡6-8፤ 1ኛ ሳሙ. 15፡22፤ ማቴ. 23፡23፤ ሆሴዕ 14፡2፤ ኢሳ. 1፡11-18።

3. እነዚህ ከዚህ የሚከተሉት የዘሌዋውያን ሥርዓታዊ ደንቦች እንዴት ተመርጠው በመቆየት እንደተላለፉ አሳይ። ሀ. ጸጋ ለ. እምነት ሐ. ኅብረት መ. ጽድቅ ሠ. ተስፋ

መልስ።

ሀ. ጸጋ፡- እግዚአብሔር የኃጢአት ዋጋ ሞት እንደሆነ በሕግ አሳይቷል። ሕግም ሰዎች ሁሉ የተፈረደባቸው ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያሳያል (ሮሜ 3፡20፤ ያዕቆብ 2፡10)። ለምሳሌ ያህል ሕግ «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር» ይላል (ዘጸአት 20፡16)። ስለዚህ ውሸተኞች ሁሉ ሕግን እንዳፈረሱ ስለሚያውቁ ይፈረድባቸው ነበር።

ሥርዓታዊው ሕግ የእግዚአብሔር ጸጋ ለኃጢአተኞች ምሕረትን እንደሚሰጥ ያሳያል። የደሙም መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ስለ ኃጢአታቸው እንደሚሞት አከታትሎ ያሳስባቸው ነበር። ያውም ደግሞ እነርሱ በኃጢአታቸው ከተናዘዙና ከኃጢአታቸው ፍርድ እንደሚድኑ ያመኑ እንደሆነ ነው። እንደዚሁም ሰንበት እግዚአብሔር ዓለምንና በዓለም ያለውን ነገር ፈጥሮ በጨረሰ ጊዜ እንዳረፈ ሁሉ የሕዝቡን ደኅንነት ደግሞ ሠርቶ መጨረሱን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ማንም ሰው በዚህ እግዚአብሔር

በክርስቶስ በኩል ሠርቶ በጨረሰው ሥራ በእምነት ቢመጣ ወደ ነፍሱ እረፍት ይገባል። በዚህ መንገድ ሥርዓታዊው ሕግ ምሕረትንና ጸጋን ያሳያል።

ስለዚህ እነርሱ ይህንን እረፍት በሥራቸው ለማግኘት ስለሞከሩ የእግዚአብሔር ፍርድ ወደቀባቸው። ምክንያቱም ደኅንነት ንስሐ በመግባት በእምነት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነፃ ስለሆነ ነው።

ለ. እምነት:- ይህ ሥርዓታዊ የሆነ ሕጋዊ ደንብ ለኃጢአተኞች ደኅንነት የሚገኝበትን መንገድ በሞላ አቅርቦላቸዋል። የመሥዋዕቱ አቀራረብ ሥርዓት ኃጢአትን በመናዘዝ የሚደረገውን ንስሐ ያመለክታል። ከዚህም በቀር ለመሥዋዕት የሞተው እንስሳ የክርስቶስን ሞት ያመለክታል። የደሙ መሥዋዕትና ሰንበት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን በክርስቶስ ላይ በመፍረድ የደኅንነታቸውን መንገድ እንደጨረሰ ያመለክታል። ከዚህም በቀር በእዳኙ በኩል እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋ በእምነት ተቀብለው ማመን እንዳለባቸው ያሳያቸዋል (ገላ. 3፡24)። በሕግ ኃጢአት ይታወቃል (ሮሜ 3፡20)።

ሐ. ኅብረት (ከጌታ ጋር የሚኖረን አንድነት):- በሚቃጠለው መሥዋዕት የኃጢአተኛው ኃጢአት ይቅር ይባላል። ምክንያቱም ኃጢአቱን ይመጣል ተብሎ በተስፋ ለሚጠብቀው ክርስቶስ በእምነት ስላቀረበ ነው። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምና ኅብረት ይኖረዋል። ከዚህ ወዲያ ኃጢአቱ ይቅር የተባለው ሰውዬ የፍቅርና የደስታ፥ የምስጋና መሥዋዕት የሆነውን የሰላም መሥዋዕት ያቀርባል። የኃጢአተኛው ኃጢአት ስለተወገደ ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትና አንድነት ይኖረዋል። ከዚህም በኋላ እንደ ዳዊት በሕግ ደስ ይለዋል፤ ምክንያቱም በክርስቶስ በኩል ያገኘውን ደኅንነት ስለሚያሳየው ነው [መዝ. 118(119)፡97፥ 35፡92፤ መዝ. 2]። ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሕሊና ያገኛል።

መ. ጽድቅ:- ሕግ እግዚአብሔር ኃጢአትን በመቅጣት ጻድቅ እንደሆነ ለኃጥአን ያሳያቸዋል። ሕግም ኃጢአተኛው ከኃጢአቱ ካልተለየና ጻድቅ ካልሆነ እንደሚፈረድበት ይነግረዋል። ይህንን በማየት ኃጢአተኛው የደኅንነትን መንገድ ስለሚናፍቅ ሥርዓታዊው ሕግ ወደ ክርስቶስ ያመለክተዋል። «እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኗል(ገላ. 3፡24)»። ኃጢአተኛው በክርስቶስ በሚመሰለው እንስሳ ላይ እጁን ጭኖ በኃጢአቱ በመናዘዝ ኃጢአቱን በእንስሳው ላይ ማድረግ ነበረበት። ከዚያም እንስሳው ታርዶ ሲያይ በእምነት ስለ በደሉ የሞተለትን ክርስቶስን ስለሚመለከት እንደ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል (ዘሌዋ. 1፡4፤ 3፡2፤ 16፡21፤ 4፡4)።

ሠ. ተስፋ:- ኃጢአተኛው በሕግ እንደተፈረደበት በአወቀ ጊዜ የሥርዓቱ ሕግ ክርስቶስ ስለ ኃጢአቱ የሞት ቅጣት እንደሚቀበልለት እንዳመነና በኃጢአቱ እንደተናዘዘ ይድናል። ሕጉ ሁለቱንም ነገሮች ያደርጋል። ማለት በኃጢአት ላይ ሲፈርድ እንደዚሁም የክርስቶስን የመዋጀቱን ሥራ በማሳየት የዘለዓለም ሕይወትን ተስፋ ይሰጣል።

4. ከዘሌዋውያን ምዕራፍ 1 እስከ 7 ድረስ ካለው ክፍል የመሥዋዕት ዓይነቶችን ጥቀስ።

መልስ።

1. ምዕራፍ 1 የሚቃጠል መሥዋዕት። የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት። ክርስቶስ ያለ ምንም ግድፈት ራሱን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦአል። የአራተኛውን ጥያቄ መልስ ተመልከት። የዚህ መሥዋዕት ሕግ በዘሌዋውያን 6፡8-23 ባለው ክፍል ላይ ይገኛል።

2. የእህል ቁርባን መሥዋዕቱ ጥራጥሬ ነበር። የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት። ክርስቶስ በሰብአዊነት ፍጽምና በመከራ ተፈተነ። የዚህ መሥዋዕት ሕግ ደግሞ በዘሌዋውያን 6፡14-23 ይገኛል። ለ5ኛ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ተመልከት።

3. ምዕራፍ 3 የደኅንነት መሥዋዕት። የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት። ክርስቶስ የእኛም ሰላም (ኤፌ. 2፡14-18)። የዚህ መሥዋዕት ሕግ በዘሌዋውያን 7፡11-21 ባለው ክፍል ይገኛል። የ4ኛውን ለ ጥያቄ መልስ ተመልከት።

4. ምዕራፍ 4 የኃጢአት መሥዋዕት። ጣፋጭ ሽታ ያልሆነ መሥዋዕት። ክርስቶስ የበደላችን የኃጢአት እርቅ ሆነ (ዕብ. 13፡11፥ 12)። የዚህ መሥዋዕት ሕግ በዘሌዋውያን 6፡25-30 ባለው ክፍል ይገኛል። የ5ኛውን ለ ጥያቄ መልስ ተመልከት።

5. ምዕራፍ 5 የበደል መሥዋዕት። ጣፋጭ ሽታ ያልሆነ መሥዋዕት። በኃጢአት ምክንያት ለመጣ ጉዳት ወይም ቁስለት ክርስቶስ እርቅ ሆነ። የዚህ መሥዋዕት ሕግ በዘሌዋውያን 7፡1-7 ባለው ክፍል ይገኛል። የ5ኛውን ለ ጥያቄ መልስ ተመልከት።

6. ምዕራፍ 6፡1-7 የበደል መሥዋዕት። የወሰደውን መመለስ። የዚህን መሥዋዕት ሕግ በዘሌዋውያን 7፡1-7 ባለው ክፍል ተመልከት።

ከምዕራፍ 1-3 ያለው ክፍል የሚገልጸው የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት የክርስቶስን ቅድስናና ፍጽምና ምሳሌ ነው። ጣፋጭ ሽታ ያልሆኑ መሥዋዕቶች ምሳሌነት ደግሞ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጥዕ እንደሆነልን ያሳያል። ሁለቱም ምሳሌዎች ክርስቶስ የሰው አዳኝ እንደሆነ ያሳያሉ (2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

5. እንደ እነዚህ እንደ እያንዳንዱ ስድስት መሥዋዕቶች ሥራ የሚመስለው መሥዋዕት ምን አንድ ታላቅና ጠቃሚ ተግባር ያሳያል? ይህስ በመሥዋዕቱ ሥርዓት በምን ዓይነት ሁናቴ ተገልጿል?

መልስ።

ምዕራፍ 1 የሚቃጠል መሥዋዕት (6፡8-13)። የሚቃጠለው መሥዋዕት ኃጢአተኛው ከክርስቶስ ጋር እንደሞተ ያመለክታል (ሮሜ 6፡6፤ ገላ. 2፡20፤ 5፡24)።

1. ለመሥዋዕትነት የሚመረጠው እንስሳ የክርስቶስን ምሳሌነት የያዘ መሆን አለበት። እንስሳውም ከመንጋዎች መካከል እንጂ የዱር እንስሳ መሆን የለበትም። ክርስቶስ ያለነቀፋ እንደሆነ እንስሳውም ያለነቀፋ የሆነ ንጹሕ መሆን አለበት (ዘሌዋ. 1፡2፥ 3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፥ 19)።

ኃጢአተኛውም እንስሳውን በፈቃደኝነት ማምጣት ነበረበት። በልቡም ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን ፍላጎት ሊኖረው ይገባል (ዘሌዋ. 1፡3)። ወደ ክርስቶስ የመቅረብን ኃላፊነት ተሸክሞ ለዓለም የተሰቀለ ሆኖ መገኘትን መፈለግ ነበረበት (ገላ. 6፡14፤ ዕብ. 13፡12፥ 13)።

ዘሌዋ. 1፡4 ኃጢአተኛውም እጁን በእንስሳው ራስ ላይ ያደርጋል። እርሱም ይህን በማድረጉ ከክርስቶስ ጋር ለእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ያሳያል። ክርስቶስ ለኃጢአቱ እንደሚሞትለት ኃጢአተኛው ደግሞ ዳግመኛ በዓለም ርኩሰት ላለመጠላለፍ ለዓለምና ለኃጢአት ይሞታል። ይህም ደግሞ ኑዛዜ ይባላል። እንግዲህ እዚህ ላይ ኃጢአተኛው በእምነት ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናል ማለት ነው [ዕብ. 9፡11-14፤ 10፡5-7፤ መዝ. 39(40)፡6-8፤ ፊልጵ. 2፡8]።

2. ምዕራፍ 1፡6 መሥዋዕት የሆነውም እንስሳ (ይገፈፋል)። ይህም በእግዚአብሔር ፊት ያልተሰወረና የተገለጠ መሆኑን ያሳያል። ኃጢአተኛውም እንደዚሁ ኃጢአቱን በእግዚአብሔር ፊት አይሰውርም። እርሱም ሁሉን ነገር በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ ልቡን በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ ያደርጋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአቱን ሁሉ እንዲመለከት ነው።

1፡8 የእንስሳውም ራስ ይቃጠል ነበር። እንደዚሁም የኃጢአተኛው ራስ ለእግዚአብሔር አልፎ በመሰጠት አሳቡ ሁሉ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል።

የእንስሳውም ልብ በመቃጠል ለእግዚአብሔር ይሰጣል። የኃጢአተኛውም ውስጣዊ መልካም ነገሩ ማለት ሕይወቱ ለእግዚአብሔር ይሰጣል። የልቡም ውስጣዊ መልካምና የተወደደውም ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ንብረት ነው።

1፡9 የሆድ ዕቃውና እግሮቹ በውኃ ከታጠቡ በኋላ በመሠዊያው ላይ ይቃጠላሉ። የኃጢአተኛውም ውስጣዊ ርኩሰትና በደል ሁሉ በሚያደርገው ኑዛዜና ክርስቶስን በመቀበል በክርስቶስ ይነጻል። የእንስሳው እግሮች የኃጢአተኛውን በዚህ ዓለም መመላለስ ይመስላሉ። እግሮቹም ታጠቡ። ኃጢአተኛውም አረማመዱን በእግዚአብሔር ፊት አንጽቶ ለእግዚአብሔር ቅዱስ አድርጎ ያስረክበዋል።

ይህም «ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ ነው።» ጌታም በዚህ ነገር እጅግ ደስ ይለዋል። ይህም ለእግዚአብሔር ብቻ በልብ በአእምሮና በአካሄድ መኖር ነው እንጂ ለሥጋ፥ ለዓለምና ለራስ መኖር አይደለም 1ኛ ጴጥ. 1፡8፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡14፤ መዝ. 118(119)፡11 ዕብ. 10፡5-10፤ ኤፌ. 5፡1]።

ለመቃጠል መሥዋዕት አምስት የተለያዩ እንስሳት ብቻ የተፈቀዱ ናቸው።

ሀ. በሬ፡- ዘሌዋ. 1፡5 እርሱም በታጋሽነት ለማገልገል ፈቃደኛነቱ በክርስቶስ ይመስላል (1ኛ ቆሮ. 9፡9፥ 10፤ ዕብ. 12፡2፥ 3)። ለሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ (ኢሳይያስ 52፡7-12፤ ፊልጵ. 2፡5-8)።

ለ. በግ፡- ዘሌዋ. 1፡10 በጉም የዋህና በደል የሌለበት በመሆኑና ለመሠዋት ፈቃደኛ በመሆኑ በክርስቶስ ይመሰላል (ኢሳ. 53፡7፤ የሐዋ. ሥራ 8፡32-35፤ ራእይ 13፡8)።

ሐ. ፍየል፡- ዘሌዋ. 1፡10 ክርስቶስ ያለ በደሉ እንደ በደለኛ በመቆጠሩ ፍየሉ በክርስቶስ ይመሰላል (ኢሳ. 53፡12)። ስለ እኛም «ኃጥዕና እርጉም» ሆነ (ገላትያ 3፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)። እርሱም የኃጢአተኞች ምትክ ሆኖ እንደ በደለኛ በመሆን በወንበዴዎች መካከል ተሰቅሎ ሞተ።

መ. ዋኖስና ርግብ፡- 1፡14 ሁለት ዓይነት ርግቦች አሉ። በየዋህነት ምንም ጥፋት ሳይኖርበት በሚቀበለው መከራ ይመሰላሉ። ማለት ክርስቶስ በደል የሌለበት ሲሆን ሳለ በየዋህነት ለበደላችን እንደቃተተ ያመለክታል (ኢሳ. 38፡14፤ 59፡11፤ ማቴ. 23፡37፤ ዕብ. 7፡26)።

ድሀ የሆነ ብቻ ነበር ርግብ የሚሰጠው (ዘሌዋ. 5፡7)። ክርስቶስም ሀብታም ሆኖ ሳለ ስለ እኛ ደኸየ (ሉቃስ 9፡58፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡9፤ ፊልጵ. 2፡6-8)። እነዚህ መሥዋዕቶች የሚቀርቡት መሥዋዕቱን በሚያቀርበው ሰው ድህነትና ሀብታምነት መጠን ነው።

የሚቃጠለው መሥዋዕት ክርስቶስን በአዳኝነቱ ያሳያል። መሥዋዕትን የሚያመጣው ኃጢአተኛ ራሱን ለክርስቶስ ይሰጣል። ይህንንም የሚያደርገው ከዓለም ከተመለሰ በኋላ ለዓለም ሞቶ ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን ነው።

ምዕራፍ 2 የእህል ቁርባን (ዘሌዋ. 6፡14-23) የእህል ቁርባን ከደም መሥዋዕት ጋር አንድ አይደለም፤ ነገር ግን ከዱቄት የሚሠራ እርሾ የሌለበት ቂጣ ነው (ዘሌዋ. 2፡4)።

1. ይህም መሥዋዕት ከመልካም ዱቄት የተጋገረ መሆን አለበት (ዘሌዋ. 2፡1)። ይህም ደግሞ በክርስቶስ ይመሰላል። ለእኛ የሕይወት እንጀራ ለመሆን እንደ ስንዴው በመረገም በብዙ ኃዘንና ሞት ተቀጣ። ማንኛውም መሥዋዕት የሚያቀርብ ሰው ራሱን ከክርስቶስ ጋር ይሰይማል። እርሱም ደግሞ በእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲያገኝ በንስሐ የተደቆሰና የተሰበረ ልብ ሊኖረው ይገባል። ካለዚያ ይህ ሁሉ መሥዋዕት በከንቱ መቅረቡ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መልካም ባሪያ ሆነ። ምክንያቱም ለእኛ በፈቃዱ መከራ ስለተቀበለ ነው። አማኞች መልካም የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንዲሆኑ በእውነተኛ ንስሐ ልባቸው የተሰበረ መሆን አለበት [መዝ. 50(51)፡17]።

2. ዱቄቱ በውስጡ የተደባለቀ ዘይት ሊኖረው ይገባል(ዘሌዋውያን 2፡1፤ 4፡7)። ዘይትም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ኢየሱስ ክርስቶስም ከመንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኖ ተወለደ። (ማቴ. 1፡18፥ 20፤ ሉቃስ 1፡35)። ከዚህም በቀር ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል። ኃጢአተኛውም በዚህ መሥዋዕት ራሱን ከክርስቶስ ጋር ይሰይማል። በእውነተኛ ኑዛዜ የተሰበረ ልብ ሲኖረው በዚህ ጊዜ በእውነት በኃጢአቱ አዝኖ ስለተጸጸተ ክርስቶስን በእምነት ይቀበልና መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጡ ይገባል። ከዚያም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ይሆናል። አንድ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ተባብሮ የኃጢአትንም ፍቅር ወደ ልቡ እንዳይገባ ካደረገ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሠራል። ምክንያቱም ዘይቱ በውስጡ ስላለ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡20-27)።

3. ቂጣውም በብረት ምጣድ ወይም በመጥበሻ ይጋገራል (2፡4፥ 5፥ 7)። በምጣድ መጋገሩ የክርስቶስን የሥጋ ሳይሆን የልብ መቃተት ይመስላል። መጥበሻው ግን ተከድኗል። ማንም ሰው በልብ ውስጥ የሚሆነውን መጋገር ማየት አይችልም። ማንም ደግሞ ክርስቶስ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ተሸክሞ የአባቱን ፍርድ ሲቀበል በልቡ የነበረውን መቃተት የሚያይ የለም (ዕብ. 2፡18፤ ማቴ. 27፡45-46)። ማንም ሰው እያየው በመጥበሻ ውስጥ የሚጠበሰው መሥዋዕት ማንም ሰው ሊያየው በቻለው በክርስቶስ ከባድ ጭንቀት ይመስላል (ማቴ. 27፡27-31)። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የመሰለውን መቃተት ስለቃተተልን የሕይወት እንጀራ ሆኖልናል።

ራሱን ከክርስቶስ ጋር ሰይሞ ለሚኖር ክርስቲያን ይህ በታላቅ ትኩሳት የሚጋገረው ቂጣ በክርስቲያን ዘንድ ራሱንና ሥጋውን ለመካድ በውስጡ ተጣብቆ ከዚያው ልማድ ለመላቀቅ በሚያደርገው ትግል ይመሰላል።

ይህም ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠትና የሥጋውንም ፈቃድ ለመተውም ሆነ እግዚአብሔር በፈለገበት ቦታ ሁሉ እንዲጠቀምበት ለማድረግ እራሱን ለእግዚአብሔር በሚሰጥ ሰው ሁሉ ላይ ያለ ትግል ነው። ይህ ነው እንግዲህ ብዙ አማኞች ስተው የወደቁበትና ያለ ፍሬ እንዲሆኑ ያደረጋቸው። እነርሱም ይህን የእህል ቁርባን ወደ እግዚአብሔር አያመጡም። በእግዚአብሔር የተጠሩ ቢሆንም እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠሩለት አልመረጣቸውም (ማቴ. 20፡16፤ 22፡14)። ምክንያቱም የምጣዱን ቃጠሎ ስለማይችሉት ነው። ማለት ልባቸውን ማንጻት አይሆንላቸውም። ከዚህም በቀር በዓለማውያን ስድብና ማሽሟጠጥ የሚመስለውን የመጥበሻውን ትኩሳት አይችሉትም።

4. ዘሌዋ. 2፡4፥ 15 ቂጣው ከተጋገረ በኋላ በዘይት ይለወሳል። ክርስቶስም በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቷል (ዮሐ. 1፡32)። አማኝ ዳግመኛ በተወለደ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ይሆናል (ቁጥር 1)። ነገር ግን በምጣዱ ላይ በተጋገረ ጊዜ ማለት ራሱን ለእግዚአብሔር ፈጽሞ ባስረከበ ጊዜ ለአገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ይቀባል (1ኛ ዮሐ. 2፡20-27)። ከዚያም በኋላ

ኃይል ይኖረዋል። ሁሉ በልብ ቅጣት የሚመስለውን የምጣዱን ጋገራ መሸከም ስለማይፈልጉ ሁሉ ለአገልግሎት አይቀቡም (1ኛ ቆሮ. 11፡31)።

5. ዘሌዋ. 2፡11 በመሥዋዕቱ ላይ ምንም ዓይነት እርሾ አይፈቀድም። እርሾ በኃጢአት ይመሰላል (ማቴ. 13፡33)። አንዱ ሰው ሊናዘዝበት የማይፈልገውን ኃጢአት በልቡ ሰውሮ ከያዘ እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሱን መሥዋዕት አድርጎ መስጠት አይችልም። ይህም በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው። እርሾ የደጎነት መሥዋዕት ቂጣ ውስጥ ብቻ እንዲደረግ ይፈቀዳል። ምክንያቱም እርሾ ገና በኃጢአት ስለሚኖር በኃጢአቱ ተናዞ ራሱን ነዋሪ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ በሚፈልግ አማኝ ይመሰላል (ሮሜ 12፡1፤ ዘሌዋ. 7፡13)።

6. በማንኛውም መሥዋዕት ውስጥ ማር እንዲደረግ አይፈቀድም (ዘሌዋ. 2፡11)። ማር የተፈጥሮ ጣፋጭነት ምልክት ነው። የተፈጥሮ ጣፋጭነታችንና መልካምነታችን እግዚአብሔርን ሊያገለግል አይችልም። ይህ የሥጋ ነው፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆነ ብቻ ነው በመንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን ማገልገል የሚችለው። ዛሬም እነርሱ በሚያደርጉት መልካም ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የሚጥሩና የሚታገሉ ሰዎች ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው። ይህም የማር መሥዋዕት ስለሆነ ተቀባይነት የለውም። ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር በእግዚአብሔር ዘንድ ከቶ ተቀባይነት አያገኝም።

7. በእህሉ ቁርባን ላይ ሁሉ ጨው መጨመር አለበት (ዘሌዋ. 2፡13፤ ማር. 9፡47፥ 50፤ ቆላ. 4፡6፤ ዘኍልቁ 18፡19)። ጨው ያነጻል። ጨው በቁስል በሚደረግበት ጊዜ በቁስሉ ላይ ያሉትን የሕመም ተውሳኮች ሁሉ ይገላል። በቁስል ላይ ሲደረግ ይለበልባል፥ ነገር ግን ይፈውሳል። እንደዚሁም ሰው የሚወዳቸውን ኃጢአቶች መተው በጣም ይከብደዋል። ነገር ግን ለመፈወስ ኃጢአቶች ግድ መተው አለባቸው፥ ጨው በቁስል ላይ ሲደረግ በቁስሉ ላይ ያሉትን ተውሳኮች እንደሚገድል ሁሉ የእግዚአብሔር ጨው የሆነው የእግዚአብሔር ቃልም የኃጢአትን ዘር እንዲያጠፋ በሰው ልብ ውስጥ መጨመር አለበት። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ በልቡ የተሠወረ ኃጢአት እንዳለ በተገነዘበ ጊዜ ሁሉ ያንን የቃሉን ጨው በልቡ መነስነስ አለበት። ይህም እግዚአብሔርን ያስደስተዋል።

ጨው ቂጣው እንዲጥምና እንዲጣፍጥ ያደርገዋል፥ እንደዚሁም የቃሉን ጨው በልቡ ውስጥ የሚያደርግም አማኝ በሰዎች ዘንድ ጥሩ ምስክርነት ይኖረዋል። «እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ (ማቴ. 5፡13)።»

8. ዕጣን ከመሥዋዕቱ ጋር ይቃጠላል (ዘሌዋ. 2፡16)። ዕጣን በምስጋና ይመሰላል። እግዚአብሔር ሕይወትን ሊሰጠን ክርስቶስን መሥዋዕት አድርጎ ስላቀረበልን እናመሰግነዋለን። ነገር ግን አሁን አማኞች ክርስቶስን በምድር ይወክሉታል። እነርሱም በራሳቸው ጥበብና ኃይል ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ

ኃይል ይሠራሉ። ለእነርሱም የሚቀርበው ምስጋና ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ብዙው የእህል ቁርባን ወደ ሰው ቢመጣ እንኳን የዕጣኑ መሥዋዕት ሁሉ ለእግዚአብሔር ነው። ማንኛውም የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሰው የሚቀርብለትን ምስጋና ቢቀበል እግዚአብሔርን ይሰርቃል። ምክንያቱም የመንፈሳዊ ሥራ ምስጋና ሁሉ የእግዚአብሔር ሀብት ስለሆነ ነው። ሰውዬው እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ዕቃ ብቻ ነው።

9. ከመሥዋዕቱ አብዛኛው ለሰው ሲሆን ጥቂቱ ለእግዚአብሔር ይሆናል (ዘሌዋ. 2፡16፤ 6፡14-16፥ 18)። ክርስቶስ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆነ። ነገር ግን ለሰዎች የሕይወት እንጀራ ነው። ስለሆነም ሰዎች ከእርሱ ከበሉ በሕይወት እንዲኖሩ ነው እርሱ መከራ ተቀብሎ የሞተው። መንፈሳዊ ብርታት እንዲያገኙና በሚገባ እንዲያገለግሉ ከእህሉ ቁርባን የሚመገቡት ካህናት ብቻ ነበሩ። ክርስቶስም ለካህናቱ የሕይወት እንጀራ ነው። አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት ናቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡9)። እነርሱም እግዚአብሔርን ለማገልገል ብርታትን ከክርስቶስ ይቀበላሉ።

<u>ምዕ. 3 የደኅንነት መሥዋዕት</u>። ክርስቶስ ሰላማችን ነው (ኤፌ. 2፡14-18፤ ዘሌዋ. 7፡11-21፤ 19፡5-8፤ 22፡21-25)። የምስጋና ወይም የሰላም መሥዋዕት በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር በተዋጁት አማኞች መካከል ያለውን ሰላም ያሳያል። ይህም የደስታ መሥዋዕት ነው። ሦስት ዓይነት የሰላም መሥዋዕቶች አሉ።

1. የምስጋና መሥዋዕት ዘሌዋ. 7፡11፥ 12 (ምስጋና)

2. የስዕለት መሥዋዕት ዘሌዋ. 7፡16 (ስዕለት)

3. የፈቃደኝነት መሥዋዕት ዘሌዋ. 7፡16 (ፈቃድ)

የክርስቲያኖች ሰላም የክርስቶስን ሥራ በሙሉ በምሳሌነት ያጠቃልላል። እርሱም ሰላምን አቆመ (ቆላ. 1፡20)። እርሱ ሰላምን አወጀ (ኤፌ. 2፡16፥ 17)። እርሱ ሰላማችን ነው (ኤፌ. 2፡14)። በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር አብና ኃጢአተኛ በሰላም ይገናኛሉ። እግዚአብሔር ይረካል፤ ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል። እግዚአብሔርም ሆነ ኃጢአተኛው ክርስቶስ በሠራው ሥራ ይረካሉ። ሆኖም ይህ ሁሉ የተገኘው በደሙና እንደ እሳት በሆነው መከራው በከፈለው ነው። በሰላሙ መሥዋዕት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተደረገው ኅብረት ይታያል።

<u>የምስጋና መሥዋዕት</u>፡- ከሦስቱ ዓይነቶች የሰላም መሥዋዕቶች የበለጠውና የላቀው ነው። ይህም መሥዋዕት በምስጋና ከተሞላ ልብ ለእግዚአብሔር የቀረበ ነው [መዝ. 106(107)፡8፥ 15፥ 21፥ 22፥ 31] «አ እነዚያ ሰዎች በእውነትም ጌታን ማመስገን ነበረባቸው።» አሁንም ቢሆን አማኞች የእርሱን ምስጋና በይበልጥ ማሳየት ይገባቸዋል (1ኛ ጴጥ. 2፡9)።

1. መሥዋዕት አቅራቢውም መሥዋዕቱን ከፍቅር ከምስጋና ልብ በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር ያቀርባል (ዘሌዋ. 19፡5፤ 22፡29፤ 3፡9-11፤ 3፡4፥ 14-16፤ መዝ. 72(73)፡28፤ ያዕ. 4፡8)።

2. መሥዋዕት አቅራቢው በመሥዋዕቱ ላይ እጁን ጭኖ ራሱን ከመሥዋዕቱ ጋር ሰይሞ «ክርስቶስ ራሱን እንደሰጠ እኔ ደግሞ በምስጋናና በሙሉ ልብ ሕይወቴን ሁሉ ለእግዚአብሔር አስረከብኩ» ይላል (ዘሌዋ. 3፡2)።

3. ዘሌዋ. 3፡2፥ 8 መሥዋዕት አቅራቢው ራሱ ያመጣውን መሥዋዕት ያርዳል። ይህም ደግሞ በግል ለእግዚአብሔር ያቀረበው ስጦታ ነው።

4. ዘሌዋ. 3፡3-5፤ 9፡11፥ 14-16። የውስጡን ማለት በጣም የተከበረውንና የተወደደውን ለእግዚአብሔር ይሰጣል። ይህም በውስጥ ያለ ልብና ኩላሊት ነው። ስለዚህ ቀድሞ መሥዋዕት አቅራቢው መልካሙንና የውስጠኛውን ክፍል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ እንደሚያቀርብ ሁሉ ዛሬም አማኝ የውስጡንና ለእርሱ እጅግ የከበረውን ነገር በሙሉ ከውስጣዊ ልቡ ከፍቅር መስጠት አለበት።

5. መሥዋዕት አቅራቢው ከቤተሰቡ ጋር በሙሉ ከካህኑ ጋር በጌታ ፊት ይበላል። ይህም በቤተሰቡ በካህናቶቹና በእግዚአብሔር መካከል ደስ የሚያሰኝ ኅብረት ነው (ዘሌዋ. 19፡5-8፤ ዘዳ. 12፡6፥ 7፥ 17፥ 18፤ 16፡10፥ 11)።

6. ዘሌዋ. 19፡7፥ 8 ከሦስት ቀን በኋላ መበላት የለበትም። እርሱንም መብላቱ አጸያፊ ነው። ይህም ከልብ የሆነውን ደስታ አለማወቅ ነው። በዘልማድ የሚደረግ ሥርዓታዊ አምልኮ ነው። ከልብ ደስታ የመነጨ ምስክርነት ጌታን ደስ ያሰኘዋል። ነገር ግን አንድ ዓይነት ምስክርነት በየጊዜው እየተደጋገመ የሚሰጥ ከሆነ ይህ ምስክርነት በዘልማድ የሚደረግ ነው እንጂ ከልብ የመነጨ አይሆንም፤ ጌታም እንዲህ ያለውን ምስክርነት ፈጽሞ አይቀበለውም።

7. ዘሌዋ. 7፡8 ማንኛውም ሰው ኃጢአት በልቡ እያለ ከዚህ መሥዋዕት አይበላም ነበር። ቢበላ ግን በሞት ፍርድ ይቀጣል። አማኝም በልቡ ኃጢአትን ከያዘ ከእግዚአብሔር ጋር ደስ የሚል አንድነትና ሰላም አይኖረውም። ነገር ግን አፋዊ አማኝ መናፍቅ ነው። የሚሰጠውም ምስክርነት ውሸት ነው። ከኃጢአቱም ፈጽሞ ገና አልዳነም። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ቢቀርብ በሞት ይፈረድበታል።

8. ዘሌዋ. 7፡11፥ 12 የደኅንነቱ የመሥዋዕት ቂጣ ያለ እርሾ ስለተጋገረ በዘይት ተለውሶ ለመሥዋዕት ይቀርባል። እርሾ የሌለበት ቂጣ ኃጢአት በሌለበት በክርስቶስ ይመሰላል። እርሾ የሌለው ቂጣ ንጹሕ በሆነ ልብ ይመሰላል። ዘይትም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል።

9. ዘሌዋ. 7፡13 እርሾ ያለበት ቂጣ ደግሞ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል። አማኙም ራሱን ከክርስቶስ ጋር ሰይሞ ራሱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል። ሆኖም እስከ አሁን እንደ ክርስቶስ አይሆንም። ምክንያቱም ይህ በኃጢአት የተበከለ ሥጋ አሁንም አብሮት ስላለ ነው። በውስጡም እርሾ አለበት፥ ሆኖም እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ አካሉን ነፍሱንና መንፈሱን ተቀብሎታል። እርሱም ለእግዚአብሔር ሕያው መሥዋዕት ነው (ሮሜ 12፡1)። ምክንያቱም ያለ እርሾ የሆነው ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት እንዳደረገ እኛ ደግሞ ምንም በዚህ በኃጢአት ሥጋችን ብንሆን ከልባችን ንጽሕና የተነሣ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገን ብናቀርብ እግዚአብሔር ይቀበለናል።

10. ዘሌዋ. 7፡32-35 የካህናቱ ድርሻ ወርችና ፍርምባ ነው። ይህም ደግሞ የመወዝወዝ መሥዋዕት ወይም የማንሳት ቁርባን ይባላል (ዘሌዋ. 7፡34)። ካህኑ ወደላይ እንዳነሣው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀርበዋል። ከዚያም በኋላ ወደ ራሱ መልሶ ይወስደዋል። ፍርምባው የልብን ፍላጎት ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ከመስጠት ጋር ይመሰላል። ልባችንንና የልባችንን ምኞት በሙሉ መሥዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር እንሰጣለን። እግዚአብሔርም የልባችንን ምኞት ከእኛ ወስዶ በምትኩ የእርሱን መንፈስ ቅዱስ ይሰጠናል።

ወርቹ ወይም ትከሻው በብርታት ይመሰላል። የእኛን ኃይል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገን እናቀርባለን። ሆኖም በምትኩ መንፈሳዊ ኃይላችንን ሁሉ ከክርስቶስ እንቀበላለን። ለእርሱም መሥዋዕት አድርገን የሰጠነውን መልሰን ከእርሱ ስለምንቀበል ለእርሱ እንጠቀምበታለን። እኛ ለእርሱ አገልግሎት የራሳችንን ብርታት እንሰጠዋለን። እርሱ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ይሰጠናል።

<u>ምዕራፍ 4 የኃጢአት መሥዋዕት</u> (ዘሌዋ. 4፡1-5፤ 6፡24-30)። ይህ የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት አይደለም። ምክንያቱም ይህ መሥዋዕት ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጥዕ መሆኑን የሚያመለክት በእርሱ የሚመሰል መሥዋዕት ነው። እግዚአብሔርም ወደ ኃጢአት በደስታ መመልከት አይችልም (ዕብ. 13፡11፥ 12፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

1. ይህ መሥዋዕት ባለማወቅ ለተደረገ ኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት ነው (ዘሌዋ. 4፡2፥ 13፥ 22፥ 27)። አንድ ሰው ሳያውቅ ኃጢአት ቢሠራ ስለ ኃጢአቱ የግድ ማስተሰርያ ያስፈልገዋል። ሰው ሁሉ ኃጢአትን ወርሷል። የኃጢአት ዘር በሙሉ በውስጡ አለ። ሰውዬው ምንም እንኳ ሳያውቅ ኃጢአትን ቢያደርግ በሥጋው ለተሠራው ኃጢአት ባለ እዳ ወይም ወንጀለኛ ነው። ሕፃናቶች በኃጢአተኛ ሥጋ ስላሉ አውቀው ሳይሆን በውስጣቸው ባለው ኃጢአት የተነሣ ክፉ ነገር ያደርጋሉ። ክርስቶስ ለእነርሱም ስለሞተ ይድናሉ (1ኛ ዮሐንስ 2፡2)።

2. በዚህ መሥዋዕት ውስጥ ያለው የደም መሥዋዕት ከቀሩት የደም መሥዋዕቶች ሁሉ ይበልጣል (ዘሌዋ. 4፡5-7)። ይህ ደም ለኃጢአት ማስተሰርያ ሆኖ ለነፍስ የሚቀርብ ነው (ዘሌዋ. 17፡11፤ ማቴ. 26፡28፤ ሮሜ 5፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፥ 19፤ ራእይ 1፡5፤ 5፡9፤ 7፡14)። ሰይጣን የክርስቶስን ደም ይፈራል።

ካህኑ በጌታ ፊት በመጋረጃው ላይ ሰባት ጊዜ ደም መርጨት አለበት (ዘሌዋ. 4፡6)። የቁጥር 7 ትርጉም ፍጽምና ማለት ነው። ይህም ማለት መዋጀታችን በክርስቶስ ደምና ሞት አልቋል ተፈጽሟል ማለት ነው።

ጥቂት ደምም በዕጣኑ መሠዊያ ቀንዶች ላይ ይደረጋል (ቁጥር 7)። ዕጣን በጸሎትና በምስጋና ይመሰላል። ትርጉሙም በክርስቶስ ሞት የሚዋጁ ሁሉ በክርስቶስ ስም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አብ ቢቀርቡ እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ሲል ይሰማቸዋል። የመሥዋዕቶቹ ቀንዶች ደግሞ ለመደገፊያ ናቸው። እንደዚሁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የፈሰሰው ስለ እኛ ስለሆነ እግዚአብሔርን በጸሎት እንይዘዋለን። የናሱ መሠዊያ የቆመው እውነተኛ የይቅርታ ኑዛዜ በሚደረግበት ጊዜ እንዲያዝ ነው (1ኛ ነገሥት 2፡28)።

የቀረው ደም በሞላ የክርስቶስ ደም ከመስቀሉ ተርፎ በመንቆርቆር በምድር ላይ እንደፈሰሰ ሁሉ ከሚቃጠለው መሥዋዕት መሰዊያ ፊት ይፈሳል። መሠዊያው የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ነው (ዘሌዋ. 4፡6)።

3. መሥዋዕቱ ነቀፋ የሌለበት እንስሳ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም ያለ ምንም ኃጢአት ነበር። ይህም የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት አልነበረም። ኃጢአት የሌለበት ኢየሱስ ስለ እኛ ኃጥዕ ሆነ (2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ኢሳ. 53፤ መዝ. 22፤ ማቴ. 26፡28፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡24፤ 3፡18)።

4. ስቡ በሞላ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ይቃጠል ነበር (ዘሌዋ. 4፡8-10)። ክርስቶስ ያለውን መልካም ነገር ለዓለም ኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። አማኝም ራሱን ከክርስቶስ ጋር በመሰየም ያለውን መልካም ነገር ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

5. የቀረው የእንስሳው አካል ከሰፈር ውጭ ይወጣል (ዘሌዋ. 4፡11፥ 12፥ 20፥ 21፤ 6፡30)። ከዚያም የከተማው አመድ በሚፈስበት ቦታ በእሳት ይቃጠላል። በዚያም ስፍራ ከከተማው የተጣለ ቆሻሻ ነገር ሁሉ ይፈሳል። በዚያ ስፍራ መሥዋዕቱ ስለተቃጠለ ያ ስፍራ ንጹሕ ይባላል። እንደዚሁም ኃጢአተኛው ከሰፈር ወጥቶ ይሄዳል። እንደዚሁም ኃጢአተኛው ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆኖ ለመቆጠር ዓለምን ይተዋል (ዕብ. 13፡10፤ ዮሐ. 19፡17፥ 18)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወንበዴዎች ከከተማ ውጭ ተጥለው በሚሰቀሉበት ስፍራ ከከተማ ውጭ ተጥሉ ተሰቅሎ ተገደለ። እርሱም በሰዎች እጅ እንደ ጉድፍ ተጣለ። ስለ እኛም ኃጢአት የእግዚአብሔርን የሚቃጠል እሳታዊ ፍርድ ተቀበለ። እኛም ደግሞ ከኃጢአታችን እንድንድንና ከክርስቶስ ጋር አንድ

እንድንሆን የክርስቶስን ነቀፋ ከከተማ ውጭ እንሸከም (ዕብ. 13፡13)። እኛም ደግሞ ከዓለም ተለይተን በክርስቶስ እንደተሾፈበት ይሾፍብን። እኛ ዓለምን ከወደድንና ዓለም እኛን ከወደደችን ክርስቶስን መከተል አንችልም (ማቴ. 5፡11፥ 12)።

6. መሥዋዕቱ የተቃጠለበት ስፍራ ምንም የሰፈርና የከተማው አምድና ጉድፍ የሚጣልበት ስፍራ ቢሆን እንኳ ንጹሕ ቦታ ተባለ (ዘሌዋ. 4፡12)። በሰዎቹ ንጹሕ እንዳልሆነ ቦታ ይቆጠራል። ጎልጎታ ወይም ቀራንዮ ንጹሕ ስፍራ አልነበረም። ወንበዴዎችና ነፍስ ገዳዮች በዚያ ስፍራ ይሰቀሉ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ በተሰቀለ ጊዜ ግን ያ ስፍራ ለአማኞች ሁሉ ንጹሕና ቅዱስ ስፍራ ሆነ። በዚያ ነው የኃጢአታቸውን ይቅርታ የተቀበሉት (ዮሐ. 19፡17፥ 18፤ ዕብ. 13፡10-14)።

7. ካህናቶቹ የኃጢአቱን መሥዋዕት ይበላሉ። ምግቡም በጣም ቅዱስ ነው። ምክንያቱም በክርስቶስ ይሰየማልና ነው። የዓለም ኃጢአት በሙሉ በክርስቶስ ላይ ቢፈረድም ክርስቶስ እጅግ በጣም ቅዱስ ነው። የእርሱም ሞት የካህናቶቹ ኃይል ሆነ። የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ የእግዚአብሔር ካህናት ናቸው (ዘሌዋ. 6፡26፥ 29፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡9)።

8. ማንኛውም ደሙ ወይም ምግቡ የነካው ሰው እጅግ በጣም ቅዱስ ይሆናል። ሥጋውም የተቀቀለበት ሸክላ ሌላ ሥራ ተሠርቶበት እንዳይረክስ ይሰበራል። ከብረት የተሠራ ድስት ከሆነ ግን ተራ ነገር ተሠርቶበት እንዳይረክስ ደኅና ተደርጎ ይታጠባል። ምክንያቱም ምንም ዓይነት ቅዱስ ነገር ለተራ ጉዳይ ስለማይውል ነው (ዘሌዋ. 6፡28)። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውም ሰው በክርስቶስ ደም ስለተገዛ ማናቸውም የዓለም ርኩሰት ሊነካውና ሊያረክሰው አይገባም።

ምናልባት የመሥዋዕቱ ደም ልብስ ቢነካ እንደ ቀላል ነገር አይታይም። ስለዚህ ደሙ በተቀደሰ ስፍራ ከልብሱ ላይ መታጠብ አለበት። እንደዚህም ስለ ክርስቶስ ደም ስናወራ ወይም ስንወያይ በቀልድና በፌዝ ልናላግጥ ወይም እንደ አንድ ቀላል ነገር ልንቆጥረው አይገባም። ምክንያቱም የክርስቶስ ደም ከኃጢአትና ኃጢአት ከሚያመጣው ፍርድ የሚያነፃና የሚያድን ነው (ዘሌዋ. 6፡27)። ከዚህም በቀር የእግዚአብሔር ልጅ ደም ስለሆነ ነው። ተራ ነገሮች ቅዱሱን ነገር ሊነኩት አይገባም።

9. ኃጢአተኛው በሚሠዋው እንስሳ ላይ እጁን በመጫን እራሱን ከመሥዋዕቱ ጋር መሰየም አለበት። ትርጉሙም ኃጢአቱን ተናዞ ለዓለም ለሥጋና ለኃጢአት ከክርስቶስ ጋር እንደሞተ ለማሳየት ነው። ከዚያም በኋላ የኃጢአቱን ይቅርታ ይቀበላል (ዘሌዋ. 4፡4፥ 15። 24፥ 29፥ 33)።

10. መሥዋዕቱ የሚሰጠው እንደሰውዬው ችሎታ ነው። ሕዝቡ ሁሉ ኃጢአትን ያደረጉ ከሆነ በሬ ማምጣት አለባቸው (ዘሌዋ. 4፡13-21)። ገዥው

ኃጢአት የሠራ እንደሆነ ፍየል ያመጣል (ዘሌዋ. 4፡22-26)። ከሕዝቡ አንዱ ሳያውቅ ኃጢአትን ቢያደርግ ግልገል ያመጣል (ዘሌዋ. 4፡28፣ 32-35)። ይህም የሚያሳየው ሁሉም በክርስቶስ ደኅንነትን ማግኘት እንደሚችሉ ነው። ማንም ሰው ድሀ በመሆኑ መጥፋት የለበትም። ምክንያቱም ደኅንነት ለሚፈልጉ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የነፃ ስጦታ ስለሆነ ነው።

<u>ምዕራፍ 5 የበደል መሥዋዕት</u>:- ይህም የጣፋጭ ሽታ መሥዋዕት አይደለም። ይህ መሥዋዕት ለተደረገው በደል ክርስቶስ ያቀረበውን መሥዋዕት ያሳያል (ዘሌዋ. 6፡1-7፤ 7፡1-7)። ይህ መሥዋዕት ገና በልብ ላልተደረገ ኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት አይደለም። በምዕራፍ 4 የተጠቀሰው የኃጢአት መሥዋዕት ግን ለዚህ ነው። አንዳንድ ለኃጢአት የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ናቸው። ከእነዚህም አንዳንዶቹ ከአሥር አንድ ለጌታ አለመስጠትና አለመጸለይ ናቸው። ከአሥር አንድ የጌታ ነው (ዘሌዋ. 27፡30፣ 34)። ስለ አስራት ለመረዳት ዘፍ. 14፡20፤ 28፡22፤ ዘሌዋ. 27፡30፤ ዘኁልቁ 18፡21፤ ዘዳግም 12፡6፤ 14፡28፤ 26፡12-15፤ 2ኛ ዜና 31፡5-8፤ ሚልክያስ 3፡10 ተመልከት። በዘሌዋ. 5፡16 አንድ ሰው አሥራቱን ካልከፈለ አንድ አሥረኛውን ከፍሎ የቀረውን አንድ አምስተኛ አጠፌታ ጨምሮ እንዲከፍል ይደረግ ነበር። ከዚያ በኋላም ከእግዚአብሔር ይቅርታ መቀበል አለበት። ጸሎትን የሚያደክመው መሥዋዕት አለማቅረብና ስጦታ አለመስጠት አይደለም (1ኛ ሳሙ. 12፡23)። ምስጋና በመተውና ሌላም ብዙዎች ይህንን የመሳሰሉትን ኃጢአቶች ስለማድረግ ኑዛዜ መደረግና የበደል መሥዋዕት መቅረብ አለበት። ሁለት ዓይነት የሚደረጉ ኃጢአቶች አሉ፦ ባለማወቅ የሚደረጉ (ዘሌዋ. 5፡14-19) እና በማወቅ የሚደረጉ (ዘሌዋ. 6፡1-7)።

1. ባለማወቅ የሚደረጉ ኃጢአቶች ስንል በስሕተት የሚደረጉትንና በማወቅ የሚደረጉትን ማለታችን ነው። አውቀው የተደረጉና ያለማወቅ የተደረጉ ኃጢአቶች ምንም ልዩነት የላቸውም። ያም ሆኖ ይህ ኃጢአቱ ተፈጽሞአል (ዘሌዋ. 5፡19)። ይህም ደግሞ በልብ ስለሚደረግ ኃጢአት ነው። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ቢመኝ በሕግ የተጻፈ ኃጢአት እንደሆነ እስከተረዳ ድረስ ኃጢአት መሥራቱን አያውቅም ነበር። «አትመኝ» (ዘጸአት 20፡17)። ከዚህ በኋላ ይህን ኃጢአት በልቡ እንደሠራ ይገነዘብና ሕግን ስላፈረሰ ይናዘዛል (ዘሌዋ. 5፡5)።

2. አውቀው የሚደረጉ ኃጢአቶች ስንል አንድ ሰው ያ የሚያደርገው ነገር ኃጢአት እንደሆነ እያወቀ በፈቃዱ የሚያደርጋቸው ነገሮች ማለት ነው። ለምሳሌ ስርቆሽ እስራኤላዊው ሰው በታማኝነት በዚህ ጥፋቱ ሲናዘዝ ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል፤ ነገር ግን ከተናዘዘ በኋላም ቢሆን አስቀርቶት የነበረውን ገንዘብ ከፍሎ በላዩ ላይ አጠፌታ አንድ አምስተኛውን ጨምሮ መክፈሉ አይቀርም (ዘሌዋ. 6፡5፤ 5፡16)። የበደሉን መሥዋዕት ሲያቀርብ መጥቶ ስለ በደሉ ደሙን ሲያፈስለት ባለው አዳኝ ማመኑን ያሳያል።

ዘኪዎስ በዳነ ጊዜ ልቡ በእግዚአብሔር ፍቅር ስለተሞላ እንዲህ አለ። «አራት እጥፍ እመልሳለሁ።» (ሉቃስ 19፡1-10፤ ዘጸአት 22፡1)። ተመልከት። ከዚያ ወዲህ ገንዘብን ሳይሆን እግዚአብሔርን ወደደ። እርሱም የወሰደውን መልሶ የመስጠትን ሕግ ያውቃል። ስለዚህ የወሰደውን አራት እጥፍ መልሶ ሲሰጥ ምንም ቅር ሳይለው በደስታ አደረገ።

ዳዊት አውቆ በፈቃዱ ኃጢአት ባደረገ ጊዜ በመዝ. 50(51)፡4 ላይ እንደተገለጸው በኃጢአቱ ተናዞ ይቅርታን ፈለገ። ኃጢአተኛ የበደለውን ሰው ይቅርታ ጠይቆ ወዳጅነታቸው ተመልሶ መታደስ አለበት (ዘሌዋ. 6፡5፤ 5፡16)። በዳዩም ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት (ዘሌዋ. 5፡5)። ከዚያም በኋላ ለመሥዋዕት በግ ማምጣት አለበት (ዘሌዋ. 5፡18፤ 6፡6)። በጉም የዓለም በግ ሆኖ በተገደለው በእግዚአብሔር በግ በክርስቶስ ተመስሎ ይታረድ ነበር። ከዚያም በኋላ የኃጢአተኛው ኃጢአት ይቅር ይባላል (ዘሌዋ. 5፡10)።

የበደል መሥዋዕቱ ግን እንደ አቅራቢው ችሎታ ይሰጣል። ድሀው ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገል ወይም ዱቄት ያመጣል (ዘሌዋ. 5፡6፥ 7፡11)። ይህም ደኅንነት ለሀብታሞች ብቻ ሳይሆን በኃጢአታቸው ተናዘው ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ያሳያል።

6. ... በናዳብና በአብዩድ ላይ ስለደረሰው ከባድ ፍርድ ምን ትላለህ?
ምዕ. 10

መልስ።

ጌታ እስከ አሁን ድረስ ገና ዕጣን የማጤስን ሕግ አልሰጠም ነበር። ይህንን ሕግ የሰጠው በዘሌዋውያን 16፡12 ላይ ነው። እሳቱ እግዚአብሔር ራሱ ካያያዘው ከሚቃጠለው ከመሥዋዕቱ መሠዊያ ላይ መወሰድ ነበረበት። ይህም ከሰማይ የሆነ እሳት ነው። መሠዊያው በክርስቶስ መስቀል ሲመስል እሳቱ ደግሞ ለዓለም ኃጢአት በክርስቶስ ላይ በወረደው የእግዚአብሔር ፍርድ ይመስላል። ከዚህ እሳት ማለት ከዚህ ፍርድ የተነሣ ኃጢአተኞች ከበደላቸው ስለነጹ ምስጋናን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ። (የሚቃጠለው ዕጣንም በምስጋና ይመሰላል።) ይህንንም እግዚአብሔርን ለማገልገል ያደርጉት ነበር። በኃጢአታችን ላይ ካልተፈረደ በስተቀር እግዚአብሔርን በጸሎት ልንቀርበው አንችልም።

ናዳብና አብዩድ እግዚአብሔር እንግዳ ብሎ የጠራውን የራሳቸውን እሳት በዕጣኑ ላይ አኖሩ፥ ይህም እግዚአብሔርን በሥጋ ከማምለክ ጋር ይመሰላል። ወይም በሃይማኖታዊ ሥራ ይመሰላል እንጂ በመንፈስ ቅዱስ የሚሠራ ሥራ አይደለም። ይህም እግዚአብሔር የማይቀበለው ሃይማኖታዊ ሥራ ነው። እግዚአብሔር ልባቸው በመንፈስ ቅዱስ እሳት የተያያዘውን ሰዎች አምልኮ ብቻ ይቀበላል። ማለት በመንፈስና በእውነት የሚያመልኩትን ብቻ ማለት ነው (ቆላ. 2፡23)። እግዚአብሔር ራሱ በሰዎች ልብ የለኮሰውን እሳት ብቻ ይቀበላል።

በእውነት እግዚአብሔርን ማምለክ የሚችሉት እነዚህ በኑዛዜ በመስቀሉ ሥር ኃጢአታቸውን ያራገፉና መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ዳግመኛ የተወለዱ ብቻ ናቸው። የቀሩት ሁሉ ግን በሚያመልኩና በሚጸልዩ ጊዜ ዕጣኑን በእንግዳ እሳት ያጤሳሉ። የሞት ፍርድ አሁንም በራሳቸው ላይ አለ። እግዚአብሔር ናዳብና አብዩድን በሞት ፍርድ የቀጣው ሃይማኖታዊ ሥራ ማንንም ማዳን እንደማይችል ለማመልከት ነው (ዘሌዋ. 10፡2)። እግዚአብሔር እንደፈረደባቸው ያሳያል።

ናዳብና አብዩድ ጠጅ የጠጡ ይመስላል፥ ምክንያቱም ወዲያው ስለ እነርሱ ሲናገር ከቆየ በኋላ በምዕራፍ 10፡9 ላይ እንዳትሞቱ የወይን ጠጅና የሚያሰክርን ነገር ሁሉ አትጠጡ» የሚል ቃል እናገኛለን። ይህም ለካህናት ሁሉ የተሰጠ ትእዛዝ ነው። የሚያሰክር ነገር የሚጠጣ ራሱን ያረክሳል፤ ከዚህም በቀር አሳቡን ሊገታ አይችልም። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ ሊሠራ አይችልም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ አማኞች ሁሉ ካህናት እንደሆኑ ተገልጾአል። ስለዚህ በኃይለኛ መጠጥ ራሳቸውን ማርከስ አይገባቸውም (1ኛ ጴጥ. 2፡9)። ስለ ጠጅ በይበልጥ ለመረዳት ምሳሌ 20፡1፤ 23፡29-35፤ 31፡4-6፤ ኢሳ. 5፡11፤ 28፡7፤ ኤፌ. 5፡18 ተመልከት።

7. የምዕራፍ 11 ሥርዓት ለእስራኤላውያን ለምን እንደተሰጠ አብራርተህ ግለጽ።

መልስ።

እስራኤላውያን የተለዩ አእዋፋትንና እንስሳትን እንዲሁም ዓሣዎችን እንዳይበሉ የተከለከሉበት ሦስት ዐብይ ምክንያቶች አሉ።

1. ሥጋ የሚበሉ አእዋፋትን ሁሉ እንዳይበሉ ተከልክለዋል። ምክንያቱም ሥጋ የሚበሉት አእዋፋት በበሽታ ምክንያት የሞቱትን ሚች ነገሮች ሁሉ ስለሚበሉ ብሽታው ወደ ሕዝቡ እንዳይዛመትና እስራኤላውያንም በጤንነት እንዲኖሩ እግዚአብሔር ስለፈለገ ነው።

2. አንዳንድ እንስሳት ሃይማኖት በሌላቸው አረመኔዎች ለጣዖቶቻቸውና ለሰይጣን መሥዋዕት ሆነው ይቀርቡ ነበር። የእነዚህን እንስሳት መሥዋዕት እስራኤላውያን አይበሉም ነበር። ምክንያቱም ምስክርነታቸውን ስለሚያጠፋባቸው ነው። አሳማ ወይም እሪያ አብዛኛውን ጊዜ ለሰይጣን መሥዋዕት ሆኖ ይቀርብ ነበር (ኢሳ. 65፡3፥ 4፤ 66፡3፥ 17)።

3. የእነዚህ እንስሳት የአኗኗር ሁናቴ ደግሞ ርኩሳን አድርጎአቸዋል። አንዳንዶቹ ጥንብ ይበላሉ። አንዳንዶቹም የደም ጥማት ስላለባቸው ሌላውን እንስሳ የሚገድሉ ናቸው። አንዳንዶቹም ማለት እንደ ጅብና እንደ ጉጉት ያሉት ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለሚወዱ አይበሉም ነበር።

8. እንደ ምዕራፍ 13 እና 14 ገለጻ የእስራኤል ንጉሥ ስለ ሕዝቦቹ ሕመም ምን ያደርግ ኖሯል?

መልስ።

ለምጽ የኃጢአት ምሳሌ ነው። ለለምጽ የሚቀርበው መሥዋዕት ለኃጢአት ከሚቀርበው መሥዋዕት ጋር አንድ ነው (ዘሌዋ. 14፡12፥ 13፥ 19)። ለምጽ ያለባቸው ሁሉ ከሕዝቡ ተለይተው ይወገዱ ነበር።

1. ይህም በሽታ እንደ ኃጢአት በአገሩ ውስጥ በየቦታው ይገኝ ነበር (ሉቃስ 4፡27)።

2. ለለምጽም መድኃኒት አልተገኘለትም። ለኃጢአት የሚሆን መድኃኒትም በሰው እጅ አይገኝም። ሁለቱም በእግዚአብሔር ተአምራዊ ሥራ ይድናሉ (2ኛ ነገሥት 5፡7)።

3. ለምጽም እንደ ኃጢአት ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ይተላለፋል።

4. ለምጽ ያለበት ሰው ሰውነቱ ደንዝዞ እንደማይሰማው ሁሉ የኃጢአተኞችም ልብ እየደነዘዘ ስለሚሄድ የሕሊናቸውና የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ አይሰማቸውም። ከዚያ በኋላማ ኃጢአት ማድረግን ዳግመኛ አይፈሩም (1ኛ ጢሞ. 4፡2፤ ኤፌ. 4፡19፤ የሐዋ. ሥራ 28፡27)።

5. ለምጽ ያሳውራል። ኃጢአትም ኃጢአተኛው የሚመጣበትን ፍርድ እንዳያይ ያሳውረዋል።

6. ለምጻም ንጹሕ ስለአይደለ ከቀሩት ሰዎች ሁሉ ይለያል። ኃጢአተኛም በአካሉ፥ በነፍሱና በመንፈሱ ንጹሕ ስላይደለ በኃጢአቱ እንዳያረክሳቸው ከእግዚአብሔር ሰዎች መለየት አለበት። ልማደኛ ኃጢአተኛም ከቤተ ክርስቲያን ምእመናን መሀል መውጣት አለበት።

ዘሌዋ. 13፡45 ለምጻም የሆነ ሰው ጤነኛ የሆኑ ሰዎች እንዳይቀርቡት ማስጠንቀቅ አለበት። ለምጻሙም «ርኩስ ነኝ ርኩስ ነኝ» አትቀረቡኝ ብሎ መጮኽ ነበረበት። ኃጢአተኞችም እነርሱ በወደቁበት ኃጢአት ሌላ እንዳይጠመድ ሌላውን ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል።

7. ለምጻም ሁልጊዜ ጤነኞችን የመጨበጥ ፍላጎት አለው ይባላል፡ በዚህ መንገድ በሽታውን ያስተላልፋል፥ እንደዚሁ ሁሉ ኃጢአተኞች ደግሞ ሰዎችን ወደ ኃጢአት ለመምራት ይፈልጋሉ።

8. ዘሌዋውያን 13፡12፥ 13 ለምጽ የሰውዬውን አካል በሞላ ሲያዳርሰው ሰውዬው ንጹሕ ነኝ ብሎ ያውጃል። ከዚህ በኋላ በሽታው ለሌሎች አደገኛ መሆኑ ይቀራል።

ኃጢአተኛም በኃጢአቱ ሲበከልና ሲርመጠመጥ ወዙ ሁሉ አልቆ ለማየት እንኳን ያስጸይፋል። ማንም ደግሞ በኃጢአቱ ሊተባበረው ጓደኛ አይሆነውም። እርሱም በርኩሳን መናፍስትና በመጠጥ በሚሞላበት ጊዜ ሰዎች አይቀርቡትም። ኃጢአቱም ከእንግዲህ ወዲያ ማንንም አይማርከም ወይም አይፈትንም።

9. ኢየሱስ ለምጻሙን በፈወሰ ጊዜ «እምነትህ አድኖሃል» አለው (ሉቃስ 17፡19)። ለምጻሙ ለመንጻት ካልፈለገ አይነጻም (ማቴ. 8፡2፥ 3)።

ኃጢአተኛም ከኃጢአቱ ለመፈወስ ቢፈልግ በእምነት ብቻ ከኃጢአቱ ሊፈወስ ይችላል። ኑዛዜ ከሌለ ደግሞ ፈውስ አይኖርም (ዘሌዋ. 14፡12፥ 13፥ 19)። ለምጻም ከለምጹ በነጻ ጊዜ ለኃጢአቱ የሚያቀርበውን የመሥዋዕት ዓይነት በማቅረብ ተናዞ ይቅርታን ይጠይቃል፥ እርሱም የኃጢአትንና የበደልን መሥዋዕት ያቀርባል።

10. ዘሌዋ. 14፡13፥ 14 ከዚህ በኋላ የነጻው ለምጻም ራሱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል፤ የቀኝ ጆሮውንም በደም ይቀባል። ይህም ማለት ወደፊት እግዚአብሔርን እንጂ ዓለምን አይሰማም ማለት ነው ወይም አይታዘዝም። ደሙንም የቀኝ አውራ ጣቱን ያስነኩታል፥ ይህም ማለት ወደፊት ለእግዚአብሔር ብቻ ይሠራል ማለት ነው። ከዚህም በቀር ደሙን የቀኝ እግሩን አውራ ጣት ይቀባል። ይህም ማለት አረማመዱ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ይሆናል ማለት ነው። ደሙም የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ይወክላል።

ዘሌዋ. 14፡15-18 ካህኑም ጥቂት ዘይት በእግዚአብሔር ፊት ከረጨ በኋላ በቀረው ደግሞ ከለምጹ የነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮ የእጁንና የእግሩን አውራ ጣቶች ይቀባል። ይህም ማለት ከለምጹ የነጻው ሰውዬ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ በመስማት ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ መንፈስ ወደመራውና እንደመራው ይመላለሳል ማለት ነው። ከዚያም በኋላ ሰውዬው በቀረው ዘይት ይቀባል። ይህም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ በመቀባት ይመሰላል። ከዚያም በኋላ ያ ሰውዬ በጠቅላላው የእግዚአብሔር አገልጋይ ይሆናል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በክርስቶስ ደም ስለዳነ በቀረው የሕይወት ዘመኑ በመንፈስ ቅዱስ አመራርና ኃይል ተመርኩዞ በሥራም፥ በኑሮም፥ ለመንፈስ ቅዱስ ይታዘዛል።

ዘይቱ ሰባት ጊዜ ይረጫል። ሰባት የፍጽምና ቁጥር ነው። መንፈስ ቅዱስ አማኞች የሚሠሩትን ሁሉ ይሠራላቸዋል። የአማኞችም መንፈሳዊ ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። አማኝ በራሱ የተፈጥሮ ጥበብና ችሎታ የሚመካ ከሆነ ሥራው ሁሉ ገለባና እብቅ ብቻ ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 3፡12-15)። አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ የእግዚአብሔር ፍሬአማ አገልጋይ መሆን ይችላል።

የለምጻሙ ከለምጽ መዳን የአንድን አማኝ ከኃጢአቱና ከበደሉ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ኃጢአቱን ተናዞ በእምነት በመዳኑ ይመሰላል። የዳነው ኃጢአተኛ ደግሞ በታዛዥነት በጌታ ለመሥራትና ለመራመድ ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል። እርሱም ደግሞ በውስጡ በሚኖረው ኃይሉና መሪው በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቷል። የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ክርስቶስ ሕዝቦቹ የሆኑት የእስራኤላውያን ፈዋሽ ነበር። እርሱ ብቻ ከለምጽና ከኃጢአት ሊያነጻ ይችላል።

ዘሌዋ. 14፡1-7ን ከሮሜ 4፡25 ጋር አነጻጽር። አንዱ ወፍ ክርስቶስ ለእኛ ኃጢአት በሞተው ዓይነት ምሳሌ ሞተች። ሁለተኛዋ ወፍ በርራ እንድትሄድ ትለቀቃለች። የተለቀቀችይቱም ወፍ በክርስቶስ ትንሣኤ ትመሰላለች። እኛ በጽድቅ እድንኖር ተነሣ። የሚወርደውም ውኃ ይህን ሁሉ ሥራ ባከናወነው በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ኃጢአተኞችም ከክርስቶስ ጋር ለዓለምና ለኃጢአት በመሞት እንደ እግዚአብሔር ልጆች በሕይወት ለመኖር ከክርስቶስ ጋር በአዲስ ሕይወት ተነሥተዋል (ሮሜ 8፡2፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡18)።

9. በማስተሰርያው ቀን ለሚደረገው አገልግሎት ዋነኛውና መካከለኛው አሳብ ምንድን ነው? (ዘሌዋ. 16፤ ዕብ. 9፡1-14)።

መልስ።

መካከለኛና ዋነኛው የማስተሰርያው ቀን አገልግሎት አሳብ እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ሁሉ ተናዘው ከበደላቸውና ከዓመጻቸው እንዲነጹ ነው።

1. እስራኤላውያን መናዘዝ አለባቸው (ዘሌዋ. 16፡29፥ 31)።

2. ከኃጢአታቸው እንዲድኑ (ዘሌዋ. 16፡5፥ 6፥ 10፥ 11፥ 16-19፥ 21፥ 22፥ 30-34)።

ይህ ዕለት የማስተሰርያው ቀን ትንቢት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ እስራኤልን ነፃ ሲያወጣና ለ1000 ዓመት ሲነግሥ፥ እስራኤሎች የወጉት ክርስቶስን አይተው የእስራኤል ነገዶች በሙሉ አንድ ቀን ተናዘው ይድናሉ (ዘካርያስ 12፡10-14፤ 13፡1)።

ዘሌዋ. 16፡7-10፥ 15፥ 21፥ 22 ሁለቱ ፍየሎች የክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው። ፍየሎች የተመረጡት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እነርሱ ኃጥዕ እንደሆነ ለማሳየት ነው። የታረደው ፍየል በቀራንዮ መስቀል ላይ ለዓለም ኃጢአት የተሰቀለውን ክርስቶስን ተመስሎ ነው። ሁለተኛው ፍየል ደግሞ የእስራኤል ሊቀ ካህን የነበረው አሮን የሕዝቡን ሁሉ ኃጢአት በራሱ ላይ ከተናዘዘ በኋላ ዳግመኛ ሳይታይ ወይም ሳይመለስ ወደ ምድረ በዳ በነፃ ይለቀዋል (ዘሌዋ. 16፡21፥ 22)። ይህም ደግሞ በደላችንንና ኃጢአታችንን ሁሉ በራሱ ላይ ተቀብሎ እግዚአብሔር የዋጀን ሰዎች ዳግመኛ ኃጢአታችንን ለዘለዓለም እንዳናይ ባራቀልን በክርስቶስ ይመሰላል።

ክርስቶስ ኃጢአታችንን በራሱ ላይ ተቀበለ (1ኛ ጴጥ. 2፡24፤ ኢሳ. 53፡5፥ 6)። ክርስቶስ ከኃጢአታችን ለየን። ኃጢአታችንንም አራቀልን። እነርሱም ዳግመኛ ፈጽሞ አይታዩም [መዝ. 102(103)፡12፤ ሚክያስ 7፡19]። ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን አንድ ጊዜ ከተፈረደበት በኋላ ዳግመኛ በኃጢአታችን አይፈርድብንም (ዮሐ. 3፡18፥ 36፤ 5፡24)። ይህ በምድረ በዳ የተለቀቀው ፍየል አንዳንድ ሐሰተኞች አስተማሪዎች እንደሚያስተምሩት ለ1000 ዓመት ኃጢአታችንን የተሸከመው የሰይጣን ምሳሌ አይደለም። እንደ

መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ኃጢአታችንን የተሸከመው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (1ኛ ጴጥ. 2፡24፤ ኢሳ. 53፡5፥ 6)።

10. በምዕራፍ 17-22 በተሰጡት ሥርዓቶች እስከ መቼ ነበር የተገለገሉባቸው?

መልስ።

ዘሌዋ. ምዕራፍ 17-22 ያለው ሥርዓት ለእስራኤላውያን የተሰጠው ከሚያረክሳቸው ነገር እንዲጠበቁና እንዲጠነቀቁ ነበር። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ የእግዚአብሔር ሰዎች ደግሞ ቅዱሳን መሆን አለባቸው። እነርሱም ዓለማውያን የሚያደርጉትን ያልተቀደሰ ነገር ሁሉ ማድረግ የለባቸውም፤ ምክንያቱም የሰይጣን ባርያዎች አይደሉም። የዓለምንም ወግ በመከተል ሰይጣንን መታዘዝ የለባቸውም። ለምሳሌ ዘሌዋ. 19፡28 «ስለሞተው ሰው ሥጋችሁን አትንጩ፥ ገላችሁንም አትንቀሱት፥ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥» እግዚአብሔር ሰይጣን አምላካችሁ አይደለም ይለናል። «እኔ ነኝ» ስለዚህ የሰይጣን ባሪያዎችን ምልክት በገላችሁ ላይ አታድርጉ።

ዘሌዋ. 21፡5፥ 6 እራሳቸውን አይንጩ፥ ጢማቸውንም አይላጩ፥ ሥጋቸውንም አይንቀሱ፥ ለአምላካቸው ቅዱሳን ይሁኑ፥ የአምላካቸውንም ስም አያጎሳቁሉ። ጌታ እግዚአብሔር ጌታቸው ስለሆነ የዓለም ጌታ በሆነው በሰይጣን ምልክት ራሳቸውን ማርከስ የለባቸውም።

አሁን ከሕግ በታች ብንሆን ኖሮ እነዚህ ሴቶችን የሚገርዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ፍርድ በወረደባቸው ነበር። ምክንያቱም ይህ የዓለምና የሰይጣን ምልክት ስለሆነ ነው። ይህም ደግሞ ሰይጣን በሚገዛበት ቦታ ይደረጋል። እግዚአብሔር ጌታችሁ ነው። ለምን ሰይጣንን ትታዘዛላችሁ? እግዚአብሔር ይህንን ሕግ ለእስራኤል በሰጠበት ጊዜ ኃጢአትን በሚጠላ መጠን አሁንም ይጠላቸዋል። እግዚአብሔርም ቤተ ክርስቲያኖቹ ከዓለም ወግ ካልተለዩና ካልታዘዙት አይባርካቸውም [ዘዳግም 14፡1፤ መዝ. 73(74)፡20፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡16]።

እግዚአብሔር እስራኤላውያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ይህም ማለት በአሳብ ማለት ነው። በነፍስም ቅዱሳን እንዲሆኑ ይፈልግባቸዋል። ይህም በልባቸው ፍላጎት ማለት ነው። ከዚህም በቀር በሥጋ ቅዱሳን እንዲሆኑ ይፈልጋል። ይህም ማለት በሥራና በአካሄድ ማለት የዓለምና የሰይጣንን ምልክት ሳይቀበሉ እንዲከተሉት ነው። እስራኤላውያን እግዚአብሔር አምላካቸው ቅዱስ እንደሆነ ከዓለም ልማድና ወግ ተለይተው ቅዱሳን መሆን ነበረባቸው። እንደዚሁም ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች ቅዱሳን መሆን አለባቸው (ዘሌዋ. 18፡30፤ 19፡2፥ 18፥ 30፥ 34፤ 20፡26፤ 21፡1፥ 4፥ 6፥ 8፥ 11፥ 15፥ 23፤ 22፡32)። እግዚአብሔርም «እኔ አምላካችሁ ነኝ» ይላል። የዚህ ዓለም አምላክ ሰይጣን ነው። የዓለምን ልማድ አትከተሉ፤ እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ ቅዱሳን ሁኑ።

11. ሀ. እስራኤላውያን የተጠሩበት የቅድስና መጠን ምን ያህል ነው? ዘሌዋ. 19፡2፤ 20፡26።

መልስ።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር አምላካቸው ቅዱስ እንደሆነ ቅዱሳን መሆን ነበረባቸው። ዓላማቸውም ንጉሣቸው ክርስቶስ ቅዱስ እንደሆነ ቅዱሳን ለመሆን ነበር። ይህ ደግሞ የእኛ የአዲስ ኪዳን ዘመን አማኞች ዓላማና ግብ ክርስቶስን ለመምሰል ነው። እኛም በልባችን አዲስ ፍጥረት ስለሆንን ፍጹማን መሆን እንችላለን (ኤፌ. 5፡27)። ከዚህም በቀር በየዕለቱ ወደ እግዚአብሔር እየቀረብን በሄድን ቁጥር እንነጻለን። በዕለት ጉዞአችን የምናደርገው እርምጃ ከኃጢአተኛው ሥጋ ጋር፥ ከፈተና ጋርና ከኃጢአተኛው ተፈጥሮአችን ጋር በሕይወታችን ዘመን ሁሉ የምናደርገው የየዕለቱ ውጊያ ነው። ከዚህም በቀር በጉዞአችን ከዕለት ወደ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ በማደጋችን መጠን ክርስቶስን እየመሰልን እንሄዳለን። የእግዚአብሔር ልጆች ከትንሣኤ በኋላ ኃጢአት የሌለበትን አካል በሚለብሱበት ጊዜ ብቻ በሥጋቸው በተሟላ ሁናቴ ቅዱሳን ይሆናሉ።

11. ለ. ይህንን ሥርዓታዊ ጉዳይ የሚገናኝ ኃይል የት ነው ያለው? ዘሌዋ. 21፡8፤ 22፡32፥ 33።

መልስ።

እስራኤል ቅዱስ መሆንን በፈለገች ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ እንደሚገልጸው ቅዱስ ሆነች፤ እነርሱም ቅዱስ ለመሆን የሚያስችላቸው የራሳቸው ኃይል አልነበራቸውም። ስለዚህ እግዚአብሔርም የልባቸውን ፍላጎት ዐይቶ ቅዱሳን አደረጋቸው። አሁንም ቢሆን ሰው ኃጢአቱን ሁሉ ታናዞ ከኃጢአቱ ቢመለስና ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ቢቀበል ጻድቅ እንደሆነ በእግዚአብሔር ይነገርለታል። በልቡ ኃጢአትን ማድረግ አይፈልግም። ሆኖም ኃጢአትንና ፈተናን እንዴት አድርጎ ማሸነፍ እንደሚቻል እስከ አሁን አያውቅም። ያም ሰው እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ቅዱስ ነው። ምክንያቱም የኃጢአቱ ፍርድ በክርስቶስ ላይ ተቀጥቷል። እርሱም አዲስ ፍጥረት ነው። አዲሱ ተፈጥሮው ኃጢአትን አይወድም፤ ሆኖም ኃጢአተኛው ሥጋው አሁንም ኃጢአት ማድረግን ይናፍቃል። እግዚአብሔር ራሱም ሰው በአካሄዱ ቅዱስ እንዲሆን ይፈልግበታል (1ኛ ጴጥ. 1፡14-16፤ ዕብ. 12፡14፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡1)።

12. የእስራኤላውያንን ታላላቅ በዓላት በቅደም ተከተል በመጥቀስ ከክርስቶስ ሥራ ጋር የሚመሳሰሉበትን መንገድ ግለጽ። ዘሌዋ. 23

መልስ።

1. ምዕ. 23፡1-3 የየሳምንቱ ሰንበት። 44ኛውን የዘጸአት ጥያቄ ተመልከት።

2. ምዕራፍ 23፡4፥ 5 ፋሲካ። ይህ እኛ ከዓለም ባርነት ነፃ እንድንወጣና ከፍርድ እንድንድን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በእኛ ምትክ መሞቱን የሚያሳይ ምሳሌ ነው (1ኛ ቆሮ. 5፡7፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፥ 19)። 12ኛውንና 13ኛውን የዘጸአት ጥያቄ ተመልከት።

3. እርሾ የሌለው የቂጣ በዓል (ምዕራፍ 23፡6-8፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23-26፤ 5፡6-8፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡1፤ ገላ. 5፡7-9)።

እርሾ የሌለበት የቂጣ በዓል የሚውለው የእስራኤላውያን የመጀመሪያው ወር በገባ በአሥራ አምስተኛው ቀን ነው። ይህም ደግሞ ፋሲካ በዋለ በማግሥቱ ይሆናል። ይህም ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ በማግሥቱ የሚውለው ቀን ነው።

ይህ አማኞች በግል ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን አንድነት ያሳያል። ክርስቶስ ደሙን በመስቀል ላይ ስላፈሰሰ የእስራኤላውያን አማኞችና የዛሬዎቹ አማኞች ከክርስቶስ ጋር አንድነት ሊኖራቸው ቻለ። እስራኤላውያን እርሾ የሌለበት ቂጣ መብላት ነበረባቸው። እርሾ የኃጢአት ምሳሌ ነው። ይህም ማለት ከደኅንነት የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ወደፊት በኃጢአት አይወሰድም። በመጀመሪያ በክርስቶስ ሞት ተዋጅተዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ ኃጢአትን በልብ በመካድ በደስታ መጓዝ ነው። የጌታ እራት ይህን ያሳስበናል (1ኛ ቆሮ. 11፡23-26)።

4. ምዕራፍ 23፡9-14 የመከር በዓል የክርስቶስን ትንሣኤ ይወክላል (1ኛ ቆሮ. 15፡22፥ 23)። ይህ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣ ሊያደርግላቸው ያለው ነገር ትንቢት ነው።

በመከር ጊዜ ከእያንዳንዱ ሰው እርሻ አንዳንድ ነዶ እየታጨደ በእግዚአብሔር ፊት ከፍ ተደርጎ ይያዛል። ከዚያ በኋላ መከሩ በሙሉ ይታጨዳል። የተዋጁ ሁሉ የጌታ ታላላቆቹ መከሮች ናቸው። እግዚአብሔር በምድር ካለው መከር መጀመሪያ ክርስቶስን ከመቃብር አስነሣ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞቱት መካከል በመጀመሪያ ጊዜ ተነሥቶ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። ከዚያ በኋላ የዓለም ሁሉ መከር መሰብሰብ ይጀመራል። ይህም የሚሆነው በትንሣኤ ቀን አማኞች ሁሉ ከምድር ሲነጠቁና ሙሽራው ክርስቶስ ወደ ሙሽራይቱ ሲመጣ ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡23፤ 1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። ያም በዓል «እስከ ሰንበት ማግሥት ድረስ ይጠበቃል።» ይህም እሁድ መሆኑ ነው (ቁጥር 11)። ክርስቶስ ከመቃብር በዕለተ እሁድ ተነሣ።

5. ዘሌዋ. 23፡15-22 የጴንጠቆስጤ በዓል የቂጣ መወዝወዝ በዓል ይባላል። ይህም ከሰማይ መጥቶ በሰው ልብ የሚያድረው የመንፈስ ቅዱስ ትንቢት ነው። ያም ቀን የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የተወለደችበት ቀን ነው። ይህም የሆነው ክርስቶስ ከመቃብር በተነሣ በ50ኛው ቀን ነው (የሐዋ. ሥራ 2፡1-4፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)።

ሁለት ቂጣዎችም ለእግዚአብሔር ይቀርባሉ። በውስጣቸውም እርሾ አላቸው (ቁጥር 17)። ይህም ቂጣ ለእግዚአብሔር ሊሰጥ የታቀደ የአዲስ ኪዳን አማኞች ትንቢት ነው። በብዙ ቅንጣት ስንዴዎች አንድ ቂጣ ይሠራል። የብዙ ሰዎችም ክምችት አንድ ቤተ ክርስቲያን ይፈጥራል። ቂጣውም ከወፍጮ በታች ገብቶ ሥቃዩንና ርግማኑን ከተቀበለው ጴቄት ይጋገራል። አማኞችም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚቀላቀሉት ሕሊናቸው በመንፈስ ቅዱስ ሲወቀስና ሲከሰስ በእምነት ንስሐ ይገባሉ። በእንጀራው ውስጥ እርሾ አለ። ይህም በምድር ያሉ አማኞች አሁንም ከኃጢአተኛው ሥጋቸው ጋር እንዳሉ ያመለክታል። ሆኖም ልባቸው ንጹሕ ስለሆነ እግዚአብሔር ከኃጢአተኛ ሥጋቸው ጋር እንኳ የግሉ አድርጎ ተቀብሏቸዋል። መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ብዙ አማኞች አንድ ቤተ ክርስቲያን ሆነው ተመሥርተዋል። (አንዱ ቂጣ) 1ኛ ቆሮ. 10፡16፥ 17፤ 12፡12፥ 13፥ 20።

6. ዘሌዋ. 23፡23-25 የመለከት ድምፅ መታሰቢያ። ይህም በመጨረሻ ዘመን እስራኤል ከተበታተነችበት አገር ሁሉ ተሰብስባ መንግሥቷን እንደምታቋቁም የሚገልጽ ትንቢት ነው (ኢሳ. 18፡3፥ 7፤ 27፡12፥ 13፤ 58፡1-14፤ ኢዩኤል 2፡15-32)።

ይህም በዓል በሰባተኛው ወር ይከበራል። በዓሉም የጴንጠቆስጤ በዓል ከዋለ ብዙ ቆይቶ የሚከበር በዓል ነው። ይህም የአሕዛብ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ረጅም እንደሆነ ያመለክታል። የቤተ ክርስቲያን ዘመንም ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ዘመን ጀምሮ ወደፊት እስከ አማኞች ትንሣኤ ድረስ ይሆናል። እኛም አሁን በዚህ ዘመን ውስጥ ነው ያለነው። ይህም እስከ 2000 ዓመት ድረስ ይቆያል። እስራኤላውያንም እግዚአብሔር ከተበተኑበት አገር ሰብስቦ እንደገና በኢየሩሳሌም ሕዝቦቹ እስኪያደርጋቸው ድረስ አሁን በአሕዛብ መካከል ተበታትነዋል። የመለከቱ ድምፅ መታሰቢያም እግዚአብሔር እስራኤልን መልሶ የመጥራቱ ትንቢት ነው (ኢሳ. 18፡3፤ 27፡13፤ 58፤ ኢዩኤል 2፡1-3 አንብብ)።

7. ዘሌዋ. 23፡26-32 የማስተሰርያው ቀን (ዕብ. 9፡1-16) ይህ በዓል የመለከት ድምፅ መታሰቢያ በዓል በዋለ በ10ኛው ቀን ይደረጋል። እንደዚሁም እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ከነዓን ተጠርተው ከመጡ ከጥቂት ወራት ወይም ዘመናት በኋላ በሐሰተኛው ክርስቶስ በሚደርስባቸው ውጊያ መከራ ይቀበላሉ። እግዚአብሔርም ይህ እንዲሆን የሚፈቅደው እነርሱ ወደ ንስሐ እንዲመጡ ነው። ከእነርሱም አንድ ሦስተኛዎቹ ብቻ በሕይወት ይቀራሉ። እነዚህ የቀሩትም ንስሐ ገብተው እግዚአብሔርን ይጠሩታል። ከዚያም በኋላ ክርስቶስ ተመልሶ ወደ ምድር ይወርዳል። እነርሱም ሲመጣ አይተው አዳኛቸው አድርገው ይቀበሉታል። ክርስቶስም ሐሰተኛውን ክርስቶስን ከፈረደበት በኋላ ለ1000 ዓመት የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በዳዊት ዙፋን በሰላም ተቀምጦ ይገዛል። ይህ እንደሚሆን በዘዳግም 30፡1-10 እና በኢዩኤል 2፡11-15 ትንቢት ተነግሮአል። በዘካርያስ 12፡10-13 ደግሞ ከማስተሰርያው ጋር ተጣምሮ ተነግሮአል (ዘካርያስ 13፡1)።

በማስተሰርያው በዓል ጊዜ እስራኤላውያን ሁሉ በኃጢአታቸው ተጸጽተው ያለቅሱ ነበር (ዘሌዋ. 23፡27፥ 29፥ 32)። ይህም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ እስራኤላውያን በሙሉ እያለቀሱ ንስሐ ገብተው ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው እንደሚቀበሉት የሚያሳይ ትንቢት ነው። እስራኤላውያንም በዚያን ቀን ምንም ሥራ እንዳይሠሩ ተከልክለው ነበር። አባባቸውም በዚያ ዕለት በኃጢአታቸውና በንስሐቸው ላይ ተመስርቶ መዋል አለበት፤ ያለዚያ ግን በሞት ፍርድ ይቀጣሉ (ዘሌዋ. 23፡28-30)። ያለ እውነተኛ ኑዛዜ ምንም ዓይነት ደኅንነት ማግኘት አይቻልም።

8. ዘሌዋ. 23፡33-44 የማደሪያው ድንኳን በዓል (ዕዝራ 3፡4፤ ዘካ. 14፡16-19፤ ራእይ 21፡3)። የማደሪያው ድንኳን በዓል እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ማለት ወደ ከነዓን እንዳገባቸው ያሳስባቸዋል (ዘሌዋ. 23፡43)። እነርሱም የዛፍ ቅርንጫፍ በመቁረጥ ዳስ ሠርተው ከጥላው በታች ያድራሉ። ይህም እነርሱ የዚህ ዓለም ስደተኞችና ባይተዋሮች መሆናቸውንና ወደ ተሻለው አገር የሚሄዱ መንገደኞች እንደሆኑ ያሳስባቸዋል። ይህም ደግሞ እኛም አማኞች ቤታችን ከዚህ ከምድር እንዳልሆነ ያሳስበናል። ከዚህ በስተቀር እግረ መንገዳችንን በምድር እንደ እስራኤል በበረሃ አቋርጠን እናልፋለን እንጂ አገራችን እግዚአብሔር ወደሚመራን በሰማይ ነው።

የማደሪያው ድንኳን በግል ደግሞ ትንቢታዊ ነው። ይህም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባላቸውን ተስፋ ያሳስባቸዋል። ይህም በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ከተበታተኑበት አገር ማለት ከአሕዛብ መካከል ከሐሰተኛው ክርስቶስ ባርነት እጅ አርነት ካወጣቸው በኋላ እንደገና ንጉሣቸው ሆኖ ለ1000 ዓመታት በምድረ ከነዓን እንደሚገዛቸው ያሳስባል። ከዚያ በኋላ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ከእስራኤል ጋር የማደሪያውን ድንኳን በዓል ያከብሩና ዓለም በሰላም ትኖራለች (ዘካ. 14፡16-21)።

13. ሀ. የእስራኤል ልጆች የሰባተኛውን ዓመት ሥርዓት እንዲቀበሉ እንዴት ተመሩ? ምዕ. 25፡1-7።

መልስ።

በየሰባት ዓመቱ እስራኤላውያን እርሻቸውን ማረስ ወይም በእርሻቸው ዘርን መዝራት አይፈቀድላቸውም። የሳምንቱ ሰባተኛው ቀን የእረፍት ቀን እንደመሆኑ ሁሉ ከስድስት ዓመት በኋላ የሚመጣው ሰባተኛው ዓመትም ደግሞ የእረፍት ዓመት ነው።

እንደዚሁም ከአዳም ጊዜ ጀምሮ ሰባት ሺህ ዓመት ሲሆን ከዚያ በኋላ ያለው 1000ው ዓመት የእረፍት ዓመት ይሆናል። ከዚያም በዓለም ጦርነት ቀርቶ ሰይጣን በጥልቁ ውስጥ ይታሰርና ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ሁሉ ላይ ይገዛል (ራእይ 20፡1-4)። እንግዲህ የዓለም ሕዝብ ሁሉ የሚያርፍበት የሰባት ሺህኛው

ዓመት ሰንበት ይህ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ 1000 ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው [መዝ. 89(90)፡4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡8]። በእግዚአብሔር አቆጣጠር የሳምንት መጨረሻ ሰባተኛው ቀን ነው። ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት የ1000 ዓመቱ የሰላም አገዛዝ ከአዳም ጀምሮ በ7000 ዓመት ላይ ነው። ይህም እግዚአብሔር መፍጠር ከጀመረበት ቀን አንስቶ አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የራሱ ሊሆኑ የሚፈልጋቸውን ሕዝቦች ለመምረጥ 7000 ዓመት ወስዶበት ነበርና ነው።

13. ለ. ይህ የሰባተኛው ዓመት ሕግ የተወረሰበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ።

1. እርሻው ለቀሩት ዓመታት እንዳይመክንና ጥሩ ፍሬ እንዲሰጥ አንድ ዓመት ከመታረስ ያርፋል። እርሻ ያለ እረፍት በየዓመቱ ሲዘራበት ጥሩ ምርት መስጠቱን ያቋርጣል።

2. ሁለተኛው ደግሞ ለሌሎች ምስክር እንዲሆኑ የተጠሩት እስራኤላውያን ለራሳቸው ጥቅም የመንፈሳዊ አምልኮ ጊዜ እንዲኖራቸውና ለሌሎችም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ስለሚረዳ ነው።

14. ሀ. 50ኛው ዓመት የተወረሰበትን መንገድ በሚገባ አብራራ። ምዕ. 25፡8-55።

መልስ።

49ኛው ዓመት የ7 ዓመት እረፍት አለው። ምክንያቱም የ7 ጊዜ 7 ብዜት 49 ስለሚመጣ ነው። ስለዚህ የ7 ጊዜ 7 ብዜት 49 ስለሚሆን እስራኤላውያን በ49ኛው ዓመት ላይ አንድ ዓመት ጨምረው ማረፍ ነበረባቸው፤ ይህም ማለት 50ኛውን ዓመት ሲጨምሩ ሁለት የእረፍት ዓመት አላቸው ማለት ነው። ስለዚህ ይህ 50ኛው ዓመት የደስታ ዓመት ይባላል።

በዚያ ዓመት ለሌላ ሰው የተሸጠ መሬት ሁሉ ለቀድሞ ባለቤቱ በነፃ ተመልሶ ይሰጣል። ምክንያቱም መሬቱ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰጠው ቤተ ሰብ እንዲጸናለት ነው። የመሬቱም ዋጋ የደስታው ዓመት እስኪደርስ ድረስ ያሉት ዓመታት ናቸው (ዘሌዋ. 25፡13-17፥ 25-34)።

በእዳ ምክንያት ባሪያ የሆኑ ሰዎችም በደስታ ዓመት ነፃ ይወጣሉ (ቁጥር 10፡35-46)። በዘመኑ ስለ እዳ ባሪያ ሆኖ የተገዛ ሰው ቢኖር ደግሞ በዚህ በደስታ ዓመት ነፃ ይለቀቃል (ዘሌዋ. 25፡50-52)።

14. ለ. ስለ እስራኤላዊው ባለ ርስት ይህ ምን ያሳስበናል?

መልስ።

የምድሩ ባለቤት እግዚአብሔር ስለሆነ ማንም መሬቱን ሊሸጥ አይፈቀድለትም። መሬቱም ለሕዝቦቹ የተሰጠው በዚሁ መንገድ ስለሆነ መሬቱ

የሕዝቦቹ ርስት ሆኖ ይጸናል (ቁጥር 23)። የእስራኤልም ሕዝቦች ለእግዚአብሔር የተሰጡ ሀብቶቹ ስለሆኑ በሰው እጅ ተሸጠው ሊቀሩ አይቻልም። ስለዚህ ምናልባት በእዳ ተይዘው ለሌላ ሰው ተሸጠው እንደሆነ በተሸጡ በ50ኛው ዓመት ነፃ ይለቀቃሉ (ምዕ. 25፡42)። በዚህ መንገድ ነፃ ሕዝቦች ሁልጊዜ መሬታቸውን ያገኛሉ።

14. ሐ. ይህን ባሕል ወይም ልማድ በመከተል ማለት የ50ኛውን ዓመት ሕግ በመከተል ምን ጠቃሚ ውጤት ይገኛል?

መልስ።

1. የእግዚአብሔር ሰዎች ምንም ጊዜ የተገዙ ባሪያ ሕዝቦች መሆን አይችሉም። ምክንያቱም ከግብፅ ባርነት በደም ተዋጅተው በእግዚአብሔር አርነት ወጥተዋልና ነው። ስለዚህ አሁን የእግዚአብሔር ስለሆኑ ለማንም የተሰጡ አይደሉም። እንደዚሁም ሁሉ ከኃጢአት ባርነት አርነት የወጡ አማኞች ሁሉ ተመልሰው ፈጽሞ የኃጢአት ባሪያዎች አይሆኑም (ዮሐ. 8፡36)።

2. መሬታቸውም በሌላ ሰው ፈጽሞ አይወሰድም። መሬት የእግዚአብሔር ስለሆነ ሁልጊዜ መሬቱ እግዚአብሔር ለሰጣቸው ቤተሰቦች ተመልሶ ይጸናላቸዋል። አንዳንዶቹ ቤተሰቦች ርስታቸውን በማጣታቸው ቢደኸዩም ተመልሰው ከድኅነታቸው የሚያገግሙበት ተስፋ አላቸው።

3. እግዚአብሔርን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ስለካዱ በዓለም ውስጥ በየቦታው ቢበታተኑም እንኳ በተስፋ ትንቢት የተነገረላቸው የደስታው በዓል የወደፊት ታላቁ ተስፋቸው ነው። ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ሲመለስ ታላቁ የደስታ በዓላቸው ይሆናል። ምክንያቱም ክርስቶስ ምድራቸውን መልሶ ስለሚሰጣቸውና እንደገና በደሙ የተዋጁ ሕዝቦቹ ሆነው ለ1000 ዓመት በሰላም ከክርስቶስ ጋር ስለሚነግሡ ነው።

15. ሀ. እስራኤላውያን ትእዛዙን በምን ሁኔታ ቢጠብቁ ነው እግዚአብሔር እባርካችኋለሁ ብሎ ተስፋ የገባላቸው? በምንስ ዓይነት በረከት ነው እባርካችኋለሁ ያላቸው? ምዕ. 26፡1-13።

መልስ።

እስራኤላውያን ትእዛዙን ሁሉ ቢጠብቁ ምድራቸውንና ዛፎቻቸውን ሁሉ እንደሚባርክ ነገራቸው (ቁጥር 4)። ከዚህም በቀር ዘራቸውንና የሚሰበስቡትን እህል ይባርካል (ቁጥር 5)። በምድራቸውም ሰላም ሊሰጣቸውና ከዱር አውሬዎችም ይጠብቃቸዋል (ቁጥር 6)። ጠላቶቻቸውንም ድል ያደርግላቸዋል (ቁጥር 7 እና 8)። ዘራቸውን ያበዛዋል (ቁጥር 9)። እግዚአብሔርም በመካከላቸው ይኖራል (ቁጥር 11-13)።

15. ለ. እነርሱ ሕጎቹን ካልጠበቁ ምን ዓይነት ቅጣት አመጣባችኋለሁ አላቸው? 26፡14-29።

መልስ።

እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል፥ ከተቀጡ በኋላ ንስሐ ባይገቡ በአንድ ጥፋት ሰባት እጥፍ መልሶ ቅጣታቸውን ይጨምርባቸዋል።

1. ቁጥር 16፡17 እግዚአብሔር በሽታ፥ ጠላትና ፍርሃት ይልክባቸዋል።

2. ቁጥር 18-20 እግዚአብሔር በቅጣታቸው ላይ ሰባት እጥፍ ይጨምርባቸዋል። በምድራቸውም ላይ ምንም ዝናብ አይሰጥም፥ አይባርካቸውምም።

3. ቁጥር 21፡22 ቅጣታቸው እንደገና ሰባት እጅ ይጨምራል። የዱር አውሬዎችም ልጆቻቸውንም ከብቶቻቸውንም ያጠፋባቸዋል።

4. ቁጥር 23-26 ጠላት፥ ሕመምና ረኃብ ይልክባቸዋል።

5. ቁጥር 27-31 ምድራቸው ይጠፋል። ከረኃብ የተነሣም ልጆቻቸውን ይበላሉ። እግዚአብሔርም ይጨክንባቸዋል።

6. ቁጥር 32-39 በዓለም አሕዛብ መካከል ይበተኑና ባሪያዎች ይሆናሉ። ይህም በሞላ በእስራኤላውያን ላይ ተፈጽሞአል።

7. ቁጥር 40-46 እግዚአብሔርም በሞላ አያጠፋቸውም። እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ስለገባለት ያንን ተስፋ ይጠብቃል። በመጨረሻ ጊዜም ተመልሰው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይሆናሉ። የቀሩትም ክርስቶስን ተቀብለው ከእርሱ ጋር ለ1000 ዓመት ይነግሣሉ። ቁጥር 42።

16. እስራኤላውያን በሲና ምን ያህል ጊዜ ቆዩ? ወደዚያ መጓዛቸውንስ የሚገልጸው የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው?

መልስ።

በዘጸአት 19፡1 ላይ እስራኤላውያን ሲና ተራራ እንደደረሱ ስናነብ፥ በዘኍልቁ 10፡11 ደግሞ ከሲና ተነስተው ወደ ከነዓን እንደተጓዙ እናነባለን። በዚህም ጊዜ ግብፅን ከለቀቁ ሁለት ዓመት ሆኖአቸው ነበር። ከዘጸአት 19፡1 ጀምሮ ዘሌዋውያንን ሁሉ ጨምሮ እስከ ዘኍልቁ 10፡11 ያለው ክፍል ሁሉ እስራኤል ድንኳኗን በሲና ተራራ እንደተከለች የሚያወራ ታሪክ ነው። ምናልባትም የዘፍጥረት ታሪክ ለሙሴ በእግዚአብሔር (በክርስቶስ) የተነገረው በሲና ተራራ ላይ ሳይሆን አይቀርም። እነርሱም ክርስቶስ ሳይወለድ በፊት በ1491 እና በ1490 ዓ.ዓ. መካከል በሲና ነበሩ።

# ኦሪት ዘኍልቁ።

በዘኍልቁ የተጠቀሰው ታሪክ የ39 ዓመት ጊዜ የወሰደ ነው። ይህም ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1491 እና 1451 ዓ.ዓ. መካከል የተደረገ ነው። ይህም መጽሐፍ በምድረ በዳ መንከራተታቸውን የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። ዘፍጥረት ስለ ፍጥረት አፈጣጠርና ስለ ሰው ልጅ በኃጢአት መውደቅ የሚያወሳ መጽሐፍ ነው። ዘጸአት የመዋጀት መጽሐፍ ሲሆን፥ ዘሌዋውያን የአምልኮና የኅብረት መጽሐፍ ነው። ዘኍልቁ ደግሞ የአገልግሎትና የጉዞ መጽሐፍ ነው። በዘኍልቁ እስራኤላውያን የራሳቸውን ፈቃድ እንዳያደርጉ እግዚአብሔር አመልክቷቸዋል። እያንዳንዱም እስራኤላዊ ተቆጥሮ የየግል ሥራ በእግዚአብሔር ተሰጥቶታል። የዘኍልቁ መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ከሚገኘው ከ1ኛ ቆሮ. 12 ጋር ማለት ስለ አምልኮና ስለ ጉዞ ከሚናገረው መጽሐፍ ጋር ሊወዳደር ይችላል። በዘኍልቁ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ካዱት።

ዘኍልቁ አምስት ታላላቅ ክፍሎች አሉት።

1. 1፡1-10፡10 የሠራዊቱ ሥነ ሥርዓት።
2. 10፡11፥ 12፥ 16 ከሲና እስከ ቃዴስ በርኔ።
3. 13፡1-19፥ 22 እስራኤላውያን በቃዴስ በርኔ።
4. 20፡1-33፥ 49 የበረሃው ውስጥ መንከራተት።
5. 33፡50-36፡13 የመጨረሻው መምሪያ። ዘኍልቁ 1፡1-20፡13።

1. ዘጸአትና ዘኍልቁ የተጣመሩበት ነገር ምንድን ነው?

መልስ።

በዘሌዋውያን የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ክርስቶስ የአገዛዙን ሕግ ሰጣቸው። ስለዚህ አሁንም እነርሱ ምድራዊ ሕዝቦቹ ናቸው። እነርሱም እስከ አሁን የሚኖሩበት አገር የላቸውም። በዘኍልቁ የማይታይ ንጉሣቸው ክርስቶስ ወደ ምድረ ከነዓን እንዲገቡና ምድሪቷን እንዲወርሱ አዘጋጅቷቸዋል።

2. ሀ. አገልግሎቱ ለ. እርምጃ የመውሰድ ሁናቴ ሐ. በእስራኤል ሰፈር ላይ የሚቆመው የደመና ምልክት ምንድን ነው? 9፡15-23።

መልስ።

ሀ. የደመናው አገልግሎት።

የደመናው በማደሪያው ድንኳን ላይ መሆን ንጉሣቸው የሆነው ክርስቶስ ሊጠብቃቸው፥ ሊመራቸው፥ ሊያበረታታቸውና እምነታቸውን ሊያጠነክር በእስራኤል መካከል እንዳለ የሚያሳይ ምልክት ነው።

ለ. የደመናው ምስጢራዊ ነገር።

ክርስቶስ (እግዚአብሔር) እስራኤላውያንን በደመና መራቸው። ደመናው ሲንዝ እስራኤላውያን ይከተሉ ነበር። ደመናው ሲያርፍ እስራኤላውያን ያርፉ ነበር (9፡23)። ደመናው ፊት ፊታቸው እየሄደ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን መራቸው።

ሐ. የደመናው ምልክትነት።

እስራኤላውያን የራሳቸውን ፈቃድ ስለማያደርጉ የፈለጉበት መሄድ አይችሉም። ነገር ግን መታዘዝና መከተል ብቻ ነበረባቸው። እነርሱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ማድረግ ይችላሉ። አስቀድመው ግን መች መንዝ እንዳለባቸውና ወዴት መንዝ እንደሚገባቸው አያውቁም ነበር። ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ክርስቶስ ሊሄዱ ወደሚፈቅድበት አቅጣጫ ለመሄድ ዝግጁ ሆነው ይጠብቃሉ። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ወደጠራውና ወደመራው በደስታና በታዛዥነት ለመሄድ ሁልጊዜ ዝግጁ ለሆነ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ጥሩ (ምሳሌ) ነው። መታዘዝን አስቀድመን ከተማርን በኋላ ማዘዝ አያስቸግረንም። መታዘዝን ያልተማረ እራሱ ደግሞ ጥሩ አዛዥ መሆን አይችልም።

3. ሀ. በዘኍልቁ 1፡1-10፡11 ምን ነገር እንደሆነ ተጽፏል?

መልስ።

በመጀመሪያ የእስራኤል ሕዝቦች በየነገዳቸውና በየቤተሰባቸው ተቆጠሩ። እያንዳንዱ ሰው የማን ወገን እንደሆነና ወደ ከነዓን ለመሄድ በሚያደርጉት ጉዞ ላይ የግል ሥራውን ያውቃል። እያንዳንዱም ሰው እስራኤላውያን ድንኳናቸውን በተከሉ ጊዜ የራሱን ድንኳን የት እንደሚተክል ያውቅ ነበር። በዚህም ምንም መደናገር አልነበረም። ተዋጊዎቹ ወታደሮችም በሞላ የተቆጠሩ ስለሆኑ ወዴት እንደሚንዙ ያውቁ ነበር። ካህናቱም ሥራቸውን ተረክበው ነበር። ከዚያም በኋላ እስራኤላውያን በምዕራፍ 7 ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቀደሱ። እግዚአብሔርም ለካህናቶቹ የአገልግሎቱን መመሪያ ሰጣቸው (ምዕራፍ 8)። ከዚያ በኋላ የፋሲካ በዓል ተከበረ (9፡1-14)። ከዚያም በኋላ እስራኤላውያን ደመናውን እየተከተሉ ሲሄዱ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲታዘዙ መምሪያ ተቀበሉ (9፡15-23)። በ10፡1-10 መለከት በሚነፋበት ጊዜ ለጦርነት እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸው መምሪያ ተሰጣቸው። ከዚያም በኋላ እስራኤላውያን ሄደው ከነዓንን ለመውሰድ እንደሚገባ ሆነው ተዘጋጁ።

3. ለ. ይህ ነገር የተደረገው በየት ነው?

መልስ።

እነዚህ ነገሮች የተደረጉት በሲና ተራራ ነው (10፡11-12)።

4. ሀ. እስራኤላውያን የተቆጠሩበትን ሁናቴና ምክንያት አብራራ። 1፥2-4።

መልስ።

1፥2-4 ዓላማው እስራኤላውያን ለጦርነት ዝግጁ እንዲሆኑ ነው። ምክንያቱም ምድረ ከነዓንን መውሰድ ስላለባቸው ነው።

ሁናቴው፡- እነርሱም በየነገዱና በየቤተሰብ ይቆጠሩ ነበር። እያንዳንዱም ነገድ የራሱ የሆነ ወታደርና አለቃ ነበረው። እያንዳንዱም ሠራዊት በየወገኑና በየቤተሰቡ ከአለቃው ጋር ይከፈል ነበር። በወታደርነት ውስጥ ያሉት ሰዎችም ዕድሜአቸው ከ20 ዓመት በላይ የሆነ ነው (1፥3-16፥18)። በሠራዊቱም ውስጥ ያሉት ወታደሮች ቁጥር 603550 ነበር (1፥46)።

4. ለ. በዚህ ቁጥር ውስጥ ተቀላቅሎ ያልተቆጠረ የማን ነገድ ነው? ለምንስ አልተቆጠረም?

መልስ።

ሌዋውያኖች ከጦረኞቹ ጋር ተቀላቅለው አልተቆጠሩም (1፥49፤ 2፥33፤ 3፥45)። እግዚአብሔር አገልጋዮቹ እንዲሆኑ ስለፈለገ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ በመንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ ያገለግሉታል። እነርሱም በበኩር ልጅ ፋንታ ለእግዚአብሔር የተመረጡ ሆኑ (3፥5-13፥12)። የሌዊ ነገዶች በአሁኖቹ አማኞች ሁሉ ይመስላሉ (ዮሐ. 17፥6)። እነርሱም የእግዚአብሔር የበኩር ልጆችና አገልጋዮቹ ናቸው። አሮንም የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ሌዋውያን ተረግመው ነበር፤ ነገር ግን ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቀደሱ (ዘፍ. 49፥6፥ 7፤ ዘጸአት 32፥25-28፤ ዘኁልቁ 18፥4፥ 6)። ዛሬም የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት አማኞች ሁሉ ቀድሞ ስለ ኃጢአታቸው ተረግመው ነበር። ነገር ግን አሁን ተናዘው ወደ እግዚአብሔር ተመልሰዋል። ከዚያም በኋላ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆኑ። እያንዳንዱ ሌዋዊ የሚሠራውን ሥራ ይቀበል እንደነበረ ዛሬም እያንዳንዱ አማኝ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሥራ አለው። ለአንዱ አንድ ሥራ ለሌላው ደግሞ ሌላ ሥራ አለው።

5. ምድሩን ሊሰልሉ ስለሄዱት መልእክተኞችና ስለአልተመሳሰለው መልሳቸው እንዲሁም መልሳቸው ተቀባይነት ያገኘበትን መንገድ የሚገልጽ መግለጫ ስጥ። ምዕራፍ 13 እና 14።

መልስ።

እስራኤላውያን የከነዓን ወደብ ወደሆነው ወደ ቃዴስ ባርኔ በደረሱ ጊዜ ከየነገዱ አንዳንድ ሰው አድርገው 12 ሰዎች ምድረ ከነዓንን እንዲሰልሉ ተላኩ። እነርሱም ከ40 ቀን በኋላ ሰልለው ተመለሱ። መልሳቸውም ምድሪቱ ለምለምና ሀብታም እንደሆነችና ሰዎቹም ከእስራኤሎች ይልቅ በጣም ግዙፎችና ኃይለኞች እንደሆኑ የሚገልጽ ነበር። በዚህም መልሳቸው መልእክተኞቹ ሕዝቡን ተስፋ በማስቆረጥ አስፈራሩት። ከመልእክተኞቹ መኃል ካሌብና ኢያሱ ብቻ ነበሩ

እግዚአብሔር ይዋጋልናል፥ ጠላቶቻችንን አሸንፈን ምድሪቱን እንወርሳለን ያሉት። ሕዝቦቹም በካሌብና በኢያሱ ላይ ተቆጥተው ሊወግሯቸው ፈለጉ፥ ወዲያውም ለራሳቸው አለቃ ሹመው ወደ ግብፅ ለመመለስ አቀዱ። እግዚአብሔርም ሕዝቦቹ እምነት ስላጡ፥ ስላንጎራጎሩበትና ስለተቋቋሙት በጣም ተቆጣ። እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን በሞላ ሊያጠፋቸው ፈለገ፤ ነገር ግን ሙሴ ጸለየላቸው (14፡13-19)።

እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ተአምራትና ኃይል ሁሉ ምንም ቢመለከቱ እስከ አሁን እግዚአብሔር እንደሚዋጋላቸውና ምድረ ከነዓንን እንደሚያወርሳቸው አላመኑም ነበር። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ከ20 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ወደታች ያሉትን ጨምሮ ከካሌብና ከኢያሱ በስተቀር የቀሩት በሞላ በምድረ በዳ ውስጥ ያልቃሉ አለ። ልጆቻቸው ግን ምድረ ከነዓንን ይወርሳሉ አላቸው።

6. ካለማመናቸው የተነሳ እስራኤላውያን ከነዓን ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ወሰደባቸው?

መልስ።

እስራኤላውያን ከነዓን ለመግባት 38 ዓመት ወሰደባቸው። በሲና ተራራ አጠገብ ሁለት ዓመት ተቀምጠዋል። ከዚህ በሲና ተራራ አጠገብ ካሳለፉት ሁለት ዓመት ጋር በጠቅላላው ምድረ ከነዓን ለመግባት 40 ዓመት ወስዶባቸዋል። ይህም ከግብፅ ተነስተው ከነዓን ለመግባት የወሰደባቸው ዓመት ነው (14፡33-34)።

7. በተለይ ስለዚህ ጊዜ የተሰጠ በጽሑፍ የሰፈረ ሌላ ተጨማሪ መግለጫ አለ?

መልስ።

ምዕራፍ 11 እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ሊሄዱ ጉዞ በጀመሩ ጊዜ ወዲያውኑ ማጉረምረም ስለጀመሩ እግዚአብሔር በእሳት ፈረደባቸው (11፡1-3)። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር በሰጣቸው ምግብ ደግሞ ይነጫነጩ ጀመር (11፡4-9)። አሁንም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ነገር አይረኩም (11፡10-15)። ሙሴም ሕዝቦቹን ታግሶ መሸከም በጣም በዝቶብኛል ብሎ አንጎራጎረ (11፡16፥ 17፥ 24፥ 25)። ስለዚህ እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝቡን በመምራት እንዲረዱት 70 የእስራኤል ሽማግሌዎችን አዘጋጀ (11፡18-23)። መንፈስ ቅዱስ በተመረጡት ሽማግሌዎች ላይ ወርዶ ትንቢት ተናገሩ። እነርሱም እግዚአብሔር እንደሰጣቸው ሰበኩ። እግዚአብሔርም ለሕዝቡ ሥጋ ለመስጠት ተስፋ ገባላቸው (11፡18-23)። ሁለቱም ሰዎች በሰፈር ውስጥ ሆነው ትንቢት ሲናገሩ ሙሴ ደስ አለው። ሙሴም የእግዚአብሔርን ሥራ ለብቻው በመሥራት ክብርን ሁሉ በግሉ መቀበል አልፈለገም (11፡26-30)። እግዚአብሔርም የእስራኤላውያን መሪዎችን በምሳሌ የተሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት እንዳስተማራቸው

አያጠራጥርም። ከዚያም እስራኤላውያን የዚህ የመንፈሳዊ ማስጠንቀቂያ ትምህርት ትርጉም ምን እንደሆነ ገብቷቸዋል።

ድርጭቶቹና መቅሰፍቱ (11፡31-35)።

1. እስራኤላውያን እግዚአብሔር በሰጣቸው ነገር አልረኩም።

2. ከማጉረምረም በስተቀር የሚፈልጉትን ነገር እግዚአብሔርን አልጠየቁትም። የእግዚአብሔርን መንገድ ሳይሆን የራሳቸውን መንገድ ፈለጉ [መዝ. 105(106)፡13-15]። እግዚአብሔርም የለመኑትን ሰጣቸው ለነፍሳቸው ግን ክሳትን ላከ።

3. ሆኖም እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን ሥጋ ሰጣቸው። እግዚአብሔርም ከምድር ሁለት ክንድ ከፍ ብለው የሚበሩትን ድርጭቶች አመጣላቸው። ምክንያቱም ሕዝቦቹ ድርጭቶቹን በቀላሉ ይዘው አርደው እንዲበሉዋቸው ነው። ከሁሉ ጥቂት የሰበሰበ አሥር የቆሮስ መስፈሪያ የሚያህል ሰበሰበ (ቁጥር 32)። እግዚአብሔርም በሚከተለው ምክንያት ተቆጣ።

4. ተመኙ፡- ቁጥር 34። እነርሱም ለራሳቸው ብዙ ማግኘት ፈለጉ። እነርሱም እግዚአብሔርን ሳይሆን መብልንና ሆዳቸውን አመለኩ። ይህም «የሥጋ ምኞት» ይባላል። አሥር የቆሮስ መስፈሪያ ከ20 በርሚል ይበልጣል። እነርሱም ያንን ሁሉ መብላት አይችሉም። ምግቡም በላያቸው ላይ ተዝረከርኮ አጥፍቷቸው ነበር፤ ነገር ግን አሁንም መሰብሰባቸውን አላቋረጡም። የዕለት ምግባቸውን መስጠት የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ዕለት ዕለት ምግባቸውን እንዲሰጣቸው መታዘዝና በእግዚአብሔር መታመን ደግሞ የእስራኤላውያን ሥራ ነበር። የራሱን ጥቅም ብቻ የሚፈልግ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊሆንና እግዚአብሔርን ማገልገል አይችልም (ማቴ. 6፡25-34)። ከምኞታቸው የተነሳ እግዚአብሔር በታላቅ መቅሰፍት ፈረደባቸው (ዘኍልቁ 11፡33)።

እስራኤላውያን ሕግን ከመቀበላቸው አስቀድሞ እግዚአብሔር ታገሳቸው። ምክንያቱም እንደ ሕፃናት ስለሆኑ ገና በእምነት አላደጉም ነበር። እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ነገርም አላወቁም ነበር። ሕፃናቶች አንዳንድ ነገር ሲፈልጉ እንደሚያለቅሱ ሁሉ እነርሱም እንደ ሕፃን ይነጫነጩና ያለቅሱ ነበር። ቤተሰቦች ሕፃናቶቻቸውን እንደሚታገሱ ሁሉ እግዚአብሔር ደግሞ ታገሳቸው። እስራኤላውያን ከክርስቶስ ጋር ለሁለት ዓመት በሲና ተራራ ላይ ከቆዩ በኋላ እግዚአብሔር ሕግን ሰጣቸው። ሕጉንም ተማሩ። የእግዚአብሔርን ኃይል ተአምራትና ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ተመለከቱ። ከዚያ በኋላ በእግዚአብሔር ላይ ሲቆጡ ጊዜ እግዚአብሔር ከፋኛ ቀጣቸው። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በዕድሜ ገፋ እንዳለ ልጅ እምቢተኛ ስለሆኑና አልታዘዝ ስላሉ ነው። እንዲህ ያለ ልጅ ቅጣት ይቀበላል። አዲስ ክርስቲያኖችን እግዚአብሔር ይታገሳል፤ በአደጉ ጊዜ እምቢተኛ ሆነው አልታዘዝ ሲሉ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

ዘኁልቁ 12፡- ሙሴ በጣም ትሑት ሰው ነበር። ምንም ዓይነት ኩራትም አይታይበትም ነበር (12፡3)። አሮንና እህቱ ማርያም ግን ክፉ ነገር ተናገሩበት። እነርሱም መሪዎች ሊሆኑና ሙሴ የተቀበለውን ዓይነት ክብር መቀበል ፈለጉ (12፡6-8)። እግዚአብሔርም በማርያም ላይ ፈረደባትና ለምጻም ሆነች (ቁጥር 10)። ሙሴም ጸለየላትና ከቀን በኋላ ተፈወሰች፤ ለክብር ሲባል የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን መፈለግ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ኃጢአት ነው። እንደ እነዚህ ያሉት ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር ስለሌለ ቤተ ክርስቲያንን ያጠፋሉ። እነርሱም የሕሊና ሰምጽ አለባቸው። ማርያም ክብሩ ወደ ሙሴ ሚስት ስለሚሄድ በሙሴ ሚስት ላይ ደግሞ መጥፎ ነገር ተናገረች። ይህም ምቀኝነት ነው፤ በዘጸአት 2፡15-21 እና በዘኁልቁ 10፡29 ስለ ሙሴ ሚስት አንብብ።

ዘኁልቁ 15፡37-41፡- እስራኤላውያን ሁሉ ከልብሳቸው ዘርፍ ላይ ሰማያዊ ጨርቅ ማድረግ አለባቸው። ይህም ቀለም የሰማያዊው አገር ልጆች እንደሆኑ የሚያሳይ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው። ከዚህም በቀር የመንግሥተ ሰማያት ልጆች ስለሆኑ የቅድስናን ኑሮ መኖር እንዳለባቸው ያሳያል። ይህም ደግሞ ቤታቸው ከሰማይ የሆነ ንጉሣቸውም ከሰማይ የሆነ ሰማያዊያን ሰዎች ከዓለምና የዓለም በሆነው ነገር ለመያዝ ፈቃደኞች እንዳይሆኑ ያሳስባቸዋል። ሊታዘዙት የሚገባቸው አምላክ ጌታቸው ስለሆነ እነርሱም ቅዱሳንና ንጹሐን እንዲሆኑ እግዚአብሔር መርጧቸዋል። እነርሱም የዚህ ዓለምን ጌታ መታዘዝ የለባቸውም (ቁጥር 41)።

ዘኁልቁ 16፡1-40፡- ቆሬና አባሪዎቹ በሕዝቡ ላይ ኃይል እንዲኖራቸውና ከሕዝቡ ክብርን ለመቀበል የክህነቱን ማዕረግ ለመውሰድ ፈለጉ። በእነርሱም ላይ እግዚአብሔር ፈረደባቸው። ምድርም ተከፍታ ከነሕይወታቸው ወደ ሲኦል ወረዱ።

1. እግዚአብሔር ራሱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ይመርጣል። ለማዕረግ ሽሚያ ለመመረጥ ራሳቸውን የሚገፋፉትን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።

2. በእግዚአብሔር የተመረጡት ካህናት ብቻ እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ተፈቅዶላቸዋል። በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን የሚገኙ አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት ናቸው (1ኛ ጴጥ. 3፡5-9)። ላላመኑት የሚያስተምሩ ያላመኑ አስተማሪዎች ሁለቱም ዕውሮች ስለሆኑ ማንኛቸውም ኃጥአን ባልተቀጡበት ፍርድ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል (ማቴ. 15፡14፤ ሉቃስ 6፡39፤ ማቴ. 23፡14፤ 3ኛ ዮሐ. 9-11፤ ይሁዳ 11)።

የቆሬ ልጆች አልሞቱም ነበር (ምዕ. 26፡11)። እነርሱም በአባታቸው ኃጢአት ስላልተባበሩ አባታቸው ፍርድን ከመቀበሉ አስቀድሞ አብረው እንዳይቀጡ ከዚያ ስፍራ ገለል መደረጋቸው አያጠራጥርም። በኢያሱ ምዕራፍ 7 ላይ የተጠቀሰው አካን እንዳያደርጉት በጥብቅ የተከለከለውን ኃጢአት የማድረግ ምሳሌ ነው። ልጆቹም ከእርሱ ጋር የነበረው ኃጢአት ምሳሌ ስለሆኑ ከእርሱ ጋር

አብረው ተፈረዱ። ቆሬ የካህንነት ሥራ ለመሥራት ስለፈለገ የኃጢአት ምሳሌ አይደለም። 1ኛ ዜና ምዕራፍ 6፡22፥ 37 ተመልከት።

250 ሰዎች ካህናት ሆነው በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ለመቆም ፈለጉ(ቁጥር 35)። የጸሎት ምሳሌ የሆነው ዕጣናቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም። እግዚአብሔርም ፈረደባቸው የእግዚአብሔር ካህናት ያልሆኑ ማለት (አማኞች ያልሆኑ) ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር መምራት አይችሉም።

ሕዝቦቹም እንደገና በሙሴና በአሮን ላይ ባጉረመረሙ ጊዜ እግዚአብሔር መቅሰፍት ልኮ 14 700 ሰዎችን ገደለ (ዘኍልቁ 16፡41-50)። ይህም እግዚአብሔር የቀባቸውን አገልጋዮቹን ማንም እንዳይጎዳቸው ወይም እንዳይነካቸው ማስጠንቀቂያ እንዲሆናቸው ለሕዝቡ ሰጠ። የእግዚአብሔርን ሰዎች ስለ ወንጌልና የእነርሱን ስፍራ ለመውሰድ በምቀኝነት ለሚያስጨንቋቸው ሰዎች ወዮላቸው [1ኛ ዜና 16፡21፥ 22፤ መዝ. 104(105)፡14፥ 15]።

የእግዚአብሔር መቅሰፍት ኃጢአትን ባደረጉት ሰዎች ላይ ሲመጣ አሮን ዕጣን ያለበትን ማጥንት ይዞ ሊያጥን ወደ ሰዎቹ መኃል ሮጠ። ከዚያም መቅሰፍቱ ስለቆመ የቀሩት ሰዎች ከእግዚአብሔር መአት ለመዳን ቻሉ። ዕጣን የጸሎት ምሳሌ ነው። አማኞችም ለጠፉት ነፍሳት ከልባቸው በሚጸልዩላቸው ጊዜ እግዚአብሔር ያድናቸዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ለምእመናኖቻቸው ኃጢአትን ድል አድርገው በአሸናፊነት ኑሮ እንዲመላለሱ ሲጸልዩላቸው እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ይመልሳል። ምእመናኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መሪዎቻቸውን ነው የሚመስሉት። ኃጢአተኞችና ደካማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃጢአተኛና ደካማ ምእመናኖች ይኖራቸዋል። በመንፈሳቸው ንጹሐን የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች መንፈስ ንጹሐን ምእመናን ይኖራቸዋል። እስራኤላውያን በመጨረሻ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደ ሙሴ ሆኑ። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት የሙሴን ምስክርነትና መንፈሳዊ አመራሩን ስለተከተሉ ነው (ዘፍ. 19፡18-23፤ ራእይ 5፡8፤ 8፡3፥ 4)።

ዘኍልቁ 17። ይህንንም በማድረጉ እግዚአብሔር እራሱ አገልጋዮቹን እንደሚመርጥ ለእስራኤላውያን አሳያቸው። የእስራኤላውያን ቤተሰቦች አንጋፋዎች በትሮቻቸውን ከአሮን በትር ጋር ቀላቅለው እንዲያስቀምጡ አደረገ። በአንድ ሌሊትም የአሮን በትር አቆጥቁጣ፥ አብባና ፍሬ አፍርታ አደረች። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር አሮንን ብቻ ሊቀ ካህን እንዲሆን እንደመረጠው የሚያሳይ ምልክት ነው። አሮንና በትሩ ደግሞ የክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው። የቀሩት በሞላ የሃይማኖት መሪዎች ለመሆን ፈልገው ነበር፤ እግዚአብሔር ግን አንድ ሰው ብቻ መረጠ። ብዙ ሰዎች ሃይማኖትን ለማቋቋም ጀምረው ነበር፤ ነገር ግን አሁን ሁሉም ሞተዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አሮን በትር ሞቶ ነበር። ነገር ግን እንደ አሮን በትር እንደገና ሕይወትን ዘርቶ ስለተነሳ አሁንም ለወደፊትም እስከ ዘለዓለምም ይኖራል።

የአቆጠቆጠችው በትር የማይታየው ንጉሣቸው ክርስቶስ ከሚቀመጥበት ዙፋን ሥር ማለት ከስርየት መክደኛው በታች በታቦቱ ውስጥ ተቀመጠች። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ የዓለም አዳኝ እንዲሆን እንደመረጠው ያሳያል። የቀሩት በሞላ አታላዮች ናቸው (የሐዋ. ሥራ 4፡12)።

ዘኁልቁ. 20፡2-13 ሕዝቦቹ ውኃ ስላልነበራቸው እግዚአብሔር ዓለቱን ተናገረው፤ ሕዝቡም በቂ ውኃ ያገኛል ብሎ ሙሴን አዘዘው። ሙሴም በሕዝቡ ተቆጥቶ ዓለቱን መታው። ሆኖም በቂ ውኃ ለሕዝቡ ፈለቀ፤ ነገር ግን ሙሴ ለእግዚአብሔር አልታዘዘም።

በዘጸአት 17፡5-7 እግዚአብሔር ሙሴ ድንጋዩን እንዲመታ አዞት ነበር። ሙሴም ይህን አደረገና ከዓለቱ በቂ ውኃ ለሕዝቡ ፈለቀ። ይህም የክርስቶስ ሞት ምሳሌ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለት ነው። ስለ እኛ ኃጢአት ኢየሱስ ክርስቶስ ተመታ ተፈረደበትም። እርሱም ስለሞተልን እኛ የሕይወት ውኃ ሊኖረን ቻለ። ክርስቶስም አንድ ጊዜ ብቻ ነው መሞት ያስፈለገው። ከዚህ በኋላ ማንም የሕይወት ውኃን ለመቀበል እግዚአብሔርን በጸሎት ቢጠይቅ ይቀበላል (ዮሐ. 7፡7-9፤ 4፡14)። ሙሴ ድንጋዩን ዳግመኛ በመታ ጊዜ የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነውን ክርስቶስን አጠፋ። ሙሴም ወደ ምድረ ከነዓን እንዳይገባ ቅጣት ተሰጠው። መዝ. 105(106)፡32፥ 33 ተመልከት።

ብዙ ሰባኪያንና ሽማግሌዎችም እግዚአብሔርን አይታዘዙም። ሙሴ ባለመታዘዝ ድንጋዩን ሲመታ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቂ ውኃ እንደሰጠ ሁሉ እንደዚሁም እግዚአብሔር ስለ ስሙ ሲል ዛሬ በማይታዘዘው ወንጌላዊ ሆኖ እንኳን ቃሉን ይባርካል። ነገር ግን ሙሴ ባለመታዘዙ ሽልማቱን እንዳጣ ዛሬም የማይታዘዝ ሰባኪ ሽልማቱን አይቀበልም። በዘጸአት የሚገኘውን የ24ኛውን ጥያቄ መልስ ተመልከት።

8. እስራኤላውያን በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅርና አንድነት ተለይቷቸው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሳይገኝ ቀርቶ ነበርን? ዘዳ. 2፡7፤ 8፡2፥ 4፤ 29፡5፥ 6፤ ዘኁልቁ 9፡19-21።

መልስ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለሕዝቡ እንደተጠነቀቀላቸው የሚያሳይ ነው። እነርሱም በእግዚአብሔር ላይ አምጸው አልታዘዝ ቢሉት እግዚአብሔር ደግሞ ቀጣቸው። እነርሱም ከነዓን የመግባታቸው ሽልማት ቀረባቸው። ስለዚህም በምድረ በዳ ውስጥ ሞቱ፥ ሆኖም ክርስቶስ በምድረ በዳ ሆነው ይንከባከባቸው ነበር። ከጠላቶቻቸውም ይከላከልላቸው ነበር። በደመና ዓምድም ይመራቸው ነበር። የሚበሉትንም መና ሰጣቸው። ልብሳቸውም ጫማቸውም አላለቀም፥ እግራቸውም አላበጠም ነበር። መልካም አባት ልጆቹን በእንክብካቤ እንደሚይዝ እግዚአብሔር ደግሞ በእንክብካቤ ይዟቸው ነበር።

አሁንም የእግዚአብሔር ልጆች አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ስለማይታዘዙ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል። ሆኖም በእምነታቸው እንዲያድጉ ይጠብቃቸዋል። እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ ደስታ፥ ሰላምና መንፈሳዊ ፍሬ እንዳልነበራቸው ሁሉ የማይታዘዙ የእግዚአብሔር ልጆችም ደስታ፥ ሰላም፥ መንፈሳዊ ፍሬ እንዲሁም በሰማይ የተጠበቀላቸው መዝገብ ወይም ሀብት አይኖራቸውም (ምዕ. 20፡14-36፡130)።

9. ሀ. በዘኍልቁ 20፡14-21፡35 የተጠቀሰው ነገር የት ነው የተደረገው?

መልስ።

በዚህ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰው ነገር የሆነው በምሥራቅና በደቡብ በኩል በሙት ባሕር አካባቢ ነው። (የጨው ባሕር የሚገኘው) በሲና ምድረ በዳና በዮርዳኖስ ባሕር ምሥራቃዊ በኩል ነው። በምዕራፍ 20፡14 ላይ እንደተገለጸው አሁን እስራኤላውያን ከምድረ በዳው መውጣት እንደጀመሩና በዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ያለውን ምድር እንደያዙ እናያለን። ዓላማቢስ የሆነው መንከራተታቸው አበቃ። በእግዚአብሔር ላይ አጉረምርመው የነበሩት ሰዎች በሞላ አለቁ። ልጆቻቸውም እግዚአብሔርን በመተማመን በእምነት እያደጉ ናቸው። ስለዚህ አሁንም ከዮርዳኖስ ምሥራቅ ያለውን ምድር ለመያዝ ዓላማ አላቸው።

9. ለ. ምን እንደተደረገ ግለጽ።

መልስ።

20፡14-22 እስራኤላውያን በኤዶማውያን ምድር በሰላም አቋርጠው ሊያልፉ ፈለጉ፥ ነገር ግን ኤዶማውያን አልፈቀዱላቸውም። በኋላም እግዚአብሔር ከዚህ የተነሣ ኤዶማውያንን ቀጣቸው፤ ኤዶማውያን የያዕቆብ ወንድም የዔሳው ልጆች ናቸው።

20፡23-29 አሮንም ሞተ። እርሱም ወደ ከነዓን እንዲገባ አልተፈቀደለትም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን አልታዘዘም ነበር (20፡7-12)። ሙሴም ካለመታዘዝ የተነሣ ወደ ከነዓን እንዳይገባ ተከለከለ (20፡12፥ 13፤ ዘዳግም 32፡48-52፤ 21፡1-4)። እስራኤላውያንም ከነዓናውያንን በደቡብ ዮርዳኖስ ድል አደረጓቸው። 21፡5-9 የናሱ እባብ። እስራኤላውያን በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ክፉ ነገር ተናገሩ (ቁጥር 5)፤ ይህም የልብና የምላስ ኃጢአት ነው። ወደ ከነዓን በእምነት ለመሄድ እስራኤላውያን ከኃጢአታቸው የደኅንነትን መንገድ መማር አለባቸው (ዮሐ. 3፡14-15፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)። እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው በግብፅ ሳሉ የግብፃውያንን የበኵር ልጆች በመግደል የደኅንነትን መንገድ በፋሲካው በዓል አሳይቷቸዋል።

1. እግዚአብሔርም ሕዝቦቹን ኃጢአት ስላደረጉ የሚናደፈውን እባብ በመካከላቸው ሰደደ። በእባቦቹ የተነደፉት በሞላ ሞቱ፥ እባቦቹም የኃጢአት

ምሳሌ ናቸው (ዘፍ. 3፡1-7)። ኃጢአትን ያደረጉና (በኃጢአት የተነደፉ ሁሉ) ከሞት ፍርድ በታች ናቸው።

2. ሕዝቦቹም «እኛ ኃጢአትን አድርገናል» ብለው በኑዛዜ ወደ እግዚአብሔር አለቀሱ (21፡7)። ሰው በእውነት በኃጢአቱ ተጸጽቶ ንስሐ ሲገባ እግዚአብሔር ከኃጢአት ፍርድና ከበደሉ እንዲድን የደኅንነትን መንገድ ያሳየዋል።

3. እግዚአብሔርም ሙሴ የናስ እባብ ሠርቶ ሁሉ እንዲያዩት በእንጨት ላይ እንዲሰቅለው አዘዘው። ንስሐ የፍርድ ምሳሌ ነው። እባቡም የኃጢአት ምሳሌ ነው። የናሱ እባብ መሰቀልም ኃጢአት በእንጨት ላይ የመፈረዱ ምሳሌ ነው። ይህም ደግሞ የተደረገው ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችው በመስቀል ላይ እንደሚሞት ሊያሳያቸው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛና ስለ እነርሱ በመስቀል ላይ ኃጥዕ ሆኖ የእግዚአብሔር ፍርድ በእኛ ላይ ሊወርድ ሲገባ በእርሱ ላይ ስለወደቀበት እኛ ከኃጢአት ፍርድ ነፃ ወጣን (2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ገላትያ 3፡13)።

4. ማንኛውም በእባብ የተነደፈ ሰው በእንጨት ላይ የተሰቀለውን የናስ እባብ ባየ ጊዜ ይድን ነበር። አሁንም ደግሞ ማንም ክርስቶስን በእምነት በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ ቢመለከት ከዘለዓለም ሞት ይድናል። እርሱም በእምነት ኃጢአቱ በመስቀል ላይ እንደተፈረደ አይቶ ይድናል። እነዚህ ሰዎች ከግብፅ የወጡት የእስራኤላውያን ልጆች ናቸው፤ አባቶቻቸው የፋሲካውን የበግ ደም በመዝጊያቸው ላይ በማድረግ ከሞት ፍርድ የዳኑበትን የደኅንነት መንገድ ተምረዋል። ለልጆቻቸው ደግሞ እግዚአብሔር በናሱ እባብ በኩል የደኅንነትን መንገድ አሳይቷቸዋል። እነርሱም እንደ አባቶቻቸው እንዳይረሱት ግላዊ ልምምድን ተለማምደዋል።

እስራኤላውያን መንገዳቸውን እንደቀጠሉ እግዚአብሔር የሚጠጣ ውኃ ደግሞ ሰጣቸው (ዘኁልቁ 21፡16-18)። በእምነት ክርስቶስን የተመለከቱ አማኞች ደግሞ የሕይወት ውኃ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ (ዮሐ. 6፡37-39፤ 4፡14)። እስራኤላውያን በደስታ ይዘምሩ እንደነበረ ማንኛውም አማኝ የሕይወት ውኃን ሲቀበል ደስ ይለዋል። ሥርዓቱ እንግዲህ እንደዚህ ነው።

ሀ. ማስተሰርያ ወይም ደኅንነት፡- ዘኁልቁ 21፡8፥ 9፤ ዮሐ. 3፡14፥ 15።

ለ. የተሰጠው ውኃ፡- ዘኁልቁ 21፡16-18፤ ዮሐ. 7፡37-39፤ ዮሐ. 4፡14 መንፈስ ቅዱስም ተሰጥቶአል።

ሐ. ደስታ ተሰጥቷል፡- ዘኁልቁ 21፡17፥ 18፤ ሮሜ 14፡17።

መ. ኃይል ተሰጥቶታል፡- ዘኁልቁ 21፡21-24።

21፡21-35 እስራኤላውያን ከእነርሱ ጋር ያለ የእግዚአብሔር ኃይል አላቸው። እነርሱም አማሌቃውያንን ወግተው ምድራቸውን ወረሱባቸው። ታዛዥ የሆነ የእግዚአብሔር ባሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግበት ኃይል አለው።

10. ሀ. በዘኁልቁ 22፡1-36፡13 እንደተጠቀሰው ምን ተደረገ?

መልስ።

ምዕ. 22፡25 የበለዓም ትንቢትና ትምህርት።

ምዕ. 26 የሕዝቦቹ መቆጠር።

ምዕ. 27፡1-11 የወራሾች ሕግ ተሰጠ።

ምዕ. 27፡12-23 ኢያሱ በሙሴ ፋንታ እስራኤልን እንዲመራ ተሾመ።

ምዕ. 28-30 የመሥዋዕቱ ሕግና ስዕለቱ ተደገመ።

ምዕ. 31 ምድያማውያን በእስራኤላውያን ተፈረደባቸው።

ምዕ. 32 የሮቤልና የጋድ ዘሮች ምሥራቃዊውን ዮርዳኖስ እንዲለቁ።

ምዕ. 33-36 ወደ ከነዓን ለመግባት የተደረገው ዝግጅት።

10. ለ. በየት ነው ይህ ነገር የተደረገው?

መልስ።

እስራኤላውያን በምሥራቅ ዮርዳኖስ ከኢያሪኮ ፊት ለፊት በሞዓብ ሜዳ ላይ ነበሩ (22፡1)።

11. የበለዓም ትንቢት ጥቅሙ ምን እንደሆነ አብራራ። 24፡17።

መልስ።

«የያዕቆብ ኮከብና የእስራኤል በትር» የሆነው ክርስቶስ መጥቶ የእስራኤል የዘለዓለም ንጉሥ እንደሚሆን ትንቢት ተናገረ። እርሱም ለ1000 ዓመት በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ በሰላም የዓለምን ሕዝብ በሞላ ይገዛል። ኮከብ የንጉሡ የክርስቶስ ምልክት ነው (ማቴ. 2፡2)። በትሩም ደግሞ የንጉሡ ምልክት ነው።

«<u>የበለዓም ትምህርት</u>» (ዘኁልቁ 25፤ 31፡16፤ ራእይ 2፡14፤ ያዕቆብ 4፡4)። በለዓም እስራኤልን የረገመ እንደሆነ እግዚአብሔር ይፈርድብኛል ሲል ፈራ። እርሱም ደግሞ እግዚአብሔር የባረከውን ለመርገም ኃይል እንዳልነበረው ያውቅ ነበር። ስለዚህ በለዓም እስራኤላውያንን እንዴት አድርገው ማጥፋት እንደሚችሉ ሞዓባውያንንና ምድያማውያንን መከራቸው። ያም ምክር የበለዓም ትምህርት ይባላል። ምዕራፍ 25 እና 31፡16 ስታነብ በለዓም እስራኤላውያን በኃጢአታቸው እንዲጠመዱ ምድያምንና ሞዓብን ጓደኛ እንዲያደርጋቸው

እንደመከራቸው ታያለህ። በኃጢአት ከተጠመዱ በኋላ እግዚአብሔር በኃጢአተኛ ላይ ስለሚፈርድ በቀላሉ ይፈርድባቸዋል አላቸው። ዛሬም ሰይጣን ይህንኑ ማጥቂያ መሳሪያ በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንና የእግዚአብሔርን ሰዎች ምስክርነት ያጠፋል። የእግዚአብሔር ሰዎች የዓለም ወዳጅ በሚሆኑበት ጊዜ በዓለም ኃጢአት ተጠምደው ስለሚወድቁ የእግዚአብሔር በረከትና ኃይል ይገፈፍባቸዋል። የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ ክርስቶስ ለዓለማውያን ጥሩ ምስክር መሆን አለባቸው፤ ሆኖም በኃጢአታቸው በምንም መንገድ መተባበር አያስፈልግም (ራእይ 2፡14)። የበለዓም ትምህርት ለእስራኤላውያንም ሆነ ለአማኞች ከዓለማውያን ጋር እንዲደባለቁና በኃጢአታቸው እንዲተባበሩ ካደረገ በኋላ በመጨረሻ እግዚአብሔር እራሱ በሕዝቡ ላይ እንዲፈርድባቸው ማድረግ ነው (ዘኁልቁ 25)።

«<u>የበለዓም መንገድ</u>» (2ኛ ጴጥ. 2፡15፤ ዘኁልቁ 22፡5-7)። በለዓም ለገንዘብ ሲል ሰበከ። እውነትን ቢሰብክ ወይም ባይሰብክ ግድ አልነበረውም። ደመወዙን ለማግኘት ብቻ የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ ገንዘብ ስለሚሰጠው እስራኤልን በደስታ ሄዶ ሊረግም ፈለገ። ነገር ግን የፈራው እግዚአብሔር እንዳይፈርድበት ብቻ ነው። በለዓምም የሚበቃውን ያህል ወርቅ ለመቀበል እስራኤልን ለመርገም እግዚአብሔር እንዲፈቅድለት ፈለገ። በለዓምም እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ያለውን አሳብ እንዲለውጥ ብዙ መሥዋዕት አቀረበ። ለደመወዝ ተብሎ ሰዎች ሊሰሙት የሚወዱትን ስብከት መስበክ በበለዓም መንገድ መመራት ነው።

ስለዚህ ዛሬ ብዙ ሰባኪያን የበለዓምን መንገድ ይከተላሉ። ውሸተኛ ማኅበሮች ከቀድሞ ይልቅ ገንዘብና ክብር ቢሰጧቸው እንኳ ወደዚያ መሄድን ይመርጣሉ። ሆኖም ከእግዚአብሔር ያልሆነ ትምህርትን መስበክ መጥፎ ሕሊናን ይሰጣቸዋል። ስለዚህ እነርሱ ደግሞ እንዲሄዱ እግዚአብሔር እንዲፈቅድላቸው በጸሎት ይጠይቃሉ። በለዓም በተለያዩ ስፍራዎች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዳቀረበ እነርሱ ደግሞ እግዚአብሔር የፈቀደላቸው እንደሆነ የሚመስለውን ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይፈልጋሉ። እነርሱም በነገሩ ሳይጸልዩበት እግዚአብሔር በቃሉ ያላዘዘውንና የቀጠሯቸው ሰዎች ሊሰሙት የሚወዱትን ዓይነት ስብከት ሄደው ለመስበክ ሕሊናቸውን መልካም ነው ብለው ይገፋፉታል። በዚህ አድራጎታቸው የበለጠ ደመወዝ ያገኛሉ። ነገር ግን በበለዓም ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱም ላይ ይወድቅባቸዋል። በዚህ አድራጎታቸው የበለጠ ደመወዝ ያገኛሉ። ነገር ግን በበለዓም ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱም ላይ ይወድቅባቸዋል። ለገንዘብና ለክብር ተብሎ እግዚአብሔር በቃሉ ያላዘዘውንና ሰዎች ሊሰሙት የሚወዱትን ስብከት መስበክ ይህ የበለዓም መንገድ ነው።

<u>የበለዓም መቃወስ ወይም ችግር (ዘዳግም 11)</u>።

በለዓም እስራኤላውያን ከዓለም ጋር ከተደባለቁና ኃጢአትን ካደረጉ እግዚአብሔር እንደሚደመስሳቸው ያውቅ ነበር። በለዓምም እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ እንደሆነና በኃጢአት ላይ እንደሚፈርድ ያውቅ ነበር። ነገር ግን

በእውነት በመናዘዝ በመስቀል ላይ ስለ ዓለም ኃጢአት በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የኃጢአት ስርየት እንደሚገኝ አያውቅም ነበር። እግዚአብሔርም 24 000 ሰዎችን በሞት ፈረደባቸው (ዘኍልቁ 25፡9)። ነገር ግን በእውነት ለተናዘዙት ሁሉ በእነርሱ ምትክ የሚፈረድበት መሢሕ እንደሚመጣ በማመን ንስሐ ስለገቡ ከሞት ፍርድ አመለጡ።

በለዓም የተሳሳተው ትልቅ ስሕተት ምድያማውያን እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራታቸው ፍርድ ላይ እንዲወድቁ ማድረጉ ሲሆን እስራኤላውያን ግን ከፈተናው በኃይልና በቅድስና ወጡ (25፡16-18)። በለዓምም ተሰውቶ ተገደለ። ገንዘቡ ምንም ጥቅም አልሰጠውም (ኢያሱ 13፡2፤ ዘኍልቁ 31፡8)።

በመሳፍንት 11 ላይ እንደተጠቀሰው በለዓም ከተሳሳተ በኋላ ጥቂቶቹ ሰዎች ወደ ክፋትና ወደ መስሪንት ጠባይ ተወሰዱ። እነርሱም ሰውን ሳይሆን ራሳቸውን አታለሉ። የእግዚአብሔርም ፍርድ ይወርድባቸዋል። እነርሱም ማምለጥ አይችሉም።

12. ሀ. ሕዝቦቹ በሰጢም ሳሉ የተቆጠሩበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ።

አስቀድሞ በሲና ተራራ አጠገብ ተቆጥረው የነበሩት ሁሉ ባለመታዘዛቸው ሞቱ። ካሌብና ኢያሱ ብቻ ጎበዞች ነበሩ። አሁንም ደግሞ ከለመታዘዛቸው ምክንያት ያለ ጊዜአቸው ተቀስፈው የሚሞቱ አሉ (1ኛ ቆሮ. 11፡30)። እግዚአብሔርም ያሳደጓቸው ልጆቻቸው ወደ ከነዓን ወርደው ይወርሱታል ይላል። ስለዚህ እንደገና ለወታደርነት ተመልምለው ለጦርነት እንዲዘጋጁ ግድ የሚያስፈልግ ሆነ (26፡63-65)።

12. ለ. ሌዋውያን በዚህ ቆጠራ ውስጥ ገብተው ለምን አልተቆጠሩም ነበር? ምዕ. 26።

መልስ።

ሌዋውያን ከእስራኤል ልጆች ጋር ተደባልቀው ያልተቆጠሩበት ምክንያት እስራኤላውያን ምድረ ከነዓንን ሲካፈሉ እነርሱ ስላልተካፈሉና ርስታቸው እግዚአብሔር የሆነ አገልጋዮቹ ስለሆኑ ነው (26፡60-65)። እነርሱም በእውነተኞዎቹ የእግዚአብሔር ካህናት፥ አማኞችና አገልጋዮቹ ይመስላሉ። እነርሱም ምንም ዓይነት የመሬት ውርስ የላቸውም። የሚወርሱት መንግሥተ ሰማያትን ነው (1ኛ ጴጥ. 2፡9፤ ዕብ. 11፡13-16፤ ቈላስ. 3፡23፥ 24፤ ዕብ. 9፡15፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡4)።

ለሌዋውያንም 48 ከተማዎችና ከብቶቻቸው የሚሰማሩበት ጥቂት ምድር ከአካባቢው ተሰጣቸው። እነዚህም ከተማዎች በ12ቱ የእስራኤል ነገድ መካከል የተከፋፈሉ ናቸው (ኢያሱ 21፡41፤ ዘኍልቁ 35፡7)።

13. ስለ ሮቤልና ጋድ ጥያቄ አጥጋቢ ምክንያት ስጥ።

መልስ።

ከእስራኤል ነገድ መካከል እነዚህ ሁለቱ ሮቤልና ጋድ ብዙ ከብቶች ነበራቸው። ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ የሚገኘው ምድር ለከብቶች ግጦሽ መልካም ስለነበረ ለራሳቸው እንዲሰጣቸው ጠየቁ። እነርሱም ይህንን ምድር በመቀበል በሰሜናዊ ዮርዳኖስ የሚገኘውን ምድረ ከነዓንን ለመውረስ አላሰቡም። ሆኖም በምሥራቅ ዮርዳኖስ በኩል ወደ ከነዓን ሄደው ገና ድርሻቸውን ያልወረሱትን እስራኤላውያን በጦርነት ሊረዷቸውና ጠላቶቻቸውን ድል አድርገው ምድሪቱን ሊያስወርሷቸው ፈቃደኞች ሆኑ፤ ስለዚህ ያ በዮርዳኖስ በስተምዕራብ የሚገኘው ምድር ለሮቤል ለጋድና እንዲሁም ገሚሱ ለምናሴ ነገድ ተሰጠ (ዘኁልቁ 32፡1)።

እነዚህ ነገዶች ከዓለም ጨርሰው ባልተለዩ አማኞች ይመሰላሉ። እነርሱም በዓለማውያንና በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል በሚገኘው ድንበር ላይ ይኖራሉ። ከዓለም ፍቅር የተነሣ እግዚአብሔር በሰላም ትኖሩበታላችሁ ብሎ ተስፋ በሰጠው አገር ውስጥ ገብተው በሰላም መኖር አይፈልጉም። ጨርሰው ከዓለም ካልተለዩ በስተቀር ልጆቻቸው ዓለማዊውን ነገር ይከተላሉ። ከእስራኤል ነገድ መካከል በመጀመሪያ ጊዜ ቅጣትን በመቀበል በሶርያውያኖች ተማርከው የተወሰዱት የሮቤል የጋድና ግማሹ የምናሴ ነገድ ናቸው።

14. ሙሴ ለእነዚህ ነገዶች ከሰጣቸው ትእዛዝ ጋር ተወራራሽነት ያለው በክርስቲያንነታችን ልናደርገው የሚገባን ነገር ምንድን ነው? ምዕ. 32።

መልስ።

እነዚህ አስቀድመው ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ምድራቸውን የወረሱት ነገዶች የቀሩት ነገዶች ደግሞ ፋንታቸውን ርስት እስኪወርሱ ድረስ ሊረዷቸው ይገባል። ሌሎቹ ደግሞ እረፍት እንዲያገኙ ለሌሎቹ መዋጋት ነበረባቸው። እንደዚሁም ሁሉ ዛሬም በክርስቶስ እምነት የዳኑት አማኞች የጠፉት ሁሉ ድነው የጌታ ቤተ ክርስቲያን እስኪሞላ ድረስ ሥራቸውን ማቋረጥ የለባቸውም። አማኞች ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ ነፍሳትን ከሰይጣን እጅ ለማዳን ከሰይጣን ጋር አጥብቀው መዋጋት አለባቸው። ከዚያም በኋላ ፍጹም እረፍት ይሆናል። በዘኁልቁ ምዕራፍ 35 በዘዳግም ውስጥ 20ኛውን ጥያቄ ተመልከት።

# አሪት ዘዳግም።

በዘዳግም እንደተገለጸው አዲሶቹ ትውልዶች በምድረ በዳ ውስጥ አደጉ። ሙሴም ለአባቶቻቸው በጠቅላላው ከ40 ዓመት በፊት በሲና ተራራ አጠገብ የነገራቸውን የእግዚአብሔርን ሕግና ተስፋ አሁን ደግሞ በድጋሚ ለልጆቻቸው ሕግጋቱና ተስፋውን በሙሉ ነገራቸው። ሙሴም አባቶቻቸው ከእምነታቸው ጉድለትና ካለመታዘዛቸው ሳይወርሱት የቀሩትን ምድር እግዚአብሔር እንዲያወርሳቸው እንደአባቶቻቸው እልከኞችና እንቢተኞች እንዳይሆኑ ምክርና ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው። እግዚአብሔር ለእኛም በ1ኛ ቆሮ. 10፡1-12 ባለው ክፍል ላይ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያን ሰጥቶናል። (1ኛ ቆሮ. 11፡30 ደግሞ ተመልከት።)

የፓለስቲናው ኪዳን (የከነዓኑ ኪዳን) በምዕራፍ 30፡1-10 ይገኛል። ዘዳግም የጥብቅ አገዛዝ መጽሐፍ ነው። መክፈቻ ቃሉም «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ውደድ» የሚል ሲሆን መክፈቻ ቁጥሩ ደግሞ በ6፡5 የሚገኘው ነው።

የዘዳግም መጽሐፍ ሰባት ክፍሎች አሉት።

1. ምዕራፍ 1-3 የእስራኤልን ሕዝቦች ታሪክ በምድረ በዳ የሚገልጽ ፍሬ ነገር የያዘ ክለሳ።

2. ምዕራፍ 4-11 በምክርና በማስጠንቀቅ የሕጉ ዳግመኛ መመስረት።

3. ምዕራፍ 12-27 መምሪያ፥ ማስጠንቀቂያ፥ ማሳረጊያ።

4. ምዕራፍ 28-30 ገና ወደፊት ሊሆን ስላለው እስከ አሁን ስላልሆነው ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ የሚገልጽ ፍሬ ነገር የያዘ የእስራኤል ታሪክና ትንቢት። ይህ ክፍል የፓለስቲናውያንን ኪዳንና (የከነዓንን ኪዳን) አጣምሮ የያዘ ነው።

5. ምዕራፍ 31 በመጨረሻ ለካህናት ማለት ለሌዋውያንና ለኢያሱ የተሰጡ ምክሮች።

6. ምዕራፍ 32-33 የሙሴ መዝሙርና የበረከቱ ክፍል።

7. ምዕራፍ 34 የሙሴ ሞት።

ዘዳግም እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ለ40 ዓመት ያደረጉትን ጉዞ በሞላ ያጠቃልላል።

1. መቼና የት ነው የዚህ የመጽሐፍ ቃል ለእስራኤል ልጆች የተሰጠው?

መልስ።

የዚህ መጽሐፍ ቃል ለእስራኤል ልጆች የተሰጠው ግብፅን ለቀው በወጡ በ40 ዓመት ከ10 ወራቸው ነው (ዘዳግም 1፡3)። በዚህን ጊዜም ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ በፊት ወደ ከነዓን ሳይገቡ የመጨረሻውን መምሪያ ለመቀበል ድንኳናቸውን በተከሉበት በዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በሚገኘው ቦታ ነበሩ (ዘኁልቁ 36፡13፤ ዘዳግም 1፡1፥ 2)።

2. የዘዳግም መጽሐፍ ትምህርት ምንድን ነው? 1፡1-4፡43።

መልስ።

ሙሴ በምድረ በዳ የሆነባቸውን ነገር ሁሉ በድጋሚ ለእስራኤላውያን ይነግራቸዋል (1፡1-3፡29)። ለአባቶቻቸው በሲና ተራራ አጠገብ የተሰጣቸውን ትምህርት አስተማራቸው (ምዕ. 4)። አዲሶቹ ትውልዶችም እንደ አባቶቻቸው እንዳይወድቁ መታዘዝን መማር ነበረባቸው።

3. እስራኤላውያን የተገነዘቡት ስለ ምን ዓይነት ሦስት ኃጢአት ነው?

መልስ።

1. በቃዴስ በርኔ አባቶቻቸው ስላደረጉት አመጽ (1፡26)።
2. ስለ አለማመናቸው (1፡32-33)።
3. ስለ ትዕቢታቸው (ትዕቢት) (1፡43)።

4. በምዕራፍ 1፡1-4፡43 የተሰጠው መግለጫ እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት ስለሰጠው የክርስቶስ ፍቅርና ጸጋ ምን ያሳያል?

መልስ።

ምዕ. 1፡8-10፡21። እስራኤላውያን ምድረ ከነዓንን እንደሚወርሱ ተስፋ ተሰጣቸው (1፡6-23፤ ምዕ. 1፡30-34)። ጌታ እስራኤልን ተሸከማቸው፥ ይዋጋላቸውም ነበር (ምዕ. 1፡33)። እግዚአብሔርም በምድረ በዳ ባደረጉት ጉዟቸው ሁሉ መራቸው (ምዕ. 2፡7)። እግዚአብሔርም በምድረ በዳ ባረካቸው፤ የሚያስፈልጋቸውንም ነገር ሰጣቸው (ምዕ. 3፡2)። እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን በምድረ በዳው ውስጥ አትፍሩ እኔ አድናችኋለሁ፥ ጠላቶቻችሁንም በእጃችሁ አሳልፌ እሰጣለሁ አላቸው (ምዕ. 4፡5-7)። እግዚአብሔርም ከእስራኤላውያን ጋር በቅርብ እንዳለና፥ ጥበብም እንደሚሰጣቸው ተስፋ ገባላቸው (ምዕ. 4፡33)። እግዚአብሔርም እስራኤልን ተናገራቸው፥ እነርሱም የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰለሰሙ አልሞቱም፥ ይህንን ለማንም ለሌላ ነገድ አላደረገም (ምዕ. 4፡34)። እግዚአብሔር ራሱ በኃይልና በተአምራት እስራኤላውያንን ከሌላ ሕዝብ መካከል አውጥቶ የግሉ አደረጋቸው (ምዕ. 4፡37)። እግዚአብሔርም ይህንን ሁሉ ከፍቅሩ የተነሳ አደረገላቸው።

ምዕ. 4፡40 ለታዘዙትም እንዲሁ በነፃ ረጅም ዕድሜ እንደሚሰጣቸው ተስፋ ገብቷል።

5. ሙሴ ይህንን ለምን ደገመላቸው? ሕዝቦቹስ ምን እናደርጋለን አሉ?

መልስ።

የእስራኤል አባቶች በሞላ በምድረ በዳ ውስጥ ሞቱ። ልጆቻቸውም በዚያው አደጉ። ልጆቻቸውም አባቶቻቸው ከግብፅ ሲወጡ የተለማመዱትን ተአምራት አላዩትም ነበር። ሙሴም በዚህን ጊዜ ስለ አወጣጣቸው ነገር አሳሰባቸው። እርሱም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደሚወዳቸውና በአለማመናቸውና ባለመታዘዛቸው ምክንያት እግዚአብሔር እንደፈረደባቸው ነገራቸው። አሁንም አዲሱ የእስራኤል ትውልድ ለእግዚአብሔር ቢታመንና ቢታዘዝ እግዚአብሔር የበለጠ ተአምራት አድርጎ የከነዓንን ምድር ይሰጠዋል አላቸው። ለአባቶቻቸው ያልሰጠውን ሰላም፥ ደስታና በረከት ረጅም ዕድሜ እንደሚሰጣቸውም ነገራቸው። ዘዳግም 4፡40 ተመልከት። ለአባቶቻቸው በግብፃውያን ላይ እንዳደረገ ለእነርሱም ደግሞ በከነዓናውያን ላይ እንደሚያደርግላቸው ነግሯቸዋል። ስለዚህ በርቱ (ዘዳግም 4፡41-43)። በዘዳግም ያለውን 20ኛውን ጥያቄ ተመልከት።

በዘዳግም 4፡44-11፡32 ያለውን ክፍል አንብብ።

6. በዚህ ክፍል ላይ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ምን እንዲያደርጉ ይፈልግባቸዋል? 4፡44-45።

መልስ።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በሕዝቡ ፊት አኑሮአል (5፡29)። አሁን እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለእርሱ ባላቸው ፍቅር በሙሉ ልባቸው ፈቃዱን እንዲያደርጉና እርሱም ለዘለዓለም ሊባርካቸው እንዲችል ነው (6፡1፥ 2፣ 8፡1፥ 2፤ 9፡1-3፤ 11፡10-12 ና 32)።

7. በምዕራፍ 5 ላይ የተገለጸው ምን ዓይነት ለእስራኤል የሚሆን ታላቅ ምኞት ነው?

መልስ።

የእግዚአብሔር ታላቅ ምኞቱ እስራኤላውያን ኃጢአትን እንዲጠሉና ተገደው ሳይሆን ከልብ በመነጨ ፍቅር በሙሉ ልባቸው እንዲወዱትና እንዲታዘዙት ነው (5፡29፤ 8፡5፥ 6፤ ኤርምያስ 31፡32፥ 33)። እግዚአብሔር ይህንን ሕግ ለእስራኤል የሰጠው ስለወደዳቸው ነው። ስለዚህ እስራኤላውያንም ሊወዱት ይገባል (8፡5)።

8. እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ የሰጠበት ምን ምክንያት አለው? ምዕ. 6።

መልስ።

እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ ለእስራኤላውያን የሰጠው እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ነገር እንዲያውቁት ነው። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር እስራኤላውያን በዓለም ሕዝብ መካከል ሲኖሩ ጥሩ ምስክርነት ያላቸው የእግዚአብሔር ካህናት እንደሆኑ ለሕዝቡ እንዲያሳዩ ነው (6፡1-3፤12፤16 ና 18)።

9. እግዚአብሔር የከነዓናውያን ቅሬታ ሁሉ ይታረዳሉ ያለውን ትእዛዝና ዝንባሌ አሳይ። ምዕራፍ 7።

መልስ።

7. ከነዓናውያን ከእስራኤላውያን ጋር እንዲኖሩ ከተፈቀደላቸው ቅዱሳን ሕዝብ መሆን ያለባቸውን እስራኤላውያንን ወደ ኃጢአት ይመሯቸዋል ተብሎ ነው። በቅድስና ሆኖ ለመኖር ከተፈለገ የእግዚአብሔር ሰዎች ፈጽሞ ከዓለማውያን ያልተቀደሰ ኑሮ መለየት በጣም አስፈላጊ ነው። ከነዓናውያንም በኃጢአታቸው ተጣብቀው የሚኖሩ ኃጢአተኞች ስለነበሩ እግዚአብሔር ምሕረት ሊያደርግላቸው አልቻለም። እያንዳንዱ ከነዓናዊ በነፍስ ወከፍ ለምሕረትና ለይቅርታ ከተዘጋጀና ራሱን ወደ እግዚአብሔር ካቀረበ ይድናል። በጠቅላላው በአንድነት የከነዓናውያንን ዘር በሙሉ ግን ወደፊት ይቅርታ ሊያደርግላቸው ከቶ አልቻለም (7፡10)።

1. የእግዚአብሔር ፍላጎት እስራኤላውያን ቅዱሳን ሕዝቦች እንዲሆኑ ነው (7፡5፥ 6)።

2. የእግዚአብሔር ጸጋ በእስራኤላውያን ላይ ነበረ (6፡7፥ 8)።

3. እግዚአብሔር ዋጅቷቸው ነበር (7፡8)። እነርሱም ከከነዓናውያን ጋር ተዋጅተው ወደ ኃጢአታቸው ከተመሩ ይህ ሁሉ ስጦታ ይወሰድባቸዋል። እግዚአብሔርም እነርሱ ከከነዓናውያኖች ከተለዩ እንደሚባርካቸው ተስፋ ሰጥቶአል (ቁጥር 13-17)። የእግዚአብሔርን በረከት የሚፈልግ ሁሉ ከክፉ ነገር በሙሉ መለየት አለበት።

ከነዓናውያን በልባችን ውስጥ ሆኖ የሚያስቸግረን የነፍሳችን ጠላት የሆነው የኃጢአታችን ምሳሌ ናቸው። እነዚህ ኃጢአቶች በእጃችን ናቸው። እግዚአብሔርም እንድናያቸው ገልጦልናል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ርዳታ ልንደመስሳቸው ይገባል። እኛም ልናስወግዳቸውና ልንደመስሳቸው ከፈለግን ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ይረዳናል፥ ይባርከንማል። እኛ ግን የልባችንን ኃጢአት ለመደምሰስ ፈቃደኞች ካልሆንን የእግዚአብሔር በረከት ፈጽሞ በእኛ ላይ አይወርድም። ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚወድ ያስጠነቅቃቸዋል።

10. ታዛዥ ልብ ላለው ሰው ምን ሊደርግለት ተስፋ ተሰጠ?

መልስ፡፡

እስራኤላውያን በሙሉ ልባቸው በፍቅር እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ነገር ቢፈጽሙ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የገባላቸውን ተስፋ በሙሉ ይፈጽምላቸዋል (7፡12፥ 13)፡፡ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ልጆቻቸውን፥ ከብቶቻቸውን፥ ርስታቸውን፥ እነርሱንና ያላቸውን በሙሉ ባርኮ ያበዛቸዋል (7፡15)፡፡ እግዚአብሔርም በሽታቸውንና ሕመማቸውን በሞላ አስወግዶ በጠላቶቻቸው ላይ በሞላ ይፈርዳል፡፡

ዘዳግም 7፡15 የግብፃውያን ሕመም እነርሱ እስራኤላውያንን አንለቅም በማለታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከባቸው ሕመም ነው፡፡ እግዚአብሔርም እስራኤላውያን ከታዘዙኝ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁባቸውን በሽታ አላመጣባቸውም አለ፡፡ የግብፃውያን ሕመም ለቅጣት ከእግዚአብሔር የመጣባቸው ነው፡፡ ይህም በሽታዎች ደካማ ሥጋ ስለለበስን እኛን የእግዚአብሔር ልጆችንም የማያምኑትንም የሚያጠቁ ዓይነት በሽታዎች አይደሉም (1ኛ ቆሮ. 11፡29-32፤ 5፡1-5፤ በተለይ ቁጥር 5፥ 1ኛ ጢሞ. 1፡20ን አንብብ)፡፡

11. በምዕ. 8 ላይ እንደ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ዕቅድ እስራኤልን እንደመራና እነርሱም ተግሳጹን ወይም ቅጣቱን እንደተቀበሉ ሁሉ እግዚአብሔር ከምን እንዲጠበቁ ነው ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው?

መልስ፡፡

ዘዳግም 8፡2 እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ምድረ በዳ የመራቸው እነርሱ የራሳቸው የሆነ ብርታት ስለሌላቸው ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉና ትሕትናን እንዲማሩና በሁሉ ነገር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ እንዲችሉ፥ በእርሱ መታመንን እንዲለማመዱ ነው (8፡2-6)፡፡ ከዚህም በቀር ሰውነትን ከሚያዳብር ምግብ ይልቅ ነፍሳቸው እጅግ ጠቃሚ እንደሆነች ማረጋገጫ ትምህርት አገኙ (ቁጥር 3)፡፡

ዘዳግም 8፡5 እስራኤላውያንም እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ወደ ጽድቅ ሊመራቸው እንደሚቀጣ መማር አለባቸው (ዕብ. 12፡6፥ 7፤ ራእይ 3፡19)፡፡

ዘዳግም 8፡11 እስራኤላውያን ሀብታሞች በሚሆኑና በሚደላቸው ጊዜ እምቢተኞች እንዳይሆኑና ትእዛዛቱንም እንዳይረሱ እግዚአብሔርም በዚህ ምክንያት እንዳይፈርድባቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው (8፡11-20)፡፡ እነርሱም ያላቸው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው መገንዘብ ነበረባቸው፡፡ በመሳፍንት መጽሐፍ እስራኤል እግዚአብሔርን ደጋግመው እንደረሱትና እግዚአብሔርም በንስሐ ወደ እርሱ እንዲመለሱ እንደቀጣቸው ተጽፏል፡፡

እንደዚሁም አማኞችና የእነርሱ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ እኔ እግዚአብሔር ለወንጌል መስፋፋት ሰጥቻችኋለሁና ከሰጠኋችሁ ላይ መልሳችሁ ስጡኝ ብሎ ስለጠየቀን በደስታ መስጠት አለብን፡፡ እግዚአብሔር ብዙዎቹን ብዙ ገንዘብ በመስጠት አይባርክም፥ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ረስተው

ገንዘባቸውን ስለሚያመልኩ ነው። እነርሱም በዚህ ምክንያት በመንፈሳዊ በኩል ይጎዳሉ።

12. በምዕ. 9 ለማስታወስ ከፍ ከፍ የሚያደርጉት ነገር ምንድን ነው?

መልስ።

1. እግዚአብሔር ስለ ጽድቃቸው ወደ ከነዓን ምድር እንዳላመጣቸው እስራኤላውያን ሁልጊዜ ማስታወስ አለባቸው። እነርሱ ኃጢአተኞችና ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ሕዝቦች ናቸው (9፡4-6፡24፥ 27)።

2. ከክፋታቸው የተነሳ እግዚአብሔር ከነዓናውያንን አጥፍቶ ምድራቸውን ለእስራኤላውያን ሰጠ (9፡3-5)።

3. እግዚአብሔር የከነዓናውያንን ምድር ወስደ፥ እስራኤላውያንም የሰጣቸው የሚገባቸው ሆኖ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ብሎ ነው (9፡5፥ 27)።

13. እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን የሚፈልግባቸውን ነገር ከምዕራፍ 10 እና 11 ላይ አሳይ። እንደዚሁም ደግሞ ይህ የሚፈለግባቸው ነገር በምን ሁናቴ መደረግ እንደሚገባው ግለጽ።

መልስ።

ዘዳግም 10፡12 እግዚአብሔር ከእስራኤል የሚፈልግባቸው ነገር እንዲፈሩት፥ በመንገዱ እንዲራመዱ፥ እንዲወዱትና በሙሉ ልባቸውና ነፍሳቸው እንዲያገለግሉት ነው። ቁጥር 3 ትእዛዛቶቹንና ሥርዓቶቹን እንዲጠብቁ። ቁጥር 20 በእርሱም እንዲማበቁ። ምዕ. 10፡14-16፤ 11፡1፥ 8፥ 13፥ 18፥ 22 ተመልከት። ልጆቻቸውንም የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያስተምሩ ኃላፊነት አለባቸው (11፡18-21)። እግዚአብሔር ይህንን ጉዳይ በዚህ ሁናቴ አጥብቆ አሳሰባቸው።

1. እርሱ በጽድቅ የሚፈርድ ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነ አሳሰባቸው (10፡10-19)።

2. በአለፉት ዘመን ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ አሳሰባቸው (10፡22-11፡7)።

3. እነርሱ እግዚአብሔርን ስለአገለገሉት እግዚአብሔር እንደ ዋጋ አድርጎ በብዙ በረከት ባረካቸው (11፡8-16፤ 22-25፤ 26፡27)።

4. ባይታዘዙ ፍርድን ያመጣባቸዋል (11፡16፥ 17፥ 26-29)። የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ መፈጸሙ እግዚአብሔርን ማመን ነው።

ዘዳግም 12-26 አንብብ።

14. በዚህኛው የዘዳግም መጽሐፍ ክፍል የሚገኘው የአሳብ ሁናቴ እንዴት ነው?

መልስ።

ከምዕራፍ 12 እስከ 26 እግዚአብሔር ሕዝቦቹ በተሰጣቸው ምድር ላይ ሲኖሩ የሚተዳደሩበትን ሕግና በምን ዓይነት ሁናቴም እንደሚገዙ በጥልቅ ያስረዳል።

15. የእስራኤልን ሕዝብ ልብ ለእግዚአብሔር የሚያስገዛ በምዕራፍ 12 ላይ ምን ዓይነት ሥርዓት ተሰጣቸው?

መልስ።

1. የማምለኪያውን ዐፀድና የከነዓናውያንን የጣዖት መሠዊያዎች ከየማምለኪያ ቦታዎቻቸው ፈጽሞ እንዲያጠፉና እነርሱም የእነርሱ አምልኮት ነገር ፈጽሞ ትዝ እንዳይላቸው እግዚአብሔር አዘዛቸው። እስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር ብቻ ማስብና የተቀደሰውን የማምለኪያ ቦታ ብቻ መመልከት አለባቸው (12፡2፥3)።

2. እስራኤላውያን እግዚአብሔር ባሳያቸው ቦታ ብቻ ሊያመልኩት ይገባል፥ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ብቻ በእውነትና ከልብ በሆነ ፍቅር ሊያመልኩት ስለሚገባ ነው (12፡5-7፡ 11-14)። (በታዛዥነት 12፡8 በፍቅር 12፡12) እነርሱም እግዚአብሔር በመረጠው ሥፍራ ሊያመልኩት ይገባል (12፡5፥ 11፥ 14)።

3. እስራኤላውያን በታዘዙበት ቦታ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በሚያቀርቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ነገር ሁሉ በፊቱ በታላቅ ደስታና ምስጋና በተሞላ ሐሴት መብላት ነበረባቸው። መሥዋዕት አቅራቢውም ከሚያቀርበው መሥዋዕት ለምሳሌ ከስዕለት ቁርባንና በፈቃደኝነት ከሚቀርበው ቁርባን ይበላ ነበር (12፡6፥ 7፥ 17፥ 18)። በዚህ መንገዱ እስራኤላውያን ከከነዓናውያኖችና በአካባቢያቸው በሚኖሩት አሕዛብ አምልኮ፥ በኃጢአት፥ በርኩሰት፥ በተበላሸ አምልኮ፥ ልባቸው በመንገዳቸው አልተወሰደም ነበር። ስለ እግዚአብሔርና ስለአደረገላቸው መልካም ነገር ሁሉ ትዝ ባላቸው ጊዜ ከመውደቅ ባዳናቸው በጌታ ፍቅር ልባቸው በደስታ ይሞላል።

በእኛም ልብ ደግሞ ተመሳሳይ ነገር በእውነት ይፈጸማል። አሳባችንና ዓይናችን ወደ መራን ቦታ ሁሉ ልባችን ይከተላል። እግዚአብሔር ያደረገልንን ስናስብ ልባችን በእርሱ ፍቅር ይሞላና ፈተናችንን ሁሉ ድል እናደርጋለን። ወደ ዓለም ነገሮች የተመለከትን እንደሆነ እንወድቃለን (ሮሜ 12፡9)።

16. በምዕራፍ 13 ላይ ስለ ጣዖት አምልኮ ምን ተጨማሪ ሕጎች አሉ? ምዕራፍ 13 ስለ ሐሰተኞች ነቢያት (ሰባኪያን) ነው።

መልስ።

13፡1-5 ማንኛውም ሰው ሊሆን ስላለው ነገር ሕልም ቢያልምና ተአምራትን ቢያደርግ እንደዚሁም እስራኤልን ወደ ሌላ አማልክት ለመምራት ምልክቶችን ቢያደርግ ይገደል ነበር። እስራኤላውያን ውሸተኞች አስተማሪዎች በመካከላቸው እንዲገኙ መፍቀድ የለባቸውም ነበር። እነርሱ የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማታለል በሰይጣን ኃይል ተአምራትን ያደርጉ ነበርና (13፡3-11)።

ከቤተሰባቸው በጣም የተወደደው ሰው እንኳ ሌሎችን አማልክት እናምልክ ብሎ ትንቢት ቢናገር ያለ ምንም ርኅራኄ በመጀመሪያ የሰማው ሰው በድንጋይ ወግሮ መግደል አለበት። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ምንም ዓይነት ምሕረት የለውም። የእግዚአብሔር ልጆችም በኃጢአት ላይ ምንም ዓይነት ምሕረት ማሳየት የለባቸውም። ምክንያቱም ሰውን ወደ ዘለዓለም የገሃነም እሳት ስለሚሰድ ነው። ይልቅም ደግሞ ከሰይጣን በሆነ በማንኛውም ነገር መደሰትና መተባበር ፈጽሞ አይገባንም።

13፡12-18 ከእስራኤል ከተማዎች አንዱ እንኳን ጣዖትን ከሚያመልኩት ወገን ወደ ከተማው ትምህርታቸውን እንዲያሰራጩ ቢያስገባ ያ ከተማ ምናምን እንኳ ሳይቀርለት እልም ተደርጎ መደምሰስና በውስጡም የነበሩት ነዋሪዎችም ያለምሕረት ፈጽሞ መጥፋት ነበረባቸው።

የእግዚአብሔርም መቅሰፍት አሁንም ቢሆን እነዚህ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ለይተው ወደ ክፉ ነገር ሁሉ በሚመሩ ሰዎች ላይ ነው። እነርሱም ክፉውን ሥራቸውን እንዲያሰራጩ ቢፈቅዱላቸው ኖሮ ብዙዎቹን ወደ ዘለዓለም ጥፋት ያስገባሉ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ከእነዚህ ክፉ አድራጊዎችና ከሰይጣናዊ ምግባራቸው ፈጽሞ መለየት አለባቸው፤ ምክንያቱም ይህ ክፋታቸው እንደተላላፊ በሽታ በሰው ላይ ስለሚጋባ ነው። ዘዳግም 18፡9-14 ደግሞ በተጨማሪ ተመልከት።

17. በምዕራፍ 15 ውስጥ ምን ዓይነት ሥርዓትና ፍቅር ነው የተጠቀሰው?

መልስ።

15፡1-6 በየሰባት ዓመት የተሸጠ ነገር በሙላ ለቀድሞ ባለቤቱ ተመልሶ ይሰጣል። ነገር ግን ማንኛውም ለድሀ የተበደረ ነገር ከሆነ ግን ለድሀው በነፃ ይቀርለታል። ይህም ደግሞ ለተቸገሩ ድሆች ያለውን ፍቅር ይገልጻል።

15፡7-11 ለድሆች የእግዚአብሔር ልጆች በየዕለቱ በደስታና በፍቅር በነፃ መስጠት ይገባቸዋል። እነርሱም በስስት ጥቅም ወይም ትርፍ ለማግኘት ማድረግ የለባቸውም (ቁጥር 9)። ከፍቅር የተደረገ እንደሆነ እግዚአብሔር ይባርካል (ቁጥር 10)።

15፡12 አንድ እስራኤላዊ ባሪያ ሆኖ የተገዛ ቢሆን በሰባተኛው ዓመት ጌታው ነፃ ይለቀዋል፤ ጌታውም ባሪያውን በነፃ ለመልቀቅ ደስተኛ መሆን አለበት (ቁጥር 18)። ጌታውም ነፃ የወጣው ባሪያው በችግር ላይ እንዳይወድቅ የሚያስፈልገውን ስጦታ ሁሉ ሰጥቶ ማሰናበት አለበት።

15፡16-18 ባሪያውም በሰባተኛው ዓመት ጌታዬን እወዳለሁ ነፃ አልወጣም ቢል ይህ አገልጋይ ለጌታው ተወዳጅ ባሪያ ሆኖ እስከ ሞት አብሮት ይቆያል (ቁጥር 15፡17)። ከዚያም ጌታው ከከተማው በር አውጥቶ ጆሮውን (በወስፌ) ይበሳዋል። ይህም ማለት ባሪያው እስከሞት ድረስ ጌታውን በፍቅር ያገለግላል ማለት ነው። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነ ሁሉ ጌታውን እንጂ ማንንም እንዳይሰማ የሚያመልከት ምልክት ነው። እንደዚሁም ደግሞ በአማኞችና በክርስቶስ መካከል ላለው አንድነት ምሳሌ ነው። አማኞች ለክርስቶስ በፍቅር የሚገዙለት ባሪያዎቹ ናቸው። አማኙም ራሱን በፈቃዱ የሰጠ ስለሆነ ጌታውን ክርስቶስን በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ማገልገል ይወዳል።

18. በምዕራፍ 17 የሚገኘው መምሪያ እስራኤልን ከእግዚአብሔር (ከክርስቶስ) ጋር በፍቅር ለማጣመር በእስራኤል ላይ ሊገዛ ስለሚገባው ንጉሥና የእግዚአብሔርን ዓላማ አሳክቶ ለመሥራት ብቁ ለሚሆነው ንጉሥ ጠባይ ምን ይላል?

መልስ።

17፡14-20።

1. እስራኤላውያን እግዚአብሔር እራሱ የመረጠው ንጉሥ ሊኖራቸው ይገባ ነበር (ቁጥር 15)።

2. እርሱም ለራሱ ብዙ ፈረሶች ማጠራቀም የለበትም (ቁጥር 16)። እርሱም ለጦርነት ጊዜ እንዲረዱት በእግዚአብሔር እንጂ በፈረሶችና በጉልበቱ መመካት አይኖርበትም።

3. ብዙም ሚስቶች ለራሱ መሰብሰብ አይገባውም ነበር (ቁጥር 17)። የልቡ ፍላጎትና ፍቅር ወደ እግዚአብሔር መሆን ነበረበት።

4. እርሱም ለብልጽግና መጓጓት አይኖርበትም ነበር (ቁጥር 17)። ብልጽግናን ከእግዚአብሔር አብልጦ መውደድ የእግዚአብሔርን ሕግ ማፍረስ ነው። ንጉሡ ይህንን ሕግ እንዲጠብቅ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት ከሁሉ ነገር አስበልጦ እግዚአብሔርን ሲያፈቅር ለሕዝቡ ጥሩ ምሳሌ ከመሆኑም በላይ ለርዳታና ለአመራር የእግዚአብሔርን ድጋፍ ሲሻ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በታማኝነት ያደርጋል እንጂ የራሱን ፈቃድ አያደርግም።

5. 17፡18-20 ንጉሡም በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል አንብቦ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ እንዲያደርግ የእግዚአብሔር ቃል ከእርሱ ጋር ሊኖረው ይገባል። በዚህ መንገድ ንጉሡ ትሑትና ገር በመሆን ለሕዝቦቹ ጥሩ

ምሳሌ ስለሚሆን ከእግዚአብሔር ጋር የተጣመረ ፍቅር እንዲኖራቸው ያደርጋል። ሰዎች መሪያቸውን ተከትለው ወደ ኃጢአትም ሆነ ወደ ጽድቅ መመራት ይችላሉ። ይህም ነገር በመጽሐፈ ነገሥትና በመጽሐፈ ዜና በግልጽ ታይቷል። ንጉሣቸው መልካም ሰው ሲሆን ሕዝቡ ደግሞ መልካም ይሆናል። ንጉሣቸው ክፉና ኃጢአተኛ ሲሆን ሕዝቦቹ ደግሞ ኃጥአን ይሆናሉ።

19. በምዕራፍ 18 ምን ዓይነት ትንቢት ይገኛል?

መልስ።

ምዕራፍ 18 ቁጥር 15፡18 እና 19 ክርስቶስ የሰውን አካል ለብሶ በሰው አምሳል ከሰማይ እንደሚወርድ ትንቢት ተነግሯል። እግዚአብሔር ሰው ሆነ። ሙሴም ከክርስቶስ ጋር አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከቆየ በኋላ ፊቱ ሰዎች ሊያዩት እስከማይችሉ ድረስ ስለአንጸባረቀ ሸፈነው። ዘጸአት 34፡30-35። ክርስቶስም ከነክብሩ ቢወርድ ኖሮ ከግርማው የተነሣ ማንም ሊያየው ባልቻለም ነበር። ስለዚህ ክብሩን የሰው አካል በመልበስ ሸፈነው። ሙሴ በፊቱ ላይ ያለውን ክብር በጨርቅ እንደሸፈነው ሁሉ ክርስቶስም ክብሩን በአካሉ ሸፈነው። ስለዚህ ክርስቶስ በዘጸአት 18፡15፥ 18፥ 19 ላይ እንደተጠቀሰው ትንቢት እንደ ሙሴ ነቢይ ሆነ።

እስራኤላውያን በዮሐ. 1፡21፥ 45 እንደተጠቀሰው በክርስቶስ ዘመን ሊመጣ ያለው ነቢይ ክርስቶስ ራሱ እንደሆነ ያውቁ ነበር። ይህም በተለይ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በቁጥር 46 በግልጽ ተጽፏል። ስለዚህ በዮሐንስ 1፡21፥ 45 እና በሚከተሉት ጥቅሶች ሕዝቦቹ ስለ ክርስቶስ አውቀዋል ማለት ነው (ዮሐ.2 6፡14፤ የሐዋ. 3፡22፥ 23፥ 26፤ 7፡37)። ብዙዎቹም አዳኝና የእስራኤል ንጉሥ እንደሚሆን አውቀው ነበር።

20. ከምዕራፍ 19-26 ካለው ክፍል ውስጥ የተቻለህን ያህል ለሰውና ለእግዚአብሔር ሊኖረን ስለሚገባን ፍቅር የሚገልጹትን ሕጎች ግለጽ።

መልስ።

19፡1-13፤ ዘኁልቁ ምዕራፍ 35፤ ዘዳግም 4፡41-49፤ ኢያሱ ምዕራፍ 20፤ በአንድነት አንብብ። የመማጸኛው ከተማ። አንድ ሰው በልቡ ቂም ሳይኖርበት በድንገት ሳያውቅ ሌላውን ሰው ቢገድል አውቆ ሆነ ብሎ ስላልገደለውና ንጹሕ ልብ ስላለው ከደም ተበቃዮቹ ሸሽቶ ራሱን ለማዳን በመማጸኛው ከተማ ውስጥ ገብቶ ያመልጣል። ደም ተበቃዩ የሟቹ ወገኖች ከሆኑት አንዱ ነው (ዘኁልቁ 35፡19)። በእስራኤልም ውስጥ 6 የመማጸኛ ከተማዎች ነበሩ። እነዚህም ከተማዎች ሦስቱ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ሲገኙ የቀሩት ሦስቱ ደግሞ ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ ነበሩ። ከማንኛውም ከእስራኤል አካባቢ ከተማዎች በዛ ቢባል ያንድ ቀን ጉዞ ብቻ ተሄዶ ይደረስባቸዋል (ዘኁልቁ 35፡13-15)።

ነፍሰ ገዳዩ ወደ መማጸኛው ከተማ በሚሸሸበት ጊዜ ደም ተበቃዩ በጭራሽ አይነካውም ነበር። ሆኖም የከተማው ሽማግሌዎች ፍርድ ይሰጡ ነበር። ሽማግሌዎቹም ነፍሰ ገዳዩ ሟቹን የገደለው በልቡ ጥላቻና ቂም ስለነበረ መሆኑን ካወቁ ገዳዩ በሞት እንዲቀጣ ያደርጉ ነበር። ነገር ግን ሳያውቅ በድንገት በእጁ ሞቶ እንደሆን ሊቀ ካህኑ እስኪሞት ድረስ በዚያው በመማጸኛው ከተማ ውስጥ ይኖራል (ዘኁልቁ 35፡28)። ሊቀ ካህኑ ከሞተ በኋላ ግን ገዳዩ ነፃ ወጥቶ ወደ ነበረበት አገር ይመለሳል። ተበቃዩም ከዚህ በኋላ የመግደል ሥልጣን የለውም (ዘኁልቁ 35፡15-34)።

ይህም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ላለው መከለልና ከዘለዓለም ሞት የመትረፍ ምሳሌ ነው። እንደዚሁም ሁሉ አዲስ በመወለድ ለክርስቶስ ያልተሰጠ ኃጢአተኛ ሁሉ እንዲያድነው ወደ ክርስቶስ ቢሸሽ አሁንም ቢሆን በሞት ፍርድ መቀጣቱ አይቀርም። ምክንያቱም ኃጢአቱን እስከ አሁን በልቡ ስለተሸከመና የኃጢአትም ዋጋ ሞት ስለሆነ ነው። እንዲህ ያለውም ሰው በልቡ በመሸከም በኃጢአቱ ወደ ፊት በመግፋት የዘለዓለምን ደኅንነት ለማግኘት በሚፈልግ በአፋዊ ክርስቲያን ይመሰላል። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው በድንገት ወይም በድካሙ በኃጢአት ቢወድቅ እርሱ በልቡ ኃጢአተኛ አይደለም። እርሱ ኃጢአትን የሚጠላ ልብ አለው፥ ነገር ግን በኃጢአት ተሸነፈ። ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነና በልቡም ኃጢአትን ለመጥላት ስለሚፈልግ ነው።

እንደ እስራኤል አገር ደንብ፥ በደል የሌለበት ነፍሰ ገዳይ በመማጸኛው ከተማ ውስጥ ይቀመጣል። እንደዚሁም ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ መቀመጥ አለበት። ሊቀ ካህኑ ከሞተ በኋላ ነፍሰ ገዳዩ ወደ አገሩ ተመልሶ መሬቱን የመውረስ መብት ወይም ነፃነት አለው። እንደዚሁም ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ በሙሉ ነፃ ስለሆነ ማንም ሊነካው አይችልም። በዚህም በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ምንም ዓይነት ፍርድ ሊወርድበት አይችልም። ምክንያቱም ሊቀ ካህኑ ክርስቶስ ሞቶለታልና ነው።

በ1ኛ ዮሐ. 2፡1 እንዲህ እናነባለን። «ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» ይህ ጥቅስ የተጻፈው ለአማኞች ነው። ይህም ጥቅስ ያ እስራኤላዊ ነፍሰ ገዳይ ሳይወድ ባለማወቁ ነፍስ እንደ ገደለ ሁሉ አማኝም በኃጢአት ሊወድቅ ይችላል። አማኞችም ኃጢአትን ለማድረግ አይወዱም፤ ክርስቶስን በተቀበሉ ጊዜ በኃጢአታቸው ተናዘው ከኃጢአታቸው ወደ ክርስቶስ ተመልሰዋል። ስለዚህ በኃጢአት በወደቁ ጊዜ የመማጸኛ ከተማቸው ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ለይቅርታ ይሸሻሉ። ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ነው ይላል። እርሱም ይህ ኃጢአት ከልብ የሆነ ሳይሆን ድንገተኛና ከድካም የተነሣ የተደረገ እንደሆነ ያመለክታል። ስለዚህ ወዲያውኑ ይቅር ይባላል። ኃጢአት ሁሉ የሞት ፍርድ በላዩ ላይ አለበት (ሮሜ 6፡23)፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን የኃጢአት ፍርድ በኃጢአታቸው ተናዘው

ኢየሱስ ክርስቶስ በምትካቸው እንደተፈረደበት የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ ኃጢአት በላዩ ላይ ተሸክሟአል። ለዚህም በመማጸኛው ከተማ የተማጸነው ሰውዬ በደም ተበቃዩ በጥላቻ ሳይገደል ቅን ፍርድ ከተፈረደለት ፍርድ ትምህርት መውሰድ እንችላለን። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር ይገልጣል። ዘዳግም 19፡2-9፤ ከዘጸአት 21፡13፤ መዝ. 45(46)፡1፤ 141(142)፡5፤ ኢሳ. 4፡6፤ ሮሜ 8፡1፥ 33፥ 34፤ ፊልጵ. 3፡9፤ ዕብ. 6፡18-19 ጋር አመዛዝን።

19፡14 ይህ ደግሞ ለሰው ያለውን ፍቅር ያሳያል። እግዚአብሔርም ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ምድሩን ርስት አድርጎ ሰጠ። ማንኛውም ሰው የድንበሩን ምልክት አፍርሶ የጓደኛውን ድንበር መግፋት አይፈቀድለትም ነበር። ይህም ለጓደኞቻቸው ያላቸውን ፍቅር ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርንም ሕግ አክብሮ መታዘዝን ያሳያል።

19፡15-21 ይህ ሕግ በውሸት በወገኑ ላይ በፈረደው ፍርድ ተመልሶ በራሱ ላይ እንዲፈርድበት ለሕዝቡ ገዢ የተሰጠ ሕግ ነው። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ በማክበር ክፉውን በመጥላት ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ያሳያል። ክፉ የሆነ ሁልጊዜ የሚቀጣ ከሆነ ሁሉ ሰው በሰላም ይኖራል (ቁጥር 20)።

ምዕራፍ 20 ከነዓናውያን በማጥፋታቸው ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ያሳያሉ። ለከነዓን ሕዝብ ይሰጥ የነበረው የምሕረት ጊዜ አልፎአል፤ እስራኤላውያንም እነርሱን በማጥፋታቸው ለእግዚአብሔር ታዘዋል።

ሌሎች አሕዛቦች ግን ስለ ኃጢአታቸው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ልኮባቸው በሚቀጣቸው ጊዜ ራሳቸውን አሳልፈው የመስጠት ዕድል አጋጥሟቸዋል። ከተገሠጹ በኋላ ራሳቸውን አሳልፈው የመስጠት ዕድል ማግኘታቸው እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፍቅር ያሳያል (20፡10፥ 11)።

21፡15-17 ትክክለኛውን ነገር በማድረግ ለሰው ያለውን ፍቅር ያሳያል። በ21፡18-23 የተገለጸው ኃጢአትን በመጥላትና ኃጢአትን በማራቅ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ስለ ማሳየት ነው። ከዚህም በቀር ለጓደኞቻቸው ያላቸውን ፍቅር ኃጢአትን ከመካከላቸው ለማስወገድ፥ ቢያስፈልግም ደግሞ በልጆቻቸው ላይ እንኳን መፍረድ አለባቸው።

22፡1-4፡8 ይህም ለሰዎች የነበራቸውን ፍቅር ያሳያል። በወታደርነት ውስጥ ያሉት ተዋጊዎች በእግዚአብሔር እምነት በማጣት ቢፈሩ ወደ ጦርነት እንዲሄዱ አይፈቀድላቸውም። በዚህ ፋንታ ግን ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ይፈቀድላቸዋል።

22፡9-12 ይህም ለእግዚአብሔር የነበራቸውን ፍቅር ያሳያል። የተለያዩ ዓይነት ልብሶች እንስሳቶችና እህሎች እንዲቀያየጡ አይፈቀድም ነበር። ይህም ደግሞ እስራኤላውያን ከዓለም ጋር ሳይደባለቁ በገለልተኛነት በቅድስና ራሳቸውን

ለእግዚአብሔር እንደለዩ የሚያሳይ ምልክት ነው። በሌላ አነጋገር ኃጢአትን ጠልተው እግዚአብሔርን እንዲወዱ ነው። ሁለቱንም አጣምራችሁ በአንድነት መውደድ አትችሉም (1ኛ ዮሐ. 2፡15፤ ማቴ. 6፡24)።

23፡15፥ 16፥ 19፥ 20፥ 24፥ 25፤ ይህ እኛ የሰው ልጆች እርስ በርሳችን ሊኖረን የሚገባንን ፍቅር ያሳያል (23፡21-23)። ይህም ደግሞ ለእግዚአብሔር የሚኖረንን ፍቅር ያሳያል።

ዘዳግም ምዕራፍ 24፡1-4ን ከ1ኛ ቆሮ. 7፡12-15 እና ከማቴዎስ 19፡8 ጋር አመዛዝን። ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 19፡8 ላይ ሙሴ ፍቺን የፈቀደው ስለልባቸው ድንዳኔ ነው ይላል። በዘዳግም 24፡1-4 ፍቺ የተፈቀደው እነርሱ የማያምኑ ስለሆኑ ነው። ጳውሎስ ደግሞ በ1ኛ ቆሮ. 7፡12-15 ባለው ክፍል ላይ ያላመኑ ሰዎች እንዲፋቱ ይፈቅዳል።

የማያምነው የመፍታት መብት ስላለው አማኙ ከጋብቻ እስር በታች አይደለም ማለት ነው። ይህም እስር ቋሚ ያልሆነ የጋብቻ እስር ነው። እግዚአብሔር በሙሴ ውስጥ ሆኖ በዘዳግም 24፡2 ላይ ምናልባት እንደገና ማግባት ትችላለች ይላል። ኢየሱስ ግን በማቴ. 19፡9 ላይ (በዝሙት ምክንያት ካልሆነ ሰው ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን ቢያገባ ያመነዝራል ይላል።) እርሱም አመንዝራ እንድትሆን ሚስቱን ይፈታል ይላል። አመንዝራ ማለትም አዘውትሮ ከወንድ ጋር የዝሙት ኃጢአት መሥራት ማለት ነው። ይህም ደግሞ አንድ ጊዜ በፍትወት ኃጢአት ላይ መውደቅ ሳይሆን በአመንዝራነት ባሕርይ ወይም ኑሮ መኖር ማለት ነው። ከሁለት ባልና ሚስቶች አንዳቸው ዝሙት ቢሠሩ የጋብቻው እስር ይፈርሳል። ከዚያም በኋላ መልሶ መታደስ አይቻልም። በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ አመንዝራ መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል። ይህም ማለት በዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ግን አመንዝራ አይደለም። ኃጢአትንም አያደርግም። ምክንያቱም በጋብቻ ሕግ ታስረው የነበረው አሁን በምንዝርና ስለፈረሰ ነው። ዘማዊነት ጋብቻውን ያፈርሳል። ከዚህ በስተቀር በሌላ ስሕተት ወይም ጥፋት የጋብቻን እስር ማፍረስ አይቻልም። የጋብቻውን ኅብረት የሚያፈርስ አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ያውም ከሁለቱ አንዱ በጋብቻ የተገኘውን አንድ አካልነት አፍርሶ ከሌላ ጋር በመጣመር ነው።

አንድ አማኝ በዝሙት ምክንያት ሚስቱን ቢያባርራት ስሕተቱ የሁለቱም ነው። ያባረራት በአማኝ መካከል ሊደረግ ስለማይገባው የፍትወት ኃጢአት ሳይሆን በሌላ ምክንያት ነው። አማኞች ኃጢአታቸውን ተናዘው መታረቅ አለባቸው (1ኛ ቆሮ. 7፡10-11)። ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል ብሎ ኢየሱስ በማቴዎስ 5፡32 ላይ ተናግሯል። ስለዚህ በሌላ ነገር ምክንያት አማኝ የሆነ ሰው ሚስቱን ቢፈታ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ክርስቶስ ይፈርድበታል። አንዳንዶቹ አማኞች ሚስቶቻቸውን ለመፍታትና ሌላይቱን ለማግባት ሲሉ ከሌላይቱ ጋር ያመነዝራሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር

በልቡ ያለውን ክፋት ያይና በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር በባልዬው ላይ ይፈርድበታል። ምክንያቱም ሚስቱን በመፍታት ኃጢአትን ስለሠራ ነው።

24፡4 ሴቲቱም ባልዋን ፈትታ ሌላውን ካገባች በኋላ ወደ ቀድሞው ባልዋ ተመልሳ በመጋባት ዳግመኛ ሚስት ልትሆነው ፈጽሞ አትችልም (24፡4)። ምክንያቱም ይህን ማድረግ «በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነው።» ይህ ነገር በእስራኤላውያን ዘንድና በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ከሆነ አሁንም ቢሆን በአማኞች ዘንድ እና በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነው።

ምዕ. 24፡5-22 ለጎረቤትህም ሆነ ለሌላው ፍቅር ይኑርህ፤ (25፡13-16፤ ምዕ. 25)። በምድርዋ ላይ ትክክለኛነት እንዲኖር የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም ሌሎች ለእግዚአብሔር ፍቅር እንዲኖራቸው አስተምር።

ዘዳግም 27-34።

21. በጌባልና በገሪዛን ተራራ ላይ ለተደረገው ርግማን የእግዚአብሔር ዓላማ ምን ነበር?

መልስ?

እነዚህ ሁለት ተራራዎች በእስራኤል አገር ውስጥ በመካከለኛው ሥፍራ ይገኛሉ። እነርሱም መታሰቢያ ሆነዋል። እስራኤሎችም ዓይናቸውን አንስተው እነዚህን ተራራዎች በተመለከቱ ቁጥር ለእግዚአብሔር ቢታዘዙ የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚቀበሉና ባይታዘዙ ደግሞ መርገሙ እንደሚወርድባቸው ትዝ ይላቸዋል። እነዚህም ተራራዎች እስራኤላውያን በየዕለቱ ለእግዚአብሔር በታዛዥነት እንዲያገለግሉ ጥሩ ማስታወሻ ሆነዋቸዋል።

22. እስራኤላውያን በሚታዘዙ ጊዜ ምን ዓይነት በረከት ሊሰጣቸው ተስፋ ተደረገላቸው

መልስ።

እግዚአብሔርን ቢታዘዙት ዘራቸውን፥ እርሻቸውን፥ ከብቶቻቸውንና ቤተሰባቸውን ለመባረክ ተስፋ ገባላቸው። ከዚህም በቀር በመንፈሳዊ በረከትም ሊባርካቸው ተስፋ ሰጥቷቸዋል (ዘዳ. 28፡1-14)።

23. ባለመታዘዝ ምን ዓይነት መርገም ይከተላችኋል ተብለው ነው ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው?

መልስ።

እግዚአብሔር ከተማቸውን፥ እርሻቸውን፥ በጎተራ ያለውን እህላቸውንና በማድጋ ያለውን ዘይታቸውን፥ ልጆቻቸውን፥ የምድራቸውን ፍሬና ከብቶቻቸውን ይረግማል። እግዚአብሔርም የሚያደርጉትን ነገር በሞላ ይረግማል። በሽታንም ዘወትር በላያቸው ላይ ያጣብቃል። እነርሱም በጠላቶቻቸው ተሸንፈው ለሌላ ሕዝብ ባሪያዎች ሆነው ይገዛሉ። እነርሱንም

የዱር አውሬዎችና የሰማይ አዕዋፋት ይበሏቸዋል፤ በረሃብም ልጆቻቸውን ይበላሉ። በአሕዛብም መካከል ተሽጠው በዓለም ውስጥ በየስፍራቸው ይበታተናሉ (28፡15-68)።

24. ምዕራፍ 29 እና 30 ይህ ጉዳይ ነገሩ አስቀድሞ ሳይሆን በፊት በተቀዳሚ በመታዘዝና ባለመታዘዝ የሚመጣውን በረከት ወይም መርገም በመግለጽ ስለ ክርስቶስ ዓላማ ምን ያሳያል?

መልስ።

እስራኤላውያን ባለመታዘዝ የሚደርስባቸውን መርገምና በመታዘዝ የሚሆንላቸውን በረከት አውቀው በገዛ ፈቃዳቸው በፍቅር ሕይወትን እንዲመርጡ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) አስቀድሞ አስጠንቀቃቸው (30፡19)። ስለዚህ እግዚአብሔር ውጤቱ ምን እንደሚሆን በጣም ግልጽ አድርጎ ለእስራኤላውያን በማሳየት አውቀው በገዛ ምርጫቸው ወይም ፈቃዳቸው እንዲታዘዙትና በሕይወት እንዲኖሩ አደረገ (30፡11-15)። በ30፡14 ላይ ደግሞ ቃሎቹ በልባቸው መሆን እንዳለባቸው አሳይቷቸዋል። በልባቸው አዲስ ፍጥረት መሆን ሲችሉና የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆች ሲሆኑ በዚያን ጊዜ ብቻ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መፈጸም ይችላሉ። ከዚያም በኋላ እውነተኞች ምድራዊ ሕዝቦቹና መንፈሳዊ ልጆቹ መሆን ይችላሉ። ጳውሎስ በሮሜ 10፡5-9 ባለው ክፍል ላይ ሙሴ ለእስራኤላውያን በእምነት የሚገኘውን የደኅንነትን መንገድ እንዳሳያቸውና አዲስ በመወለድ በአዲስ ልብ እግዚአብሔርን ማገልገል እንደሚችሉ እንዳስረዳቸው ጠቅሷል። ዘዳግም 30፡11-15ን ከሮሜ 10፡5-13 ጋር አመዛዝን። እስራኤላውያን እንደ አዲስ ኪዳን ምእመናኖች በእምነት ለመዳንና ክርስቶስን በልባቸው ለመቀበል የግል ምርጫና ፈቃደኝነት ሊኖራቸው ይገባ ነበር። ክርስቶስን ካልመረጡ በስተቀር በምድር የክርስቶስ የሥጋ ወገኖች መሆናቸው ብቻ ሊያድናቸው አይችልም። ከአዳም ጊዜ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ማለት እስከ የሺህ ዓመት ግዛቱ ድረስ አንድ የመዳን መንገድ ብቻ ይኖራል። ይህም ክርስቶስ ሠርቶ በጨረሰው ሥራ ማመን ብቻ ነው።

30፡18-21 እግዚአብሔር የእስራኤላውያን የኃጢአት ፍርድ ምንም ጊዜ እንደማይቀር እንዲያውቁ ይፈልጋል (29፡22-29)። እንግዳ የሆኑ ሰዎች እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ መአት ሲያወርድና እስራኤላውያንንም ስለ ኃጢአታቸው ሲቀጣ ሲያዩ እነርሱም ደግሞ ምናልባት እግዚአብሔርን ይፈሩና ኃጢአትን ከደው የእግዚአብሔርን ደኅንነት ይፈልጉ ይሆናል።

30፡1-10 የፓለስቲናን (የከነዓን) ኪዳን ይዟል። ይህ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ካደረጋቸው ኪዳኖች አምስተኛው ነው። የፓለስቲናው ኪዳን እስራኤላውያን በምን ሁናቴ ወደ ተስፋይቱ ምድር ማለት ወደ ከነዓን እንደገቡ የሚያሳይ ነው። ይህም ኪዳን ሰባት ክፍሎች አሉት።

1. ባለመታዘዝ የሆነ መበታተን፤ (ዘዳግም 30፡1፤ 28፡63-68)።

2. ተበታትነው ሳሉ ወደፊት የሚያደርጉት ኑዛዜ፤ ( 30፡1-5)።

3. የጌታ መመለስ፤(30፡3፤ አሞጽ 9፡9-14፤ የሐዋ. ሥራ 15፡14-17)።

4. ወደ ምድረ ከነዓን ተመልሰው እንደሚገቡ፤ (30፡5፤ ኢሳ. 11፡11፥ 12፤ ኤር. 23፡3-8፤ ሕዝ. 37፡21-25)።

5. የዜጋዎቹ መለወጥ፤ (30፡6፤ ሮሜ 11፡26፥ 27፤ ሆሴዕ 2፡14-16)።

6. እስራኤላውያንን የሚያስጨንቁ ሰዎች ፍርድ፤(30፡7፤ ኢሳ. 14፡1፥ 2፤ ኢዩኤል 3፡1-8፤ ማቴ. 25፡31-46)።

7. የሕዝቦቹ መበልጸግ፤(30፡9፤ አሞጽ 9፡11-14)።

ከእነዚህ ኪዳኖች ብዙዎቹ ወደፊት የሚፈጸሙ ናቸው። እስራኤላውያንም እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል የገባለትን ምድር በሞላ ይወርሳሉ። እስራኤላውያንም የተሰጣቸውን ምድር በሞላ እስከ አሁን አልተቀበሉም (ዘፍጥረት 15፡18)። ክርስቶስ እንደተመለሰ ምድራቸውን በሞላ ይረከባሉ።

እስራኤላውያን አንድ ጊዜ ወደ አሶር ወደ ይሁዳና ወደ ባቢሎን ለ70 ዓመት ተበታትነው ነበር። በኋላም ወደ ምድራቸው ይመለሳሉ። ከዚያም በኋላ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን በካዱ ጊዜ ደግሞ መልሰው ተበታተኑ። ደውም በጠቅላላው ለ2000 ዓመት የበተናቸው ሲሆን አሁን ግን እግዚአብሔር ወደ አገራቸው ሰብስቦ ለዳዊት እንደገባው ቃል ኪዳን ንጉሥ ክርስቶስ እንደተመለሰ እንደገና ምድራቸውን ይሰጣቸዋል (ዘዳግም 30፡3፤ ኤርምያስ 23፡5-8፤ ሕዝ. 37፡21-25፤ ሉቃስ 1፡3-33፤ የሐዋ. ሥራ 15፡14-17)

እግዚአብሔር ከሰው ጋር የገባው ቃል ኪዳን።

1. የዔደን ገነት ኪዳን፤ (ዘፍጥረት 1፡28)።

2. አዳማዊ ኪዳን፤ (ዘፍጥረት 3፡15)።

3. የኖኅ ኪዳን፤ (ዘፍጥረት 9፡1)።

4. የሙሴ ኪዳን፤ (ዘጸአት 20፡1-26)።

5. የከነዓን ኪዳን፤ (ዘዳግም 30፡1-10)።

6. የዳዊት ኪዳን፤ (2ኛ ሳሙኤል 7፡16)።

7. አዲስ ኪዳን፤ (ዕብ. 8፡7-13)።

ማንም ኃጢአቱን ተናዞ ክርስቶስን የተቀበለ ሁሉ ከጌታ ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል። እርሱም ደግሞ ከኃጢአት ተለይቶ እንደ አዲስ ፍጥረት ከእግዚአብሔር ጋር ሊራመድ ቃል ገብቷል።

25. ሀ. ስለ እስራኤል ምን ተነገረ? ምዕ. 31፡14-20።

መልስ።

ክርስቶስ እስራኤላውያን ፊታቸውን ከእርሱ እንደሚመልሱና እርሱ ደግሞ ከእነርሱ ዞር እንደሚል ተናገረ። ስለዚህ እስራኤላውያን እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት እንደተለያቸውና ይህ ሁሉ መከራ እንደደረሰባቸው ማወቅ አለባቸው።

25. ለ. ክርስቶስ ሙሴን በ32፡1-43 የተጠቀሰውን መዝሙር እንዲጽፍ በመራው ጊዜ ዓላማው ምን ነበር?

መልስ።

መዝሙሩ ሰዎች ሊሰሙት ቢወዱ ወይም ቢጠሉ ዘወትር ይዘመራል። ሰዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በማያነቡ ጊዜ እንኳን ስለ ቃሉ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። በዚህ መዝሙር እስራኤላውያን እግዚአብሔር እንዴት እንደመረጣቸው፥ እንደወደዳቸው፥ እንደጠበቃቸው፥ ምድርን እንዳወረሳቸውና በረከቱን እንደሰጣቸው እንዲያስታውሱ ይደረጉ ነበር። ከዚህም በቀር ባለፈው ጊዜ ባለመታዘዝና በእምቢተኝነት ስለመጣው የእግዚአብሔር ፍርድና ኃዘን ሁሉ ያስታውሳቸዋል። ይህንን ሁሉ መዝሙር በመስማት እግዚአብሔር ንስሐ ገብተው ከኃጢአታቸው እንዲመለሱና በሚመጡት ዘመናት ምናልባት ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ምሕረትን አግኝተው ወደ ምድራቸው ይመልሳቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደሚጋብዛቸው ይመለከታሉ። ይህም በመዝሙር ለእነርሱ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፍቅር በማስጠንቀቅ ያበረታታቸዋል (ዘዳግም 31፡21)።

26. በዚህ መዝሙር ለዕብራውያኖች የተነገሩላቸውን ትንቢት በጥቂት ቃላቶች ግለጽ። 32፡1-43።

መልስ።

በዚህ መዝሙር 32፡1-14 እግዚአብሔር ምን ያህል በምሕረት የተሞላ አምላክ እንደሆነላቸውና ከቀሩት ፍጥረቶቹ ለይቶ በመምረጥ ምድርን እንደሰጣቸው ያሳያል (ቁጥር 8)። ከዚያም በኋላ ለእነርሱ ባለው ታላቅ ፍቅር ተነሳስቶ ወደዚያ ወደ ምድረ ከነዓን መራቸው።

32፡15-18 ክርስቶስ (እግዚአብሔርም) እስራኤላውያን እንዴት በኃይል እንደሚበለጽጉና ከዚያም በኋላ እንደሚከዱት፥ ጣዖትንና ሌሎችን አማልክት በመከተል ሰይጣንን እንደሚያመልኩ ትንቢት ተናግሯል። ስለዚህ አሁን ልክ ትንቢት እንደተነገረው ተፈጽሟል (32፡19-25)። ስለዚህም ክርስቶስ

በኃጢአታቸው ተጸይፏቸው ስለነበር ፈርዶባቸዋል (32፡26-38)። ንጉሣቸው የሆነው ክርስቶስ በእስራኤላውያን ላይ በሚያመጣው መቅሰፍት በኃጢአታቸው ፈጽሞ ሊያጠፋቸው ሳይሆን ምሕረትን ሊያሳያቸው ነው። እነርሱም ወደ አሶርና ወደ ባቢሎን ተማርከው ሄደው ነበር፤ ሆኖም እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ፈርዶ መልሶ ወደ አገራቸው አመጣቸው። እንደገና ደግሞ ሊበታተኑ ነው።

32፡39-43 እግዚአብሔር ሕዝቦቹን መልሶ ያሳርፋቸዋል (ቁጥር 39)። እግዚአብሔርም መልሶ ለስሙ ክብርን ይሰጣል። እግዚአብሔርም ከእስራኤልና ከእስራኤል ጠላቶች ጋር በሚያደርገው ነገር የዓለም አሕዛብ ሁሉ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ። ጠላቶቻቸውም በእግዚአብሔር ፊት ይፈራሉ (ቁጥር 40-42)። ይህም ደግሞ ወደፊት የሚሆን ለእስራኤል የተነገረላት ትንቢት ነው። በሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን እግዚአብሔር ጠላቶቹን አጥፍቶ እስራኤልን ያድናታል።

32፡43 በክርስቶስ የ1000 ዓመት የሰላም መንግሥት ጊዜ እስራኤላውያንና የዓለም ሕዝቦች በሙሉ በጌታ ፊት ደስ ይላቸዋል። ይህም መዝሙር እስራኤል ከ1000 ዓመት በኋላ ስለሚኖራት ነፃነት ይናገራል። ይህም የ4500 ዓመቱ የእስራኤል ታሪክ ነው። አብዛኛው ተፈጽሟል፤ ወደፊት የሚሆንም ጥቂት አለ። እናንተ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ምክንያቱም አሕዛብም ለ1000 ዓመት በበረከቱ ውስጥ ስለሚሆኑ ነው።

27. ምዕ. 32፡2፥ 3 የተጠቀሰው ለየትኛው ጊዜ ነው?

መልስ።

ይህ ጥቅስ በሲና ተራራ ላይ ስለተሰጠው ሕግ ይናገራል። እነርሱም በዚያ የእግዚአብሔርን ሕግ ተቀበሉ። ከዚያ ወዲህ እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ነገር አወቁ። ምናልባት በቁጥር 2 ቅዱሳኖቹ የሚለው ቃል የተጠቀሰው ለእስራኤላውያን ይሆናል። እንደገናም በተጨማሪ በቁጥር 3 ላይ ቅዱሳኖቹ ይላል።

28. እንደ ንጉሥ ይሹሩን ሆኖ የተነገረለት ማን ነው? 33፡4፥ 5።

መልስ።

እንደተከታዩ ጥቅስ ከሆነ ሕግጋቶቹን የሰጠው ንጉሡ መሆን አለበት። እርሱም እንከን የሌለበት የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ክርስቶስ መሆን አለበት። ከቁጥር 26-28 ያለውን ደግሞ ተመልከት። ይሹሩን ማለት «ጻድቁ እስራኤል» ማለት ነው። ይህም የእስራኤል ትንቢታዊ ስም ነው። ምክንያቱም በ1000 ዓመታት መንግሥቱ ጊዜ ጻድቃኖች ስለሚሆኑ ነው። ዘካርያስ 14፡16፥ 20፥ 21፤ ኢሳ. 35፤ በተለይ ቁጥር 10፤ ኤርምያስ 23፡6፤ ዘዳግም 33፡29 ተመለከት።

29. ቁጥር 26 እና 29 ወደፊት የሚያመለክቱት የትኛውን ጊዜ ነው?

መልስ።

ይህ ቁጥር በትንቢት የሚያስረዳው ስለ ክርስቶስ የ1000 ዓመት መንግሥትና እግዚአብሔር በምድር ላይ እንደሚፈርድ ነው። ይህም ገና ወደፊት የሚሆን ነው። ስለዚህ ተመሳሳይ ጊዜ የሚናገረውን ራእይ 19፡11፥ 12 ተመልከት። (ራእይ 20፡4-6።)

ይህ ቁጥር በትንቢት የሚያስረዳው ስለ ክርስቶስ የ1000 ዓመት መንግሥትና እግዚአብሔር በምድር ላይ እንደሚፈርድ ነው። ይህም ገና ወደፊት የሚሆን ነው። ስለዚህ ተመሳሳይ ጊዜ የሚናገረውን ራእይ 19፡11፥ 12 ተመልከት። (ራእይ 20፡4-6)።

እስራኤላውያን ወደ ንስሐ እንዲመጡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ሊያመጣው ባለው በከፍተኛው የዓለም መከራ ጊዜ ክርስቶስ ዳግመኛ ተመልሶ ሐሰተኛውን ክርስቶስ ከወታደሮቹና ከሕዝቦቹ ጋር ይቀጣል። ከሞት የተረፉት እስራኤላውያን ሁሉ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ንጉሣቸው አድርገው ይቀበሉታል። ከዚያም በኋላ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ ለ1000 ዓመት በሰላም ይገዛል (ራእይ 20፡4-6)። የተዋጁትም በሞላ ከእርሱ ጋር ይነግሣሉ።

30. ማን የጻፈው ይመስልሃል? ዘዳግም 34

መልስ።

ይህ ምዕራፍ የተጻፈው ሙሴ ከሞተ በኋላ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ማን እንደጻፈው አይናገርም። ሙሴ ከመሞቱ በፊት በትንቢት ሊሆን ያለውን ነገር ምናልባት አልጻፈ ይሆናል። ምክንያቱም የታሪኩ ሁኔታ ነገሩ ከሆነ በኋላ የተጻፈ ይመስላል። ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እንደሚያምኑት ይህ ክፍል የተጻፈው በኢያሱ ነው ብለው ይናገራሉ። ምክንያቱም ኢያሱ የሙሴን ሥራ ተረክቦ በእርሱ ምትክ የሚሠራና በጥበብ መንፈስም የተሞላ ስለሆነ ነው ይላል። ዘዳግም 34፡9።